# ሽብር ነዣሪው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት



# ሽብር ነኻሪው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት

አበበ በዛብህ

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

አታሚ ድርጅት፣

## መቅድም

ይህ መጽሐፍ ለ31 ዓመታት አባላቸው ሆኜ ስለአገለገልኩት ስለይሖዋ ምስክሮች አነሳስ፣ አደረጃጀትና ርዕዮተ ዓለማቸው የሚገልፅ ነው:: ስለዚህ ስለይሖዋ ምስክሮች የቃላት አጠቃቀምና አሠራር ባሕል በመጠኑ መግለጥ አስፈላጊ ነው::

የይሖ ምስክሮች በመካከላችን የደረጃም ሆነ የማዕረግ ልዩነት የለም:: እንደዚህ ያለ ባሕል ባዕዳችን ስለሆነ አናውቅም ይላሉ:: እውነት ይሆን? ቀጥለን የምንአየው ጉዳይ ይሆናል:- የይሖዋ ምስክሮች እንደሌሎች ሐሰተኞች የሃይማኖት ድርጅቶች ከምዕመናኖቻችን ገንዘብ አንለምንም ወይም ቆሬም ሆነ ገበቴ አናዞርም፣ እንደዚህ ያለ ባሕልም ሆነ አሠራር የለንም ይላሉ:: ይኸንንም በመጽሐፉ የምንአየው ይሆናል::

የይሖዋ ምስክሮች በመካከላችን የማዕረግ ልዩነት የለም ቢሉም በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊ ደረጃ ፍጹም የጉላ የማዕረግ ልዩነት እንደአላቸው ማንም የሚረዳው ነው:: የይሖዋ ምስክሮች ድርጅታችን የቴኦክራቲክ (Theocratic) ማለት የመለኮታዊውን አመራርና አሠራር ዘዴን ይከተላል ይላሉ:: ይህ ቴኦክራቲክ የሚለው ከአንድ እዝ ብቻ የሚወጣ አሐዳዊ ማዕከል እንደአለና አስፈጻሚዎችም እንደሚኖሩ ቃሉ እራሱ ይጠቁመናል:: የቴኦክራቲክ ሥነሥርዓት አስፈጻሚዎች ከቶውኑ ዴሞክራት ሊሆኑ አይችሉም:: ስለዚህ በመካከላቸው ያለው የስልጣን እርከን በማሳያ ክብ ሣጥን ቀጥለን እንመለከታለን:-






## ስለማሳያው ክብ ሣጥን መግለጫ

የማሳያ ክብ ሣጥን ቁጥር አንድ ከሁሉ በላይ የሆነ የአጥናፈ ዓለሙ ፈጣሪን የሚያመለክት ነው:: የሣጥኑ ትንሽነት ኃይል ከግዝፈት እንዳልሆነም ይጠቁመናል:: በይሖዋ ምስክሮች የይሖዋ አምላክ ብቸኛ ደረጃን አመልካች ነው::

ከተመልካች በስተቀኝ ትንሽ ወረድ እንደማለት ያለው ቁ.2 ክብ ሳጥን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቦታን ያመለክታል:: ከዚሁ ክብ ሣጥን ተያይዞ ወደ ታች የሚወርደው ቀስት የጌታ ኢየሰሱ ከሰማያዊ ዙፋኑ ወደ ምድር ወርዶ መወለዱን የሚያመለክት ነው::

ከታች ግራና ቀኝ ያሉት ቁጥር 4ሀ እና 4ለ በአምላክ ዙፋን ፊት ግራና ቀኝ ቆመው የሚያገለግሉ መላእክት ናቸው:: በዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 7 ስለዚህ አገልግሎታቸው ተብራርቷል:: ቁ.5 የቁብአን ቀሪዎችን ደረጃ ያሳያል::

በሰፊው ክብ ሬክታንግል ውስጥ ያለችው ትንሽዋ ባለ 6 ቁጥር ሣጥን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከክብራማ ቦታ እጅግ በጣም እራሱን ዝቅ አድርጐ በፊልጵስዮስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 6-8 በተገለጸው መልኩ ወደ ዓለማችን መውረዱን የሚገልፅ ነው::

ስድስት ቁጥር በውስጡ የተጻፈበት ሬክታንግል ቁጥር 7 ነው:: ይህ በቁጠር 7 የተመደው ትልቁ ሬክታንግል በዚህ ምድራዊ ዓለማችን ውስጥ ሌሎች በጐች ተብለው የሚጠሩትን ልበቢሶች ደረጃ የሚያመለክት ነው::

ከተመልካቹ በግራ፣ ከስዕሉ አንፃር በቀኝ በቁጥር 3 የተመለከተው ክብ ነገር ኢየሱስ ሞቶ ከተነሣ በኋላ በአባቱ ቀኝ መቀመጡንና ከእርሱም ጋር ከምድር 144.000 ነገሥታት መርጦ

እንዲነግሡ መፍቀዱን አመልካች ነው:: የቀስቶቹ ወደ ክብ ቁጥር 3 ከታች ወደ ላይ መቀሰት ይህንኑ አመልካች ነው:: እነዚህ 144 ሺህ ነገሥታት የተባሉት ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ከተመለሰ በኋላ የመለመላቸው መሆኑን ዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 4 እስከ 8 ያመለክታል:: እነዚህ ይህንን ትልቅ ሥልጣን ያገኙት በዚህ ባለፉት 2000 ዓመታት ውስጥ ብቻ ነው ይላሉ ምስክሮቹ::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መላእክት ጥንት መሬታችን ከመፈጠርዋ በፊት ጀምሮ ያገለግሉ እንደነበር ኢዮብ ምዕራፍ 38 ከቁጥር 4-8 ይገልጻል:: መሬታችን በተፈጠረች ጊዜ እጅግ በጣም የደስታ ዝማሬ እንዳሰሙ ታውቋል:: እነዚህ እንዲህ ባለ መልኩ ሌት ተቀን ዝንተ ዓለም እያገለገሉ ናቸው የተባሉት መላእክት በዚህ በቅርቡ 2000 ዓመታት ውስጥ 144 ሺህ ያገኙትን ማዕረግ በፍጹም አላገኙም:: ይመኛሉ፣ ይፈልጋሉ፣ ግን እንዲሾሙ ወይም እንዲሻሻሉ አልተደረጉም:: እንኳን የእነዚህ የ144 ሺህን ማዕረግ ማግኘት ክብራቸውን በዓይናቸው ብቻ ማየት እንኳን እንደሚመኙ ከቅዱስ ጽሑፍ እንረዳለን ይላሉ ምስክሮቹ:: ስለዚህ 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 12 እንደሚከተለው ይጠቅሳሉ:- «ይህንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ::» የይሖዋ ምስክሮች ቴኦክራቲክ (Theocratic) የሚሉት እንዲህ ያለውን አሠራር ነው:: ይህ ፍጹም አምባገነናዊ፣ ቆራጭ ፈላጭ ወሰን አልባ ሥልጣንን ያመላክታል:: ታዲያ በመካከላችን የስልጣን ልዩነት የለም የሚባለው ምን ተይዘው ነው? እንዲህ ያለው አሕዳዊ ከላይ እስከታች አምባገነናዊነትን የሚያንፀባርቅ ነው::

ከዚህ ዓይነት አድሎ የተነሣ ሣይሆን ይቀራል እግዚአብሔርን የሚወጉ መላእክት የተፈጠሩት? የእነሱን ሐሳብ



ስለአላወቅነው ነው እንጂ ምርሮአቸው፣ ከዚህስ ሞት ይሻላል ብለው የተነሱ ይመስላል:: ራዕይ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 7-12 እነዚህ መላእክት ይዋጉ እንደነበር ይገልፃል:: ወደ ነቢዩ ዳንኤልም መልእክት ለማድረስ የተላከው መልአክ በውጊያ ላይ ነኝ እና ቶሎ ልሂድ እንደአለው ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 10 ቁጥር 20 ያስረዳል:: ከዚህም መራራ ውጊያቸው የተነሣ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4 ቁጥር 4 እንደምንአየው ምድራችንን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው እያስተዳደርዋት ነው ተብለናል:: እነዚህ አፈንጋጮች ሰይጣን ይባላሉ:: ሰይጣን ማለት ተቃዋሚ ቡድን ማለት ነው:: ዘንዶ ተብሎም ይጠራሉ:: የእሩቅ ምስራቅ ነፃ አውጭዎች ታይሜል ታይገር እያሉ ለራሳቸው ስም እንደአወጡ አይነት መሆኑ ነው:: ጃፖኖችም ቀይ ዘንዶ የሚባሉ ነበራቸው:: በአገራችንም ጥቁር አንበሳ የሚባል አሻፈረኝ የሚል የአርበኛ ቡድን እንደነበር የሚታወስ ነው:: ይህ እንግዲህ የላይኛውም እንደታችኛ ው የታችኛውም እንደ ላይኛው የሚለውን የአበው አባባልን ያስታውሰናል:: በማንኛውም የጥንት ቤተክርስቲያናት ውስጥ ብትገቡ በቤተክርስቲያኑ ግድግዳዎች ላይ የእነዚህ ሠራዊተ ሰማይ ውጊያን ያሳያል:: ቀራርቶና ፉከራው ሁሉም ለየራሳቸው በየወኪሎቻቸው ያሰማሉ:: አንዱ አሸናፊው እኔ ነኝ ይላል፣ ክርስቲያኖች አሸናፊው እግዚአብሔር ነው ብለው ያምናሉ:: የይሖዋ ምስክሮችም የሚያሸንፈው ይሖዋ ነው፣ በአርማጌዶን ጦርነት ይላሉ:: ራዕይ 16 ከቁጥር 14-16 ተመልከቱ::

በሌላ መልኩ ስንመለከት ተፈጥሮ ነው:: የተፈጥሮ መሠረት ልዩነት ነው:: ይህንን በሣይንስም ሆነ በመንፈሳውያን ርዕዮት አቅጣጫ በመግቢያችን የምንመለከተው ይሆናል::

## መግቢያ

የተፈጥሮ መሠረት ልዩነት ነው:: ተፈጥሮ መሠረትዋ ልዩነት አልባ አይደለችም:: ተፈጥሮ ተመሣሣይነት ወይም ፍጹም አንድነት የላትም:: ስለሆነም ምንም ይሁን ምን ወይም ማንም ይሁን ማን አንድ ፍጡር አንድ ተቃራኒ ይኖረዋል:: ተፈጥሮ በልዩነት ላይ የተመሠረተች ለመሆኑ እራሱ የሰው ልጅ አንድ ምሳሌአችን ይሆናል::

ይህንን ጉዳይ ከወንዴና ሴቴ ጾታ አንፃርም ካየን እውነታው ግልፅ ነው:: ወንዴና ሴቴ ፆታ መሠረታዊ ልዩነታቸው አንዱ ማድረግ የሚችለውን ሌላ ማድረግ አይችልም:: ማርገዝና መውለድ የምትችለው ሴቴ ጾታ ብቻ ናት:: ወንዴ ጾታ ይህንን ማድረግ አይችልም:: ስለሆነም የሰው ዘር የማትረፍ ተግባር መሠረቱ የተጣለው በተፈጥሮ ልዩነት ነው::

የተፈጥሮ መሠረት በልዩነት ላይ ነው ስንል አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ልዩነት ለማመልከት ብቻ ሣይሆን አለሌላ የማንኛውም ፍጥረት በተናጥል መሠረቱ ልዩነት ላይ የተገነባ መሆኑንም ጭምር ለማመልከት ነው:: ይህንን ጉዳይ የአንድ ሕፃን ምሳሌን ወስደን እንመልከት:- አንድ ሕፃን ተወልዶ ወደዚህች ዓለም ሲመጣ በሕይወት ሊያቆየው የሚያስችለውን ሙለ ሴሎችን ወይም ሕዋሳትን ይዞ ይወለዳል:: እነዚህ አብሮ የተወለዱት (Cells) የአካሉ ሴሎች ሁለት ዓይነት ተግባር ሲያከናውኑ ይታያሉ:: ይህ ተግባራቸው የአንዱ ተግባር የሌላውን ተግባር የሚቃረን እንደሆነም እንረዳለን:: ለምን ቢባል የተፈጥሮ መሠረት የተገነባ በልዩነት ላይ ስለሆነ ነው:: ከዚህ



አንፃር መሠረታዊ ልዩነት ቢኖረንም በዚህ ልዩነት ላይ ጊዜያዊ አንድነት መሥርተን እንኑር የሚሉን ይመስላል::

ከላይ የተጠቀሰው የሕፃኑ (Cells) ሕዋሳት ልዩነት በተግባር ሲገለጡ አንዱ ሕፃኑን የሚያሳድግ ሴሎች መፍጠር ሲሆን ሌላኛው ተቃራኒው ሴሎች ደግሞ ስራቸው እነዚህ የተፈጠሩትን የሕፃናትን ሴሎች መግደል ነው:: አንዱ ሲፈጥር ሌላው ሲገድልበት በ7ኛው ዓመት መጨረሻ ላይ አብረው የተወለዱት የሕፃኑ ሴሎች ተገድለው ያልቃሉ:: ስለሆነም ሂደቱ እየቀጠለ በየሰባት ዓመት መጨረሻ ሙሉ የአንድ ሰው ሴሎች ተገድለው አልቀው አዲስ በተፈጠሩት የሚተኩ ይሆናል:: ይህ ከሜዲካል ሣይንስ አንፃር የተረጋገጠ እውነት ነው:: ስለዚህ በሕፃንነቱ፣ በወጣትነቱ፣ በጉልማሳነቱ ያምር የነበረው ሰው እንደዚህ ባሉት የተፈጥሮ ልዩነት ተቃርኖ የተነሣ ከሰባ ዓመት ዕድሜው በኋላ ፊቱም ሆነ ሞላው ሁኔታው እንደወረቀት የተጨማደደ የሚመስል ይሆናል:: የተፈጥሮ መሠረት ልዩነት ነው ስንል ይህንንና ይህንን ከመሳሰሉት አንፃር ነው::

ይህንን ነገር ከሣይንስ ምሑራን አንፃር ብቻ ሣይሆን ከሥነ መለኮታውያን አንፃርም ከተመለከትን ተመሣሣይ ሐሳብ እናገኛለን:: እንደሥነመለኮታውያን ትምህርተ ሃይማኖት ከሆነ እንደዚህ ያለውን ልዩነት እና ተቃርኖ የፈጠረው እራሱ እግዚአብሔር ነው ይሉናል:: ሙሴ የተባለው የአይሁድ ሃይማኖት መሥራች በመጽሐፉ ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 15 ላይ ተፈጥሮን በተባዕታይና በእንስት መስሎ እንደሚከተለው ይላል:: «በአንተና በሴቲቷ መካከል፣ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነት እፈጥራለሁ::» መሠረታዊ ልዩነትን እፈጥራለሁ

ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ነው ተፈጥሮ ልዩ ነው የምንለው፡፡ በአግባቡ ካልተያዘ ከዚህ ልዩነት የተነሳ ጠላትነት ይፈጠራል፡፡

በዚህ በጠላትነት ሂደት ወቅት አንዱ ሌላውን የማሸነፍ ሁኔታ ይከሰታል፡፡ ስለሆነም የበላይና የበታችነት ልዩነት ተፈጠረ ማለት ነው፡፡ የበላይ የሆነው አሸናፊው መደብ ተሸናፊው እንዳያድግ ሁልጊዜ የበታቹ እንዲሆን ይጨቁነዋል፡፡ በሙሴ አነጋገር «እራሱን ይቀጠቅጧል» ተሸናፊውም ቢሆን ከታች ሆኖ መሠረቱን ለመናድ ይፍጨረጨራል፡፡ በአንድ ወቅት ሲሣካለትም በሶካና የተመሠለው መሠረቱን ንዶ ይገለብጠዋል ወይም ይጥለዋል፥በተራው ራስ ቀጥቃጭ ወይም ጨቋኝ ይሆናል፡፡ ስለሆነም እንዲህ ባለው የተፈጥሮ ሂደት እራስ ቀጥቃጭ የነበረው ሰኮና ነካሽ፥ሰኮና ነካሽም እራስ ቀጥቃጭ ይሆናል፡፡ «የላይኛውም እንደታችኛው ነው፣ የታችኛውም እንደላይኛው» ይሏችኋል ይኼው ነው፡፡

<u>ሰው ከተፈጥሮ አንዱ ነው</u>

ሰው ከተፈጥሮአዊ ቁስ አካል አንዱ ነው፡፡ ቁስ አካላት ስንል ሰውን ጨምሮ መሬት፣ ሰማይ፣ በውስጣቸው ያሉት ጠጣር ፍጥረታትን ሁሉ ጭምር የሚያጠቃልል ነው፡፡ ጠጣር ያልሆኑት እንደ ውሃ ያሉት ፈሳሾችና የሚተኑ ጋዞች ሁሉ ቁስ አካላት ናቸው፡፡ ጋዝ ሲተን በዓይን አይታይም፡፡ ቢሆንም የማይታይ ቁስ አካል ነው፡፡ ይህንን ሰው የተባለውን ቁስ አካል እግዚአብሔር የፈጠረው በመልኩ ነው ይለናል ሙሴ፡፡ ዘፍጥረት 1 ቁጥር 27 ተመልከቱ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እንደ ሰው ነው፣ ሰውም እንደ እግዚአብሔር ነው፡፡ ይህ አባባል ትልቅ ድፍረት



ይመስላል፣ ግን እውነታው እንዴት እንደሆነ ቀጥለን እንመልከት፡-

አንድ የውቅያኖስ የውሃ አካል አለ እንበል፡፡ ከዚህ የውቅያኖስ ውሃ በተወሰነ ደረጃ በፀሐይ ኃይል የሚተንበት ውሃ ወደ ላይ ወጥቶ ከቀዘቀዘ በኋላ ተመልሶ በዝናብ መልክ ይወርዳል፡፡ በዚህ መልኩ በዝናብ የወረደው ውሀ በአንድ የመስታዎት ግድግዳ ላይ በወጨፎ መልክ ይዘንብበታል፡፡ አሁን በመስታዎቱ ላይ የሚታየው የውሀ እንክብሎች አሉ፡፡ ይህንን በመስታዎቱ ላይ የዘነበውን ውሃና ያንን ትልቁን የውቅያኖስ ውሃ ወስደን በላቦራቶሪ ብንመረምራቸው ፍጹም አንድ ዓይነት ሆነው እናገኛለን፡፡ የተፈጥሮ ልዩነት አይታይባቸውም፡፡ የውቅያኖሱ ውሃ የመስታዎቱን ውሃ በራሱ መልክ ፈጥሯል ለማለት እንደፍራለን፡፡ ከዚህ አንፃር በፍጹም አንድ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ልዩነት የላቸውም ማለት አይደለም፡፡ ልዩነቱ ግን የዓይነት ሣይሆን የመጠን ብቻ ይሆናል፡፡ የውቅያኖስ ወሃ ትልቅ ነው፡፡ ትልቅነቱ የትዬለሌ ነው፡፡ በንፋስ፣ በፀሐይ፣ በሌላም ሌላ ነገር ቢተን አያልቅም፡፡ የተነነውም ቢሆን በዝናብ መልክ ተመልሶ ወደወቅያኖሱ ይገባል፡፡ በመስታዎት ላይ የተረጨው ግን በንፋስ፣ በፀሐይ እና በመሳሰለው ቶሎ የሚጠፋ ነው፡፡ ዘላለማዊነት የሌለው ጊዜያዊ ጤዛ ነው፡፡ ልዩነቱ ይኸው ብቻ ነው፡፡

እነዚህ የጥንታውያን ሰዎች እራሳቸውን ትንንሽ እግዚአብሔሮች አድርገው የሚገምቱት ከዚህ አንፃር ሣይሆን ይቀራል ትላላችሁ? በመጽሐፈ ሙሴ ዘፍጥረት ምዕራፍ 4 ቁጥር 26 ላይ የዚያን ጊዜ ዘመን ሰዎች እራሳቸውን

እግዚአብሔር ብሎ መጥራት ወይም መሰየም እንደጀመሩ የሚገልፀው ይኸንኑ የሚያረጋግጥ ነው:: በግብፅ አገርም የግብፅ ፈርኦኖች እንደ እግዚአብሔር ይታዩ እንደነበር (PHARAON was viewed as a god, the living Horus) ከታሪክ እንረዳለን:: ኢ ን ሣይት ኦን ኢስክሪፕቸር ቮልዩም 1 ገጽ 532 የ1988 እትም እ.ኤ.አ. በዓለም አቀፍ ተማሪዎች ማህበር የታተመውን ተመልከቱ::

ከዚህ በላይ እንደአየነው ከሆነ በዚህ ዓለም ላይ ካሉት ከሁሉ የበለጠና የበላይ ሰው ብቻ ነው:: ይህ ሰው ከሚታየውና ከማይታየው ቁስ አካላት እንደተፈጠረ በሣይንስም እንረዳለን:: በሰው ውስጥ ብዙ የማይታዩ፣ እንደ ኤሌክትሪክ ያሉት ቁስ አካላት አሉ:: እስትንፋሳችን እራሱ በባዶ ዓይናችን አይታየም:: ሙሴም ቢሆን በዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ 2 ቁጥር 7 ላይ ሰው ከሚታየውና ከማይታየው ቁስ አካላት እንደተፈጠረ ይገልፃል:: ስለሆነም የሚታይ ቁስ አካል እና የማይታይ ቁስ አካል የተባሉ አካሎች አሉ:: እግዚአብሔር ከማይታዩት ቁስ አካላት አንዱ ነው:: ይህንን እውነታ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ቁጥር 40 ላይ «ሰማያዊ አካል አለ፣ ምድራዊ አካል አለ፣ ነገር ግን የሰማያዊ አካል ክብር ልዩ ነው፣ የምድራዊውም አካል ክብር ልዩ ነው» ይላል ሰው ግን ከእነዚህ ሁለቱ አካላት የተዳቀለ ነው:: የምድራዊ አካልና የሰማያዊ አካል ውህድ እንደሆነ እንመለከታለን:: ሐዋርያው ጳውሎስም ታሪክን በማጣቀስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17 ቁጥር 28 ላይ የዘመኑ የግሪክ ፈላስፎች ከላይ ከተገለፀው አንፃር ከእግዚአብሔር ጋር የሰው ዘር ብቻ ዝምድና እንደአለው መግለፃቸውን ያስረዳል::



ስለዚህ በፈጥሮ መሠረታዊ ልዩነት ላይ የተገነባ ይህ የሰው ዘር ከሁሉ የበለጠ ማሰብ ስለሚችል በማሰብ ኃይሉ በመቀጠም ልዩነት መፍጠር መቻል አለበት:: ልዩነት መፍጠር መቻል አለበት ሲባል በተፈጥሮ ልዩነት ላይ የተመሠረተውን የቁስ አካላትን ልዩነትና አንድነት አስተውሎ የአንድነት ጉኑን ማስፋት መቻል አለበት:: ተፈጥሮአዊ የልዩነት መሠረቱን ተቀብሎ ከተፈጥሮ መሠረታዊ ልዩነት በተውጣጣውና በተቀመረ ልዩነቱን ማጥበብ መቻል አለበት ማለት ነው:: ሰው ከፈለገ ይህንን የማድረግ ችሎታ አለው:: ስለሆነም አእምሮን ከዚህ አንፃር ማሰልጠን፣ ማንቃት፣ ማሠራት አስፈላጊ ነው:: ከዚህ አንፃር ልዩነት ሲጠብ ሰው በልዩነት አንድነት በተመሠረተው ኃይል ተአምር መሥራት እንደሚችል ይታመናል::

አንቲ ማተር የሚባል ነገር አለ:: አንቲ ማተር (Anti Matter) ፀረ ቁስ አካል ማለት ነው:: ማንኛውም ቁስ አካል ከፀረ ቁስ አካል ከተገናኘው ተቀጥሎ ይጠፋል:: ነገር ግን ሣይንቲስቶች ይህ ትልቅ የኃይል አምቅ ያለው ፀረ-ቁስ አካል የተፈጥሮ ሕጉና አሠራሩ ታውቆ በዘዴ ከቁስ አካላት ጋር ከተቀናጀ ታይቶ የማይታወቅ ተአምር እንደሚሠራ በሣይንቲስቶች ይታመናል:: ጥናቱም እየተደረገ ነው:: በሌላ በመንፈሳዊ አባበል ፅድቅና ኩነኔን፣ ክፉና ደግን አስተውሎ ከክፋት ደግነትን መርጦ ክፉን በደግ ማሸነፍ የመቻል ጉዳይ ነው:: ከመንፈሳዊ አባባል አንፃር አንድ ሰው ፀደቀ የሚባለው ክፋትን በደግነት ያሸነፈ ከሆነ ነው:: እነዚህ ነገሮች የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው:: ስለዚህ መንፈሳዊያን ነን የሚሉ፣ የሕዝብ ሰባኪዎች ወይም መንፈሳዊ መሪዎች ነን

የሚሉ ሕዝብን ከዚህ አንፃር ማንቃት አለባቸው እንጂ ልዩነት ፈጥሮ የልዩነትን እሳት ለማንደድ ማራገብ የለባቸውም:: እንደዚህ ያለው አሳዛኝ ሁኔታ ግን በዓለማዊነት ከተፈረጁት ይልቅ መንፈሳዊያን ነን በሚሉት በአንድ አንድ የመንፈሳዊ ድርጅት መሪዎች ሲራገብ እየተስተዋለ ነው::

ተፈጥሮ እራስዋን በተለያየ መልኩ ታንቀሳቅሳለች:: ከተፈጥሮ አንዱና በችሎታ የበላይ የሆነውም ሰው ተፈጥሮን ለቀናነት ለማዋል ተንቀሳቅሷል:: ስለሆነም ባሕልን ፈጥረዋል:: በዚህ በባሕሉ ለገራውም ሆነ ላልገራቸው ተፈጥሮአዊ ነገሮች ትርጉም እየሰጠ እራሱን በመንፈሳዊ እሴቶችም ሆነ በሥጋዊ ሕይወት ለማቆየት ብዙ ነገሮችን ፈጥረዋል:: ሰው በእነዚህ በፈጠራቸው ነገሮች መልሶ እራሱን አልቋል:: አንድ አንዱም እነዚህ የፈጠራቸው ባሕሎች እራሱኑ መልሰው ሲገዙት ይታያል:: እራሱንም እያስገዛ ነው:: ለዚህም ነው ጐጂ ባሕል እንደአለ የሚነገረው:: ከባሕል ዘርፎች አንዱ ሃይማኖት ነው:: ይህ የባሕል ክፍል የሆነው ሃይማኖት ቅርጽ ተበጅቶለት ከጐጅም አንፃር ሆነ ከበጐ አኳያ ራሱን በጉልህ አንፀባርቋል:: ስለሆነም የሰው አመለካከት ከእነዚህ ጐጂ ባሕሎች በላይ ካልሆነ ከፍተኛ ችግር ያስከትላል:: ለራሱና ለዘሮቹም መጥፋት መከንያት ሲሆን ይችላል::

የሰው ልጅ በፈጠረው ባሕላዊ አመለካከት የመጀመሪያ በኩር ልጄን በእሳት አቃጥዬ ለአምላኬ መስዋእት ካላቀረብኩ ሌሎቹ አያድጉልኝም በሚል ሕሳቤ ጉዳት አድርሰዋል:: ይህንን አመለካከቱን ያልተጋሩትንም እንደርኩሶች እያየ የመጠፋፋት ምክንያቶችን ከብሪት ጭረዋል:: በዚህ ጎጂ በሆነው የሃይማኖት



ባሕል በዓለም ላይ ብዙ ጉዳቶች እንደደረሱ ከታሪኮች ገጽ እናነባለን:: የቅርቡን ታሪክ ለአብነት ለመጥቀስ ካስፈለገ በጀርመንና ቤልጂግ ሚስዮኖች ከጥቅም አንፃር የተቃኘ ጐጂ ባሕል የአፍሪካን ልጆች እንደአጨራረሰ በታወቁት ታላላቅ ሰዎች (Panel by eminent personality about Ruwanda Genocide) የቀረበ ሪፖርት ይህንኑ ያሳያል:: ስለዚህ እንደሚከተለው ለማለት እንችላለን:-

<u>ሐይማኖትን ለጎጂ ባሕል ማዋል</u>

የጀርመንና ቤልጅግ ሚሲዮኖች፣
በጎሣ ቅራኔ እንዲጨራረሱ፣ ሑቱና ቱሲዎች፣
ቱሲን በማቀፍ አፍቅሮ፣
ብዙሐትን ሑቱ ቆጥረው እንደ ደንቆሮ፣
ቱሲ የበላይ ሆኖ እንዲያስተዳድር፣
ብዙሐትን ሑቱ አድርጐት ገባር
ከ1800 ዓ.ም. ማገባደጃ ጀምሮ፣
የጀርመንና ቤልጅግ ሚስዮኖች ተንኮል ቀምሮ፣
የአናሣ ቱሲ ጎሣ የማንነቱ አሻራ፣
እንዲሆኑ አደረጉት፣ የብዙሐን ሑቶች መብት የሻረ::
ሌላ ሌላውን እንዲያርድ፣
ከዚያም ወዲያ አዘቅት እንዲያወርድ፣
በዘረኝነት ስብከት አድርገውት፣
ሁቱን የዲያቢሎስ ልጅ፣
ለመጨረስ ተነሣ የቱሲን ዘር ልጅ::
ይባስ ብለው ልዩነቱ ጉልቶ እንዲወጣ፣
የጎሣቸው ማንነት በመታወቂያቸው ላይ ወጣ::

ሁቱና ቱሲዎች ይህንን ደባ ሣይገነዘቡ፣
እንዴት እንደሆነ በደንብ ሣያስቡ፣
ችግሩን ተገንዝበው መፍታት ሲገባቸው፣
በጥቅማ ጥቅም ተደልለው፣ ማሰብ ተሳናቸው::
ስለዚህ አንዱ ጐሣ ለሌላው ጐሣ ሆኖ ጠላት፣
አምርረው ተነሱ እርስ በእርስ ለመጠፋፋት::
ከዚህ አንፃር የምንገነዘበው፣ የከፋው ጐሣ ሆዱ ሲብስ፣
ጭካኔው አይባልም፣ ከዚህ በመለስ::
ስለሆነም እጅግ የሚሰቀጥጥ፣
ሁቱዎች ጀመሩ፣ የቱሲን ሕፃናት በሙቀጫ መውቀጥ፣
ለመቆየት ከፈለገች በሕይወት፣
ቱሲን ያገባች፣ ሁቱዋ እናት፣
የገዛ ልጆችዋን እንድትአርድ፣
ሁቱዎች ጀመሩ፣ ማስገደድ::
የቱሲ ነፍሰጡር ሴት፣
በሣንጃ ሆድዋ ሲሰነጠቅ ማየት፣
ሚስቱ ተደፍራ፣ በባልዋ ፊት ስትገደል፣
ተገድደው ልጆቿ እንዲያዩ፣ አባታቸው ሲቃጠል፣
በቆንጨራ ፈንታ በጥይት እንዲገደል፣
የሁቱዎች ከቱሲዎች ጉቦ መቀበል፣
በመሳሰሉት ጭካኔዎች ሁቱዎች አምርረው፣
ሕብረታቸውን አስተባብረው፣
ሁቱዎች ቱሲዎችን ጨፍጭፈው
በ1960 ዓ.ም. ሁቱ ስልጣን ሲይዝ በካራ፣
ነጮች ቱሲን ከድተው፣ ከሁቱ ተሰለፉ በጋራ::



ይህ በሚሲዮኖች የተዘራ የተንኮል ውጤት፣
ከ1960 ዓ.ም. ጀምሮ፣ ለሁለቱ ጐሣዎች መተራረድ
ሆንዋል ምክንያት::
ከ1960 ዓ.ም. ጀምሮ ሁቱዎች ስልጣን ይዘው በጋራ፣
በ1994 ዓ.ም. ለማጥፋት ተነሱ፣ ቱሲዎችን በካራ::
እንደአየነው ቅኝ ገዥዎች ሆነው የበላይ፣
አንድ ቋንቋ፣ አንድ ባሕል፣
ያላቸውን ሕዝብ በመከፋፈል
በመታወቂያ ላይ እያዩ፣ ቱሲን ሲያጩ ለሹመት፣
ብዙሐኑን ሁቱ አደረጉት ሥራ ፈት::
ጥቂቱን የቱሲ ጐሣ አቅፈው
ብዙሐኑን ሁቱ ነቅፈው፣
በዚህ መልኩ የዘሩት የጥፋት ዘር
ሲያጠፉ ችለዋል 800 የቱሲዎችን ዘር
በዚህ ዘረኝነታቸው የተነሳ
የብዙሐኑ ሁቱ መንግሥት፣
ጨርሶ ለማጥፋት የቱሲን ጐሣ
በ1994 ዓ.ም. ቆርጦ ተነሣ
ይህን ሁሉ እያወቁ፣ አሜሪካና የተባበሩት መንግሥታት፣
በዝምታ ቱሲዎችን አሳልፈው ሰጡ ለጥፋት::
የገዥ መደቦች መግዛት እንዲመቻቸው፣
ለጥቅም ብለው አንዱን ጐሣ
ከሌላ የማበላለጥ ሴራቸው
መሆኑን ስናይ፣ ዘር የሚያጠፋ እውነታ፣
እስኪ አስቡበት ይህን ነገር በእርጋታ!

ሁሌ ማስፈራራት ከሆነ፣ ምክር ለሚለግስ
መካሪ ከጠፋ የሚል ተወው ከዚህ በመለስ
ከዚህ በላይ የተባለውን በውል፣
በአእምሮ ድክመት ከሆነ፣ የማናስተውል፣
ነገሮቹ የማይከሰቱ እየመሰለን፣
እንዲህ ያለ ቅራኔን ሚፍታት ካቃተን
አንዱን አግለለን፣ ሌላውን መምረጥ፣
የአእምሮ ዝቅጠት ነው የሚጥል ወደ ረመጥ::
እኛም ከጀርመኑ ሂትለር ከሩዋንዳው በመለስ፣
ጭላንጭሉን አየን፣ በእንቁፍቱ እንጦርጦስ::
ስለዚህ የባሕልም ሆነ የሌሎች ችግር መፍቻ፣
ከተመሠረተ በጥላቻ ላይ ብቻ፣
እንዲህ ያለ ዲሞክራሲያዊ አመለካከት አልባ፣
መሆኑን ተረዱ፣ ገደል የሚያገባ::

በዓለም ላይ ያሉት ሃይማኖቶች ሁሉ ውሸታሞች ናቸው። የእኔ እምነት ባሕል እና ሃይማኖት ብቻ እውነተኛ ነው። ከማለትም አልፎ ተርፎ አሁን በቅርቡ ትጠፋላችሁ ብሎ ሽብር መንዛት በተፈጥሮ መሠረታዊ ልዩነት ላይ ተመርኩዞ የክፋትን ጉንጉን እያጉሉ የባሠ ልዩነትን ማራገብ ነው:: ይህ መጽሐፍ እንዲህ ካለው አቀጣጪ ጆሮ ያለው እንዲሰማ፣ ዓይን ያለው ዓይቶ እንዲጠነቀቅ የሚረዳ ነው:: ይህ መጽሐፍ በይሖዋ ምስክሮች ሌሎች በጎች እየተባሉ ለሚጠሩት እና ለማንኛውም ዲሞክራሲያዊ አመለካከት ላለው ሰው ሁሉ የቀረበ ነው:: ይህ አመለካከት በጥላቻ ላይ ያልተመሠረተ፣ ሐቅን ብቻ መሠረት ያደረገ አቀራረብ ነው:: እራሳችሁ አይታችሁ፣ አንብባችሁ



ፍረዱ:: አትይ፣ አትቅመስ፣ አትመልከት የተባለው የአሪት ሕግ ቀርቷል:: እውነትን በዓይናችሁ አንብባችሁ ተረዱ:: ስለዚህ:-

እንደ እባብ ብልህ፣
እንደ ርግብም የዋህ፣
መሆን መቻል ሲገባ፣
የዋህ ብቻ መሆን፣ ብልህነት አልባ፣
ግራና ቀኙን አለማጤን በሚገባ፣
ሊሆን ይችላል፣ ገደል የሚያገባ::
በግዙፉ የባሕር ውሃ፣
አስተውሎ መጠቀም የማይችል የዋህ፣
ስለሆነ ጥበብ ያልተካነ፣
ለፍቶ መና ይሆናል፣ ከንቱ የባዘነ::

አንባቢ ሆይ! የዚህ መጽሐፍ ደራሲ እራሱ የይሖዋ ምስክሮች አባልና እንዲሁም የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ የበላይ አካል ተመልካች ወይም ኃላፊ የነበረ ሰው ነው:: ከ31 ዓመታት ያላነሰ የልጅነት ጊዜውን ይኸንኑ ድርጅት ከልብ በማገልገል ያሳለፈ ነው:: ስለሆነም ማን ያርዳ የቀበረ፣ ማን ይመስክር የነበረ እንዲሉ ስለ ይሖዋ ምስክሮች ለማወቅ የሚፈልግ ሁሉ የዚህ ድርጅት ምስጢር ከተረዳው ሰው ምስክርነት መስማቱ ወይም አንብቦ መረዳቱ ይመረጣል::

መልካም ንባብ
ደራሲው
አበበ በዛብህ
እ.ኢ.አ 1998 ዓ.ም

# ሽብር ነዥ ድርጅት

## ምዕራፍ አንድ

ሰዎች ሰዎችን ከሚያሞኙበት ዘዴዎች አንዱ እምነትን ወይም ሃይማኖትን ሰበብ በማድረግ ነው:: በሃይማኖትም ሆነ በሆነ ርዕዮት አማካኝነት የሚሞኙ ስለርዕዮት ጉዳይ ጥልቅ እወቀት የሌላቸው ናቸው:: ስለዚህ ሁሉም ወይም አብዛኛው ሕዝብ ይህችን አለማችንን የፈጠረው አንድ ፈጣሪ አለ፣ በሚለው መልካም የእምነት ባሕል የሚመራ ነው:: ይሁን እንጂ ከላይ እንደተባለው በቅንነት የፈጣሪን መንገድ አግኝቻለሁ በማለት የተነገረውን በእምነት ብቻ ተቀብለው ሣይመራመር የሚከተል ሕዝብ ይበዛል::

ስለዚህ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በየወቅቱ የተነሱት ብልጣብልጥ የርዕዮት ነጋዴዎች አትመራመር የሚል መፈክር በማሽከም እኛ የእግዚአብሔር ወኪሎች ነንና የነገርንህን አምነህ ተቀበል እያሉ ብዙዎችን ሰዎች በፈጠሩት ሽብር ነዥ ድርጅቶቻቸው አማካኝነት አታልለዋል::

የዛሬ 190 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. «ይህች ዓለማችን የምትጠፋበትን ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ከቅዱሳን መጻሕፍት ተረድቼአለሁ:: እግዚአብሔርም ይህንን እውነት እንድሰብክ አዞኛል:: በኖህ ዘመን የኖህን የምስክር ቃል ያልሰማው የዚያ ዘመን ትውልድ መጥፋቱን አትዘንጉ! የዚያን ዘመን ሞላው ሕዝብ ሲጠፋ የኖህ ስምንት ቤተሰቦች ብቻ የምስክርነት ቃሉን ሰምተው ወደ መዳኛው መርከብ እንደገቡና እንደዳኑ ሁሉ፣ ዛሬም በኖህ መርከብ በተመሰለችው

የእግዚአብሔር ምድራዊ ድርጅት ውስጥ ገብታችሁ እራሳችሁን አድኑ» ብሎ የሚሰብክ አንድ ግለሰብ ተነሣ! ይህ ግለሰብ ዊሊያም ሚለር ይባላል::

ከላይ እያየን እንደመጣነው ሕዝብ የሚድንበት የተባለው ድርጅት እራሱ ዊሊያም ሚለር ከጥቂት ግብረ አበሮቹ ጋር ያቋቋማት ድርጅት ናት:: በዚህ ድርጅት ስም እየተጠቀመ ዊሊያም የሚከተለውን ሽብር ሙንዛት ጀመረ::

«ጥንት በኖህ ዘመን እግዚአብሔር ሕዝብን ከውሃ ጥፋት ንስሐ በመግባት እንዲድኑ ለ120 አመታት በመታገስ እድል ሰጥቶአቸዋል:: ዛሬ ግን ከጥፋት እንድንድን እግዚአብሔር የሰጠን የንስሐ መግባት ጊዜ 28 አመት ብቻ ነው እያለ ዊልያም የዓለም ጠቅላላ ጥፋት መቃረቡን አበክሮ በመስበክ ሕዝቡን ማሸበር ጀመረ:: ዊልያም ይህንን የሽብር ስብከቱን መስበክ የጀመረው በ1816 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ነው:: ስለዚህ ዊሊያም ጠቅላላው የዓለም መጨረሻ በ1844 ዓ.ም. እንደሚሆን በአፅኖት ሰበከ::

ከዚህም የተነሣ ምድረ የሃይማኖት እሥረኛ እየፈራና እየተጃጃለ (ከ1816+28) ከ1844 ዓ.ም. በፊት ከጥፋት ለመዳን ወደ ዊልያም ሚለር ድርጅት መጉረፍ ጀመረ:: ሁል ጊዜ እንደዚህ የሚለው የዊልያም ሚለር ስብከት በጆሮአቸው እያቃጨለ እረፍት ይነሳቸው ነበር:፦ «ገና ጊዜ አለን ብላችሁ ካቅማማችሁ፣ ከአሁኑ ለንስሐ የሚገባውን የሥራ ፍሬ በተግባር ካላስመሰከራችሁ፣ የሰውን ልብ በሚያነብ ጌታ ፊት ጥፋተኞች ናችሁ::» ስለዚህ ምዕመናን (ምድረበግ) ሁሉ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፣ እውቀት ያለው በእውቀቱ፣ ጉልበት ያለው በጉልበቱ



ለዊልያም ድርጅት ሁለገብ እርዳታንና አገልግሎትን ስለአበረከቱ የዊልያም ድርጅት እጅጉን ከበረ::

ዊልያም በሰበካቸው ስብከት መሠረት እምነው ከዓለም ጥፋት እራሳቸውን ለማዳንና የመዳን ዋስትናንም ለመጨበጥ «ሌባ ወደማይሰርቀው፣ ብል ወደ ማይበላው፣ ዝገትም ወደ ማይኖረው የቅርስ ዋስትናን ማከማቸታቸው ነው::

ከላይ በተገለፀው መልኩ ዊልያም ከተሰባኪ ምእመናኖቹ ሁለገብ እርዳታን በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ስለአገኘ ከበረ:: የዊልያም ሚለር ምእመናኖች ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ከማሰብ የበለጠ ለዊሊያም ድርጅት ማሰብ ጀመሩ:: ከላይ በተገለፀው መልኩ ከዊልያም ሚለር ስብከት አንፃር አቋማቸውን ካስተካከሉ በኋላ የመዳን ዋስትናን ተስፋ የጨበጥን የብርሃን ልጆች ነን ብለው በማመን ያ የተዘጋጁለት የጥፋት ቀን መቼ እንደሚደርስ እንደ እርጉዝ ሴት ቀን መቁጠር ጀመሩ:: ጊዜያችንን ለግል ሥጋዊ ሃብት ማከማቻ ላይ ከምንአውል የሚታየው የእግዚአብሔርን ምድራዊ ድርጅትን በመርዳት ላይ እናውል እያሉ የዊልያምን ድርጅት በመርዳት ላይ አብዛኛውን ጊዜአቸውን አጠፉ::

የዚህ ጽሑፍ አንባቢ ልብ እንዲል የምጠየቀው ዊልያም ሚለር ምንም ወጪ ሣያወጣ በቃላት አጠቃቀም ብቻ የሰዎችን አእምሮ በማዘዝ በሰው መነገድ መጀመሩን ነው:: ከዓለም ሀብት ማፍሪያ መሣሪያዎች ሁሉ የበለጠ ሰው ነው:: ከምንም ተነስቶ ዊልያም ሀብት ያገኘው ከላይ በተገለፀው መልኩ በሰዎች በመነገድ ነው::

አንድ ነጋዴ በልዩ ልዩ ምክንያት ሊከስር እንደሚችል ሁሉ ዊልያም ሚለርም ስብከቱን አዳምጦ የሚቀበል ሰው ካጣ ይከስራል:: ተሰባኪ ጠፋ ማለት የዊልያም ድርጅት ውድቀት ሆነ ማለት ነው:: ይህንን ነገር ዊልያምና አጋሮቹ በደንብ አወቀውታል:: ስለዚህ ዊልያምና አጋሮቹ መንታ ትርጉም ባዘሉት ቃላት መጠቀምን ተካኑ:: ከመንታ ትርጉም ቃል ግን አንደኛውን ትርጉም ብቻ እያጕሉ በአፈጮማ ሰባኪዎቹ ዊሊያም ሕዝቡን እንደሐሸሸ ማደንዘዝ ጀመረ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጊዜ ጊዜን ወልዶ ለዊልያም ሀብታም መሆን ምክንያት የሆነችው የዓለም ጥፋት ይሆናል የተባለችው ዓመት መቃረብ ጀመረች:: በትንቢቱ መሠረት የጥፋቱ ዓመት ተቃረበ፤ 1843 ዓ.ም. ሆነ:: በዚህን ጊዜ ዊልያምና ተባባሪዎቹ እጅግ ተጨነቁ:: በዚህ ባልነው አመት የዓለም ጥፋት ባይሆንስ? ሲል ዊልያም ተጨነቀ፤ በአንፃሩ ተራ ምእመናኖቹ በትንቢቱ መፈፀም መቃረብ እጅግ ፈነደቁ:: በዚህ መልኩ የጀሌዎቹ መፈንደቅ ዊልያምንና አጋሮቹን እጅጉን አሳሰባቸው:: እንደተባለው በ1844 ዓ.ም. የዓለም ጥፋት ካልሆነ ምን እናድርግ? የሚል ሃሳብ አስጨነቃቸው::

ከዚህ በላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ወደሚጠቀሙበት መንታ ትርጉም ወደ አዘለው የቃላት አጠቃቀም ዘዴአቸው ዞር አሉ፤ ምዕመናኖቻቸው እንዳይበተኑ የማስተባበያ ፍልስፍና መቀመር ግድ ሆነባቸው::

ስለዚህ በዚህ መልኩ በ1844 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. እንደተባለው ዓለም ካልጠፋች የምእመናኖቻቸውን አእምሮ የሚያሳምኑበት (የሚያዙበት) ፍልስፍና መቀመር ጀመሩ::



<u>በ1844 ዓ.ም. ዓለም ባለመጥፋትዋ የተሰጠ ማስተባበያ</u>

ብዙውን ጊዜ የፖለቲካ አምባገነኖች፣ እንዲሁም እንደ ዊልያም ሚለር ያሉት የሃይማኖት መሪዎች ሁለት መንታ ትርጉም ባዘሉት ቃላት እየተጠቀሙ የአንደኛው ትርጉም የሃሳብ መስመር የማያዋጣቸው በሆነ ጊዜ ወደ ሌላኛው የትርጉም የሃሳብ መስመር ይዞራሉ:: የተመረጠው አንደኛው የሃሳብ መስመር ሣያዋጣቸው በቀረ ጊዜ፣ እንደዚህ ማለታችን ሣይሆን እንደዚህ ማለታችን ነው ይላሉ:: በዚህም ተርታውን ምእመናኖቻቸውን ያሞኛሉ:: ወይም ደግሞ ከሁለት ትርጉሙ ቃላት አዘል ጋር ሲሄድ የሚችል የትርጉም አመጫት ይፈጥሩና ያስተባብላሉ፤ እግዚአብሔር ጨክኖ እንደ ኖህ ዘመን በዊልያም ሚለር ትንቢት መሠረት በ1844 ዓ.ም. ዓለምን ሣያጠፋ በቀረ ጊዜ ያደረጉት ይህንኑ ነው::

«በ1844 ዓ.ም. ጌታ ሣይመጣ ቀረ ብላችሁ የምታስቡ ወንድሞች ሆይ! ቀርቷል ብላችሁ አታስቡ፣ ጌታ አይቀርም:: እስከዛሬ የዘገየው ለመቅረት ሣይሆን ላለመቅረት ሥራውን እየሠራ ስለሆነ ነው:: ልብ በሉ! ጌታ ሕይወትን ያህል፣ ያውም የዘላለምን ሕይወት ሲያስረክብ ወይም ሲሰጥ አስቀድሞ ትንሽ ፈተና ቢጤ ያዘጋጃል:: ያችን ፈተና የተቀበለና ያለፈው ሰው ብቻ ነው የዘላለምን ሕይወት የሚያገኘው:: አዳምና ሔዋን የወደቁት በትንሽ ፈተና ነው፤ መታገስ አቅቷቸው በትንሹ ፈተና ወደቁ፤ ሐዋርያው ያዕቆብ የእምነት ፈተና እንደአለና የዘላለምን ሕይወት የሚጐናፀፈው ፈተናውን ያለፈ ብቻ እንደሚሆን በመልእክቱ ምዕራፍ አንድ ላይ በደንብ አስቀምጧል::

ስለዚህ አሁንም ጌታ መጥቶ በ1844 ዓ.ም. ዓለምን አጥፍቶ ለታማኞቹ የዘላለምን ሕይወት ያልሰጠበት ምክንያት የሚታየው ከዚህ አንፃር ነው:: ትንሽ በመዘግየት ፅናት አልባ ገለባዎችን ለመለየት ስለፈለገ ዘገየ እንጂ ጨርሶ ለመቅረት እንዳልሆነ ልብ በሉ! ከእንግዲህ ጌታ የሚዘገየው ለ20 አመታት ብቻ ነው:: እስከዚያ ከምድራዊ ድርጅቱ ጋር ፀንቶ በታማኝነት እያገለገለ ለሚቆየው ጌታ የፅናቱን ብድራት የሚከፍለው በ1864 ዓ.ም. ነው:: በ1864 ዓ.ም. ይህ የሰይጣን ዓለም በሚጠፋበት ሰዓት የመንግሥቱን የስብከት ቃል ተቀብለው ከድርጅቱ ጋር የቆዩ የብርሃን ልጆች ዋጋቸውን ይቀበላሉ:: በዚያን ጊዜ የብርሃን ልጅነቱን ያረጋገጠ ሰው በእሬሣዎች መካከል ቆሞ የሚገኝ ይሆናል::»

«ንጉሥ ሰለሞን የፃድቃን መንገድ እንደ የጠዋት ፀሐይ ጮራ ነው:: እያደርም እየፈካ ይሄዳል» እንዳለው የእኛ ድርጅትም የአምላክ ድርጅት ስለሆነ አምላክ የእውቀት ብርሃን ጮራውን ለድርጅቱ የሚገልፀው እያደር ነው:: ድርጅታችን አሁን ከምንም ጊዜ በላይ የበለጠ የመንፈሳዊ እውቀት ብርሃን ማስተዋል ችሎታን ተጐናፅፏል» እያሉ በብዙ መልኩ በመወትወት ምእመናኖቻቸውን አሳመኑ:: በዚህ መልኩ ሕዝቡን ካረጋጉ በኋላ እንደገና ለሌላ 20 ዓመት የሚያጓጓ የቃላት ዳቦ እየመገቡ አማኞቻቸውን እንደብልሃተኛ ከብት አርቢ ማለብ ጀመሩ:: ብልሃተኛ ከብት አርቢ አንድ ላም ስትነጥፍ ሌላዋ እንድትወልድና መታለብ እንድትጀምር በፕሮግራምና በእቅድ እያስጠቃ እንደሚያልብ ሁሉ አኩርፎ የማይቀበላቸውን እያስወገዱ፣ የቀረበለትን ፍልስፍና የተቀበለውን ግን ማለብ ጀመሩ:: ሁለገብ አገልግሎት ለድርጅቱ እንዲያበረክቱም አደረጉ:: ይሁን እንጂ አሁንም ለ2ኛ ጊዜ በ1864 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ይሆናል የተባለው ትንቢት የሚፈፀምበት ወቅት ተቃረበ:: ቀኑ በመቃረቡ በእነዊልያም ሚለር ስብከት ከዓለሙ ጥፋት የመዳን ዋስትናን የተቀበሉ የመሰላቸው ምድረ በጐች እንደልማዳቸው መፈንደቅ ጀመሩ! እነርሱ ብቻ ከዓለም ጥፋት ድነው፣ የተቀረ ሞላው የዓለም ሕዝብ እንዲጠፋ መፈንደቃቸው፣ ምን ያህል እራስን ብቻ የመውደድ መንፈስ እንደተጠናወታቸው ያመለክታል::

ይሁን እንጂ ለዊልያም ሚለርና ለተከታዮቹ ብሎ እግዚአብሔር ዓለምን በሙሉ ቀርቶ በግማሹም ሣያጠፋ ቀረ:: በዚህን ጊዜ ዊልያም እጅጉን ደነገጠ:: በሃይማኖትና በፖለቲካ ብዙ ጊዜ ሰውን ማሳመንና ማሞኘትም እንደሚቻል ያልገባው ሚለር የዓለም ሕዝብ ባለመጥፋቱ አኩርፎ የስብከት ሥራውን በመተው በማታለል የሰበሰውን ገንዘብ ይዞ ከስብከት መድረክ ተሰወረ::

ምንም እንኳን በዚህ አይነት ዘዴ ሕዝብን እያታለሉ ገንዘብ የማግኘት ሙስና አስጠልቶት ወይም ሌላ የማሳመኛ ፍልስፍና ቀመር መፍጠር የማይቻል መስሎት ስብከቱን ቢያቆምም፣ ከግብረ አበሮቹ አንዱ ግን ምክንያት በመፍጠር ሕዝብን እንደገና ማሞኘት እንደሚችል አምኖ ተንቀሳቀሰ! ይህ ግለሰብ ኤን. ኤች. ባርቦር ይባላል:: ባርቦር ቀልጠፍ ብሎ ሕዝቡ እንዳይበተን አስፈላጊውን ፍልስፍና ቀምሮ ሲያበቃ የንጋት ኮህ በተሰኘው ጋዜጣው አማካኝነት ጭምር በ1864 ዓ.ም. በተደረገው

ትንቢት መሠረት የዓለም መጨረሻ ጥፋት ለምን እንደአልመጣ እንደሚከተለው ማስተባበል ጀመረ።

«በ1864 ዓ.ም. ዓለም ትጠፋለች ብለው ከዛሬ 20 ዓመት በፊት የተናገሩት ሰዎች ወይም አባሎቻችን የሆኑ ወንድሞቻችን ተሳስተዋል። ዓለም እንደምትጠፋ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መነገሩ በፍጹም የማይጠረጠር እውነት ነው። በቅርቡ የዓለም ጥፋት በእርግጥ ይሆናል! ትንቢቱም እውነት ነው። የተነበዩትም ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልተው እንደሆነም የማይታበል ሐቅ ነው! ነገር ግን እዚህ ላይ ልብ ማድረግ ያለባችሁ ነገር»ይህንን እውነተኛውን ትንቢት ሲተረጉሙ ፍጹም ያልሆኑ ሰዎች በስሕተት ተረጐሙ። እንደምን እውቀው ፈጣሪ በሰማይ ቤት ሁለት ቤተመቅደሶች አሉት። 1ኛው. ቅድስት፣ 2ኛ ው ቅድስተ ቅዱሳን ይባላሉ። ይህንን ሐቅ በዕብራዉያን መጽሐፍ ምዕራፍ 12 ከቁ. 22-24 ባሉት ጥቅሶች **እንዝክራለን**። ስለዚህ በ1864 ዓ.ም. ጌታ ከአንዱ የሰማያዊ ቤተመቅደስ ወደ ሌላኛው ቤተመቅደስ የገባበትን ቀን ወይም ወቅት ፍጹም ያልሆኑ ነገር ግን ቅን ምድራውያን አምላኪዎቹ ባለመገንዘባቸው ወይም መገንዘብ ባለመቻላቸው ድክመት የተነሣ ተሣሥተው በ1864 ዓ.ም. የዓለም ጥፋት ይሆናል ብለው ተረጐሙ። ጌታ ከአንዱ ቤተመቅደስ ወደ ሌላኛው ቤተመቅደስ መግባቱ ፍጹም ላለመቅረት፣ እና ለመምጣት ዝግጅት ማድረጉን የሚያረጋግጥ ነው እንጂ መቅረቱን የሚያመላክት አይደለም። ስለሆነም ጌታ ከአንዱ ቤተመቅደስ ወደ ሌላኛው የገባ፣ በትንቢቱ መሠረት በ1874 ዓ.ም. የሚመጣ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ስለሆነም የዓለም መጨረሻ በ1874 ዓ.ም. ይሆናል ብሎ ሰበከ።



በዚህ ዘመን የሃይማኖት ድርጅቶችን ትምህርት ሁሉ እየዞረ የሚያጠና አንድ ወጣት ሰው ነበር። ይህ ወጣት ሰው ሲ.ት.ራሴል ይባላል። ይህ ሰው የሃይማኖት ድርጅቶች ሁሉ ትምህርት ከአምላክ ፍቅር ጋር በፍጹም የማይጣጣም ነው። ከእግዚአብሔር የሚመነጭ ትምህርት አይደለም ይል ነበር። ሲት ራሴል የእግዚአብሔር ባሕሪ ፍቅር፣ ፍትሕ፣ ጥበብ እና ኃይል ነው። ይህንን የአምላክን ባሕርይ የሚፃረር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን አልቀበልም። እንደዚህም ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ልክ አይደለም። ስለዚህ እንደዚህ ካሉት የሃይማኖት ድርጅቶችና እንደዚህ ያለውን ትምህርት የተጻፈበትንም መጽሐፍ አልቀበልም። ስለሆነም ከአባቴ ጋር ሉቅ ቆሜ ወንበር መሸጥ በስንት ጣዕሙ የሚል አቋም ላይ ደረሰ። ይህንን የራሴልን ክደትና አቋም እምነት በጉዞ ላይ በተሰኘው የ1957 ዓ.ም. እትም መጽሐፍ ገጽ 18 ተመልከቱ።

በዚህ መልኩ ወደ አባቱ ሉቅ ለመመለስ በመነሣሣት ላይ ሣለ ድንገት ራሴል ከአንድ አድቬንቲስት ድርጅት ስብከት አዳራሽ እራሱን አገኘ። በዚህ ድርጅት ውስጥ በዘመኑ በጣም የተማረች፣ ሀብት ያላት፣ ከድርጅቱም ባለስልጣኖች አንዱ የሆነች ሴት ነበረች። ይህች ሴት ማርያ ፍራንሲስ አክሌ ትባላለች። ይህች ከጊዜ በኋላ ራሴልን ያገባች ሴት ናት። ራሴል በዚህች ሴት ዐይን ውስጥ ገብቷል። ራሴል ክፉና የማይረቡ ናቸው ብሎ ወደተዋቸው ሃይማኖት ድርጅቶች አንዱ ወደ ሆነው አድቬንቲስቶች ድርጅት የገባው ምን ስለሆነ ነው? ራሴል እግዚአብሔር ሕዝብን በእሳት አያቃጥልም። ይህንን የሚያስተምሩት ሁሉ እምነታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ

አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስም ከዚህ አንፃር መታመን የለበትም ብሎ ነበር የካደው::

ታዲያ አሁን ምን ስለአገኘ ነው ራሴል ወደ አድቬንቲስቶች ድርጅት የገባው? አድቬንቲስቶች በ1873 ወይም በ1874 ዓ.ም. ዓለማችን በእሳት ተቃጥላ ትጠፋለች፣ ከዓለም ሁሉ የሚድነው የእኛ ድርጅትና የድርጅታችን አባሎች ብቻ ናቸው ብለው ያስተምሩ እንደነበር ከታሪካቸው እንዘክራለን:: የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ ላይ የተባለውን መጽሐፍ እ.ኤ.አ. የ1959 ዓ.ም. እትም ገጽ 15 ተመልከቱ:: ታዲያ የራሴልን አቋም ያስለወጠው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኝነትና የአድቬንቲስቶች ድርጅት ትምህርት ሣይሆን ሊያገኝ የሚችለው የስጋዊ ፍላጐት ወይም የምቾት እድል ግኝት መሆን አለበት:: በማርያ ፍራንሲስ ዐይን ስለገባ ምናልባትም ለእርስዋና ለሀብትዋ ብሎ ሊሆን ይችላል፡፡ ራሴል ወደዚህ ድርጅት በገባ በአንድ ዓመት ውስጥ ማለት ከ1868-1869 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ስልጣን ሊያገኝ ችሏል:: ራሴል የድርጅቱ ባለስልጣን ሆኖ የአድቬንቲስቶችን የጥናት ቡድን ሊመራ የቻለው በ1870 ዓ.ም. ነበር:: እንዴት በአንዴ እንደዚህ ሊሣካለት ቻለ? የተማረች ሀብታምና በዚህ ድርጅት ስልጣን ባላት በዚህች ሴት ሳቢያ እንደሆነ ይገመታል! የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ ላይ የ1959 ዓ.ም. እትም ገጽ 14 የንጋት ጎህ መጀመሪያ ንዑስ ርዕስ ሥር የተጻፈውን ተመልከቱ::

ስለዚህ ሲት ራሴል የሆዱን በሆዱ አድርጎ ወደዚህ ድርጅት ከዚህ በላይ በተገለጸው መልኩ ከገባ በኋላ ባርቦር ከሚባል ከድርጅቱ የበላይ አስተዳዳሪ ጋር እየተባበረ ከ1870 እስከ



1874 ዓ.ም. ይህንን የዓለምን ጥፋት ትምህርት አስተምረዋል:: ነገር ግን ይህች ዓለማችን ተቃጥላ በ1874 ዓ.ም. መጥፋት ትንቢታቸው ስለአልተፈፀመ እንደገና ክስረት ውስጥ ገቡ:: አሁን በዚህ በ1874 ዓ.ም. ወቅት ራሴል ከፍተኛ ድምፅ ካላቸው ከድርጅቱ ባለስልጣናት አንዱ ሆኗል:: ይሁን እንጂ የዚህ የአድቬንቲስቶች ድርጅት አጠቃላይ ዋና ሐላፊ (N.H. Barbour) ኤን.ኤች. ባርቦር ሣይቀር ሁሉም በ1874 የዓለም ተቃጥላ አለመጥፋት ምክንያት የተነሣ ተስፋ ቆርጠዋል:: ምዕመናኖቻቸው በዚሁ ተስፋ መቁረጥ እየተበተኑ ሄዱ:: ራሴል ግን ከመጀመሪያውኑ ከጥቅም አንፃር የተቀላቀላቸው ስለሆነ በሌላ ዘዴ እንዴት የሕዝብን አእምሮ እያፈዘዙ መበዝበዝ እንደሚቻል ወደማሰላሰሉ ገባ እንጂ ተስፋ አልቆረጠም:: ድሮም እንደዚህ ያለውን ቅዠት ስለማያምን ግርግሩ ለራሴል ስሜት አልሰጠውም ነበር:: ስለዚህ ራሴል አሁን የተናጋውን የሕዝቡን አቋም እንዴት እንደገና አረጋግቶ መበዝበዝ እንደሚቻል እቅድ እያወጣ ሲያሰላስል ነበር:: ተስፋ የቆረጠው ኤን.ኤች ባርቦር ግን ሲት ራሴልን ወደ ቢሮው ጠርቶ የሚከተለውን የድርጅቱን ሚስጢር አጫወተው::

## <u>የባርቦር ተስፋ መቁረጥ</u>

ይህ የድርጅቱ ዋና ሃላፊ ኤን.ኤች. ባርቦር ራሴልን በቀጠሮ ካገኘ በኋላ ተስፋ መቁረጡን ያጫወተው እንዲህ ብሎ ነበር:: «ከእንግዲህ አንዳች ነገር ለማድረግ መፈለግ እርባና ቢስነት ይሆናል:: የጎህ መሥራች ተከናታሪዎቻችን ኮንትራታቸውን አቋርጠዋል:: ምክንያቱ በ1874 ዓ.ም. ጌታ መጥቶ ዓለምን አጥፍቶ ሕዝቡን ስለአላዳነ መሆኑ ግልፅ ነው::

በ1844 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ይመጣል ተብሎ በተስፋ ሲጠባበቁ የነበሩት ያኔም ተስፋ ቆርጠዋል:: ያኔ የነበሩት ምዕመናኖቻችን አሁንም አሉ:: እጅጉን ተስፋ የቆረጡትም እነርሱ ጭምር ስለሆኑ ሁኔታውን የከፋ ያደርገዋል:: ከዚህም በላይ የማተሚያ ድርጅታችን ማሺኖች ያረጁ አሮጌዎች ናቸው:: እነርሱን እንኳ ቀይረን እንዳንቀሳቀስ እንደድሮው ከሁሉም የምንአገኘው ገቢያችን ቀሟል! በዚህ መልኩ የሞተውን ሥራ እንደገና ለማንቀሳቀስ መሞከር ትርፉ ኪሣራ ነው::» የሚል ሃሳብ ገለፀለት:: እምነት በጉዞ ላይ መጽሐፍ ገጽ 27

## የራሴል መልስ

ራሴል በዚህ ድርጅት በጥቂት ጊዜ እጅግ በጣም ከፍተኛ ባለስልጣን መሆን እንደቻለ እንመለከታለን:: ምክንያቱም እንደዚህ ያለ የማሕበሩ ክስረት ሚስጥር አለወቅቱ ለማንም ስለማይነገር ነው:: ሌላው ቀርቶ ጉዳዩ የግድ ለማይመለከታቸው ኃላፊዎች እንኳን አለወቅቱ የማይነገር ሚስጥር ነው ፤የድርጅቱ ዋና አስተዳዳሪ ለራሴል ያጫወተው። ይህንን ሚስጢር ነው::በዚህ መልኩ በቅድሚያ ሲያጫውተው ራሴል በፅሞና ካዳመጠው በኋላ በወሳኝ ድምፁ ቀጥሎ ያለውን መልስ የሰጠው:-

«ሚስተር ባርቦር ምን ማለትህ ነው? አሁን በይበልጥ ለሥራ የምንነሣሣበት ወቅት መሆኑን እያወክ እንዲህ ትላለህ? እኔ ተስፋ አልቆረጠኩም:: ከዚህ በፊት ጭራሹኑ ሰምተህ የማታውቀው ለሕዝብ የማቀርበው ሃሳብ አለኝ:: የክርስቶስ መንግስት ለሰው ዘሮች የምታመጣው በረከቶች ለሕዝብ የምገልፀው የምስራች አለ! ስለቤዛ የተሰበከ ወይም የተነገረ ምንም የለም:: ይህንን በሰፊው ከሰበክን በኋላ የጌታ መምጣትን እናፋጥናለን አሰውና ትቶ ወደመጣው ሥራ እንዲመለስ አግባባው::

በዚህ መልኩ ዋና አስተዳዳሪውን አፅናንቶ፣ ገንዘብ ጭምር ሰጥቶት ተመልሶ ሥራውን እንዲያንቀሳቅስ ነገረው:: የራሴል በአንድ አመት ውስጥ በማያምንበት በዚህ ድርጅት ኃላፊ መሆን፣ አሁን ደግሞ ዋና አስተዳዳሪውን ገንዘብ ጭምር ሰጥቶት ተመልሶ እንዲሠራ ማስደረግ መቻል ሚስጢር ምን ይሆን? ሁሉን ከካደ በኋላ ወደ አባቴ ሱቅ ተመልሼ በወንበር ሥራ ላይ እሰማራለሁ ብሎ የነበረውን የራሴልን አቋም ያስለወጠው ሚስጥር ምን ይሆን? ከሀብት ሀብት፣ ከስልጣን ስልጣን ውስጥ የመነከር ዕድል ነው! ለዋና አስተዳዳሪውም የተሰጠው ገንዘብ የሚስስ ማርያ ፍራንሴስ አክሊ እንደሆነ የሚያጠራጥር አይደለም:: ይህች ሴት በገንዘብም የአድቬንቲስቶች የጀርባ አጥንት እንደነበረች ይነገራል:: ስለዚህ እኛ ተግተን ከሠራን ጌታ በ1878 ዓ.ም. መጥቶ ዓለሙን ካጠፋ በኋላ እኛን ወደ ሰማይ ይወስደናል ተብሎ የተወሰነውን የድርጅቱን ዓላማ ተከትሎ እንዲያስተምር ስለአዘዘው ባርቦር ስብከቱን ቀጠለ:: አሁን ነገሩ የእምነት ጉዳይ ሣይሆን የጥቅም ጉዳይ መሆኑን ራሴል ገብቶት አላማዬ ብሎ ፍልስፍናውን ተያይዞታል:: ስለዚህ በ1878 ዓ.ም. ወደ ሰማይ እንወጣለን፣ ከእኛ ጋር ድናችሁ መንግስተ ሰማይ ለመውረስ ከፈለጋችሁ ተባበሩን እያሉ ሕዝብን በስብከት ማሽበር ጀመሩ! በ1877 ዓ.ም. ላይ ሶስት ዓለማት የሚል መጽሐፍ አብረው አወጡ:: ራሴል በ1878 ዓ.ም. ምንም እንደማይሆን ያምን ስለነበር ከሀብታሟ ሴት ገንዘብ ተቀብሎ አዳዲስ የህትመት መኪናዎችን ገዝቶ ከባርቦር የስራ ልምዱን 1878

ዓ.ም. ከመሆኑ በፊት በቶሎ ተማረ:: በዚህ መልኩ ሁሉን ካጠናቀቀ በኋላ የተባለው 1878 ዓ.ም. ደረሰ:: እምነት በጉዞ ላይ የ1957 ዓ.ም. እትም መጽሐፍ ገጽ 25-26

<u>ለ4ኛ ጊዜ የትንቢቱ መክሸፍ</u>

ለ4ኛ ጊዜ በ1878 ዓ.ም. ኢ.ኤ.አ. ይህች ዓለማችን በሙሉ ጠፍታ የእነርሱ አባላት ብቻ ከዓለሙ ጥፋት እንደሚድኑ በባርቦርና ራሴል በቁርጠኝነት የተነገረው ትንቢት ሣይፈፀም ቀረ:: በዚያ በ1878 ዓ.ም. የጌታ እራት ብለው በሚያከብሩት እለት ኢየሱስ መጥቶ ወደ ሰማይ ይወስደናል ብለው ነጫጭ ልብሶች በመልበስ በአንድ ትልቅ ተራራ ላይ ወጥተው እየዘመሩ መጠባበቅ ጀመሩ! በዘመኑ የነበሩ ጋዜጠኞችም ይኸንኑ ሰምተው ቦታው ድረስ በመሔድ ታሪኩን መዝግበውታል:: ምንም እንኳን አፋቸውን በትልቁ ከፍተው ቢዘምሩም ጌታ አሁንም ከ4ኛው ጊዜ መጥቶ ሣይወስዳቸው ቀረ::

የእምነት በጉዞ ላይ መጽሐፍ ደራሲ ወንድም ኤ.ኤች.ማክሚላን ከ20 አመት እድሜው ጀምሮ ከራሴል ድርጅት ጋር የተቆራኘ ግለሰብ ነው:: በመጨረሻም ከ60 ዓመት አገልግሎት በኋላ በ80ኛው እድሜው በፃፈው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በወቅቱ ለሲ.ቲ.ራሴል የሚከተለውን ጥያቄ አቅርቦለት እንደነበር ይገልፃል:: «ምን ነክቶአችሁ ነው? እንዴት ጌታ መጥቶ ይወስደናል ብላችሁ በ1878 ዓ.ም. ተራራ ላይ ወጥታችሁ መጠባበቅ ቻላችሁ?» ብሎት ነበር:: ለዚህ ጥያቄ ራሴል የሰጠውን መልስ ቀጥለን እንመልከት:-

<u>የሲ.ት ራሴል መልስ</u>



ራሴል የከረከሩት ያህል ከሣቀ በኋላ እንዲህ ብሎ መለሰለት:: «እኔ በዕለቱ በቦታው አልነበርኩም ያን ዕለት ከ4 ሰአት ተኩል ጀምሮ እስከ አምስት ሰአት ባለው ጊዜ ውስጥ መኝታዬ ውስጥ ገብቼ ነበር:: ይሁን እንጂ እንደዚህ ያለውን አድራጐት የተወሰኑ አክራሪዎች አድርገውት ይሆናል:: እኔ ግን ከመካከላቸው አልነበርኩም» እምነት በጉዞ ላይ (Faith on the March) በኤ.ኤች. ማክሚላን ተደርሶ በ1957 • ዓ.ም. በዋች ታዎር የታተመውን መጽሐፍ ገፅ 27 ይመልከቱ::

ከዚህ አመላለሱ ራሴል ምን አይነት ሰው እንደነበር መገመት ይቻላል:: በ1878 ዓ.ም. ይህች ዓለም ትጠፋለች እያለ በእምነት አጃጅሎአቸው ብዙ ገንዘብ ከሰበሰበ በኋላ በጌታ እራት ቀን የእምነቱ አባላት ጌታ መጥቶ ይወስደናል ብለው ተራራ ላይ ወጥተው ሲጠባበቁ፣ የራሴል ከመካከላቸው መለየት የማያመንበትን ውሸት ለሕዝብ ይሰብክ እንደነበር ይገልፃል:: ይባስ ብሎ እንደዚህ ያደረጉት አክራሪዎች ናቸው ብሎ አረፈ! የድርጅቱ አስተዳዳሪ ባርቦር ግን ጌታ እንደሚወስዳቸው አምኖ አባላቱን ወይም ቤተክርስቲያን የሚላቸውን ታማኞቹን ይዞ በተራራ ላይ ተገኝቶ ነበር:: በዚሁ እምነት በጉዞ መጽሐፍ ገጽ 26 ላይ መመልከት ይቻላል::

<u>የባርቦር መለየት</u>

ባርቦር በ1878 ዓ.ም. ለ4ኛ ጊዜ ጌታ በአለመምጣት እንደ አሳፈራቸው በእየ ጊዜ ጨርሶውኑ እንደዚህ ያለውን የስብከት ሥራ ተወው:: ራሴል ግን ድሮም በዚህ አይነቱ የስብከት ዘዴ ገንዘብ ለማግኘት እንጂ እምነት ስለአልነበረው፣ በለመደው የሙስና ሥራው መቀጠልን ፈለገ። በዚህን ጊዜ ባርቦር እንደዚህ

ያለ ስብከት ውሸት ነው፣ አሁንም እንደገና ሲያሞኛችሁ ራሴል የሚሰብካቸውን ስብከት አትመኑ፡፡ እያለ ሕዝቡን በራሴል ላይ መቀስቀስ ጀመረ:: ነገር ግን አሁን ከራሴል ጋር ሣይስማማ ስለቀረ-ድሮ ዝም ብሎ ሕዝቡን ሲሰብክ የነበረወን አሁን መልሶ ሲቃወም ጥቅሙ ስለተነካበት ነው ተባለ እንጂ ተቀባይነትን አላገኘም:: እውነቱን አበከሮ ኪያወራም ባርቦር ተቀባይነት አጣ:: እንደእውነቱ ከሆነ ባርቦር በእምነቱ ይንቀሳቀስ እንደነበር መገመት የምንችለው ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው ወደ ሰማይ ለመወሰድ ከምእመናኖቹ ጋር ተራራ ላይ ወጥቶ መገኘቱ ነው::

ከዚህ በኋላ ዋና አስተዳዳሪ የነበረው ኤን.ኤች ባርቦርን ጨምሮ ከእንግዲህ ወዲያ ዘመን «እየቆጠርን» ዓመት እየቀጠርን ይህች ዓለም ተቃጥላ ትጠፋለች ብለን መስበኩ ስሕተት ነው ብለው እርምት አደረጉ:: ይህንን እርምት የተቀበሉት ከድርጅቱ ጋር ሲቀጥሉ እርምቱን ያልተቀበሉት ድርጅቱን ጥለው ወጥተዋል:: ታዲያ ራሴልን እንዴት ሆነ? ከዚህ በኋላ ምን አድርገዋል? ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት በቅድሚያ የራሴል የሕይወት ታሪክ በአጭሩ እንመልከት::



## ምዕራፍ 2

## የሲት ራሴል ሕይወት ታሪክ

ሲት ራሴል ማን ነው? ሲት ራሴል በየካቲት 16 ቀን 1852 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. አይሪሽ ኢስኮት ከሆኑ ቤተሰብ ተወልዶ እስከ ጥቅምት 31 ቀን 1916 ዓ.ም. ኖሮ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ ግለሰብ ነው:: እራሱን እስከ ቻለ ጊዜ ድረስ ከወላጆቹ ጋር ወደ ካልቪኒስት ቤተክርስቲያን ይሄድ ነበር:: ራሴል ዕድሜው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ በእኛ አገር የሕዝብ ትምህርት እየተባለ በሚጠራው የግል ትምህርት ቤት ገብቶ ለተወሰነ ጊዜ እንደተማረ ይነገራል:: ይሁን እንጂ የራሴል የትምህርት ደረጃ በግልፅ የሚገልፅ ታሪክ የለም::

ዕድሜው 15 ዓመት ገና እንደሞላ ወንበር ሻጭ ከሆነ አባቱ ጋር እየዋለ በወንበር መሸጡ ሥራ ያግዝ እንደነበረና በትርፍ ጊዜ ከአንዱ የሃይማኖት ድርጅት ወደ ሌላ የሃይማኖት ድርጅት እየተዘዋወረ ይመራመር እንደነበር ታውቋል::

የራሴል እናት ራሴል በተወለደ በ9 ዓመት ዕድሜው ጥላው ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለየች ግማሽ የሕፃንነት ዘመኑን በአባቱ አሳዳጊነት አሳልፏል:: ከላይ እንደተባለ ራሴል ከ14 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ ከወላጆቹ ሃይማኖት ውጭ እየዞረ ከመመራመሩም በላይ በወወከማም ድርጅት እንቅስቃሴ ተሣትፎ ነበረው::

በመጨረሻም በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ እንደአየነው የሃይማኖት ድርጅቶች ምርምር ውጤቱ ሃይማኖተኛ እንዲሆን በማስቻል ፈንታ ተጠራጣሪና እምነተ ቢስ ስለአደረገው የሃይማኖት ጉዳይን እርግፍ አድርጐ ትቶ ከአባቱ ጋር በወንበር

ሽያጭ ሥራ ላይ ለመሰማራት መወሰኑን ተመልክተናል:: ይሁን እንጂ እጮኛው በነበረች በሚስስ ማርያ አማካኝነት ወደጠላቸው የሃይማኖት ድርጅት ስብከት እንደተመለሰም ገምተናል::

ራሴል ባያምንበትም ከኤን.ኤች ባርቦር ጋር ሆኖ ከ1870 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1878 ዓ.ም. ድረስ ዓለም ተቃጥላ ትጠፋለች እኛም ወደ ሰማይ እንወሰዳለን፣የሚለውን ስብከት አስተምረዋል:: ነገር ግን የራሴል እጮኛ ሚስስ ማርያና ሌሎችም የድርጅቱ ኃላፊዎች እንደጠበቁት ሳይሆን ቀርተዋል:: ሁለተኛ እንደዚህ ያለውን ትምህርት አናስተምርም ብለው ድርጅቱን ለመልካም ዓላማ ማዋል ስለቆረጡ ራሴል ተበሳጨ፤ ራሴል ጥቅም የሚያስገኘው እንዲህ ያለ የሽብር መንዛት ስብከት መሆኑን አመነ:: በሌላ ሙያ እንዳይተዳደር ልዩ ሙያ የሌለውና ዘልቆ ያልተማረ ሰው ስለነበር፣ እንዲህ ባለው የማጭበርበር እና በማሸበር ሥራ መሠማራቱን መረጠ:: እጮኛው ሚስስ ማርያም ከራሴል ጋር በ1878 ዓ.ም. ወደ ሰማይ ከወጡ በኋላ የመጋባት ተስፋ ስለነበራት ላለፉት ዘጠኝ አመታት በእጮኝነት ስም ብቻ አብረው ከረሙ:: ነገር ግን ሰማይ የመውጣት ተስፋቸው ሳይሣካ ቀረ::

በዚህ መልኩ ተስፋ ስለቆረጠች ሚስስ ማርያ ከዘጠኝ ዓመቱ እጮኛው ከራሴል በስተቀር የሚያፅናና ሌላ አጋር አጣች:: ስለዚህ ከአድቬንቲስት ድርጅት ከሲት ራሴል ጋር መገንጠልን መረጠች::

ራሴል በ1870 ዓ.ም. የአድቬንቲስት ድርጅት አባልና የአንድ ቡድን መሪ ሆኖ ተሹሞ እንደነበር የሚታወስ ነው:: ስለዚህ ማሪያ እንደተባለው ከ1878 ዓ.ም. ክስረት በኋላ ለዘጠኝ



ዓመት በእጮኛ ስም አብራ የቆየችውን ራሴልን ለማግባት ተገደደች:: አስቀድሞ በሚስስ ማርያ ገንዘብ ገዝቶ አሠራሩን ከባርቦር የተማረበትን የህትመት መኪናውን ይዞ ከማርያ ጋር በ1879 ዓ.ም. በገሐድ ከአድቬንቲስት ድርጅት ተገነጠሉ:: እዚህ ላይ ማርያን እንድትገነጠል ሊያደርግ የቻለው ሲት ራሴል እንደሆነ ግልፅ ነው:: ሚስስ ማርያ ሲት ራሴልን በዚሁ በተገነጠሉበት ዓመት ማለት በ1879 ዓ.ም. በሕግ ተጋቡ:: ምስክሮቹ በመለኮታዊ ሥራ ላይ የሚለው መጽሐፍ ገጽ 17 ፓራግራፍ 6 ተመልከቱ::

ሚስስ ማርያ እድሜዋ ጠና ያለ ነበር:: ሲት ራሴል ማርያን ሲያገባ እድሜው 30 ዓመት እንኳን አልሞላም ነበር:: ራሴልም በቀላሉ በገንዘብ ውስጥ የመነከር ዕድልን ስለአገኘ እንደሚገባ ተጠቅሞበታል:: እንደ እውነቱ ከሆነ ራሴል ያገባ ሃብቷን ነበር ለማለት ያስደፍራል:: ከዚህ በኋላ በራስዋ ገንዘብ የተቋቋመውን የህትመት ድርጅትን የድሮዋ ማርያ ፍራንሲስ አክሌ የአሁንዋ ሚስስ ሲት ራሴል በዳይሬክተርነት መምራት ጀመረች:: ምስክሮቹ በመለኮታዊ ሥራ ላይ የ1959 ዓ.ም. እትም መጽሐፍ ምዕራፍ 7 ገጽ 45 ፓራግራፍ 2 ተመልከቱ::

ከተገነጠሉ በኋላ ይህ ያቋቋሙት የህትመት ድርጅታቸው ስም የፅዮን መጠበቂያ (Zion's Watch Tower) ማማ ይባል ነበር:: ምስክሮቹ በመለኮታዊ ዓላማ መጽሐፍ ገጽ 22 ተመልከቱ:: ሚስስ ራሴል በዳይሬክተርነት ለ17 ዓመታት የመራችው በዚሁ የፅዮን መጠበቂያ ማማ፣ የህትመት ድርጅት ስም ነበር:: አሁን በዚሁ ድርጅት እየተጠቀሙ፣ የመጠበቂያ ማማ በተሰኘው ጋዜጣቸውና በሌሎችም ሕትመቶች ላይ

የመጣብህ መጣብሽ ሽብር ስብከታቸውን ቀጠሉ:: ራሴል የ1878 ዓ.ም. የጌታ አለመምጣትን ምክንያት ካስተባበለ በኋላ ዓለም የምትጠፋበትን ሌላ የትንቢት ቀጠሮ አወጀ:: ይህንን የራሴልን ትንቢት በሌላ ምዕራፍ በሰፊው እንመለከታለን::

በእነዚህ ሁሉ ዘመናት ውስጥ ወጣቱ ራሴል የዚህችን ሀብታም አሮጊት ስልጣንም ሆነ ገንዘብ እንዴት ከእጅዋ ሊያወጣ እንደሚችል ሌት ተቀን ያሰላስል ነበር:: ስለዚህ የምትአምንበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ፈልጐ ያንን እየጠቀሰ ሊያሞኛት ፈለገ:: ይኸው ዘዴ ተሳክቶለት ከእለታት አንድ ቀን ቀጥሎ ያሉትን ጥቅሶች አገኘ:: ጥቅሶቹ እንደሚከተለው ይነበባሉ::

«ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፣ ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር፣ ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም» 1ኛ ጢሞቲዎስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 12

2ኛው ጥቅስ ደግሞ እንዲህ ይነበባል:- «የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነው፣ የሴት ራስ ወንድ፣ የክርስቶስ ራስ እግዚአብሔር ነው::» 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 3

3ኛው ጥቅስ ደግሞ እንዲህ ይላል:- «ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ነው፣ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት:: ሴት ለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ለሴት አልተፈጠረም::» 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 11 ቁ. 7 ራሴል እነዚህን ሁሉ ጥቅሶች እየጠቀሰ ሴት ወንድ እያለ፣ በተለይም ራስዋ የሆነ ባልዋ እያለ ሥልጣን ይዞ የማዘዝ መብትን እግዘአብሔር አይፈቅድም:: ይህ ድርጅትሽ መሆኑ ይገባኛል:: ነገር ግን የአምላክ ፈቃድና ትእዛዝ ደግሞ ይህ ነው:: በእርግጥ አንቺ ንብረትሽ በዋና ፀሐፊነት በገንዘብና ንብረት ተቆጣጣሪነት



መስራት ትችያለሽ:: ከእምነታችንና ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ አንፃር ግን ወንድ ልጅ ያውም ራስሽ የሆነ ባልሽ እያለ የበላይ አካል ሆነሽ በዳይሬክተርነት መምራት አትችይም:: እኔና አንቺን የሰየ ምንም ስለሌለ የዳይሬክተርነት ማዕረጉን ለእኔ አስረክቢ ብሏት አረፈ::

ሞኟዋ ማርያም የድርጅቱን ንብረት ከተቆጣጠርኩ ፀሃፊና ገንዘብ ያዥ ከሆንኩ ችግር የለም:: ከዚህ በላይ ደግሞ ከሁሉ የበለጠ የምንአምንበት የአምላካችን የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ ነው:: ስለዚህ ይሁን ብላ ካመነች በኋላ ሲት ራሴል የድርጅቱ መሪ እንዲሆን ፈቀደችለት::

ከዚህ በኋላ ምላጩ ራሴል ጉዳዩ ወደሚመለከተው መስሪያ ቤት ሄዶ ፅዮን መጠበቂያ ማማ (Zion's Watch Tower) የሚለውን ስም እንዲሠረዝ አድርጎ «የሕትመት መጠበቂያ ማማ የግል ኩባንያ» ብሎ አስመዘገበ:: እንዲሁም የዚህ ኩባንያ ንብረት የራሱ የሲ.ቲ.ራሴል መሆኑን፣ ኩባንያውንም የሚመራ እራሱ መሆኑን በሕግ አፀደቀ:: ምስክሮቹ በመለኮታዊ ሥራ የ1959 እትም መጽሐፍ ገጽ 27 ከሕዳጉ ማስታወሻ የመጨረሻው አረፍተ ነገር እንዲህ ይነበባል:: «The property was originally held in title legally by the tower publishing company, a private concern personally managed by C.T. Russel.»

ከዚህ በኋላ የራሴል ሴራ ይፋ መውጣት ጀመረ:: ራሴል ድሮም አሮጊትዋን ያገባው ለገንዘቧ ብሎ ሲሆን፣ እርስዋም በ1878 ዓ.ም. ወደሰማይ የመውጣት ተስፋ ከተሟጠጠ በኋላ

ማጣፊያ ሲያጥራት እና ሲጨንቃት የ9 አመት እጮኛዋን ለማግባት ተገድዳለች:: ሲት.ራሴል ከዚህ በላይ በተገለፀው መልኩ አሮጊቷን ከስልጣን ካባረረ በኋላ አይኖቹን በአጉጠጉጤ ኮረዶች ላይ መጣል ጀመረ:: ገንዘብ መጣ ፍቅር በጓዳ ወጣ እንኳን እንዳይባል ከበፊቱም ለገንዘብዋ እና በእርስዋ ረዳትነት ላገኘው የዕድገት ደረጃ ብሎ ነገር እንጂ የጋለ ፍቅር ኖሮት አልነበረም:: አሁን ደግሞ በተጨማሪ ገንዘብ በኪሱ እንደጉርፍ መጉረፍ ስለጀመረ ማርያ በራሴል ዐይን አሮጌ ቆርቆሮ አያገለግልም እንደሚባለው አይነት ሆነች:: ራሴል ዐይኑን የጣለባት ሴት ወይዘሪት ሮዝቤል ትባላለች:: ራሴል ከዚህች ወጣት ሴት ጋር አጠራጣሪ በሆነ ቦታ ሁሉ መታየት ጀመረ:: ማርያ ይህንን የራሴልን ጉድ ስለደረሰችበት ፈጣኝ እርምጃ ለመውሰድ ተንቀሳቀሰች::

## <u>የማርያ እርምጃ</u>

ስልጣንዋን ለባልዋ አስረክባ ግን በገንዘብ ያዥነትዋና በንብረት ተቆጣጣሪነትዋ እንደሚገባ ስለአልሠራች በራሴል ክስ ገንዘብ እንደጉርፍ መጉረፍ እንደጀመረ ተመልክተናል:: ይባስ ብሎ ራሴል አሮጊትዋን እየናቀ መምጣቱን ስለተረዳች ጅብ ከሄደ በኋላ ውሻ ጮኸ እንዲሉ ማርያ ድርጅቴን መቆጣጠር ይገባኛል ብላ ተነሣች:: አንዳች መጽሔት ያስፍቃዴ አይታተምም፣ አንዳች ወጭ እኔ ሣላውቅ አይደረግም:: ካልሆነ በሕግ እጠቀማለሁ ብላ ተነሣች:: እንዲሁም አድራጉቱን አውግዛ ካልታረመ እርምጃ እንደምትወስድ አስጠነቀቀችው::

ይህ ራሴል ያላሰበበት ድንገተኛ አደጋ ነበር:: ስለዚህ ራሴል አፋን አለስልሶ ያለችውን ሁሉ በእሽታ ከተቀበለ በኋላ ሴላ



ሴትን የመመልከቱን ግን ውሸት ነው እያለ በውሸት መሐላ አሣመናት:: እኔ ከአለአንች አላውቅም፣ ንብረትሽን ደግሞ ከአንቺ ሴላ ማን ይቆጣጠራል ታዲያ፣ በዚህ ስጋት አይግባሽ ብሎ በሐሰት ፍቅር በመደባበስ አረጋጋት:: ማርያም የመቆጣጠር ሥራዋን ጀመረች::

ከዚህ በኋላ ራሴል ዓመሉን አለስልሶ እኔ ከአለ አንቺ ምን አለኝ እኔ አፈቅርሻለሁ ብሎ ሚስቱን በውሸት ፍቅር እየዳበሰ በሌላ በኩል ደግሞ እርስዋን በማያዳግም መልኩ ሙልጭዋን ለማስወጣት እቅድ ማዘጋጀት ጀመረ:: ራሴል ይህ በራሱ ስም የተመዘገበውን የማማ ማተሚያ የግል ድርጅትና የግል ንብረት መሰወጥ ፈለገ:: ለምን? ለምን ቢባል ባልና ሚስት ስለሆኑ እና ከተጋቡ በኋላ የተቋቋመ ስለሆነ በጥል ከተለያዩ ቢያንስ የንብረቱን ግማሽ በሕግ ትካፈላለች:: ራሴል ግን አሮጊቷን ቤሳ ቤስቲኒ ሣይሰጣት የሚያበርርበትን ዘዴ ቀየሣ:: ይህም ዘዴ ከላይ እንደተገለፀው በራሱ ስም የግል ንብረት ተብሎ እንዳይመዘገብና የራሱም ንብረት እንደአልሆነ በሕግ ማፀደቅ ነው:: ከዚህ በፊት ይህ ድርጅት ከፅዮን ማማነት ወደ ማማ የግል ንብረት የሕትመት ድርጅት መለወጡ የሚታወስ ነው:: አሁን ደግሞ ከማማ የግል ንብረት ማተሚየ ቤትነት ወደ የመጠበቂያ መጽሐፍ ቅዱስና የትናንሽ ጽሑፎች ማህበር እንዲሰወጥ ተደረገ:: በዚህ መልኩ ሁሉን ካጠናቀቀ በኋላ የዚህ የመጠበቂያ ማማ መጽሐፍ ቅዱስና የትንሽ ጽሑፎች ማኅበር የሚለውን ስም በሕግ አፀደቀ:: ይህ ለ3ኛ ጊዜ ከላይ በተጠቀሰው አዲስ ስም ከተመዘገበ በኋላ ይህ ድርጅት በቦርድ ዳይሬክተሮች እንደሚመራ፣ ንብረትነቱ የግለሰቦች ንብረት ሣይሆን የበጎ

አድራጎት ንብረት መሆኑን፦ድርጅቱም የበጎ አድራጎት ድርጅት ስለሆነ አትራፊ ነጋዴም ድርጅት አለመሆኑን ጭምር አስመዘገበ

የማሕበሩም ዋና አላማ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን በልዩ ልዩ የህትመት ጽሑፎች፣ ትናንሽ መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና አመቺ በሆነ መንገድ ሁሉ በነፃ ለህዝብ ማስተማርና ማሰራጨት ነው:: ከላይ እንደተባለው ይኸ በጎ አድራጊ ድርጅት የሚመራው በቦርድ ዳይሬክተሮች ነው ተብሎም በሕግ እንዲመዘገብ አስደረገ:: በመጨረሻም እነዚህ የቦርድ ዳይሬክተሮች ለማህበሩ ኘሬዝዳንት ተጠሪ መሆናቸውም ተመዘገበ:: እነዚህ የቦርድ ዳይሬክተር ተብዬዎች እራሱ ራሴል በመጽሐፍ ቅዱስ ያጃጃላቸውና እንደ ልብ የሚያዛቸው ሰዎች ናቸው:: ከእነዚህ ሰዎች ጋር ከላይ በተቀሰው መልኩ ተመካክሮ ከጨረሰ በኋላ በማያዳግም መልኩ በማርያ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ተነሳ::

<u>የራሴል እርምጃ</u>

ሚስስ ራሴል ጉድዋን ሣትአውቅ እየዞረች በጉባኤዎች የሕዝብ ንግግር ታደርግ ነበር:: በጣም የተማረችም ሴት ስለሆነች በወር ሁለት ጊዜ እየታተመ ለሚሰራጨው ለዋች ታዎር ጋዜጣ ሁልጊዜ የሚታተም ጽሑፍ ታበረክት ነበር:: እንደ ድሮው መስኋትና አገር ሰላም ነው ብላ ሚስስ ራሴል በዋች ታዎር ጋዜጣ ላይ የሚወጡትን ጽሑፎች ጽፋ እንዲታተም ለራሴል ሰጠችው:: በዚህን ጊዜ ራሴል ፊቱን አኮሣትሮ ጽሑፏን ሠርዞ መለሰላት:: የድሮው መስኋት በምን ምክንያት? ብትለው ሴት በወንድ ላይ መሰልጠንና ወንድን ማስተማር አትችልም በማለት መልስ ሰጣት:: ለመከራከር ስትሞክር እያጣደፈ ከቤት አባረራት:: ምስክሮች በመለኮታዊ



አላማ የ1959 ዓ.ም. እትም መጽሐፍ ምዕራፍ 7 ገጽ 45 ተመልከቱ

ራሴል ይህንን ተንኮል የአሜሪካን መንግስት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሕግ ጠበቃ ከሆነው አንድ ግለሰብ ጋር እየተመካከረና ዘዴውን እያጠና እንደነበር ግልፅ ነው:: ስለዚህ ከዚህ በቅርበት ከሚያውቀው ሰው ጋር ሆኖ በሕግ ሽፋን የአሮጊትዋን ገንዘብ ቀምቶ ሙልጭዋን እንድትወጣ አድርገዋል:: እዚህ ላይ ራሴል ምንም ግፍ የማይፈራ፣ ሌሎችን የሃይማኖት ድርጅቶችን ከራሱ የግል ፍላጎት አንፃር የሚኮንን፣ በየጊዜው የእግዚአብሔር ባሕሪይ ፍቅር፣ ፍርድ፣ ጥበብና ኃይል ናቸው ብሎ በውሸት በሚያነበንባቸው መፈክሮች የማያምን፣ ካዲ ግለሰብ ነው:: ከላይ በተገለጸው መልኩ የሚስቱን ንብረት ቀምቶ ካባረረ በኋላ በ1906 ዓ.ም. በሕግ ፈታት:: ምስክሮቹ በመለኮታዊ ሥራ መጽሐፍ ገጽ 45 ተመልከቱ::

በመጨረሻም የሕግ ሽፋን እየሰጠ ሲያግዘው የነበረው በዋሽንግተን የአሜሪካ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጠበቃ የሆነው ሰው ሥራውን ትቶ ከራሴል ጋር የዚህ የዋች ታዎር የመጽሐፍ ቅዱስ እና ትናንሽ ጽሑፎች የበጎ አድራጐት ድርጅት አባልና የጥቅሙ ተካፋይ ባለስልጣን ሆኖ ማርያ በተባረረች በዓመቱ ማለት በ1907 ዓ.ም. ድርጅቱን መቆጣጠር ጀመረ:: ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ ላይ መጽሐፍ ገጽ 65 ተመልከቱ::

<u>የሚስ ራሴል ፍርድ ቤት መሄድ</u>

ሚስስ ራሴል በሕግ መብቴን እስከብራለሁ ብላ በፍርድ ቤት ራሴልን ከሰሰች:: ራሴል ግን ከላይ ከተጠቀሰው ሕግ አዋቂው ወገኑ ጋር በበቂ መልኩ የሕግ ሽፋን አበጅቶ ስለነበር

በፍርድ ቤቱ የሚከተለውን መልስ ሰጠ:: « ይህ ድርጅት የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው:: ንግዶ የሚያተርፈው ምንም ነገር የለም:: ይህ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሥራ የሚካሄደው በ7 የቦርድ ዳይሬክተሮች ነው:: እኔን በኘሬዝዳንትነት የሾሙኝ እነኝሁ የቦርድ ዳይሬክተሮችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው በጐ አድራጊ ግለሰቦች ናቸው:: እኔ/የዚህ በጎ አድራጐት ድርጅት ኘሬዝዳንት ሆኜ በመሾሜ ብቻ ንብረቱ የእኔ መስሎአት በተሳሳተ መልኩ የሌሎችን ሰዎች ንብረት ለመቀማት የምትሟገት ሴት ናት» የሚል ነበር::

ማርያ ፍራሴል አክሴይ ሀሰት ነው! ውሸት ነው! እያለች ብትጮህም ጩኸትዋ የቁራ ጩኸት ሆኖ ቀረ:: በሕግም መዛግብት ተመርምሮ ራሴል እንዳለው ሆኖ ተገኘ:: ድርጅቱ የበጎ አድራጐት ድርጅት፣ንብረትነቱ የመጠበቂያ ማማ፣ የመጽሐፍ ቅዱስና ትናንሽ ጽሑፎች (Watch Tower Bible & Tract Society) ማህበር በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚመራው ድርጅት መሆኑ ተረጋገጠ::

በዚህ መልኩ ራሴል ሚስቱን በሕግም አሸንፎ በ1906 ዓ.ም. በሕግ ፈታት:: እርስዋን በማያዳግም መልኩ ከሸኛት በኋላ ከ250ሺህ የአሜሪካን ዶላር ያላነሰ ዕጣ በድርጅቱ በማስቀመጥ በገንዘብም ሆነ በሕግ የተረጋገጠለት የኘሬዝዳንትነት ስልጣኑን የማይነቃነቅ አለት አደረገው:: ከዚህም በላይ ድርጅቱ የማይታይ የእግዚአብሔር ምድራዊ ድርጅት ነው:: መሪውንም የሚሾመው እራሱ እግዚአብሔር በመንፈሱ ነው። በሚል ፍልስፍና አባላቱን ስለአሣመነና የቦርድ ዳይሬክተሮቹም የእርሱ የእራሱ ፍጡሮች ስለሆኑ ራሴል የማይደፈር ሆነ:: ከዚህ በኋላ እነዚህ የቦርድ ዳይሬክተሮች የተባሉትን አርቴፊሻሎች በአስፈለገ ጊዜ እያባረረ፣ የሚፈልገውን እየሾመ ፍጹም አምባገነን ሆነ:: ብዙ የቦርድ ዳይሬክተሮች ሲባረሩ እስከዛሬ አንድም የተባረረ የማሕበሩ ኘ ሬዚዳንት አለመኖሩ እራሱ ምስክር ነው:: እንደዚህ ያለውን አሠራር የቴኦክራቲክ አሠራር ይሉታል:: መለኮታዊ አመራር ማለታቸው ነው:: በእነዚህ በተጀኋሉት ሰዎች እምነት የማኅበሩን ኘሬዝዳንት የሚሾመው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: የሚሽረውም እራሱ እግዚአብሔር ነው ይላሉ:: ነገር ግን ብዙ የቦርድ ዳይሬክተሮች ሲባረሩ ስንት ሞላጫ ኘሬዝዳንቶችን ያ እግዚአብሔር ዝም ብሎ ለምን እንደሚመለከት ለበጐቹ የሚከሰት አልሆነም::

<u>ራሴል በፍርድ ቤት</u>

ራሴል በተንኰል በተቀነባበረ ሴራና ማጭበርበር ሚስቱን ስለአባረረ ፓስተር ራሴል በሚል ስም መጠራት አይገባውም ተብሎ በተደጋገመ ወቅት ተከሶ ፍርድ ቤት ቀርቧል:: በዚህ መልኩ ስለመከሰሱ የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ የ1959 ዓ.ም. እትም እ.ኤ.አ. መጽሐፋቸው በገጽ 45 ፓራግራፍ 3 እራሱ ማህበሩ ጽፏል::

እንዲሁም በማርያ ጠቋሚነት ሲቲ ራሴል ሮዝ ቤል ከምትባለው ወጣት ሴት ጋር ዝሙት ሠርተዋል ተብሎ በፍርድ ቤት ሃሳቡን እንዲገልፅ በተጠየቀ ጊዜ በሚያሳፍርና በሚያጠራጥር ሁኔታ ከተባለችው ወጣት ጋር መገኘቱን እያላበው ካመነ በኋላ ምንም የዝሙት ተግባር አልፈፀምኩም ስለአለና በወቅቱ ከተባለችው ሴት ጋር መርፌና ክር ሲሆኑ ያየ

ስለአልነበረ ወይም የግንኙነት ትግባር መፈፀሙን በቴክኒክ ማስረጃ ተመርምሮ እንዲታወቅ ስለአልተደረገ ምንም ማድረግ ሣይቻል ቀረ:: ስለዚህ የፍቺአቸው ምክንያት ዝሙት በሚል ሣይሆን ሲቲ ራሴል ጨካኝና ትምክተኛ ሰው ስለሆነ፣ ሴት ልጅ እንደዚህ ካለ ወንድ ጋር መኖር ስለማትችል ተፋትተዋል በማለት ፍርድ ቤት ቢያኔውን ሽጠ:: ዘካኦስ ኦቭ ካልትስ የ1938 ዓ.ም. በጃን ቫን ባሌን የታተመውን መጽሐፍ ምዕራፍ 11 ተመልከቱ::

እንዲሁም ውሸቱን የግሪክ ቋንቋ እችላለሁ እያለ በውሸት ሲያጭበረብር ተከሶ ፍርድ ቦት ቀረበ:: በፍርድ ቤትም የእምነት ክህደቱን ሲጠየቅ አዎን እችላለሁ የሚል መልስ ሰጠ:: ይኸንኑ በማስረጃ ለማረጋገጥ በግሪክ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ተሰጥቶት በል አንብብ ቢሉት አይኑ ፈጦ ቀረ:: በመጨረሻም አለመቻሉን አምኖ በይቅርታ ተሰናብቷል::

እንዲሁም ለ3ኛ ጊዜ በስንዴ ማጭበርበር ምክንያት ተከሶ ፍርድ ቤት ቀርቧል:: ይኸው የእኔ ስንዴ ልዩ ተአመረኛ ስንዴ ነው እያለ ስለአጭበረበረ መሆኑን ከታሪክ እንዘክራለን::

በ4ኛ ደረጃ ሆን ብሎ ያረጁ ሀብታም አሮጊትና ሽማግሌዎችን እየፈለገ እግዚአብሔር ይህችን ዓለም እንደሚያጠፋ በቃሉ ገልጾልኛል:: ይህም የሚሆነው በቅርቡ በእድሜአችን ነው:: ከሁሉ ከሁሉ የሚያፀድቀው በዛሬ ጊዜ የአምላክ ቃልን የሚሰብኩ አገልጋዮችንና ምድራዊን የአምላክ ድርጅት ጉልበት ያለው በጉልበት፣ እውቀት ያለው በእውቀት፣ ሀብት ያለው ደግሞ ለምድራዊውና ዓለማዊ ልጆች ከመስጠት ለአምላክ ምድራዊ ድርጅት የስብከት ሥራ እንዲውል ማድረግ



ይገባል እያለ የሕጋዊ ወራሾችን መብት ገፍፎአል:: መላጆችንም አታልለዋል ተብሎ ተከሷል:: እነዚህን ታሪኮች ጃን ቫን ባሌ እ.ኤ.አ. በ1938 ዓመት ያሳተመውን (The Chaos of Ocult) ዘ ካኦስ ኦቭ ከልትስ ምዕራፍ 11 በተጨማሪ መመልከት ነው::

የይሖዋ ምስክሮች በሲቲ ራሴል በተጭበረበረ በማርያ ፍራሴስ ሀብት የተመሠረተውን ድርጅታቸውን በመደገፍና የታሪክን ሐቅ በማድበስበስ ታሪካቸውን ያቀረቡት በሚከተሰው መልክ ነው «Pastor Russell was married in 1879 to Maria Frances Ackley. No children blessed his union. Seventeen years later they disagreed about the management of his Journal and a separation followed» የዚህ ጽሑፍ ሐሳብ «ፖስተር ራሴል ከማሪያ ፍራንሴስ አክሌይ ጋር የተጋቡት በ1879 ዓ.ም. እንደ ኤሮፖ አቆጣጠር መሆኑን ከገለፀ በኋላ ይህ ጋብቻቸው በልጅ ፍሬ አለመታደሉን ይገልጻል:: በመጨረሻም የተፋቱበትን ምክንያት ሲገልጽ በአጭሩ «ራሴል የሚያሳትመው ጆርናል /መጽሔት/ ምክንያት የተነሣ ስለአልተስማሙ ከተጋቡ ከ17 ዓመት በኋላ ተፋትተዋል» ብሎ በአጭሩ ይዘጋል:: የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ዓላማ ሥራ በተሰኘው በ1959 ዓ.ም. መጽሐፋቸው በገጽ 17 ተመልከቱ::

## ምዕራፍ 3

## የ1878 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ትንቢቱን እንዴት እንደአስተባበለ

በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ መጨረሻ ላይ በ1878 ዓ.ም. የዓለም መጥፋት ትንቢታቸው ከከሸፈ በኋላ አድቬንቲስቶች እንደዚህ ያለውን ስሕተት ላለመድገም ለራሳቸው ቃል ገብተው ስብከታቸውን እንዳረሙና እነ ራሴል ግን አንአርምም ብለው ከሚስቱ ጋር ጭምር እንደተገነጠሉ ተረድተናል:: ታዲያ ከዚያ በኋላ የ1878 ዓ.ም. ትንቢት መክሸፍን ራሴል እንዴት ነበር ያስተባበለውና እንደገና ተከታዮችን ለማግኘ ት የቻለ? የሚለውን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ስለ ሲት ራሴል የህይወት ታሪክ እናስቀድም ብለን መስማማታችን የሚተወስ ነው:: የራሴልን የህይወት ታሪክና በሚስቱ ላይ የፈፀመውንም አሻጥር በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 2 ለይ ተመልክተናል:: አሁን ደግሞ በቀጠሮአችን መሠረት ራሴል የ1878 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ አለመምጣትን እንዴት ነበር ያስተባበለው? ወደሚለው እንመለሳለን::

ይህንን ሀሳብ ከማየታችን በፊት አንድ ምሳሌን እንመልከት:: ምሳሌውም በአንድ ትልቅ መሥሪያ ቤት የስብሰባ ጥሪ ተደረገ እንበል:: ሰብሳቢውም የመስሪያ ቤቱ ተጠሪ ወይም መሪው ነው:: የስብሰባ ዝግጅት ተጠናቆ እንደነገ ሲደረግ አንድ ቀን ሲቀረው የድርጅቱ ኃላፊው ከአቅሙ በላይ የሆነ ጉዳይ አጋጠመው:: በብዙ መልኩ ዝግጅት ተደርጎ መካሄድ ያለበት ስብሰባ ስለነበር ይህ የድርጅቱ መሪ ምክትሉንና ሌሎችም የአስተዳዳሪ ቡድን አባላትን ሰብስቦ ስለአጋጣመው ችግር ከገለፀላቸው በኋላ በምክትሉ መሪነት ሁሉም ተባብሮ ስብሰባውን



እንዲያካሂዱ አደራ ጭምር ነገራቸው:: ሁሉም ችግሩን ስለተረዱ ተባብረው የስብሰባውን ስርዓት እንደሚያስፈፅሙ ተማምነው ተለያዩ::

ከዚህ በላይ የተባለው ስብሰባ በሁሉ ትብብርና በምክትል ኃላፊው መሪነት በሚገባ በኘሮግራሙ መሠረት ተከናወነ:: ከጊዜ በኋላ የድርጅቱ ዋና መሪ ከምክትሉ ሪፖርት በሚቀበልበት ወቅት አንድ አንድ ጥያቄዎችን ጠየቀ:: ከተጠየቁት ጥያቄዎች አቶ እገሌ ወደ ስብሰባ መጣ ብሎ ቢጠይቅ ወይም ደግሞ አቶ እገሌ በስብሰባ ላይ ተገኘ ቢል በእነዚህ ሁለቱ ጥያቄዎች መካከል ምን መሠረታዊ ልዩነት አለ? ሰውዬው መጣም አለ ተገኘ ለማወቅ የፈለገው በስብሰባው ላይ መካፈሉንና አለመካፈሉን ነው:: ከዚህ አንፃር ምንም መሠረታዊ ልዩነት ያለ አይመስለኝም:: ይህንን ምሳሌ ማቅረብ የተፈለገው ራሴል ልክ እንደዚሁ ባለው መልክ በ1878 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ሆኖ ዓለም በሞላ ሲጠፉ የእኛ ድርጅት አባላት ብቻ በአሬሳዎች መካከል ቆመው ይቀራሉ:: ከዚያም ጌታ ወደ ሰማይ ይወስደናል ብሎ የተነበየው ትንቢት ሣይፈጸም በቀረ ጊዜ ያስተባበለው በዚሁ መልኩ መሆኑን ለማስረዳት ነው:: ይህንን የራሴልን ማስተባበያ ቀጥለን እንመልከት:-

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ቁጥር 3 ላይ እንዲህ የሚነበብ ጥቅስ አለ:- «እርሱም በደብረዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀመዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉ::» ሲት ራሴል መምጣትህ የሚለውን ቃል ለይቶ ካወጣ በኋላ ጌታ በ1878 ዓ ም ይመጣል የተባለው ቃል ትተን

ደገኛል በሚል ቃል መጠቀም ነበረብን:: ከጥንት እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ የተተረጐመው ኢንፋቲክ ዲያግላት የተባለው መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው መምጣት የሚለውን ቃል ሣይሆን መገኘት የሚል ቃል ነው የተጻፈበት:: በዚህ መልኩ ከጥሩ ኩሬ ምንጭ የተቀዳው የእውነት ትምህርት እየተስተዋለ ነው:: ስለሆነ እውነተኛው ትርጉሙ መገኘት የሚለው ቃል መሆኑን እንረዳለን::

እንግዲህ እኛ በ1874 ዓ.ም. እና በ1878 ዓ.ም. በተደጋጋሚ የተሳሰትነው በዚህ ምክንያት ነው:: ስለሆነም ጌታ ከ1874 ዓ.ም. ጀምሮ የመጣ በመንፈስ ነበር:: ከዚያንጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በመንፈስ ከእኛ ጋር ተገኝቶ የዕለት በዕለት ሥራችንን እየተቆጣጠረ ነው:: ፍየልና በጉን በተግባራቸው እየለየ ነው:: ይህ ፊየልና በግን ወይም ኃጢአተኛንና ጻድቃንን የመለየቱ ሥራ እስከ 40 ዓመት ይቀጥላል የሚል ስብከቱን አሰማ:: ከ40 አመት በኋላስ? የሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ራሴል የሚከተለውን መልስ ሰጠተዋል::

<u>የራሴል መልስ</u>

ራሴል እንዲህ ነበር ያለው «we consider it an established fact that the final end of the kingdoms of this world and the full establishment of the kingdoms of god will be established by the end of A.D 1914"

ከዚህ በላይ ያለው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጽሑፍ ሐሳብ «በ1914 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የዚህ ዓለም መንግሥታት ፍጻሚአቸው ሆኖ ሲያበቃ የእግዚአብሔር መንግሥት በተሟላ መልኩዋ



ትመሠረታለች ብንል የተረጋገጠ እውነት ነው::» የሚል ነው:: ልብ በሉ! ራሴል እግዚአብሔር ሕዝብን አያጠፋም! መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ካለ እራሱ ቅዱስ ያልሆነ ውሸት ነው የሚለውን አቋሙን ለጥቅም ብሎ እንዴት እንደሚለዋውጥ የሚያስገነዝበን ነው::

እንዲሁም የክርስቶስ ከ1874 ዓ.ም. ጀምሮ በመንፈስ ከእኛ ጋር ሆኖ እየተቆጣጠረን ከቆየ በኋላ የአሕዛብ ዘመን መጨረሻ ሆኖ ሲያበቃ በ1914 ዓ.ም. አንድ ሙሽራ ሙሽራይቱን እንደሚወስድ ክርስቶስም መጥቶ ወደ ሰማይ ይወስደናል እያለም ሰብከዋል ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ ላይ መጽሐፍ ገጽ 23 ፓራግራፍ 2 ተመልከቱ::

ስለዚህ በበግ የተመሰሉ ምድር የራሴል ምዕመናን ጌታ በመንፈስ የእንቅስቃሴአችንን ሁኔታ ሁሉ ዕለት በዕለት እየተመለከተ ነው:: በመጨረሻም በ1914 ዓ.ም. አንድ ሙሽራ ሙሽራነቴን እንደሚወስድ በገሐድ መጥቶ ወደ ሰማይ ይወስደናል ብለው የራሴልን ፍልስፍና ከልብ ተቀበሉ! ለአምስተኛ ጊዜ እንደገና በ1914 ዓ.ም. ዓለም በሙሉ ይጠፋል የሚለውን ትንቢት ማወጅ ጀመሩ:: የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ ላይ የ1959 ዓ.ም. እትም መጽሐፋቸው ገጽ 23 ተመልከቱ::

በጣም የሚያሳዝነው ራሴል እራሱን ፓስተር ራሴል ማለት የመንፈሳዊ እረኛ እያለ እየጠራ ነገር ግን ምንም እምነት ሣይኖረው ሌሎችን አለልክ እንዲያምኑ እያጃጃለ ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውን ባልተቆጠበ መልኩ መበዝበዙ ነው:: ምንም ነገር እንደማይፈጠር ልቡ እያመነ በ1889 ዓ.ም.

የዚህ ዓለም መንግስታት በሙሉ በ1914 ዓ.ም. እ.ኤ.አ ይጠፋሉ፣ የእግዚአብሔር መንግስትም በእነርሱ ትቢያ ላይ ትመሠርታለች እያለ ሕዝቡን ያሳምን ነበር::

የጥፋቱ ቀን የራቀ እየመሰላቸው ምዕመናኖች የቸልታ መንፈስ ስለአሳዩ በ1914 ዓ.ም. ይሆናል ተብሎ የታወጀውን ጥፋት እንደገና በማሳጠር በ1907 ዓ.ም. ይሆናል ሲል አወጀ:: ለዚህ ነው ራሴል ቅንጣት እምነት ሣይኖረው ሌሎችን በጥቅሶች እያወናበደ አለልክ አክራሪ ዓማኞች እንዲሆኑ እያደረገ ይጠቀምባቸው ነበር የሚያሰኘው፡እንደዚህ አድርጎ ማስተማሩን ቀጥለን እንመልከት::

ራሴል በ1893 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የዓለም መጨረሻ በ1914 ዓ.ም. ይሆናል የሚል አቋሙን ለውጦ እንዲህ ሰበከ:: «ትልቅ ጥፋት ተቃርበዋል:: ምንም እንኳን ይህ ትልቅ ጥፋት በትክክል በዚህን ጊዜ ይከሰታል ባይባልም፣ የማዕበሉ ጥፋት መምጣት ከ12 ወይም ከ14 ዓመት አይበልጥም::» የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ ላይ የ1959 ዓ.ም. እትም መጽሐፍ ገጽ 52 ተመልከቱ:: በ1907 ዓ.ም. ጥፋት ይመጣል ማለቱን እንዴት እናውቃለን? የሚል የየዋሆች ጥያቄ ሊኖር ይችላል:: መልሱ ቀላል ነው:: ጥፋት ከ12 ወይም ከ14 ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ይመጣል የተባለው እ.ኤ.አ. በ1893 ዓ.ም. ነበር::

ስለዚህ የጥፋቱ መከሰት ዘመን የተባለውን 14 ዓመት ወስደን ከ1893 ዓ.ም. ጋር (14+1893 ዓ.ም=1907 ዓ.ም.) ስንደምር የምንአገኘው 1907 ዓ.ም. እንደሆነ ነው:: በዚህም በመጣብህ፣ መጣብሽ ሽብር ስብከቱ ሰዎችን ለማሞኘት ችለዋል:: ከጊዜ በኋላ ደግሞ በ1907 ዓ.ም. ይመጣል የተባለው የዓለም መጨረሻ



ስለአልመጣ እንደልማዱ ሰበብ ደርድሮ ያው በ1914 ዓ.ም. እንደሚሆን መሰበኩን ቀጠለ::

<u>በ1914 ዓ.ም. የዓለም ጥፋት አለመምጣት</u>

በዚህ በ1914 ዓ.ም. የዚህ ዓለም ምድራዊው መንግስታት ጠፍተው፣ የእግዚአብሔር ሰማያዊ መንግስት በማቴዎስ ምዕራፍ 6 ቁ. 9-10 መሠረት ትመሠረታለች:: እኛም ምርጥ የቤተክርስቲያን አባላት በዚሁ በ1914 ዓ.ም. ወደ ሰማይ እንወጣለን የሚለው ትንቢታቸው አሁንም ከሸፈ:: የዓለም መጨረሻ ከሆነ በኋላ ምዕመናኖቹን እየመራ እንኳን ወደ ሰማይ መውጣት ራሴል ጥቅምት 16 ቀን 1916 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: በዚህን ጊዜ እያሞኛቸው አለደመወዝ በሆድ ብቻ ሌት ተቀን ያሠራቸው የነበሩ ከሰባቱ የቦርድ ዳይሬክተሮች አባላት ብዙዎቹ መሣሣታቸውን አወቁ:: ከእንቅልፋቸው መባነን ጀመሩ:: ከላይ እንደተባለው እነዚህ የቦርድ ዳይሬክተሮች ቤቴል በሚባለው በማሕበሩ ድርጅት ውስጥ እየኖሩ በነፃ ምግብ እየተመገቡ ሥራውን ሌት ተቀን የሚሠሩ ናቸው:: በ1957 ዓ.ም. የዚህ መጽሐፍ ደራሲ እንደሚያውቀው ከሆነ እነዚህ የቦርድ ዳይሬክተሮች እና ሌሎችም በዚህ ቦታ እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው ሰዎች ምግባቸውንና መኖሪያ ቤታቸውን በነፃ እያገኙ ለሊስትሮና ለመሳሰሉት ጥቃቅን ወጭዎች 14 የአሜሪካን ብር የኪስ ገንዘብ ይሰጣቸው እንደነበር ነው::

በሌላ አባባል በፈላጭ ቆራጭ ኀሬዝዳንት እየተመሩ በሆዳቸው ብቻ አለደመወዝ በነፃ የሚያገለግሉ ናቸው:: ጡረታቸው ለኀሬዝዳንቱና ለድርጅቱ መመሪያ እስከመጨረሻ ፍጹም ታማኝነትን የሚያሳዩ ከሆነ የተቻላቸውን እየሠሩ ምግብ

መመገብ ብቻ ነው። በዚህ መልኩ ሲያገለግሉ የነበሩት የድርጅቱ የቦርድ ዳይሬክተሮች ለአምስተኛ ጊዜ በ1914 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ አለመሆኑን በተገነዘቡ ጊዜ 2ኛ እንደዚህ እያልን ሕዝብን ማታለል የለብንም። ስለዚህ ይህንን ሁኔታ ማረም አለብን፣ መታረም አለበት ብለው ተነሱ። ይኸንኑ በወቅቱ ሚቼ ሲቲ ራሴልን ለተካው ራዘር ፍርድ ለተባለው ሰው ሐሳባቸውንና ውሳኔአቸው አስረዱት። እየተደጋገመ ሲገለፅ እንደነበረው ሁሉ የማሕበሩ ኀሬዝዳንት ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ አዛዥ ነው እንጂ በቦርድ ዳይሬክተሮች የሚታዘዝ አይደለም። በሕጉም ቢሆን የቦርድ ዳይሬክተሮች የበላይ ወሳኝ አካሎች ሆነው ኀሬዝዳንቱ ለቦርድ ዳይሬክተሮች ተጠሪ አይደለም። በሕግ በተገላቢጦሽ የቦርድ ዳይሬክተሮች ለኀሬዝዳንቱ ተጠሪ መሆናቸው ተመዝግበዋል። ከዚህም በላይ በዚህ ዓ.ም. ዓለም ትጠፋለች፣ እኛም የዘላለም ሕይወትን አግኝተን ለዘላለም እንኖራለን በሚል ቸካካ እምነት ከመመራት ውጭ የቦርድ ዳይሬክተር ተብዬዎች ምንም ነገር የሚያቁትና ለማወቅም ምንም ፍላጐት ያልነበራቸው ናቸው። አሁን በ1914 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ስለአልሆነ፣ እንዲሁም እንኳን እነርሱን እየመራ ወደ ሰማይ መውጣቱ ቀርቶ ራሴልም ስለሞተ፣ ከእንቅልፋቸው እየባነኑ ስሕተቱን ለማረም ቢሞክሩም በዚህ ልምድ አልባ ሙከራቸው ተሸነፉ! እንዴት?

ሲት ራሴል በዓለም መጨረሻ እያሞኛቸው መሠረታዊ የሕግ ሥልጣን እንዳይኖራቸው ስለአደረገ ነው። ሲት ራሴል ሁል ጊዜ ሕግን ተከትሎ በፈቃደኝነት የሠራበት ጊዜ አልነበረም። ይህ ማሕበር የተመሠረተው በፔንሶላቨኒያ ሕግ ነው። ራሴል በመጽሐፍ ቅዱስ ያጃጃላቸውንና ብዙ በትምህርት



ዓለም ያልዘለቁት ፍጹም ታዛዥዎቹን በቻ ሰብስቦ የቦርድ ዳይሬክተሮች ካደረገ በኋላ የቦርዱ ዳይሬክተሮች ለኀሬዝዳንቱ ተጠሪ መሆናቸውን በሕግ አስመዘገበ። ይህ የቦርድ ዳይሬክተርነትና ለኀሬዝዳንቱ ተጠሪ የመሆን ሹመታቸው በየዓመቱ ካልታደሰ አይሠራም። ስለዚህ አንዴ ከተመዘገቡ የዚህ ዓይነት ስልጣንአቸው በሕግ ፊት ዋጋ የሚኖረው በየዓመቱ ካሣደሡ ብቻ እንደሆነ በፔንሴላቫኒያ ሕግ የተደነገገ ነው። ራሴል ግን ማርያን ሙልጭዋን ለማባረር ብሎ እነዚህን የእምነት አክራሪ የቦርድ ዳይሬክተሮችን በሕግ እንዲመዘገቡ አድርጐ ከተጠቀመባቸው በኋላ በየዓመቱ ይህንን ስልጣንአቸው ሣያሳድስላቸው ቀረ። ስለዚህ በስም ብቻ የቦርድ ዳይሬክተሮች በሕግ ግን የሕግ መሠረት ያልነበራቸው ናቸው። በዚህ ደረጃ ላይ እያሉ ነው የድርጅቱን ዓላማ ለመቀያየርና ኀሬዝዳንቱ ለቦርድ ዳይሬክተሮች ተጠሪ እንዲሆኑ ለማድረግ የተነሱት። ራሴልን የተካው ራዘር ፎርድ የሕግ ሰው ነበር። የራሴልንም የሕግ አማካሪ የነበረ ሰው ነው። በዚህ መልኩ በሆድ ብቻ ያገለግሉ የነበሩ የቦርድ ዳይሬክተሮች የድርጅቱን ዓላማ ለመቀየርና ኀሬዝዳንቱን ለመሻር በተነሱ ጊዜ ራዘር ፎድ ኃይል ጭምር ተጠቅሞ ከድርጅቱ ጠራርጐ አስወጣቸው። በእነርሱም ምትክ የሚያምንባቸውን ፍጹም ታዛዥዎችና ታማኝዎች የሆኑትን የቦርድ ዳይሬክተር እንዲሆኑ በሕግ ወዲያውኑ አስመዘገባቸው። ከዚህ አንፃር ሕጋዊ መብት ስለሌላቸው ተባርረው ቀሩ። የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ የ1959 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. መጽሐፋቸውን በገፅ 69፣ 70 እና 71 ተመልከቱ።

## የ1914 ዓ.ም. ስሕተታቸውን እንዴት እንደአስተባበሉ

የአፋፎ ልጅ ጠላፎ እንዲሉ የሲቲ ራሴል ወራሽ ወንድም ራዘር ፎርድ እነዚህን ከድርጅቱ ያባረራቸውንና የእነርሱም ተከታዮች የነበሩትን ሰዎች ለጌታ በ1914 ዓ.ም. መጥቶ ዓለምን ማያጠፋ ‹መቅረት ምክንያት አፏረጋቸው:: እንዲህ ባለ ወቅት ሁልጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተፈልጐ በቀዶ ጥገና መልክ ትርጉም ከተሰጠ በኋላ በገሐድ ለምዕመናኖቹ ይገለፃል::

ጌታ በ1914 ዓ.ም. ያልመጣው እምነተ ቢስ ከሀዲዎች ሰዎች ስለነበሩ፣ በመጀመሪያ እነርሱን በፍርድ ከድርጅቱ እንዲሰናበቱ ለማድረግ ብሎ ነው:: ይህም አስቀድሞ በሐዋርያት የተነገረ ትንቢት ነው ብለው የሚከተለውን ጥቅስ ጠቀሱ:- የተጠቀሰው ጥቅስ በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 4 ቁ. 17 ላይ የሚገኘ ው ሲሆን እንዲህ ይነበባል:: «ፍርድ ከእግዚአብሔር ተነስቶ የሚጀምርበት ጊዜ ደርሷልና| አስቀድሞ በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን?» ታዲያ የእግዚአብሔር ቤት የትኛው ነው? በራሴል የሚመራ በእርግጥ የእግዚአብሔር ቤት ለመባል ብቃት የለውም:: በማጭበርበር የተመሠረተ የእምነተቢስ ቤት ነው::

ስለዚህ አለ ራዘር ፎርድ:- እግዚአብሔር በ1914 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የዚህችን ዓለም መንግስታት አጥፍቶ የዓለም መጨረሻን ያለአደረገው በዚህ በእግዚአብሔር ምድራዊ ድርጅት ውስጥ በነበሩት አጥፊዎች ላይ አስቀድሞ ለመፍረድ ነው ሲል ደመደመ:: ለእግዚአብሔር ሁለቱንም ማድረግ ምን ይሣነው ነበር? በመጀመሪያ በቤቱ ቀጥሎም በዓለም ሕዝብ ላይ መፍረድ አይችልም ነበርን? ብሎ የሚጠይቅ ጭንቅላት ጠፋ:: ስለዚህ



አፈንጋጮች ከሆኑት ወንድሞች የሚባረሩ ተባርሮ የተቀሩትን እንቀሣቃሽ የፍልስፍና ቤንዝን በሚገባ ተሞላ:: የፍልስፍና ቤንዝን አሞላላቸው እንዴት እንደሆነ በሚቀጥለው እንመለከታለን::

## ምዕራፍ 4

## የይሖዋ ምስክሮች አንቀሳቃሽ ቤንዝን

ሀ. የይሖዋ ምስክሮች አንቀሳቃሽ ቤንዚን የተባለው ምንድን ነው? ምን ማለት ነው? አንድ መኪና ቤንዚን ከሌላት ትቆማለች:: ስለዚህ ቤንዚን አልቆባት እንዳትቆም የመኪናዋን ቤንዚን በቤንዚን መቆጣጠሪያ ዔጅ መቆጣጠሩ አስፈላጊ ነው:: የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት ቶሎ ቶሎ ቤንዚን በሚያልቅበት መኪና ማስመሰል እንችላለን::

ለ. ቤንዚኑ ደግሞ የዚህ ድርጅት መሪዎች በየጊዜው እየፈለሰፉ በሚያውጁት የዓለም መጨረሻ ፍልስፍና ትምህርታቸው ይመስላል::

ሐ. ምስክሮቹ ደግሞ ቤንዚን አልቆባት ከቆመች በኋላ ቤንዚን ሲጨመርባት መከነፍ ወይም መብረር በምትጀምረው መኪና ይመስላሉ:: ከላይ የተገለጠው በትክክል የይሖዋ ምስክሮችን የእንቅስቃሴ ገጽታ በግልጥ የሚያሳይ ነው:: እንዴት? እንዲህ ነው:-

1. የእግዚአብሔር የሚታይ ምድራዊ ድርጅት ኘሬዝዳንትና የኘሬዝዳንቱ ፍጹም ታዛዥዎች የሆኑ ሰባቱ የቦርድ ዳይሬክተሮች በቤንዚን የተመሰለውን የዓለም መጨረሻ መምጣት ዓመት ጠቅሰው በእንዲህ ዓመተምሕረት ዓለማችን ትጠፋለች የሚል የትምህርት ፍልስፍና ማዘጋጀት ካልቻሉ የድርጅቱ ክስረት ይከሰታል:: በእውቀታቸው፣ በገንዘባቸው እና በጉልበታቸው ሁለገብ አገልግሎትን የሚያበረክት ምዕመናን አይገኝም:: እርዳታ ይቆማል:: በሌላ አበባል ቤንዚን ባለቀበት መኪና የተመሰለ የድርጅታቸው ሥራ ይቆማል::



2. ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት መሪዎች በዚህ መልክ ፍልስፍናን ካዘጋጁ ማለት ቤንዚን ተሞላ ማለት ነው:: የቆመች መኪና ወይም የክስረት ቀስት ያሳየው ድርጅት ከፍተኛ የትርፋማነት እንቅስቃሴን አሣየ ማለት ነው:: የዓለም መጨረሻ በቅርቡ ይሆናል የሚለው ስብከታቸው ከታወጀ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር አባል በንቃት ሁለገብ አገልግሎቱን ያበረክታል:: መኪናዋ መክነፍ ጀምራለች ወይም የድርጅቱ ሥራ በትርፋማነቱ እንቅስቃሴው እየተጧጧፈ ነው ማለት ነው:: ምስክሮቹ የዓለም መጨረሻ በዚሁ በሕይወታችሁ ዘመን ይመጣል:: ከዚህ ዓ.ም. እስከዚህ ዓ.ም. ድረስ ዓለም ጠፍታ፣ እናንተ የአምላክ አገልጋዮች በሬሣዎች መካከል ቆማችሁ ትቀራላችሁ ከተባሉ በጣም ተግተው ይሠራሉ:: ገንዘብን ለማህበሩም ያዋጣሉ:: ነገር ግን የዓለም መጨረሻ ቶሎ የማይመጣ ከመሰላቸውና ይኸው ስብከት በየጊዜው በጆሮአቸው ካልተንቆረቆረባቸው ምስክሮቹ ይዝላሉ:: ድርጅቱንም አያንቀሳቅሱትም:: አገልግሎታቸውን ያቆማሉ፣ መጽሐፎቻቸውን አይገዙም፣ አይሸጡላቸውም:: ምስክሮቹ በጣም ራስ ወዳድነት ስለተጠናወታቸው የዓለም ሕዝብ በሙሉ አልቆ እኛ ለምን ወደ ሰማይ አልተወሰድንም የሚለው ኩርፊያቸው አይጣል ነው:: የዓለም መንግስታት ከእነሰራዊታቸው በቅርቡ ይጠፋሉ ከተባለ ይቧርቃሉ:: የዓለም ሃይማኖቶች ለዓለም ሕዝብ ደህንነት ሲፀልዩ፣ የይሖዋ ምስክሮች ግን ሌት ተቀን የጠቅላላ ዓለም ጥፋት በቶሎ እንዲመጣ ይፀልያሉ:: ስለዚህ በ1914 ዓ.ም. የዚህ ዓለም መንግሥታት በሙሉ እግዚአብሔር ስለአላጠፋቸው አኩርፈው ድርጅታቸውን እንደጉድ ስለሰቀቁ ይህንን የአባሎቻቸውን መልቀቅ በ1ኛ ጴጥሮስ

4.ቁ 17 ላይ የተነገረው ትንቢት እንዲፈፀም ተብሎ ነው የሚል ስብከት ለቀሪዎቹ ምዕመናን ሰጡ:: የ1914 ዓ.ም. የዓለም ጥፋት ያልመጣው ስለዚህ ነው ብለው ሕዝቡን ካረጋጉ በኋላ ቤንዚን ማለቁን የማሕበሩ ኘሬዚዳንት በደንብ ተገነዘበ:: ስለዚህ ሌላ ፍልስፍና ቀምሮ የዚህች ዓለም ጥፋት በዚህ ዓ.ም. ይመጣል ማለት አስፈላጊ ሆነ:: ለ6ኛ ጊዜ ሌላ የዓለም መጨረሻ በቅርቡ መሆን ማወጅ ግድ ሆነባቸው::

## በ 1920 ዓ.ም. የተሞላ ቤንዚን

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ዓ.ም. «አሁን በመኖር ላይ ያሉት ሚሊዮኖች ከቶዉኑ አይሞቱም::» (Millions now living never die) የሚል መጽሔት አወጡ:: በዚህ መጽሔት ላይ ለ6ኛ ጊዜ በ1925 ዓ.ም. ዓለም ትጠፋለች እኛም ወደ ሰማያዊ አገራችን እንለወጣለን ብለው አወጁ:: የእግዚአብሔር መንግሥት ከፍ አለች፣ ጠላትዋ ተጋለጠ በሚል ርዕስም የሕዝብ ንግግሮችን በየጉባኤያቸው አሰሙ:: ይህንን ስለአሉ ብቻ እነአይጠናሆዱ በጐች ወደ ድርጅታቸው ጐረፉ:: ይህንኑ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል:: እንዲሁም የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ ላይ የ1959 እትም መጽሐፍ ገጽ 107 ፖራግራፍ 2 ላይ የተባለውን ተመልከቱ::

የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ዓላማ 1959 ዓ.ም. እትም በተሰኘው መጽሐፋቸው በገጽ 107 ፖራግራፍ 2 ታሪኩን



አንብቡ:: ልክ ይህንን ስብከት እንደሰሙ ወደ ድርጅታቸው ሕዝቡ መጉረፍ እንደጀመረ ቀጥሎ ባለው የንፅፅር ቀመር እንመልከት:-

**የጌታ ዕራት በዓል**

| ዓመተ ምህረት | የሕዝብ ብዛት |
|---|---:|
| በ1922 ዓ.ም. | 32,661 |
| በ1923 ዓ.ም. | 42,000 |
| በ1924 ዓ.ም. | 62,000 |
| በ1925 ዓ.ም. | 90,434 |
| በ1926 ዓ.ም. | 1,156 |

ከዚህ በላይ ያሉትን ቁጥሮች ስንመለከት የአባሎቻቸው ብዛት እንዴት እየጨመረ መጥቶ፣ በ1926 ዓ.ም. ላይ ግን ድንገት ወደ 1,156 እንደወረደ እንመለከታለን:: በዚህ በ1925 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ይሆናል ተብሎ ሲሰበክ ከከረመ በኋላ የተባለው የዓለም መጨረሻ ጥፋት ስለአልተከሰተ ሕዝቡ ድርጅታቸውን ጥሎ እንደወጣ የሚያሳይ ነው:: ይህ ማለት በአንድ ጊዜ ሁለገብ አገልግሎት የሚያበረክቱላቸው አባሎቻቸው በብዛት ተዋቸው ማለት ነው:: በአንድ ጊዜ 89,278 ሕዝብ ተዋቸው:: በሰው መነገድ ለለመደ ለዚህ ዓይነቱ ድርጅት እጅግ በጣም ትልቅ ኪሣራ ነው:: ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ ምዕራፍ 16 ገጽ 110 ፖራግራፍ 4 ተመልከቱ:: እንደፈረደባቸው እንደገና የነቁባቸውን ሸኝተው በተቀሩት ጥቂቶች በመጠቀም እንደገና ማስተባበል ጀመሩ:: ምክንያት መፍጠርና የተጣመመ የጥቅስ ትርጉሞችን መፈልሰፍ ጀመሩ::

## እያንዳንዱ አባላቶቻቸው የድርጅቱ ሸቀጥ ናቸው

እያንዳንዱ በፍልስፍናቸው ጭንቅላቱ የታጠበ የይሖዋ ምስክር የድርጅቱ ሸቀጥ ነው። አንድ ነጋዴ ሸቀጦችን እያገላበጠ እንደሚነግድበት ሁሉ ይህም ድርጅት በምዕመናኖቹ ይነግዳል። ነጋዴ ሸቀጥ ካጣ እንደሚከስር ሁሉ ይህ የምስክሮቹ ድርጅትም ተሰባኪ ምዕመናን ከሌሉት ይከስራል። የድርጅቱ ገቢ በምዕመናኖቹ ሁለገብ አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ነው። ምዕመናኖቹ ሁለገብ አገልግሎት እንዲያበረክቱ የዓለም መጨረሻ ቀርቧል፤ ስለዚህ ባላችሁ አቅም ሁሉ የአምላክን ምድራዊ ድርጅት በማገልገል የመዳን ዋስትናችሁን ጨብጡ ብሎ የዓለም ጥፋት የሚሆንበትን ዓ.ም. መወሰን ብቻ ነው። ከዚህ በኋላ አንድ ነጋዴ ከሸቀጡ ገቢ እንደሚያገኘው ሁሉ ድርጅቱም ከምዕመናኖቹ ገቢ ያገኛል።

እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር ለማሕበሩ እራሱን አሳልፎ የሰጠ ነው። እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር የእግዚአብሔር ምድራዊ ድርጅት ነው ብሎ ለሚጠራው ለዋች ታዎር ማህበር እንደአቅሙ በዓመት የተወሰነ መዋጮ ያደርጋል። ይህንኑ ወስኖ ቃል የገባውን የገንዘብ መጠን በአንድ ዓመት ውስጥ ከፍሎ እንደሚጨርስ ለዎች ታዎር ኀሬዝዳንት ቢሮ በቀጥታ የተሰፋውን ሰነድ ይልካል። ሁበታምም ከሆነ ወዲያውኑ የዓመቱን ክፍያ ይልክላቸዋል። ይህ ቃሉ አይታጠፍም። እራስን አሳልፎ መስጠት የሚለው ቃል ይኸንኑ ያመለክታል። እራስን አሳልፎ መስጠት ማለት በይሖዋ ምስክሮች ትርጉም «ከዛሬ ጀምሮ የራሴን ፈቃድ ሳይሆን በድርጅትህ እየተመራሁ የታዘዝኩትን ሁሉ ለመፈፀም ቃል እገባለሁ» ብሎ መማል ማለት ነው። ድርጅቱ ይኸንን አታድርጉ፤ ካስፈለገም ሙቱ ካሏቸው በእርግጥ ላለማድረግ ይሞታሉ። ያልታወቀባቸው አጥፍቶ ጠፊዎች ናቸው።

እንደዚህ በወረቀት ላይ ሲፃፍ ውሸት ይመስላል፣ ነገር ግን በእውነት የሚያደርጉት ነው። ለምሳሌ በማሕበሩ ሕግ ደም መብላትም ሆነ በደም ሥር በመርፌ ወደ ሰውነት ማስገባት ክልክል ነው። አንድ ሰው በድንገት አደጋ ደርሶበት ደሙ ከሰውነቱ ፈሶ ካለቀ፣ በፈሰሰው ደም ምትክ ተመሳሳይ ደም ካልተሰጠው ይሞታል። ከተሰጠው ግን መቶ በመቶ እንደማይድን በሕክምና ዓለም የተረጋገጠ ነው። በዚህ መልኩ የተጐዳው ሰው እራሱን አሳልፎ የሰጠ የይሖዋ ምስክር ከሆነ፣ ወይም የይሖዋ ምስክር ልጅና በእነርሱ ሥር የሚተዳደሩ ሰዎች ከሆኑ የፈሰሰውን ደም የሚተካ ተመሳሳዩን ደም በምንም ተአምር አይቀበሉም። ደምን ከመውሰድ ይልቅ የድርጅቱን ትእዛዝ በማክበር መሞትን ይመርጣሉ። ስለዚህም ይሞታሉ። እኔም የገዛ እህቴ አደጋ ደርሶባት ደም እንዳትወስድ ከመከልከሌም በላይ እርስዋ ባትፈቅድም አንተ ፈርምና ደም ሰጥተናት እናድናታለን ብለው በጠየቁኝ ጊዜ አልፈርምም ብዬ እህቴን አጥቼአለሁ። ለራሴም ቢሆን ያኔ ይኸው ዓይነቱ ዕጣ ይደርሰኝ ነበር። በሌሎች ምክንያቶችም ቢሆን ይኸው ነው።

ለምሳሌ ሲያድባሬ ይውደም ብላችሁ መፈክር አሰሙ፤ ተብሎ በቀበሌ ስብሰባ በደርግ ካድሬዎች በታዘዙ ጊዜ፣ እንደዚህ ያለውን መፈክር ማሕበሩ ስለማይፈቅድ አንልም ብለው በቦዘኔ የቀበሌ ካድሬዎች ተረሽነዋል። እራስን አሳልፎ መስጠት በተግባር ሲታይ ይህንን ይመስላል። በዚህ መልኩ አእምሮ

ታጥበው ለአንድ ዓላማ ብቻ የተሰለፈ ሰው ለማሕበሩ በዓመት ይህን ያህል ገንዘብ አዋጣለሁ ብሎ ካለ እንደሚያዋጣ መቶ በመቶ የተረጋገጠ ነው፡፡ ማሕበሩም ቢሆን የዓመት በጀቱን ከዚህ አንፃር እያየ በእርግጠኝነት ያዘጋጃል፡፡ ስለሆነም የይሖዋ ምስክሮች የድርጅቱ የገቢ ምንጭ ሽቀጥ ናቸው፡፡ ይህ ዋነኛ የመጀመሪያው ዓይነቱ መዋጮ ነው፡፡ ሌላ በእጅ አዙር እንደየአቅማቸው ለማህበሩ የሚያዋጡት ገንዘብ አለ፡፡ ቀጥለን እንመልከት፡-

<u>በእጅ አዙር የሚያዋጡት ገንዘብ</u>

ሀብታምም ሆነ ደሀ እንደአቅሙ በይሖዋ ምስክሮች ለሚመራው የመንግስት አዳራሽ ለሚባለው በየወሩ ለኪራይ መዋጮ ያደርጋል፡፡ የመንግስት አዳራሹን ከመከራየት ይልቅ መሬት ገዝተን እራሳችን እንሠራለን ካሉም ለዚህ ፕሮጀክት እንደአቅሙ ገንዘብ ማዋጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉም በእውቀቱና በጉልበቱ ወዘተ በመሣተፍ ይሠራል፡፡

በመጨረሻም በጉልበታቸው፣ በገንዘባቸው የተሠራው ይህ ህንፃ የይሖዋ ምስክሮች ወይም የዋች ታዎር መጽሐፍ ቅዱስና ትናንሽ ጽሑፎች ማሕበር ስም ይመዘገባል፡፡ የድርጅቱ ንብረት እንዲሆን በሕግ እውቅና አገኘ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የዎች ታዎር መጽሐፍ ቅዱስና ትናንሾች ጽሑፍ ማህበር ምንም ቤሳቤስቲን ሣያወጣ የሕንፃው ባለቤት ይሆናል፡፡ ይህ ድርጅት ሽቀጦቹ እንዲሆኑ ጭንቅላታቸውን በፍልስፍናቸው ቀመር ያጠቡአቸው የምዕመናኖችን ትርፍ በየጊዜው በዚህ መልኩ ያፍሣል፡፡



ከሁሉ ከሁሉ የበለጠ የምስክሮቹ አገልግሎት እየዞሩ ሌላ ጥቅም ሰጪ አባላትን እየሰበኩ ወደ ድርጅቱ ማምጣት ነው፡፡ በዚህ መልኩ አእምሮአቸው በስብከት እየታጠበ ወደ ድርጅቱ የሚመጡት አባላት ሁሉ ከእራሳቸው ድርጅት ውጭ ሌሎችን ጽሑፎች እንዳያነቡ ይመከራሉ፡፡ ለይስሙላ እየተመለመሉ የድርጅቱ የቦርድ ዳይሬክተሮች እንዲሆኑ በኘሬዝዳንቱ የሚሾሙ ፍጹም ታዛዥዎችና ሕሊናቸው በፍልስፍና እንደ ጋሪ የተሸበቡ ተራ አባላት መካከል የድርጅቱን ሕግ ከመጠበቅ አንፃር ልዩነት የለም፡፡ እንዲሁም በግትርነትና ትንሽም ባለማሰብ እንደ እሳት እራት ለመማገድ በመሰለፍ ረገድ ተራ አባላት ይበልጣሉ፡፡ ለዋች ታዎር ድርጅት በነፃ ሁለገብ አገልግሎት ማበርከት ማለት ለዘላለም አለመሞትን የሚያስወርስ እንደሆነም ይታመናል፡፡

<u>ሹመትን በገንዘብ ስለመሸጣቸው</u>

በድርጅቱ እምነት ያኔ እውነተኞች የይሖዋ ምስክሮች ወይም ከሁሉ አንፃር ተገምግሞ የይሖዋ ምስክሮች የሚባሉት ከ2ሺህ አይበልጡም ነበር፡፡ እነዚህ ቀሪዎች እየተባሉ የሚጠሩት የ144.000 አባላት ናቸው፡፡ እንደ ድርጅቱ የእምነት ፍልስፍና 142.000 የሚሆኑት ወደ ሰማይ ወጥተው ከክርስቶስ ጋር ተቀላቅለዋል፡፡ በሞቱ ቁጥር ወዲያውኑ ትንሣኤ አግኝተው ወደ ሰማይ ወጥተዋል ይባላል፡፡ ገና ያልሞቱት እና በምድር ላይ ያሉት የእነዚህ 144ሺህ አባላት ቅቡዓን ቀሪዎች ይባላሉ፡፡ ስለዚህ ወንጌልን በመስበክ ኃላፊነት የተጣለብን በእኛ ላይ ነው የሚሉ ናቸው፡፡ ሌሎች ሰባኪዎች የእነርሱ ረዳቶች ናቸው፡፡

ከእነዚህ ከቅዱሳን ቅቡዓን ቀሪዎች ውጭ ሌሎች በጎች እየተባሉ የሚጠሩ ምዕመናኖቻቸጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ከዓለማዊ

ትምህርትም አንባር ደከም ያሉ፣ የአእምሮ እጥበት የተካሄደባቸው ተራ ሰዎች ናቸው። ድርጅቱንም በገንዘብ፣ በጉልበት የሚያገለግሉ የቅቡዓን ቀሪዎች ሽቀጦች ወይም አገልጋዮች ናቸው። እነዚህ ይህንን ሁሉ አገልግሎት የሚያበረክቱት ከዛሬ ነገ የዚህች ዓለም መንግሥታት ሲጠፉና ቅዱሣኖቹ ወደ ሰማይ ሲሔዱ እኛ የምድር ገዥዎች ሆነን ለዘላለም በምድር ላይ እንኖራለን ብለው የሚያምኑ ናቸው። እንደዚህ ያለ የቅዥት ዓላማ ስለአላቸው ድርጅቱን በነፃ እንዲያገለግሉ ገንዘብ ከኪሣቸው አውጥተው ይከፍላሉ። ስለዚህ በሙስና የተካነው የዎች ታዎር የአስተዳደር አካል ኘሬዝዳንት በእነዚህ ዓይነቱ የሕዝብ ስሜት በመጠቀም ገንዘብ ያስከፍላቸዋል። የዎች ታዎር ድርጅት የሚታይ የእግዚአብሔር ምድራዊ ድርጅት ነው ብለው ምዕመናኑ ስለሚያምኑ ሁለገብ አገልግሎትን ለድርጅቱ ለማበርከት ይፈልጋሉ። ይህ ዓይነቱ የነፃ አገልግሎት ለፅድቅ ያበቃናል ባዮች ናቸው። በተለይ በተለይ የሐላፊነት ቦታ ላይ በነፃ በታማኝነት ማገልገል በአምላክ ዘንድ የማይረሣ ውለታ እንደሆነም ይገምታሉ። ስለሆነም ማሕበሩ በሐላፊነት ቦታ ለማገልገል የሚፈልግ ሁሉ በገንዘብ መወዳደር አለበት፤ በገንዘብ ተወዳድሮ ያሸነፈ ብቻ ለሐላፊነት ይበቃል ብሎ አወጀ።

በዚህ ድርጅት በየአገሩ፣ በየከተማው እጅግ ብዙ ጉባኤዎች አሉአቸው። አንድ ጉባኤ የሚባል ከ50-200 ሰዎችን ሊያቅፍ ይችላል። በአንድ ጉባኤ ብቻ የሚከተሉት የሐላፊነት ቦታዎች አሉ፡-



በዚያን ዘመን እኔ እንደማውቀው እና ከታሪካቸውም እንደምንአነበው 1ኛ. የአገሩ የቅርንጫፍ ቢሮ አገልጋይ 2. የጉባኤ አገልጋይ 3. የጉባኤ ረዳት አገልጋይ 4. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልጋይ 5. የጉባኤው የቴሪቶሪ አገልጋይ 6. የመለኮታዊ ትምህርት ቤት አገልጋይ 7. የዎች ታዎር ጋዜጣ ጥናት አገልጋይ ወዘተ.

ሰዎች ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች በነፃ ምንም ሣይከፈላቸው በትጋት ለማገልገል ከፍተኛ ፍላጐት ስለአላቸው፣ ማንኛውም ሰው 10 የአሜሪካን ዶላር እንደ አንድ ድምፅ ከፍሎ ተወዳድሮ ካሸነፈ ብቻ ይፈቀድላቸው ነበር። ለዚህ ዓይነቱ የሐላፊነት ቦታ የጉባኤ አባላት የሆኑና እራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ ወንድሞች ሁሉ መወዳደር ይችላሉ። ስለዚህ ብዙ ድምፅ ያገኘ ማለት ብዙ አሥር የአሜሪካን ብሮች የከፈለ ሰው አሸናፊ ይሆናል። ሁሉም የመጨረሻ ሣንቲማቸው እስከትቀር ተወዳድረው ያሸነፉት ሐላፊነታቸውን የሚረከቡ ሲሆን፣ ያላሸነፉት ደግሞ በውድድር ወቅት ለማሸነፍ ለጨረታ የጠሩት የገንዘብ መጠን ወይም ያስመዘገቡት የመጨረሻ የገንዘቡ መጠን ለዚህ ለሚያምኑበት የእግዚአብሔር የሚታየው ምድራዊ ድርጅት ማዳበሪያ እንዲሆን በፈቃዳቸው ይለግሣሉ። በዚህ ውድድር ላይ የችሎታ ብቃት የሚባል የለም። በዚህ ውድድር ወንዶች ባሉበት ጉባኤ የሚወዳደሩት ወንዶች ብቻ ሲሆኑ፣ እራሱን አሳልፎ የሰጠ ወንድ በሌለበት ጉባኤ ግን ሴቶችም እንደወንዶቹ እንዲወዳደሩ ይፈቀድላቸዋል። ሴቶች ወንዶች ባሉበት ለሐላፊነት እንዳይወዳደሩ ድርጅቱ ያልፈቀደው የዚህ ድርጅት መሥራች የሲት ራሴል ባለቤት ኩባንያ ሴት በወንድ

ላይ መሰልጠን ወይም ወንድ እያለ የአመራር ቦታን መያዝ የለባትም በሚል ደንብ እንድትባረርና ብሎም ድርጅትዋን የተቀማችበት ደንብ ስለሆነ፣ ይህን ደንብ ማሕበሩ ለመሰረዝ ስላልፈለገ ብቻ ነው:: ይህንን ዘዴ የፈለሰፈው የድርጅቱ መሥራች ሲት. ራሴል ስለሆነ ያኔ 25ሺህ የአሜሪካን ዶላር እራሱ እንደልብ በፈላጭ ቆራጭነት ለሚያሽከረክረው አዋጥቶ ሌሎችም እንዲያዋጡ ገፋፋቸው:: ይህ የሹመት ውድድር በጉባኤ ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ እየታየ በየጊዜው የሚደረግ ሲሆን ልባምና ታማኝ አገልጋዮች ለሚባሉት ለማህበሩ አሻንጉሊት የቦርድ ዳይሬክተሮች በየዓመቱ እንዲወዳደሩ ተወስኗል:: ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1917 ዓ.ም. የማሕበሩ ፕ ሬዝዳንትና ሌሎችም የማሕበሩ የቦርድ ዳይሬክተሮች ይመረጣሉ ተብሎ ተሰበሰቡ:: በዚህ ስብሰባ ላይ 600 የሚሆኑ ወንድሞች ተገኝተው ተወዳድረዋል:: ከዚህ ውድድር የተገኘው ገንዘብ 1.500.000 ዶላር እንደነበር ከታሪኩ እንዘክራለን:: ይህ እንግዲህ በየአገሮቹ በየአገሩ ጉባኤዎች ሥር ያሉት ለሐላፊነት ቦታ የሚደረገውን ውድድር አይጨምርም::

ከዚህ በላይ ከተገለፀው ታሪካቸው አንፃር ነገሮችን በአንክሮ ስናይ ይህ ድርጅት ሸቀጥን ገዝተው ወይም አምርተው በመሸጥ ከሚነግዱት ታላላቅ ኩባኒያዎች ያላነሠ ገቢ እያገኘ ነገር ግን በበጎ አድራጊ ድርጅት ስም ምንም ቀረጥ የማይከፍል፣ የሠራተኛን ደመወዝ የማይከፍል ድርጅት ነው:: እንደዚህ እያደረጉ ሞላውን አባሎቻቸውን በገንዘብ እያወዳደሩ ቁማሩን ቀምረው በቂ ገንዘብ ካገኙና ከተደራጁ በኋላ የማያሳጣ ሌላ



የቁማር ዘዴን ይፈልስፉና በገንዘብ ምዕመናኖቻቸውን ማወዳደር ተዉ:: ይህን ዓይነቱን ያቋረጡት ከ65 ዓመት በኋላ ነው::

ከሁሉ የሚገርመው እራሳቸውን ሲያመፃድቁ እኛ እንደስመ ክርስቲያኖች ቆሪ ወይም ገቢቴ በጉባኤያችን እያዞርን አናስቸግርም:: እንዲህ ማድረግ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ነው እያሉ ሌሎችን ማውገዛቸው ነው:: ይህንን ካቋረጡ በኋላ ጭንቅላታቸውን በፍልስፍናቸው ለአጠቡት አባሎቻቸው ይህንን የሚታየው ምድራዊ የእግዚአብሔር ድርጅትን ማንኛውም እራሱን አሳልፎ የሰጠ የይሖዋ ምስክር በገንዘብ መርዳት አለበት:: በዓለም ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ስለሚሰበክ፣ ለመስበክ ጊዜ የሚያጥረው ሰው ሁሉ ገንዘቡን እያዋጣ በማሰበክ የምሥራቹ ሥራ ተካፋይ መሆን አለበት፤ ስለሚሉ ሁሉም በዓመት ይህንን ያህል አዋጣለሁ እያሉ ቃል ገብተው ያዋጣሉ:: እንዲሁም ከሞታችሁ ለእግዚአብሔር ድርጅት በሕግ ተናዘዙ ስለሚባል የብዙ ቤተሰቦች ልጆች ተከደው ለምች ታምር ተናዝዘዋል፤ እየተናዘዙም ነው:: እሩቅ ሣንሄድ ስለዚሁ ታሪክ እ.ኤ.አ. ታህሣሥ 1995 ዓ.ም. በአማርኛ የታተመውን የመጠበቂያ ግንብ /የዋች ታዋር ጋዜጣ/ ገጽ 28-31 አንብቡ:: እንዲሁም የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ዓላማ ላይ የ1959 ዓ.ም. እትም መጽሐፍ ምዕራፍ 11 አንብቡ::

ራሴል ይህንን ሁሉ ተንኮል ይፈፅም የነበረው በዘመኑ እጅግ ታዋቂ እና በዋሽንግተን ዲሲ ከ1894 ዓ.ም. እ.ኤ.አ ጀምሮ የአሜሪካን መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩ ጠበቃ ከነበረው ጆሴፍ ፍራንኪሊን ራዘር ፎርድ ከሚባል ግለሰብ ጋር በመመካከርና በመመሳጠር ነበር:: በዚህ ሰውዬ ሕጋዊ ሽፋን

ሰጭነት ራሴል የሚስቱን ማለት የማሪያን ኩባኒያ አጭበርብሮ እ.ኤ.አ. በ1906 ዓ.ም. ሙልጭዋን እንዲያስወጣት ካስደረገ በኋላ ወዲያውኑ ማለት በ1906 ዓ.ም. የዋች ታዎር ማሕበር አባል ሆነ። የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ የ1959 ዓ.ም. እትም ገጽ 45-ፓራግራፍ 3 እና በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 65 ፖራግራፍ 5 እና 6 በጥሞና ተመልከቱ። በዚሁ መልኩ በራዘር ፎርድ አማካሪና ጥብቅና ማሪያ ኩባኒያዋን ከተቀማች ከአንድ ዓመት በኋላ ማለት በ1907 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የዎች ታዎር የመጽሐፍ ቅዱስና የትናንሽ ጽሑፎች ማሕበር የሕግ ተወካይ ወይም አማካሪ ሆኖ አረፈ። ይህም ማለት ሐላፊነት የተሰጠው ከማህበሩ ባለስልጣኖች አንድ ለመሆን ቻለ ማለት ነው።

ስለዚህ ልዩ የማሕበሩ መልእክተኛ ማለት በዚያን ዘመን ፒሊግሪም /Pilgrim representative/ ሆነ። ይህ ግለሰብ ሕጋዊ ሽፋን እየሰጠው በእውቀት ያልገፋው አፈጮሴ ራሴል የሚስቱን ኩባኒያ እንዲቀማት ከረዳ በኋላ የዳኝነት ሥራውን ትቶ የኩባንያ ባለሥልጣን ሆኖ የራሴል የጥቅም ተካፋይ ሆኗል። ራሴል ወዲያውኑ ሲሞት ይህ የሕግ ምሑር የቦርድ ዳይሬክተሮች የተባሉት እያሉ በቀጥታ የማሕበሩ ኘሬዚዳንት ሆነ። ከዚህ በፊት እንደተገለፀው በተቃወሙ ጊዜ አውቆ ሕጋዊ መሠረት እሣጥቷቸው ስለነበር ከኖሩበት ቤቴል ጠራርገው አስወጣቸው። አንወጣም ያሉትንም በፖሊስ ኃይል አባሯቸዋል። የአፋፎ ልጅ ጠላፎ እንዲሉ ይህ ግለሰብ ለድርጅቱ ሕጋዊ ሽፋን እየሰጠ በበለጠና በረቀቀ መልኩ የዓለም መጨረሻ ጥፋት መጣብህ መጣብሽ በሚለው ማስፈራሪያ ኘሮፖጋንዳቸው ቀጠለ። በ1914 ዓ.ም. ዓለም ያልጠፋችበት ምክንያት ማስተባበያ በትጋት



ስለተሰጠና ከአመፀኞች ጋር የተባበሩት 4 ሺህ ምስክሮች ከድርጅቱ ስለተባረሩ ድርጅቱ እንደበፊቱ ከመፍረስ ዳነ።

## ምዕራፍ 5

## የእነ አብርሃም የይስሐቅና ሣራ አሁኑኑ መነሣት ስብከት

ከእነ ዊሊያም ሚለር እስከ ሲቲ ራሴል የሕይወት መጨረሻ ዘመን ድረስ በዋናነት ሕዝብን ያሞኙበት ዘዴአቸው የዓለም መጨረሻ ጥፋት ስለደረሰ እንዳትጠፋ፣ ቶሎ እራስህን አድን የሚል ነበር:: እንደዚህ ባለ ዓመተ ምህረት የዓለም መጨረሻ ይሆናል እያሉ በየ16 ዓመት ተከል ርቀት የዓለም መጨረሻ ጥፋት ያውጁ ነበር:: ይህንኑ ታሪካቸውን / Jehovah's witnesses on the divine purpose/ የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ በተሰኘው የ1959 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በታተመ መጽሐፋቸው ከምዕራፍ 2 ገጽ 12 እስከ 15 የምንመለከተው ነው:: እስኪ እንዴት እንደሆነ በዝርዝር እንመልከት:-

| ትንቢቱ የተነገረበት ዓመት | ትንቢቱ ይፈጸማል የተባለበት ዓመት | ትንቢቱ ከተነገረበት ጊዜ ይፈጸማል እስከተባለበት ጊዜ ያለው ርቀት |
|---|---|---|
| 1. በ1816 ዓ.ም. | 1844 ዓ.ም. | 28 ዓመት |
| 2. በ1844 ዓ.ም. | 1864 ዓ.ም. | 20 ዓመት |
| 3. በ1864 ዓ.ም. | 1874 ዓ.ም. | 10 ዓመት |
| 4. 1874 ዓ.ም. | 1878 ዓ.ም. | 04 ዓመት |
| 5. 1878 ዓ.ም. | 1907 ዓ.ም. | 29 ዓመት |
| 6. 1907 ዓ.ም. | 1914 ዓ.ም. | 07 ዓመት |

ከዚህ በላይ ከተገለፀው አንፃር የጥፋት ዓመት መምጣት የሚያውጁባቸውን ዘመናት ርቀት አቬሬጅ ወይም ማዕከላዊ ግምት ስናይ በየ16 ዓመት ተከል መሆኑን እንመለከታለን:: ይህ ቋጭ በሉ ድርጅት በቅርቡ እነ አብርሃም በጉባኤያችን ከሙታን



መቃብር ወጥተው ስለሚመጡ፣ እነርሱን የምንአሳርፍባቸው ቤት እንድንሠራ ገንዘብ አዋጡ ብሎ ከምዕመናኑ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ሰበሰቡ:: በዚህ በሰበሰቡት ገንዘብ በሣንቲያጎ ካሊፎርኒያ እጅግ ውብ ቤተመንግሥት የመሰለ ቤት አሠርተው ውብ የሆኑ ውድ መኪኖችን ገዝተው መጠባበቅ ጀመሩ:: ልዑላኑ እስኪነሱ የማርያን ኩባኒያ ያስቀማው ኘሬዝዳንታቸው ራዘር ፎርድ ይኖርባትና፣ መኪኖችን እያቀያየረ ይጠቀምባቸው እንደነበር በዊሊያም ጄ ሽኒል ተጽፎ በ1969 ዓ.ም. በአማርኛ የተተረጐመው መጽሔት ገጽ 9 እዩ :: እነአብርሃም ስለመነሣት ስብከታቸው የይሖዋ ምስክሮች በመለኮታዊ ሥራ ላይ እትም 1959 መጽሐፍ ገጽ 252 ተመልከቱ:: በመጨረሻም እነ አብርሃም ስለአልተነሱ ምዕመናንንም ለማዘናጋት ቤቱንና መኪናውን ሸጠው ባለ 9 ፎቅ ሕንፃ ኒዮርክ ውስጥ ገንብተው ሙስና ፈፅመዋል::

እነዚህ የራሴል ተከታዮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይጠቅሱና በዚያ በጠቀሱት ጥቅስ ሐሳብ ዙሪያ ሌላ የፍልስፍና የሐሳብ ትርጉም ይፈጥራሉ:: በዚህ በቅርቡ በእኛ ጉባኤ ብቻ የጥንት ታማኝ ሰዎች ከመቃብር ተነስተው ይታያሉ የሚለውን ፍልስፍና መነሻ ጥቅሳቸው በመዝሙር ምዕራፍ 16 ቁጥር 45 ላይ የተጻፈው ጥቅስ ነው፤ እንዲህ ይነበባል:-

«በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ይተወለዱልሽ፣ በምድርም ሁሉ ላይ ገዥዎች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ» የጥቅሱ መጨረሻ:: ይህ ጥቅስ አባቶች ቀርቶባቸው ልጆች ይሾማሉ ይለናል:: አባቶች የተባሉት እነማን ናቸው? ከሚለዋወጠው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት አንፃር እነዚህ አባቶች የተባሉት እነማን እንደሆኑ፣

ልጆች የተባሉት ደግሞ እነማን እንደሆኑ ቀጥለን ተራ በተራ እንመልከት:-

እንደ አንድ ወቅት መጀመሪያ ስብከታቸው ከሆነ አባቶች የተባሉት የአምላክን ትእዛዝ የጣሱ እንደ አዳም ያሉት የጥንት ሰዎች ናቸው:: በሌላ በኩል ደግሞ ልጆች የተባሉት ምንም እንኳን ከአጥፊ አባቶች ቢወለዱ የአባቶቻቸውን የጥፋት ጎዳና ሣይከተሉ፣ ፈጣሪውን በማምለክ የጽድቅን መንገድ የመረጡ እንደእነ አብርሃም ያሉት ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ ከታማኝነታቸውና የእግዚአብሔር መንገድ ከመከተል አንፃር ልጆች ቢመረጡ ወይም ቢሾሙ ትክክል ነው የሚል አመለካከት ነበራቸው:: እነዚህንም ልጆች የተባሉትን በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ከቁጥር 4-32 የተዘረዘሩትና ሌሎችም ናቸው ይላሉ::

በ2ኛ ደረጃ ማሕበሩ ለዚህ ጥቅስ ሌላ ተቃራኒ ትርጉም ለመስጠት የሚፈልግበት ወቅት መጣ:: ከዚህ በላይ በቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ በአናት ለማቆም ፈለጉ:: ይህንን አዲስ የጥቅሶች ሐሳብ ቀዶ ጥገና ዘዴአቸውን በግልፅ አጉልቶ ከመግለጣቸው በፊት ተቀባይነት እንዲያገኝ መሠረተ ሐሳቡን በልዩ ዘዴ ማስተማር ጀመሩ:: ይህ መሠረተ ሐሳባቸው እንደዚህ የሚል ነበር::

በራዕይ ምዕራፍ 14 ከቁጥር 3-4 ከተጠቀሱት ቅዱሳኖች ገና በምድር ላይ የምንገኝ ቀሪዎች እኛ ነን ይላሉ:: በአሁኑ ሰዓት በምድር ላይ ያሉት የ144 ሺህ ቀሪ አባሎች ይህን ያህል ነን ብለው በዓመት መጽሐፋቸው ቁጥራቸውን ካወጁ በኋላ በምድር ላይ እንዲቆዩ የተደረጉበትን ምክንያት ዘረዘሩ:: «እኛ በምድር ላይ እስከ አሁን እንድንቆይ የተፈቀደው በምድር ላይ ገዥዎች



ሆነው የሚሾሙትን ልዑላን ተቀብለን ለማስተናገድ ነው» እያሉ በሚገባ አስተማሩ:: እነዚህም ልዑላን በመዝሙር ምዕራፍ 45 ቁ. 16 የተጠቀሱ ናቸው:: የእነዚህ ልዑላን ማንነት ለማወቅ ይሖዋ እራሱ በወሰነው ወቅት በተግባር የምንአየው ይሆናል ከሚል አጠቃላይ መግለጫ አንፃር ብቻ በጽሑፍ አስቀመጡ:: በዚህን ጊዜ እያንዳንዱ ምዕመናን እንደፈለገ ድሮ ከተገለጠለት አንፃር ወይም በሌላ አቅጣጫ የራሱን መላምት ግምት ያሰላስላል:: ድርጅቱ በግልፅ ካላስቀመጠ ግን ጽፎ ለመተርጉም ማንም አይዳዳውም:: ስለዚህ ከድሮ ትርጉም አንፃር በአባቶች ፈንታ የሚሾሙት እነ አብርሃም እና የመሳሰሉት ታማኝ ሰዎች ናቸው:: የ144 ሺህ በምድር ላይ መቆየት ደግሞ ይህንኑ እውነት ለሕዝብ በሐላፊነት እንዲያስተምሩ ነው ብለው ይደመድማሉ:: ይሁን እንጂ ለተወሰኑት ዓመታት የ144 ሺህ በምድር ላይ መቆየት ለልዩ ዓላማ እንደሆነ በደንብ በጉቻቸው እንዲገነዘቡ ካስደረጉ በኋላ እንደገና የተደበቀ ሌላ ልዩ ትርጉማቸውን በመጠኑ በጽሑፍ ብቅ አደረጉ:: ቀጥለን እንመልከት:-

<u>የ144ሺ ቀሪዎች በምድር ላይ መቆየት</u>

ከጊዜ በኋላ የ144ሺ ቀሪ አባላት በምድር ላይ መቆየት ዋና ዓላማን መግለጥ ጀመሩ:: ይኸውም በምድር ላይ ገዥዎች ሆነው የሚሾሙት እንደነአብርሃም ያሉት የጥንት ታማኝ ሰዎች ከመቃብር የሚነሱት አሁኑኑ በቅርብ፣ ከአርማጌዶን በፊት ስለሆነ ነው:: ስለዚህ በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ከቁጥር 4-32 የተዘረዘሩት የጥንት ታማኝ ሰዎችና ሌሎችም ያልተዘረዘሩት ፃድቃኖች በቅርቡ በጉባኤያችን ከአርማጌዶን በፊት ተነስተው ለሕዝቡ ይታያሉ:: እስከ አሁን እየተሰበከ ወይም እየተነገረ

ያለው የ144 ሺህ ቀሪዎች በምድር ላይ መቆየት ምክንያት እነዚህን የጥንት ታማኝ ሰዎችን እንዲቀበሉ የፈጣሪ ፈቃድ ስለሆነ ነው:: በቅርቡ የጥንት ታማኝ ሰዎች ከመቀብር ሲነሱ ከተቀበሉአቸው በኋላ ቅዱሳን ቅቡዓን ቀሪዎቹ ወደ ሰማያዊ አገራቸው ይዛወራሉ ብለው አረፉ:: ይህንን ትምህርት ወይም ስብከት በሚገባ ከዳር እስከ ዳር አደረሱት:: በየቦታው፣ በየአገሩ እና በየጉባኤዎች አፈጮማ/ ለባኪ ካድሬዎቻቸውን እየላኩ የምዕመናኖቻቸውን ጭንቅላት አጠቡ:: ምዕመናኖቻቸው: ከዚህ ድርጅት አመለካከት ውጭ ማሰብ ነገሮችን በሌላ አቅጣጫ መቃኘት የሰይጣን ድርጅት አባልና ከሰይጣን ማዕድ መመገብ ስለሆነ፣ ብርሃን ከጨለማ ጋር አንድነት የለውም ብለው በድርጅቱ ዙሪያ ተሰብስበው ሁለገብ አገልግሎታቸውን በይበልጥ ማበርከት ጀመሩ:: በዚህ መልኩ ምዕመናኖቻቸው በፍጹም ልባቸው ማመናቸውን አረጋገጡ:: ምስክሮቹ በ1959 ዓ.ም. በአሳተሙት በመለኮታዊ ሥራ ላይ በተባለው መጽሐፋቸው በገፅ 252 ፓራግራፍ 1 በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲህ ብለዋል:-

«For many years it had been the view of the Watch Tower that the faithful men of old who served God faithfully before Jesus time would be raised from the Dead in organizing Jehovah's modern - people to share in shouldering the Remnant's responsibility of representing the Lord Jesus Christ in the Capacity of overseers of the flock of God on Earth. »ይላል::

ከዚህ በላይ በእንግሊዝኛና በአማርኛ በተገለፁት ትምህርቶች ምክንያት የተነሣ ምዕመናኖቹ ወደየጉባኤያቸውና



ወደ አንድ ትልልቅ ስብሰባዎች በሚካሄዱበት ጊዜ ሁሉ ምናልባት እነአብርሃም፣ ይስሐቅና የመሳሰሉት ታማኝ የጥንት ሰዎች ከመቃብር ሲነሱ በማየት እንባረክ ይሆናል እያሉ ተስፋ ያደርጉ እንደነበር ታውቋል:: ቀደም ተብሎ በተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 252 ፓራግራፍ 3 ላይ እንደዚህ ብለዋል:-

"Because of the understanding of this text that had prevailed for so long, many of Jehovah's witnesses expected at every convention to greet Abraham, Isaac, Jacob, David and others-welcoming back from the dead." Jehovah's witnesses on the divine purpose 1959 page 252 paragraph 3.

ከላይ በተገለፀው መልኩ ደጋግመው ደጋግመው በየጉባኤያቸው ይኸን ስለሰበኩ፣ በመጨረሻ ላይ ከላይ እስከታች ያሉት ምዕመናኖቻቸው ይኸንን ቅጥፈት የተሞላበት ስብከታቸውን ተቀብለው በሚገባ አመኑ:: በዚህ መልኩ የምዕመናኖቻቸውን መቀበል ካረጋገጡ በኋላ በእምነታቸው እየተጠቀሙ ሙስና ለመፈፀም ተንቀሣቀሱ:: እንዲህ የሚለውንም ስብከታቸውን በየጉባኤያቸው ማሰማት ጀመሩ፤ አሁን በቅርቡ የጥንት ታማኝ ሰዎች ከመቃብር ሲነሱ የመቀበል ሐላፊነትን ታሪክ ጥሎብናል:: ይህንን ሐላፊነታችንን እኛ በሕይወት ያለነው የይሖዋ ምስክሮች በሙሉ መወጣት መቻል አለብን ብለው ያሉትን የስብከታቸውን መግለጫ ቀጥለን እንመልከት:-

አሁን በቅርቡ የጥንት ታማኝ ሰዎች ከመቃብር ሲነሱ የመቀበል ሐላፊነትን ታሪክ ጥሎብናል፤ ይህንን ሐላፊነታችንን

እኛ በሕይወት ያለነው የይሖዋ ምስክሮች በሙሉ መወጣት መቻል አለብን:: ይህም ሐላፊነት እነዚህ የጥንት ታማኝ ሰዎች ሲነሱ የት እናሳርፋቸው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ መሆን አለበት፤ ብለው ስለሰበኩ፣ እነአብርሃም ከመቃብር ሲነሱ የሚያሳርፉባቸውን ቤት እንሠራለን ብለው እጅግ ብዙ ገንዘብ ከምዕመናኖቻቸው ከሰበሰቡ በኋላ ባለ 9 ፎቅ ሕንፃ ሠርተው ሙስና ፈፅመዋል:: ስለዚህ በዚያን ዘመን የነበሩት የይሖዋ ምስክሮች ወደጉባኤያቸው በሚሔዱበት ወቅት ሁሉ ምናልባት ዛሬ እነ አብርሃም ከመቃብር ተነስተው በጉባኤያችን እናገኛቸው ይሆናል የተባለውም ከዚህ የተነሣ ነው::

ከዚህ በላይ በተገለፀው መልኩ ሲሰብኩ ከቆዩ በኋላ በመዝሙር ምዕራፍ 45:16 በአባቶች ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ፣ በምድርም ላይ ገዥዎች አድርገሽ ትሾሚዋለሽ ለሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ሰጥተውት የነበረውን ትርጉም የመለወጥ እቅዳቸውን ይፋ የሚያደርጉበት ወቅት መጣ:: ስለዚህ ይህንን ትርጉም በግልፅ ይፋ ከማድረጋቸው በፊት የራሳቸውን ሕዝብ በሦስት ደረጃ መክፈል አስፈላጊ መስሎ ታያቸው:: ይህ መቼም ሐተታ እያበዙ የልበቢስ በጎቻቸውን ቀልብ ለመግዛት የሚያደርጉት ጥረት ነው:: እስኪ እንዴት ሕዝብን በሦስት እንደከፈሉ ቀጥለን እንመልከት::

<u>የምስክሮቹ ሕዝብን በሦስት መክፈል</u>

1ኛ. የሕዝብ ዓይነት ገና በምድር ላይ ያሉት የ144 ሺህ አባላት ናቸው:: እነዚህም ቅቡዓን ቀሪዎች ይባላሉ::

2ኛው የሕዝብ ዓይነት በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ከቁጥር 4-32 የተዘረዘሩት የጥንት ታማኝ ሰዎች ናቸው:: እነዚህ



ከመቃብር ተነስተው ከዚህ በላይ በቁጥር 1 ላይ ከተጠቀሱት ከ144 ሺ ቅቡዓን ቀሪዎች ሐላፊነትን ይረከባሉ የተባሉ ናቸው:: ይህም ተንሣኤቸው ከአርማጌዶን በፊት ይሆናል የተባለላቸው ናቸው:: እነርሱም ከመቀብር ወጥተው ሲመጡ የሚያሳርፉባቸውን ባለ 9 ፎቅ ሕንፃ ከምዕመናኖቻቸው በተሰበሰበ ገንዘብ ተሠርቶላቸዋል::

3ኛው ሌላ የሕዝብ ቡድን በቁጥር 2 ላይ ከመቃብር ተነስተው ይሾማሉ የተባሉት ባለሥልጣናት የሚገዙአቸው ሕዝቦች ናቸው:: እነዚህ ተራ ወይም ተርታ ተገዥ ሕዝብ ናቸው:: በእንግሊዝኛ /grass root/ ግራሥ ሩት እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው:: ግራስ ሩት ማለት የታችኛው የሣር ሥር እንደማለት ነው:: ከሣር ሥር በላይ የሣሩ ግንድ፣ አበባ፣ ብሎም ፍሬው ይገኛል:: እነካርል ማርክስም የሕዝብ አተላ እያሉ እንደነዚህ ያሉትን ይመድባል:: ምስክሮቹ ደግሞ እንደነዚህ ያሉት ምዕመናኖቻቸውን በ3ኛው መደብ ደረጃ ከመደቡአቸው በኋላ በልዩ ልዩ ስሞች ይጠሩአቸዋል::

ይህን በ3ኛው መደብ ተርታ የተመደበውን ሕዝብ ማሕበሩ ጥንት እሥራኤል ሕዝብ ከግብፅ ሲወጡ እሥራኤል ያልሆኑት ሰዎች አብረዋቸው ወጥተዋል:: በዚህ መልኩ ከእሥራኤል ጋር ከግብፅ የወጣው ሕዝብ በእሥራኤል ሕዝብ ባሮች እየተባሉ ይጠሩ ነበር:: ሥራቸውም እንጨት ማቁረጥ፣ እንጨት መፍለጥ፣ ውሀ መቅዳት፣ ድንኳን መትከልና ድንኳን መንቀል የመሳሰለ የጉልበት ሥራ እንደነበር ታሪኩ ይዘክረናል:: እነራሴልም ይኸንን በመደብ 3 ተርታ የመደቡአቸውን ሕዝብ ባሮች የሚል ስም አውጥተውላቸው ይጠሩአቸው ነበር::

ከዚህ በላይ በቁጥር አንድ የመደቡአቸው የ144 ሺህ ቅቡዓን ቀሪዎችን ማሕበሩ ልባምና ታማኝ መጋቢ የሚል ቅፅል ሰጥቶአቸው ሲያሞካሹአቸው በ3ኛ መደብ ተርታ የተመደቡትን ግን ከባሪያም ሌላ ስም አውጥተውላቸዋል:: ይህ ሌላ ስም በጎች የሚል ነው:: የ3ኛው መደብ ሕዝብ ባሮችና በጎች በሚል ስም ከመጠራታቸውም በተጨማሪ ልበሲሶች እንደሆኑም ጠቁመዋል:: እራሳቸውን ታማኝና ልባም መጋቢ ያሉት አነጋገር ታማኝና ልባም ያልሆኑ ልበቢሶች መኖራቸውን የሚጠቁም ነው::

ከዚህ በላይ ለመግለፅ በተሞከረ መልኩ ሕዝብን ደልድለው ሲያበቃ፣ ሕዝብን በሚገባ አሣመኑ:: ይሁን እንጂ ጊዜ ጊዜን እየወለደ የጥንት ታማኝ ሰዎች ሣይነሱ ብዙ አመታት አለፉ:: ስለዚህ እነ አብርሃም ከመቃብር ከአርማጌዶን በፊት በቅርቡ ስለሚነሱ እነርሱን እናሳርፍባቸው ዘንድ የቤት መሥሪየ እዋጡ ተብለን አላዋጣንምን? ታዲያ የት አሉ የተነሱ? የሚል ጥያቄ ጠያቂዎች በዙ:: በዚህ ድርጅት ከመቶ ዘጠና ዘጠኙ የሕዝብ ቁጥር በጥንት ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ከግብፅ በወጡት ባሮች ወይም ደግሞ በአሁኑ አመዳደብና አስያየማቸው ከልባምና ታማኝ አገልጋይ ቡድን ያልሆኑ ልበቢስ በጎች እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው:: /ይህ ከልባምና ታማኝ ባሪያ የተለየ የበጎች ክፍል ይህንን ስያሜ በግልፅ አዋጅ የተጎናጸፉት በ1935 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. እንደነበር ከታሪካቸው እንዘከራለን:: ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ቁ. 16 ተጠቅሶ ይህ ስም በወጣላቸው ጊዜ ከባሪያ የበግ ጭንቅላት የተሻለ ይመስል እጅጉን ፈነደቁ:: ለማሕበሩም ሁለገብ አገልግሎታቸውን ከምንጊዜም የበለጠ ማበርከት ጀመሩ:: እነአብርሃም እንደተማርነው ለምን ከመቃብር ሣይነሱ እስከዛሬ



ቆዩየሚለውንም ጥያቄ እያዘወተሩ ይጠይቁ የነበሩት ሰዎች ከዚሁ ከበግ ቡድን ስለነበር፣ ይህንን ጥያቄአቸውን በትንሽ ፍልስፍና እንዲያቆሙ ለማድረግ ማሕበሩ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በ1935 ዓ.ም. ጥቅስ ጠቅሶላቸው በጎች የሚል ስም አወጣላቸው:: እውነትም ከበጎች እምብዛም የተሻለ ጭንቅላት ስለሌላቸው በዚህ ስም እጅግ ስለተደሰቱ እነአብርሃም ለምን እስከዛሬ ከመቃብር ሣይነሱ ቀሩ? የሚለው ጥያቄአቸውን ረሱ:: በዚሁ በወጣላቸው ስም እየተደነቁ ጉድ፣ ጉድ፣ ሲሉ ከረሙ:: በኋላም በ1939 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የ2ኛ ዓለም ጦርነት ተጀምሮ ነገሮች ስለተለዋወጡ ለጊዜው ሁሉም በያለበት ቆመ::

<u>የ2ኛው ዓለም ጦርነት መቆም</u>

2ኛ የዓለም ጦርነት ካበቃ በኋላ እንደገና በገሐድ ስብከቱ በተሻለ መልኩ ተጀመረ:: ሥራ ተጀምሮ ትንሽ ጊዜ ከቆየ በኋላ የእነ አብርሃም ከመቃብር እስከዛሬ አለመነሳት ጉዳይ ሁሉንም ግራ አጋባው:: ለምን እነ አብርሃም እስከ ዛሬ ከመቃብር አልተነሱም? የሚለው የጅሎች ጥያቄ ተበራከተ:: ስለዚህ ልባሙ የቅቡዓን ቀሪ ቡድን ለልበቢሶቹ በጎች ማዘናጊያ ዘዴ ፈጠረ:: የአሁኑ ዘዴ የሰዎችን ቦታ መቀያየር ብቻ በቂ እንደሚሆን ማሕበሩ ገመተ:: ለምሳሌ 3+80=83 ሲሆን ይኸንኑ ቁጥር ቦታውን ቀያይረን 80+3 ብናደርገው ያው 83 ይሆናል:: ለበጎቹ ግን ይህ ዓይነቱ አመለካከት ድንቅ ስለመሰላቸው ይዘውት ከተነሱት ጥያቄ ተዘናጉ:: እንዴት እንደሆነ ቀጥለን በዝርዝር እንመልከት:-

<u>የቦታ ቅይይር</u>

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ማሕበሩ ሌሎች በጎች የተባለውን ቡድን በብዙ መልኩ እያናናቀ ይጽፍ ነበር:: እንዲህም

ይላቸው ነበር:: «ከእኛ የተለዩ፣ እንደኛ ያልሆኑ፣ እኛ የምንቀበለውን ዋጋ የማይቀበሉ፣ ከደረጃ ጥራት እንፃርም ብቃት የጎደላቸው» እያለ ያንኳስሳቸው ነበር:: በዚህ መልክ የሚያኳስሱት ሕዝብ ቀደም ተብሎ እንደተነገረ ከምዕመናኖቻቸው 99% የሚሆኙ ሕዝብ ነው:: እንደዚህ ያለውን መጠነ ብዙ ሕዝብ ማንኳሰስ አደገኛ እንደሆነ የማህበሩ ልባም ክፍል ተገነዘበ:: ማሕበሩ ከበግ ክፍል ጭንቅላት ይመነጫል ብሎ ያልገመታቸው ማለት እንደ እነአብርሃም ለምን እስከዛሬ ከመቃብር አልተነሱም? ለእነርሱ ማሣረፊያ ቤት አዋጥተን ገዝተን የለም ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች ተነስቶ በልዩ ልዩ ዘዴ እንዲዘናጉ ተደርገዋል:: ስለዚህ ይህንን ከ99/100 በላይ የሆነውን ሕዝብ እንኳስሶና ንቆ ዝም ማለት አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ማሕበሩ ስለተገነዘበ አስፈላጊውን የቦታ ቅይይር ማድረግ ፈለገ:: ስለዚህ እንደሚከተለው ማሕበሩ መግለጫ አወጣ::

<u>መግለጫ</u>

"In this year, 1950 there are hundreds of thousands of other sheep who are fully dedicated to Jehovah. These have gone further in belief than Abel, Enoch, Noah, Abraham and Sarah, for those ancient people merely looked forward by faith to coming seed, Christ, but these other sheep of to day have actually accepted Jesus as the savior and king. In stead of pointing out in to the indefinite future to ward the kingdom, these sheep now declare the kingdom actually established." Jehovah's witnesses on the divine purpose 1959 book page 252.



ይህች ናት ጨዋታ! ከዚህ በላይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚያወራው ጽሑፍ ከዚህ በፊት ከግብፅ ከእሥራኤሎች ጋር የወጡት የባሮች ደረጃ እየሰጣቸው፣ በኋላም ደግሞ በጎች ሲላቸው፣ እራሳቸውን ግን ልባምና ታማኝ ባሪያ እያሉ በመጥራት በጎቹ ልበቢሶች መሆናቸውን በግልፅ እያመለከተ ሰያንኳስሳቸው የነበረውን የበጎች ክፍል አሁን አለልክ የሚያወድስና ዋጋቸው እጅግ ከፍተኛ እንደሆነም የሚገልፅ ነው:: በመጨረሻም እነዚህ ሲያንኳስሱአቸው የነበሩ ልበቢስ በጎች ከመቀብር ተነስተው የምድር ገዥዎች ይሆናሉ ከተባሉት ከጥንት ታማኝ ሰዎች ከእነአብርሃም፣ ሔኖክ እና ኖህ በእምነት ይበልጣሉ ብሎ አረፈ:: ስለዚሁ በደንብ እየዞሩ የሚሰብኩ የሕዝብ ንግግር አድራጊዎች በየቀበሌ ምዕመናኑን ለማሣመን ተንቀሳቀሱ:: ከድርጅቱ አባላት በቁጥር 99% የሆኑት በጎች እንዲህ ያለውን ክብር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያገኙ የሚይዙት፣ የሚጨብጡትን አጥተው በደስታ ስካር አበዱ:: ስለዚህ ይህ አሳብ ከዳር እስከዳር ተቀባይነት ማግኘቱን በሚገባ አረጋገጠ::

<u>1950 ዓ.ም.</u>

ዓለም ከ2ኛ የዓለም ጦርነት ችግር ወጥታ እንቅስቃሴ በየቦታው ማድረግ ስለተጀመረ ማሕበሩም የዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት ጀመረ:: ቀደም ብለን እንደአየነው የዚያ ዘመን የይሖዋ ምስክሮች በየጉባኤያችን በቅርቡ ከአሰታት አንድ ቀን የጥንት ታማኝ ሰዎች ከመቃብር ተነስተው ይታያሉ ብለው የሚያምኑ ስለነበር፣ በ1950 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በኒዮርክ ያንክ እስቴድየም ከሐምሌ 30 ቀን እስከ ነሐሴ 6 ቀን 1950 ዓ.ም. ስብሰባ ይደረጋል የሚል ማስታወቂያ ወጣ:: የይሖዋ ምስክሮች

እነአብርሃም የሚነሱት በዚህ ትልቁ የዓለም አቀፍ ስብሰባ ላይ መሆን እንደሚችል ገመቱ። ስለዚህ አቅም ያለው ሁሉ ጥሪቱን እያሟጠጠ ወደ ኒዮርክ ለስብሰባ ጐረፈ።

ማሕበሩ ግን ሌሎች በጎች በእምነትና በእወቀት፣ በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ቁጥር ከ4-32 ከተዘረዘሩት ከጥንት ታማኝ አገልጋዮች ይበልጣሉ እያለ ከመሰበክ ውጭ ምንም በተጨማሪ ያለው ነገር አልነበረም። እነ አብርሃም በቅርቡ ከመቃብር ይነሳሉ የሚለው አቋማቸውንም አልለወጡም። ታዲያ መቼ ነው የሚነሱት? የሚያርፉበትን ቤት አዘጋጅተንላቸው እስከዛሬ እንዴት አልተነሱም? የሚለውም የበጎች ጥያቄ ገና አልተመለሰም። ስለዚህ ማሕበሩ እነዚህን ቅሬታዎችን በመፍታት ጥያቄዎችን በሚገባ ለሁልጊዜ ለመመለስ በዝምታ ዝግጅቱን አጧጧፈ። ነገር ግን ሌሎች በጎች ከጥንት ታማኝ የይሖዋ አገልጋዮች በእምነትና በእውቀት ይበልጣሉ የሚለውን አዲስ ስብከቱን አላቋረጠም። በይበልጥ በፍልስፍና እያነፀ ሌሎች በጎችን ማሞካሸትን ተያያዘው።

ማንኛውም ጥያቄ በሚነሳበት ወቅት የድርጅቱ ካድሬዎችና የበላይ አካላት እስከ ዛሬ ለዚህ ጥያቄ ማሕበሩ በጽሑፍ ያስቀመጠው መልስ የለም። ይህንኑ ጥያቄ ይሖዋ በጊዜው በድርጅቱ አማካኝነት እንደሚመልስ ግን እርግጠኞች ነን። ትዕግሥት ይኑረን። ይሖዋ አምላክ በቅርቡ በኒዮርክ ያንኪ እስቴዲዮም ከሐምሌ 30 እስከ ነሐሴ 6 ቀን 1950 ዓ.ም. በሚደረገው የዓለም አቀፍ የይሖዋ ምስክሮች ስብሰባ ላይ እውቀቶች እንደሚገለጡ እናምናለን። ስለእነ አብርሃም እስከዛሬ ከመቃብር ከአርማጌዶን በፊት አለመነሳትም ሆነ ሌሎችም ልዩ



ልዩ ያልተረዳነው ነገሮች የሚገለፁ ይሆናሉ። ምናልባትም በዚህ ትልቅ ስብሰባ ላይ ምንም የማይሣነው ይሖዋ አምላክ እነ አብርሃምን አስነስቶ እናይ ይሆናል በማለት የማሕበሩ ሐላፊዎች መልስ ይሰጡ ነበር።

እንደዚህ ያለ ድፍን ያለ መልስ አሰጣጥ የልበቢስ በጎቻቸውን ልብ እነአብርሃም በዚህ ስብሰባ ላይ ከመቃብር ተነስተው በማየት እንባረክ ይሆናል ከሚል አንፃር በማስደሰት እምነታቸውን በይበልጥ አጠናከረ እንጂ አላላባቸውም። በዚህ አይነቱ ተስፋ ተሞልተው እ.ኤ.አ ከሐምሌ 30 እስከ ነሐሴ 6 ቀን 1950 ዓ.ም. ድረስ በኒዮርክ ያንክ እስቴዲዮም ስብሰባ ላይለመገኘት ከዓለም ሁሉ ምስክሮቹ ወደ አሜሪካን ጐረፉ /ከኢትዮጵያም ፖል. ሪየስ ኢንጅኔሪንግ ይሠራ የነበረ ኢግልሰን የሚባል ካናዳዊ ወንድም በዚህ ስብሰባ ላይ ለመገኘት ወደኒዮርክ ሔዷል፤ የሚል ነገር አለ። ነገር ግን በ1950 ዓ.ም. ሣይሆን በ1953 ዓ.ም. ነው የሚሉም የጥንት አባሎች ይናገራሉ።

በ1950 ዓ.ም. ሁሉም ሕዝብ ከዓለም በያንኪ እስታድዮም ተሰበሰበ። ስብሰባውንም የከፈተው /Brother Franc/ ወንድም ፍራንስ የሚባል፣ የማሕበሩ ምክትል ኘሬዝዳንት ነበር። ፍራንስ በመክፈቻ ንግግሩ ቀጥሎ ያለውን ሐረግ በገለፀ ጊዜ እስቴዲየሙ ታወከ። ምን ስለአለ? ቀጥለን እንመልከት:-

«ዛሬ ማታ እዚህ ከዓለሙ አቀፍ የተሰበሰባችሁ ሁሉ የአዲሲቱ ምድር ልዑላን በመካከላችን ይገኛሉ ብዬ ብላችሁ ደስ አይላችሁምን?» የሚል ነበር። ይህ አረፍተ ነገር ስለተነገረ ብቻ ከዳር እስከዳር ጩኸት፣ እልልታ፣ ጫጫታ ሆነ። ጭብጨባው ከዳር እስከዳር አስተጋባ። በዚህን ጊዜ ተናጋሪው ለብዙ

ደቂቃዎች ዝም ብሎ መቆም ግድ ሆነበት:: የደስታ ሲቃ፣ የደስታ ፉጨት፣ የእልልታ ድምፅ ለረጅም ጊዜ ከቆየ በኋላ ድንገት በድንገት ዝም አለ:: እርጭ ተባለ:: ለምን ቢባል ቀጥለው የሚለውን የተናጋሪውን የምስራች ውጤት ለመስማት ነበር:: የሚተነፍሱት የትንፋሽ ድምፅ እንኳን ጠፋ:: ለምን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ለአያሌ ዘመናት ሲሰበክላቸው የኖረ የእነ አብርሃም ከመቀብር መነሣት እውን የሆነ ስለመሰላቸው ነበር:: ምክንያቱም ተናጋሪው የአዲሲቱ ምድር ተስፈኞች ልዑላን በመካከላችሁ ይገኛሉ ብል ደስ አይላችሁምን? ስለአለ ነው:: እነ አብርሃም ከመቀብር ተነስተው ከአርሜጌዶን በፊተ በዚህች ምድር ልዑላን ሆነው ይሾማሉ የሚል ስብከት ስለነበር፣ ይህ ይሰበክላቸው የነበረ የስብከቱ ትንቢት በዚህ ታላቅ ስብሰባ ላይ ተፈፀመ ብለው አምነው ነበር:: ማንም ሣያዛቸው በፍጹም ፀጥ ያሉት እነዚህ በመካከላቸው ተገኝተዋል የተባሉትን የምድር ልዑላንን ወይም ገዥዎችን አንድ በአንድ እየጠራቸው ከተሰብሣቢዎች ጋር ያስተዋውቃል በሚል ተስፋ ቀጥሎ ያለውን ነገር ለማወቅ ስለፈለጉ በፍጹም ፀጥ አሉ:: ታዲያ እውነት እነአብርሃም ተነሱ? የቦታ ለውጥ ተደረገ እንጂ እነ አብርሃም አልተነሱም:: እንዴት? እንዲህ ነው:-

<u>መዝሙር 45:16</u>

ፍጹም ፀጥታ በሆነ ጊዜ ተናጋሪው መዝሙር 45 በቁጥር 16 ላይ የተጻፈውን ጥቅስ አነበበ:: ጥቅሱ «በአባቶች ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ በምድርም ሁሉ ላይ ገዥዎች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ::» ይላል:: ከዚህ በፊት ማሕበሩ አዳምና የአዳምን ፈለግ የተከተሉት አባቶች ሲባሉ፣ ከእነዚህ አባቶች



የተወለዱት እንደአብርሃም ያሉት ልጆቻቸው የፅድቅን ሥራ ስለተከተሉ በአባቶች ፈንታ ገዥዎች ይሆናሉ የሚል ትርጉም ይሰጥ ነበር:: ማሕበሩ እነአብርሃም በቅርቡ ተነስተው ከአርማጌዶን በፊት የምድር ገዥዎች ይሆናሉ ያለውም ስብከት ይኸው ነበር::

እኛ የቅቡዓን ቀሪዎች አባላት ደግሞ እንእብርሃም ከመቃብር ሲነሱ ተቀብለናቸው ካለማመድናቸው በኋላ ወደ ሰማይ እንወጣለን እየተባለ በፅናት ተሰብኮ ነበር:: እንዳሉትና እንደሰበኩት እነአብርሃም ከመቃብር ቶሎ ተነስተው ገዥዎች ስለአልሆኑ ለምን የሚል ጥያቄ እንደተነሣም አይተናል:: ስለዚህ እነአብርሃም ያልተነሱበትን ምክንያት ለማስረዳት የዚህን ጥቅስ ትርጉም መለወጥ የግድ አስፈላጊ ሆነ:: ስለሆነም የሚቀጥለውን ትርጉም ለዚህ ጥቅስ ሰጡ::

<u>ትርጉሙ</u>

ትርጉሙ አባቶች የተባሉት አዳምና የአዳም ፈለግ ተከታዮች የነበሩ ሣይሆኑ በዕብራውያን 11 ከቁ. 4-32 የተዘረዘሩት ታማኝ ሰዎች ናቸው:: የእነዚህ ታማኝ ሰዎች ልጆች የተመሰሉት ደግሞ አሁን በመካከላችን የሚገኙ ሌሎች በጎች ናቸው:: እውነተኛው ትርጉም ይህ ስለሆነ ለእነአብርሃም ከአርማጌዶን በፊት መነሣት አስፈላጊ አልነበረም:: በዚህ ምክንያት አልተነሱም:: ይልቁ በመካከላችሁ በሕይወት ያሉ እነዚህ ሌሎች በጎች ናቸው የምድር ላይ ልዑላን ሆነው የሚሾሙት:: ከአርማጌዶን በኋላም እነአብርሃም ከመቃብር ሲነሱ እነዚህ በምድር ላይ ልዑላን ሆነው የሚሾሙት ሌሎች በጎች ይቀበሉአቸዋል ብለው አረፉ:: እኛም የግድ በምድር ላይ መቆየት

ማያስፈልግ እያንዳንዱ የቅቡዓን ቅዱሳን ቀሪዎች አባል ሲሞት ከመቅፀበት በትንሣኤ ወደ ሰማይ የሚሰወጥ ይሆናል ብሰው ደመደሙ:: ይህንን ሲሰሙ ልበቢሉ የበግ ክፍል እጅጉን ፈነደቀ:: ከ99% ልበቢሶች በጎች የሚባሉት ስለሆኑ ይህ እንዴት ይሆናል? ልክ አይደለም የሚሉት ሰዎች ቢከሰቱም ምንም ማድረግ አልቻሉም:: ስለሆነም እንደበፊቱ በድርጅቱ ላይ የሕዝብ መበተን ኪሣራ ሣይደርስበት ቀረ:: በዚህ ስብሰባ መጨረሻ ላይ ለራሳቸው ልዩ ወይም አዲስ ስም አውጥተው ተበተኑ::

<u>ለራሳቸው ያወጡት ስም</u>

1. የሰማያዊ ጥሪ ያላቸው ቅቡዓን ቅዱሳን ቀሪዎች አዲስ ሰማይ ተብለው ተሰየሙ:: የሰማያዊ ጥሪ ያላቸው ማለት በምድር ላይ የማይኖሩ፣ ኑሮአቸው በሰማይ ከጌታ ኢየሱስ ጋር የሆነ ማለት ነው:: ምንም እንኳን በምድር ላይ በሥጋ ቢኖሩም አገራቸው ሰማይ ስለሆነ አዲስ ሰማይ ተብለው ተሰይመዋል::

2. ለምድራዊ ልውላን ማለት ልበቢስ በጎች እየተባሉ ይሰደቡ የነበሩት ደግሞ አዲስ ምድር ተብለው ተሰየሙ:: ይህ በተናጥል ለእያንዳንዱ ቡድን የተሰጠ አሰያየም ሲሆን ሁለቱም በአንድነት በአንድ ድርጅት እየተመሩ ስለሚሠሩና ማህበራቸው አንድ ስለሆነ ለማህበራቸውም አዲስ ስም አወጡ::

እስከአሁን ማህበራቸው ይጠራበት የነበረው ስም የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትናንሽ ጽሑፎች የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚባል ነው:: እንዲሁም የመጽሐፍ ቅድስ የዓለም አቀፍ ተማሪዎች የሚልም ስም አላቸው:: እነዚህ ሁሉ ስሞች ቢኖራቸውም ሦስተኛ ስም ለራሳቸው አወጡ:: ይህ 3ኛ ስማቸው የአዲስቱ ዓለም ማህበር የሚል ነው:: በተለይም ስደት



ባለባቸው አገር እንደዚህ አድርገው ስም መለዋወጡ ይጠቅማቸዋል:: እኔ የአዲስቱ ዓለም ማሕበር አባል ነኝ ማለት ተዘወተረ:: ከበፊቱ የበለጠ እንደላስቲክ እየተሳበ የማይደረስበትን የሕልም ሩጫቸውን ቀጠሉ:: በመጨረሻ ላይም ስለዚሁ የሚያብራራ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር የሚል ሰማያዊ መጽሐፍ አውጥተው ለአባሎቻቸው እንደ ጉድ ሸጠው ተበተኑ::

## ምዕራፍ 6

## <u>ትንሣኤ በድብቅ አይሆንም</u>

እንደ ክርስቲያን እምነት የትንሣኤ ሐላፊው እራሱ ክርስቶስ ነው። ትንሣኤ የሚሆነው ሥርዓት ባለው መልኩ በገሐድ በተወሰነና በተቀጠረው ቀን በታላቅ ሥነሥርዓት የሚከናወን ነው። በተወሰኑት ሰዎች ጓዳ ወይም በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በተሰበሰቡት ጥቂት ሰዎች አካባቢም የሚፈጸም አይደለም። በመሠረቱ ትንሣኤ የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለ2ኛ ጊዜ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜና ከመጣም በኋላ ነው። ትንሣኤ የሚሆነው ሙታንን ለማስነሳትና በሕያውያንም ላይ ለመፍረድ ነው። ጌታ ኢየሱስ የሚመጣው በተወሰኑት ቡድኖች ጓዳ በመገኘት ነው? በተወሰኑ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ብቻ የሚፈጸም ጉዳይ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ምን ይላል? እስኪ በማቴዎስ 24 ስለጌታ አመጣጥ የሚናገረውን እናንብብ:- «በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፣ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፣ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል።» ማቴዎስ 24 ከቁጥር 30

እራሱ ኢየሱስ አወናባጆች እየተነሱ እነሆ ኢየሱስ ተመልሰዋል፣ በእንእገሌ ቤተክርስቲያን ይገኛል፣ እነሆ በቆላ ነው፣ ወይም በደጋ ነው ቢሉአችሁ አትመኑአቸው በማለት አስጠንቅቋል። «በበረሃ ነው ቢሉአችሁ አትውጡ፣ እነሆ በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ አትመኑ፣ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል።» ሲል በማቴዎስ 24 ቁጥር 26-28 አስጠንቅቋል።



ትንሣኤ በተወሰነ ጉባኤ ነው፣ ወይም በተወሰነ ልዩ ቦታ ነው ቢሉአችሁ አትመኑ ተብሏል። ትንሣኤ የሚሆነው፣ ጌታ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ነው። ጌታ ደግሞ በታላቅ ግርማ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታየው ዓይነት ሆኖ በገሐድ ነው፣ የሚመጣው። እንዲሁም ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታ እራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት፣ ከሰማይ ይወርዳል። በክርስቶስ የሞቱትም አስቀድመው ይነሣሉ፣ እያለ በ1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 4 ቁጥር 16 ላይ አብራርቷል። ስለዚህ የትንሣኤ ጊዜ ሲደርስ ጌታ ሙታንን በሚያስነሳበት ጊዜ በከፍተኛ እወጃና ገሃድ እንጂ ምስክሮቹ የተጣመመ ትርጉም እየሰጡ በጉቻቸውን እንደሚያጃጅሉት ዓይነት አይደለም። ታዲያ በምን ተአምር ነው በይሖዋ ምስክሮች ስብሰባ ላይ ብቻ ከዓለም እይታ ተሰውረው የጥንት ታማኝ ሰዎች የሚነሱ? ለመሆኑ ትንሣኤ በሚደረግበት ጊዜ እነአብርሃም ብቻ ናቸው ተደብቀው የሚነሱ? ቢያንስ የአነሳሳቸውንስ ቅደም ተከተል ለምን አላብራሩም? ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በማጣመም ፀጉር እየሰነጠቁ ትርጉም መስጠት ይቻላል። ታዲያ ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውጭ ነው። እምነት እምነት ነው፤ ቃል ቃል ነው፤ ጌታ ያስተማረውን ቃል ለሙስና ለንል ማጣመም አይገባም። ትንሣኤ ሙታን ከዓለም እይታ ተሰውሮ በጉባኤያችን ስለሚደረግ እነአብርሃም በቅርቡ ይነሳሉ ብሎ መስበክ ታዲያ ምን ማለት ነው?

## ትንሣኤ ሁልጊዜ የሚደረግ አይደለም

ምርጥ ምርጡን ለሕፃናት እንዲሉ ምርጥ ምርጡን ለብቁአን ቅዱሳን እንደሚሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማራለን:: ለምሳሌ በራዕይ ምዕራፍ 14 ከቁጥር 1-5 ያለውን እንመልከት *«አየሁም እነሆም በጉ በፅዮን ተራራ ቆሞ ነበር፣ ከእነርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም፣ የመንፈስ ቅዱስም ስም በግንባራቸው የተጻፈላቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ:: እንደ ብዙ ውሀ እንደታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፣ ደርዳሪዎችም በገና የሚደረድሩ ያለ ድምፅ ሰማሁ:: በዙፋኑም ፊት፣ በአራቱም እንስሶችና በሊቃውንቱ ፊት አዲስ ምስጋና አመሰገኑ:: ከምድርም ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራት ሺህ በቀር ያን ቅኔ ሊማር ለማንም አልተቻለውም:: ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው ድንግሎች ናቸውና በጉ ወደሚሔድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው:: ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኵራት እንዲሆኑ ከሰዎች የተዋጁ እነዚህ ናቸው:: በአፋቸውም ውሸት አልተገኘም፣ ነውር የለባቸውም::»* ምስክሮቹ በጎቻቸውን ሲያሞኙ እነዚህ ቅዱሳን፣ ከኘሬዝዳንቱ ጀምሮ እስከተወሰነ ቁጥር፣ ምናልባም ከሺህ የማይበልጡ ሰዎችን እየጠቀሱ እኛው ነን ይላሉ:: እኛን የሚያመለክት ነው እያሉ ይሰብካሉ:: ስለሆነም ወንጌልን ለመስበክ ከክርስቶስ የተሾምን ስለሆን እኛን የተቀበለ ክርስቶስን ተቀበለ ማለት ነው ይላሉ:: ይህ መቼም ትልቅ ቅጥፈት እና ድፍረትም ነው:: እነዚህ 144 ሺህ የሚመረጡት በእግዚአብሔር ነው:: የሚመረጡበትንም መስኪያና መመዘኛን ዮሐንስ በጽሑፍ አስቀምጧል:: ይህንን መመዘኛን እገሌ አሟልቷል ብሎ የሚመርጠው እራሱ ፈጣሪ በመንፈሱ ነው::



መጽሐፍ እራሱ በአፋቸው ውሸት አልተገኘም በጉ ወደሚሔድበት የሚሔዱ ድንግሎች ናቸው ይላል:: ደግሞ እንደነዚህ ያሉት ቅዱሳን የሚመረጡት ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ሕዝብ ብቻ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል አስቀምጧል:: ታዲያ በምን ተአምር ነው ለሚስታቸው እንኳን የማይታመኑ እንደ እነራሴልና ተከታዮቹ ያሉት ያንኪዎች የሚመረጡት? ሐዋርያው ጳውሎስ እንደነዚህ ያሉትን ሲያመላክት «ሥልጣን፣ መዳን ወይም ፅድቅ ለመረጠ ወይም ለሮጠ አይደለም ከሚምረው ከእግዚአብሔር ነው እንጂ እያለ ይዘልፋቸዋል:: ሮሜ መጽሐፍ ምዕራፍ 9 ቁጥር 15-16፤ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከእሥራኤል ሕዝብ ተወልዶ ለሰው ዘር ሁሉ ቤዛ ሆኖ፣ ተሰቃይቶ እና ሞቶ ለዓለም ቤዛ ስለሆነ ከስም ሁሉ በላይ ስም፣ ከክብርም ሁሉ በላይ ክብር ተጐናፅፎ፣ የነገሥታት ንጉሥም ሆኖ፣ በአባቱ ቀኝ በሰማይ ተቀምጧል:: ይሁን እንጂ መከራንና ችግርን ቃልም ሥጋ ሆኖ አብሮ ከተጋራቸው ከእሥራኤል ወገን ቅዱሳኖችን ለናሙና አብሮ ወደሰማይ ሊወስዳቸው ፈልጓል ማለት ነው:: እነዚህም በቁጥር 144 ሺህ ናቸው:: ከእሥራኤል ወገን ስለመመረጣቸወ ጉዳይ መጽሐፍ በግልጽ እንደዚህ ሲል ያስረዳል «የታተሙትን ቁጥር ሰማሁ ከእሥራኤል ልጆች ነገድ ሁሉ የታተሙት መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ:: ከይሁዳ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከሮቤል አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከጋድ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከአሴር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከንፍታሌም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከምናሴ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከስምኦን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ

የታተሙ፣ ከሌዊ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከሳይኮር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከዛብሎን አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከዮሴፍ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ ከቢንያም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ የታተሙ::» ዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 4-8 ተመልከቱ:: ይህንን ግልፁን ነገር ነው። ልዩ ትርጉም በመስጠት በጉቻቸውን የሚያጃጅሉት:: ዮሐንስ ታትመው ያበቃላቸው መሆኑን እንጂ ገና የሚታተሙ ናቸው አላለም::

ከዚህ በላይ እንዳየነው እግዚአብሔር በሚያውቀው የሰው ልጆች ግን ሊያውቁት በማይችሉት ጥበባዊ አሠራሩ ከሁሉ ሕዝብ አስቀድሞ የሰማያዊ ዙፋኑ ተባባሪዎች የሚያደርጋቸው እነዚህ ከ12ቱ ነገደ እሥራኤል የተመረጡት 144 ሺዎች ብቻ ናቸው:: እነዚህ የዓለም ሕዝብ የሚባረክባቸው የተመረጡ የአብርሃም ዘሮች ናቸው፡፡እንዴት እና መቼስ ለዚህ ደረጃ እንደሚያበቃቸው ማንም የሚያውቅ የለም:: የይሖዋ ምስክሮች ግን እኛ እነዚህ 144 ሺዎች ነን:: ጌታ እነዚህ 144 ሺዎችንም መቼ ስልጣን ላይ እንደሚያወጣቸው አውቀናል:: አስቀድሞ የሞቱ አባሎቻችን ከመቃብር ተነስተው በ1914 ዓ.ም. ከክርስቶስ ጋር ነግሠዋል:: በ1914 ዓ.ም. የመጀመሪያ ትንሣኤ ሆኗል ብሎ በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ በሚል ርዕስ በ1982 ዓ.ም. ባሳተሙት መጽሐፋቸው በገጽ 173 ላይ ጽፈዋል:: ነገር ግን ትንሣኤ በ1914 ዓ.ም. ስመሆኑ የእነርሱ የፍልስፍና ቅዥት ካልሆነ በስተቀር ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አይገኝም:: እዋሊዳቸው ነው::



የእናንተስ በምድር ላይ ቀሪ የሆናችሁ የ144 ሺ. አባላት መቼ ነው ታዲያ ትንሣኤ የምታገኙ? ለሚለው ጥያቄ ከ1914 ዓ.ም. ጀምሮ የሚሞቱ የእኛ አባላት እንደሞቱ ወዲያውኑ ትንሣኤ አግኝተው ከጌታ ጋር ይሆናሉ ይላሉ:: የዘወትር ትንሣኤን እየሰበኩ ነው:: በ1914 ዓ.ም. እና እንዲሁም በ1925 ዓ.ም. አንድ ሙሽራ ሙሽራይቱን እንደሚወስድ መጥቶ ይወስደናል እያሉ ሲሰብኩ ከርመው ከከሠሩ በኋላ አሁን ደግሞ ስለ የዘወትር ትንሣኤና በ1914 ዓ.ም. ትንሣኤ ተደርጓል እያሉ ሕዝብን ይሰብካሉ:: እንደዚህ እያሉ ህዝብን የሚያታልሉ ሰዎች እንደሚከሰቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት እንደዚህ ይላል:: «እነዚህ ትንሣኤ ከአሁን በፊት ሆኖአል እያሉ ስለእውነት ስተው የአንዳንዶችን እምነት ይገለብጣሉ::» 2ኛ ጢሞቲዎስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 18:: እንግዲህ እነዚህ የዘመናችን ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ናቸው:: እነአብርሃምን ከመቃብር ሲነሱ ከተቀበልን በኋላ ሁሉን አሳይተናቸው ሲያበቃ ወደሰማይ እንነጠቃለን እንደአላሉ ሁሉ፣ አሁን ደግሞ እያንዳንዱ የ144.000 ቀሪ አባል ከዚህ ዓለም በሞት በተሰናበተ ቁጥር ወዲያውኑ ትንሣኤ ያገኝና በ1914 ዓ.ም. በጅምላ ከተነሱት ብዙሐን ጋር ይቀላቀላል እያሉ በመስበክ ላይ ናቸው::

## <u>እንዲሁም የክርስቶስን ዳግም መምጣትን ከደዋል</u>

ክርስቶስ ዳግም መጥቶ በ1874፣ በ1878፣ በ1907፣ በ1914 ዓ.ም. እንዲሁም በ1925 ዓ.ም. ይወስደናል እያሉ ሲሰብኩ ከከረሙ በኋላ እንደዚህ ያለውን የውሸት ትምህርት ዘዴ ይዞ መንቀሳቀስ ጥቅም የማያስገኝላቸው ስለመሰላቸው የክርስቶስን ዳግም በሥጋ መምጣትን ከደዋል:: ሌላ ስለክርስቶስ አመጣጥ

ዘዴን ፈልስፈዋል:: መምጣት ከማለት ይልቅ መገኘት የሚለው የሚያምታታ ቃላቸው በዚህ መልኩ የሠራላቸው ይመስላል:: ክርስቶስ መጥቷል፣ መምጣቱን ግን አንተ አታይም፣ ስለዚህ መጥቷል ብለህ ብቻ እመን እያሉ መጽሐፍ ቅዱስ ሲመጣ በግልፅ እየታየ ይመጣል የሚለውን ይክዳሉ:: በግልፅ ይመጣል እያሉ ለሙስና ዓላማቸው ብዙ ጊዜ ስለተጠቀሙበት ታክቲኩ አርጅቶባቸዋል:: እርሱ መጥቷል ለአንተ ግን አይታይም እያሉ መስበኩ ውጤት ያስገኘላቸው ይመስላል::

## መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል

ዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 1 ቁጥር 7 እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል:: ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፤ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለእርሱ ዋይ፣ ዋይ ይላሉ፤ አዎን አሜን ይለናል::

እራሱ ክርስቶስ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ ብሏል:: ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ቁ. 3:: ጌታ ወደዚች ምድር መጥቶ ከሕዝብ ጋር እየኖረ፣ አብሮ እየበላ፣ እየጠጣ ለ33 ዓመት ተኩል ኖሯል:: አሁን ግን የሚመጣው ደካማ ሰው ሆኖ ሳይሆን ከምድር በላይና ከሰማይ በታች የኃይለኞች ኃያል፣ የንጉሦች ንጉሥ ሆኖ በታላቅ ስልጣን ነው:: የሚመጣውም ለፍርድ ነው:: መቼ ነው? ከእርሱ ከእራሱ በስተቀር ማንም አያውቅም:: ግን ትንሣኤ የሚሆነው እርሱ በዚህ መልኩ በታላቅ ግርማ ከመጣ በኋላ ነው:: በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ቁጥር 19 ላይ «ገና ጥቂት ዘመን አለኝ ከዚህ በኋላ ዓለም አያየኝም::» የሚለው አነጋገር ጌታ እየታየ ለፍርድ አይመጣም ማለት አይደለም:: እርግጥ ከቀራጮች እንደ ቀራጭ ከሰካራሞች እራሱ ሠካራም ሳይሆን እና ሳይጠየፋቸው



በማነጋገርና በማስተማር ሁሉን ሕዝብ በማቅረብ አብሮ እየኖረ ለ33 ዓመት ተኩል ባስተማረበት ደረጃ መልኩ ኢየሱስን ዓለም ሁለተኛ አያየውም:: ቃል ሁለተኛ ሥጋ ሆኖ በሥጋውያኖች ሐጢአን መካከል ከአንግዲህ አይኖርም:: ስለዚህ ዓለም አያየኝም ሲል ከላይ በተገለፀው መልኩ በእርግጥ አያየውም:: በሌላው መልኩ ግን እንደሚያዩት እራሱ አስተምሮአል:: እርሱ የሚመጣው በከፍተኛ ስልጣን ነው:: ክርስቶስ በክብር መጥቶ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይታያል የሚለው የማቴዎስ ምዕራፍ 25 ሐሳብ በዚህ መልኩ ቢመጣ ክርስቶስ ተዋረደ፣ ከመላእክት አነሰ አያሰኝም:: ለሰው እየታዩ መልአክት ያስተላልፉ የነበሩት መልእክት ከሰዎች በኃይል አንሶ ነበር ብሎ መናገር እውነትን በሐሰት መለወጥ ነው:: ክርስቶስ ከመቃብር እንደተነሣ፣ ከመላእክት ሁሉ በላይ ኃይል አግኝቶ መነሣቱን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል:: ክርስቶስ ለ40 ቀናት በኃይል ከተነሣ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ የታየው እንዴት ነው? ፍጹም ደካማ ሥጋ ሆኖ ነው? ታዲያ ፍፁም የደካማ ሰው ስጋ ለብሶ ካልሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እየታየ ይመጣል ካለ ለምን አይታመንም? ይህ እየታየ ይመጣል የሚለውን በቅርበት እየቀጠሩ የይሖዋ ምስክሮች ለሙስና ስለተጠቀሙበት እና እነርሱ በወሰኑት ዓመታት ስለአልመጣ አይመጣም ማለት አይደለም:: እንዲሁም እነርሱ ከመጀመሪያውኑ እምነት ሳይኖራቸው ተጠቅመውበት ታክቲኩ ስለአረጀና የማይሠራ ስለሆነ እየታየ አይመጣም እያሉ ማሳመንን መረጡ:: እርግጥ ለፍራንክ ለቀማ ይህ ያዋጣቸዋል::

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ትንሣኤ በሚሆንበት ጊዜ ልዩ የበዓሉ ዋዜማ ይሆናል:: ይህንኑ ከመጽሐፍ እንደምንረዳው

ምልክት በሰማይ ይታያል ይላል። በዚያም እየታየ ጌታ ከአጃቢ መላእክቱ ጋር ይገለጣል። ከዚህ በኋላ ነው ለእርሱ የተመረጡትን ለመሰብሰብ ወይም ከመቃብር ለማስነሳት መላእክቱን ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር የሚልካቸው። በዚህ መልኩ አምነው የሞቱት አስቀድሞ ትንሣኤ ያገኛሉ። እነዚህ ለእርሱ የተመረጡት የተባሉት ምናልባትም በራዕይ ምዕራፍ 14 ከቁጥር 1-5 እንዲሁም በራዕይ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 4-8 አስቀድመን ያነበብነው ቅዱሳን ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ። በተሰሎንቄም ምዕራፍ 4 ከቁጥር 15-16 ሐዋርያው ጳውሎስ በጌታ የሞቱት አስቀድመው ይነሣሉ፣ እኛም ሕያው ሆነን የምንቀረው በኋላ እንቀላቀላቸዋለን ይላል። እኛም ሕያዋን ሆነን የምንቀረው የሚለው ቃል ጌታ በዚህ መልክ በሚመጣበት ወቅት በሕይወት የሚገኙትን ቅዱሳን ሰዎችን ያመለክታል። እውነት ጌታ እየታየ የማይመጣ ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች ይህንን አባባል ግልጽ ማድረግ አቅቶአቸው ነው፣ እየታየ ይመጣል ያሉት? እውነት ቢሆን ኖሮ አሁን ምስክሮቹ እንደሚያስረዱት ዓይነት አድርጐ ለመጻፍ ችሎታ ጐድሎአቸው ነው? ጌታ እንደዚህ አድርጐ ያልሆነውንና የማይሆነው ይሆናል እያለ የሚያጽፍ ከሆነ እያታለለን ነው ማለት ነው? ሕዝብን በማታለል ከ100 ዓመታት በላይ በዚህ መልክ ሲነግዱ የኖሩት የይሖዋ ምስክሮች የዎች ታዎር ማሕበር ነው። እነርሱ ናቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ እያጣመሙ ሕዝብን የሚበዘብዙ እንጂ ቅዱሳን ጸሐፊዎች አይደሉም። ስለዚህ የጌታ ደግሞ መምጫ ገና ወደፊት ነው።



<u>ትንሣኤን ከእኛ ችሎታ አንፃር ብቻ ባንመለከት</u>

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ከሆነ ትንሣኤ የሚከናወነው በገሃድ ነው። ነገር ግን ከመተግበሩ አንፃር ስንመለከት እንዴት ሊሆን ይችላል? እንል ይሆናል። ይህ የሃይማኖት ጉዳይ ነው። በሃይማኖት ትምህርት በቃሉ እንደተባለው ማመን ነው። በሣይንሳዊ የፍልስፍና ዘዴ እንሞክር ብለን የምናረጋግጥ ትምህርት አይደለም። ይህ መለኮታዊ እምነት ነው። ካመነ እንደቃሉ አመነ፣ ካላመነ አላመነም። ፈተናውም ይኸው ነው። ማመን ወይም አለማመን። የሚሰበክልንም ሆነ እራሳችን ከመጽሐፍ ቅዱስ የምናነባቸው ነገሮች የእምነት ትምህርት የሆነው አቅርቦትን ነው እንጂ ዝርዝር ተግባራዊ ይዘት አይደለም። አሁን የትምህርት አቅርቦት እግዚአብሔር ሙታንን ከመቃብር ያስነሳቸዋል የሚል ነው። ተነስቶም ከንጉሡ ከጌታ ኢየሱስ ፊት ይቀርባሉ ነው። ታዲያ እኛ ወደ ቴክኒካዊ ተግባር ውስጥ ገብተን ይህ እንዴት ይሆናል? ምን ቦታ ይበቃና ነው፣ ከጌታ ኢየሱስ ፊት የሚሰበሰቡ? ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሞቱት ኃጢአንም ፃድቃንም ይነሣሉ። መሬትዋም አትበቃም። ምናልባት ትንሣኤ የሚለው ቃል ሌላ ትርጉም እንዳይኖረው እያልን ከራሳችን የችሎታ መጠን ጋር እያስተያየን በጥያቄ ራሳችንን ማመስ የሚኖርብን አይመስለኝም። የታመሰ ነገር ስለማይበቅል በዚህ እንቸገር። እንደዚህማ ካደረግን የራሳችን ብቻ የሆነ የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን።

ሌላ ይቅርና ለእኛ ቀላል የማይሆን በቴክኖሎጂ ለተራቀቁት አህጉር ግን እጅጉን ቀልሎአቸው እንመለከታለን። ድሮ አንድ ወር የሚፈጅ የእግር ጉዞ ዛሬ በአንድ ቀን ማለት

የብርሃን ቀን ይጠናቀቃል:: የብርሃን ቀን ሲባል 24 ሰዓት አሰመፍጀቱን ለመግለፅ ነው:: በባሕርም ሆነ በልዩ ልዩ መጓጓዣ ድሮ ከ3 እስከ 6 ወር የሚፈጀው ጉዞ ዛሬ ግን በአንድ ቀን በረራ ይጠናቀቃል:: በሣተላይት አማካይነት በየአገሮች ያሉት ሰዎች ከአንድ ጠረጴዛ ከአንድ አዳራሽ የሚነገረውን ነገር በዓይን እያዩ፣ በጆሮ እየሰሙ እየተካፈሉ ነው፡፡ በአሉበት አገር ሆኖ ሌሎች ጥያቄውን ሲጠይቁ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ይታያሉ:: በዚህ መልኩ እየተያዩ በአሉበት ሆኖ አንድ ትልቅ የዓለምን ስብሰባ መካፈል ተችሏል:: ዛሬ ከወተት ስልባቦት ጥጆችንና በጎችን ሣይንስ ለመፍጠር የቻለበት ዘመን ነው:: የሰዎችን ያረጀ የአካለ ክፍል ለመተካት መለዋወጫ የአካል ክፍሎች ሣይንስ ለመሥራት ጥረት የሚያደርግበት ወቅት ነው:: ዘመናችን በዓለም አቀፍ ያሉት ምሁሮች እየተያዩ በአንድ ስብሰባ እየተካፈሉ ናቸው ስንል እንዴት ይሆናል የሚለውን ጥያቄ ለቴክኖሎጂ ምሁራን አፈጻጸሙን እየተውን ነው:: ዛሬ በሣተላይት ረዳትነት እንደድሮው መረብ በመጣል ሣይዳከም አሣ የተከማቸበት ቦታን በቀላሉ አውቆ በቀጥታ በመረብ የሚተፈሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ላይ ደርሰናል:: እንደ ጴጥሮስና እንድሪው ጥንታዊያን አሳ አጥማጆች መድከም ቀርቷል:: ከ5ሺህ አመት ጀምሮ በሞት ያለቀ ሕዝብ እንዴት ጌታ ፊት ሊሰበሰቡ ይችላሉ የሚለውን ተመሳሳይ ጥያቄ ለመንፈሳዊ መለኮታዊ ሣይንቲስቶች መተው ይሻላል:: የእኛ ከ400 እስከ 500 ዕድሜ የማይሞላ ቴክኖሎጂያችን እንደዚህ ከሠራ የጌታ ኢየሱስ ቴክኖሎጂ ምንና እንዴትስ እንደሚሠራ መገመት ይቻላል:: ብቻ የዚህን የቴክኒኩን ሁኔታ ለእርሱ መተው ይበጃል:: ለእኛ



የሙታን ትንሣኤ እንደሚሆን ተገልጾልናል:: የአፈጻጸሙ ቴክኒክ የመተግበሩ መላ የእርሱ ፈንታ ነው::

ለምሳሌ በምዕራፍ አንድ በዘፍጥረት መጽሐፍ ከተራ ቁጥር 6-8 የምንመለከተው አንድ የቴክኖሎጂ ጥበብ አለ:: ይህች ምድራችን ከዳር እስከ ዳር በውሀ ተሞልታ ነበር:: ውሀው የሰማዩን ጣራ የሚነካ ስለነበር መሬትዋ ፍጡር አልባ ነበረች:: ይህንን ውሀ ለማስወገድ የታዘዘው የአምላክ መንፈሳዊ መሐንዲስ ከመሬት በላይ ነገር ግን ከሰማይ በታች ሌላ የሰማይ ጠፈር ፈጥሮ ግማሹን የምድር ውሀ ከፀሐይ በታች በፈጠረው ጠፈር ላይ እንዲወጣ አደረገው:: ይህን ከምድር በላይ ነገር ግን ከፀሐይ በታች ያለውን ከላይ እንደተገለፀው ጠፈር ብሎ ሰየመው:: አሁን ግማሽ በግማሽ ውሀው ተቃሎአል:: የቀረውንም ውሀ አንድ ጉድጓዳ ሥፍራ አበጅቶ እዚያው ውስጥ እንዲገባ አደረገው:: የውሃውንም ማከማቻ ባሕር አለው:: አሁን ደረቅ ምድር ሲገለጥ ስለቻለ መሐንዲሱ ደረቁን መሬት ምድር ብሎ ሰየመው:: ያን ጊዜ ኖረን ነገሮችን ከእኛ ትንሽዋ ችሎታ ጋር እያነፃፀርን ይህ እንዴት ይሆናል? ፍጹም የማይሆን ነው እያልን ጠባብ ፍልስፍና ብናካሂድ እንሳሳታለን:: ያኔ የምድር ውሀ 2/4 ነበር አሁን ግን 3/4 ነው::አሁን ደረቅ ምድር 1/4 ብቻ ነው:: የምድራችን ውሀ ግማሽ ወደሰማያዊ ጠፈሩ ወጥቶ እንደነበር አንብበናል:: ነገር ግን በትልቁ የዓለሙ መሐንዲስ ፈጣሪና በፍጡሩ መካከል በተፈጠረው ጥል ምክንያት ወደ ሰማይ ወጥቶ የነበረው ውሀ ላልተፈለጉት ፍጡራን ማጥፊያ እንደዋለ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመለከታለን:: ስለዚህ ምኑንም የእውቀት ምንጭ ሣንዳብሰው እንደው በቃላት ስንጠቃ ትችት አንሳሳት

ማለቴ ነው እንጂ አትመራመሩ ማለቴ አይደለም:: አሁንም ፈጣሪ በተመሣሣይ ችሎታ ምንን ቴክኖሎጂ ሊጠቀም እንደሚችል ምን እናውቃለን? መተቸትም የምንችል አይመስለኝም:: የእምነት ጉዳይ ነውና፤ አንድ ሰው የማንኛውም ሃይማኖት አባል ሆኖ ግን እውነት ነው ብሎ በቅንነት የሚፈጽም ነገሮች ካሉ ነገር ግን እርሱ የሚፈጽማቸው ነገሮች ከእኛ አመለካከት ጋር ፍፁም የማይገጥም ቢሆን ከእኛ አመለካከት ግምገማ ተነስተን ግለሰቡንም ሆነ ቡድኑን መኮነኑ ይቸግራል:: ለምን ቢባል በፍጹም ቅንነት አምኖ ስለሚፈጽም ነው:: መኮነን ያለበት እውነት ያልሆነውን ነገር እውነት አለመሆኑን እያወቀ ሌሎችን በስሕተት አሣምኖ ሲያበቃ ከእምነታቸው አንፃር በሚያደርጉት የእንቅስቃሴ ውጤት የግል ተጠቃሚ ሆኖ እራሱን የሚያበለፅግ ከሆነ ነው:: ይህ ሙስና ነው:: መወገዝም ያለበት ይመስለኛል::ነገር ግን ሙሉ በሙሉ እውነት ነው ብሎ አምነው ስሕተትም ቢሆን በእምነታቸው መሠረት የሚፈጽሙት ድርጊት በጥንቃቄ መገምገም ያለበት ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ አብርሃም የሚባል የእሥራኤሎች አባት ልጁን ለማረድ ምንም ያህል አልቀረውም ነበር:: ሰውን መግደል መጥፎ ድርጊት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ትልቅ እምነት እንደአለው የሚገልጽ ነው:: ሆኖም እምነቱ ለነፍስ መጥፋት ምክንያት ሊሆን ተዘጋጅቶ ነበር:: በጥንት ጊዜ አንድ ልጄን ወይም የበኩር ልጄን መስዋት ካላደረኩ ሌሎች አይባረኩልኝም እያሉ ልጆቻቸውን በእሳት የሚሰው እንደነበሩ ታሪክ ይዘክረናል:: እነዚህንና የመሳሰሉ ነገሮችን በሕብረተሰብ መካከል ስንመለከት በደፈናው ከመኮነን ከምን አመለካከት ተነስቶ ነው፣ እንደዚህ መሥራት የቻለው ብለን



መጠየቅ ይገባናል:: ሃይማኖቶች ሁሉ ወደ አንድ ትልቅ ተራራ ላይ ወደሚኖረው አባት ለመድረስ እርሱን እያሰቡ በተለያዩ አቅጣጫ ተራራውን በሚወጡት ሰዎች ይመሰላሉ:: በቅንነት ተራራ ላይ ለመውጣት የሚታገሉትን መኮነኑ ሣይሆን ማተኮር ያለብን ከተቻለ አቋራጩን አባጣ ጉባጣ፣ እሾክና አሜኬላ የማይበዛበትን መንገድ ማሳየት ይበልጣል:: ነገር ግን በዓለም ላይ የሚታየው በአብዛኛው፣ በተለይም እኔ እራሴ በቅርብ የማውቀውና አባላቸው በነበርኩት በይሖዋ ምስክሮች ድርጅት ሰውን መነገጃ ካደረጉት ጥቂት ተንኮለኞች በስተቀር አባላቱ በሙሉ በቅንነት ፈጣሪን እናመልካለን እያሉ የሚለፉ ናቸው:: ይህ እንደ እነ ራሴል በተከታታይ የሉን ስልጣን ተረክበው እውነትን እያወቁ በሐሰት ሰውን የሚያሳስቱ ቁንጮዎችን አይጨምርም::

## ምዕራፍ 7

## የ1975 ዓ.ም. ታሪክ

ማህበሩ የዓለም መጨረሻ በ1925 ዓ.ም. ይሆናል ካለበት ዘመን አንስቶ ለአምሣ ዓመታት ስለዓለም መጨረሻ ጥፋት መምጣት ቀን መወሰንን እርግፍ አድርገው አቆሙ:: ለምን? ለተባለው ጥያቄ የሚከተሉት ምክንያቶች መልስ ሊሆኑ ይችላሉ::

አንዱ ምክንያት ቀን እየቀጠሩ፣ ዓመተምሕረት እየጠቀሱ ለ8 ጊዜያት ያደረጉት ትንቢቶቻቸው በአለመፈፀማቸው ውሸታምነታቸው በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ስለታወቀ፣ ተቀባይነት ስለአጡ ነው የሚል ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ይህንን የማታለያ የውሸት ትንቢታቸውን የዚያ ዘመን ትውልድ በደንብ ስለተገነዘበ መዘባበቻ ሆነው ነበር:: ስለዚህ ያ ትውልድ ከዚህ ዓለም በሞት እስኪለዩ መቆየቱ አስፈላጊ ስለነበርም ነው:: ስለሆነም 50 ዓመታትን በዝምታ ለመቆየት መረጡ:: ከዚህ ከ50 ዓመታት ዝምታ በኋላ አመቺ ሁኔታዎች የተፈጠረላቸው ስለመሰላቸው ያው አመላቸው አገርሽቶባቸው እ.ኤ.አ. በ1975 ዓ.ም. የዚህ ዓለም መጨረሻ ይሆናል ብለው አወጁ:: ታዲያ በእነዚህ 50 ዓመታት ሙሉ የዓለም ጥፋት ወይም የመጣበህና መጣብሽ ስብከት በጆሮአቸው ከአልተንቆረቆረባቸው መቆም የማይችሉ ምዕመናኖቻቸው እንዴት ለመቆየት ቻሉ? አባሎቻቸውን ለማቆየት የቻሉበትን ታክቲክ ቀጥለን እንመልከት:-

አባሎቻቸውን ለ50 ዓመታት በትዕግሥት እንዲጠባበቁ ለማድረግ ከቻሉት ምክንያቶች አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ሁለተኛ ወደዚህች ዓለም አይመጣም፣ እርሱ ከ1914 ዓ.ም.



ጀምሮ በመንግሥተሰማያት ከጠላቶቹ መካከል መንገሥ ጀምሯል:: ይህም በዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 13 መሠረት የተተነበየ ነው:: ስለዚህ እኛ ባላሰብነው ዓመት፣ ቀንና ሰዓት ጠላቶቹን ተነሥቶ ሊያጠፋ ነው:: እነዚህም ጠላቶቹ የዚህ ዓለም መንግሥታትና ሠራዊቶቻቸው፣ ሐሰተኞች የሃይማኖት ድርጅቶች እና በጠቅላላ ከእኛ ውጭ የሆነው ሕዝብ ሁሉ የክርስቶስ ጠላቶች ናቸው:: ስለዚህ ክርስቶስ ጠላቶቹን በቅርቡ በዘመናችን የሚያጠፋቸው ስለሆነ፣ በአርማጌዶን ጦርነት ደግ አመድ ከመሆን ትድኑ ዘንድ የእግዚአብሔርን ምድራዊ ድርጅት የሙጥኝ ብላችሁ ኑሩ፤ እያሉ ስለሰበኩ፣ በራዕይ ምዕራፍ 16 ከቁጥር 14-16 በተገለፀው መሠረት ከዛሬ ነገ አርማጌዶን ይመጣና ይህችን ዓለም ያጠፋታል፣ እኛም ከዓለም ጋር እንዳንጠፋ ዕለት በዕለት በፅድቅ ሥራ መጽመድ አለብን ብለው እየባነኑ እንዲኖሩ ስለአደረጋቸው ነው:: ስለሆነም በ1975 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ዓለም ትጠፋለች ብለው ያቀረቡት ምክንያቶቻቸውን አንድ በአንድ ቀጥለን እንመለከታለን:-

### መረጃ አንድ

1. ከሙሴ መጽሐፍ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 31 የተጠቀሰው ጥቅስ አንዱ ነው:: ይህ ጥቅስ እንደሚከተለው ይነበባል:- «እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ሁሉ አየ፣ እነሆ እጅግ መልካም ነበረ:: ማታም ሆነ፣ ጥዋትም ሆነ ስድስተኛ ቀን::»

2. ሌላ ጥቅስ ይኸንኑ ሐሳብ የሚያጠናክር ከዚሁ ከሙሴ መጽሐፍ ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1-2 የተጻፈው ጥቅስ ነው:: ይህም ጥቅስ እንደሚከተለው ይነበባል:- «ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈፀሙ:: እግዚአብሔርም

የሠራውን በሰባተኛው ቀን ፈፀመ፣ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ አረፈ።»

ከዚህ በላይ በቁጥር 1 እና 2 ሥር የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ1975ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የዓለም መጨረሻ ይሆናል ላሉት ተንቢታቸው ማሕበሩ እንደመረጃ ቁጥር አንድ አድርጐ ያቀረበው አስረጅ ነው:: ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች እግዚአብሔር ለሰው መኖሪያ እንድትሆን ለማይና ምድራችንን በ6 ቀን ፈጥሮ በ7ኛው ቀን ማረፉን ነው የሚገልፁት:: እዚህ ላይ ማየት ያለብን እነዚህ 6 ቀኖች በማን ቀን አቆጣጠር መለኪያ የታሰቡ ናቸው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ስለዚህ እነዚህ ቀኖች በማን የቀን ትርጉም እንደሆነ ቀጥለን እንመልከት:-

በማንኛውም ተርታ ሕዝብ ዘንድ ቀን የሚባለው ከንጋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ እስከምሽቱ 12 ሰዓት ያለው እንደሆነ ይታሰባል:: ሌሊት ደግሞ ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ያሉት የጨለማ ወቅት እንደሆነም ይታመናል:: ይህ አንዱ የቀን አቆጣጠር ቀመር ነው:: ሌላኛው የቀን አቆጣጠር የጂኦግራፊ ጥናት ውጤት የሆነ የቀን አቆጣጠር ነው:: ይህ የጂኦግራፊ ቀን አቆጣጠር እሥራሁለቱን የብርሃን ወቅትና 12 የጨለማን ወቅት የሚያጠቃልል ነው:: መሬታችን በእራስዋ ዛቢያ ላይ አንድ ጊዜ ስትዞር 24 ሰዓቶችን ስለሚፈጅባት ይህ የአንድ ጊዜ መሬት በእራስዋ ዛቢያ ላይ መዞር እንደ አንድ ቀን ተደርጎ እንደተወሰደ እንመለከታለን::

ሌላ 3ኛው የቀን አቆጣጠር የሃይማኖት አባቶች የሚጠቀሙበት የቀን አቆጣጠር ነው:: ከሃይማኖት አባቶች አንዱ



ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ቀን አቆጣጠር ሲያስተምር የሚከተለውን መመሪያ ሰጥቷል:: ይህ መመሪያ በ2ኛ ጴጥሮስ 3 ቁጥር 8 ላይ ይገኛል፤ እንዲህም ይነበባል:- «በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ቀን ሺህ ዓመት ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ።»

እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ይነጋገር እንደነበር ከሚነገርለት አንዱ ሙሴ የተባለው ነቢይ ነው:: መዝሙራዊ ነቢዩ ሙሴ ስለቀን ጉዳይ የተናገረውን በመጥቀስ በመዝሙር ምዕራፍ 89 ቁጥር 4 ላይ «በፊትህ ሺህ ዓመት እንደአለፈች እንደ ትናንት ቀን ናት» ማለቱን መስክረዋል:: እነዚህ የሃይማኖት አባቶች የሚናገሩት ስለየእግዚአብሔር ቀን ነው:: ስለዚህ ሰማይና ምድራችንን ለፍጡራን መኖሪያነት ምቹ ሆና እንድታገለግል እግዚአብሔር ሲፈጥራት 6 ቀኖች ፈጅቶበታል የተባሉት 6 ቀኖች የእግዚአብሔር 6 ቀኖች መሆናቸው ግልጽ ነው:: ይህንን ነገር ከተፈጥሮ ሣይንስ አንፃርም ከተመለከትን ትክክል ይመስላል:: እንዴት? እንዴት እንደሆነ ቀጥለን እንመልከት:-

## የእግዚአብሔር መኖሪያ

እኛ የምንኖረው በመሬት ላይ ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ መኖሪያው በጅምላ አነጋገር ሰማይ ከሚባለው አካባቢ በአንዱ ፕላኔት ወይም ሥፍራ ነው:: እኛ ከምንኖርባት መሬትና እግዚአብሔር ከሚኖርባት ፕላኔት ወይም ቦታ መካከል ከፍተኛ ርቀት አለ ብለን እንገምታለን:: በእነዚህ ሁለቱ ቦታዎች መካከል የሰዓትና የወቅት ልዩነት እንደሚኖር ግልፅ ነው:: በምድራችን ላይ እንኳን በሰዓቶች ልዩነት ምክንያት የአንድ አገር ሕዝብ

መሽቶበት ወደ መኝታ ቤቱ ሲሄድ፣ ሌላኛው አገር ያለው ደግሞ ነግቶለት ከመኝታው ተነስቶ ወደ ሥራ ይሄዳል:: የሃይማኖት አባቶችም ትምህርት እንዲህ ካለው ከተፈጥሮ እውነታ ጋር የሚስማማ ነው:: ስለዚህ የእኛ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ 1/1000ኛው ነው:: የእግዚአብሔር አንድ ቀን በእኛ ዘንድ 1000 ዓመት ነው:: እግዚአብሔር መሬትን የፈጠረው በራሱ የቀን አቆጣጠር ስለሆነ 6ቱ ቀኖች በእኛ አቆጣጠር 6ሺህ አመታት ናቸው:: የይሖዋ ምስክሮች ግን ይህንን ግልፁን ነገር በቀዶ ጥገና ፍልስፍናቸው እንደሚከተለው ቀመሩ:-

## የይሖዋ ምስክሮች አቆጣጠር

እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን በ6 ቀን ፈጠረ የሚለውን ሺረው እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን በ42ሺህ ዓመታት ፈጠረ ብለው ተረጐሙ:: እንደ ምስክሮቹ ስሌት አንድዋ የፍጥረት ቀን 7ሺህ ዓመት መሆኑ ነው:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ግን አንድ የእግዚአብሔር ቀን 1000 ዓመት ነው፣ ይህንን አንድ ነገር አትርሱ ሲል አደራ ጭምር አስተምሮናል:: ምስክሮቹ ግን የሌሉትን 6ሺህ ዓመታት በ1000 የእግዚአብሔር ቀን ላይ ደምረው ወደ 7ሺህ ዓመት በማሳደግ፣ አንድ የፍጥረት ቀን 7ሺህ ዓመት ነው ማለታቸውን እንመለከታለን:: ይህንን የቆርጦ ቀጥል ትምህርታቸውን እ.ኤ.አ. ግንቦት አንድ ቀን 1968 ዓ.ም. ባወጡት የመጠበቂያ ማማ በገጽ 271 እና ኢን ሣይት ኦን ኢስክሪፕቸር በተሰኘው ቮልዩም አንድ ገጽ 545 የፍጥረት ቀን በተባለው ንዑስ ርዕስ ሥር የተፃፈውን አንብቡ:: ለዚህ አባባል ምክንያታቸው እግዚአብሔር እያንዳንዱን የፍጥረት ቀን ሲጨርስ ጥዋትም ሆነ ማታም ሆነ አንድ ቀን ሁለት ቀን እያለ እስከ ስድስት ከቆጠረ



በኋላ 7ኛው የዕረፍቱን ቀን ላይ ሲደርስ ቀንም ሆነ ማታም ሆነ ሰባተኛው ቀን ስለአላለ ነው:: ስለሆነም አንድዋ ቀን 7ሺህ ዓመት ነው የሚል ትርጉሙን የሣተ የውሸት ፍልስፍና ቀመሩ:: ቀጥሎ ከምንመለከተው መረጃ ቁጥር ሁለት አስረጃቸውን ካየን በኋላ ምክንያታቸውን በይበልጥ እንረዳለን::

## መረጃ ሁለት

ይህ ለዓለሙ ጥፋት መምጣት መረጃ ነው ብሎ ማሕበሩ ያቀረበው ሐሳብ የሚከተለው ነው:- ሁለት የእስኮላሪስቶች ቡድን የሰው ዘር የመጀመሪያ ፍጡር የተፈጠረው ወይም የተከሰተው መቼ ነበር? ከሚል አንፃር የመጽሐፍ ቅዱስን ክሮናሎጂን ማጥናት ጀምረው የተለያየ የጥናት ውጤትን አግኝተዋል:: የእነዚህን የሁለቱን ቡድን ሙሑራን የተለያየ ውጤት ቀጥለን እንመልከት:-

1ኛ. አጥኝ ቡድን ጀምስ ኢሪሽ አንጀልካል የተባለው ድርጅት አባላት ተመራማሪዎች ያገኙት ውጤት ነው:- ይህ አጥኝ የኢስኮላሪስት ቡድን የመጀመሪያ የሰው ዘር በዚህች ምድር የተገኘው ወይም የተፈጠረው በ4004 ዓመተ ዓለም ነው የሚል ነው::

2ኛ. አጥኝ ቡድን የደርቪና አብርሃም ካልቮስ የተባሉት ሁለት ግለሰቦች ናቸው:: እነዚህ ሁለቱ ግለሰቦች ምሑራን ያገኙት ጥናት የመጀመሪያ የሰው ዘር በዚህች ምድር ላይ የተፈጠረው 4026 ዓመተ ዓለም ነው የሚል ውጤት ላይ ደርሰዋል:: በእነዚህ የሁለቱ ተመራማሪ ቡድኖች ምርምር ውጤት መካከል የ22 ዓመታት ልዩነት አለ:: አሁን ከእነዚህ ሁለቱ የምሑራን ቡድን ጥናት ማሕበሩ ለዓለም መጨረሻ

መቃረብ እንደ አንድ ማስረጃ የወሰደው የ2ኛውን ቡድን 4026 ዓመተ ዓለምን ነበር:: ለምን? ለምን ማሕበሩ 4004 ዓመተ አልመረጠም ? ለምን 4026 ዓመተ ዓለምን መረጠ? ትክክል ሆኖ ስለአገኘው ነው? ለምን እንደሆነ በኋላ እንመለስበታለን::

<u>የአሠሳል ዘዴአቸውን ቀጥለን እንመልከት</u>

| | |
|---|---|
| 1. በምስክሮቹ እምነት አንድ የፍጥረት ቀን 7ሺህ ስለሆነ 6 የፍጥረት ቀኖች 6×7000=42.000 ይሆናሉ | 42.000 |
| 2. አዳም የሚባለው የመጀመሪያ የሰው ዘር በ42ሺህ የፍጥረት ቀን መጨረሻ በ04.026 ላይ ተፈጠረ | 04.026 |
| 3. ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እስከ 1966 ዓ.ም. ያሉት የዘመናት ብዛት | 01.966 |
| 4. ከዚህ ዓይነቱ ስሌት አንፃር የሰው ዘር በዚህች ምድር ላይ ተገኝቶ ታሪክ ተጀመሮ ዘመን ከተቆጠረ 04026 +1966 + 8=5992 ዘመናት ሆነዋል:: | |
| 5. ከ1967 ዓ.ም. እስከ 1975 ዓ.ም. ድረስ ያሉተ ቀሪ ዓመታት 8 ነው | 0008 |
| 6. ከላይ እያየን እንደመጣ ነው እነዚህ ዘመናት በጠቅላላ ሲደመሩ | <u>48.000</u> |



<u>የክርስቶስ 1000 ዘመን ግዛት</u>

ቀደም ብለን በዕብራውያን መጽሐፍ ምዕራፍ 1 ቁጥር 13 እንደ አነበብነው ክርስቶስ በጣላቶቹ መካከል በሰማያዊ ዙፋኑ ላይ ሆኖ እየገዛ ነው:: እነዚህንም ጠላቶቹን በቅርቡ ይህ ትውልዳችን ሣያልፍ በአርማ ጌዶን ጦርነት ሊያጠፋቸው ነው:: እነዚህን ጠላቶቹን ካጠፋ በኋላ ለአንድ ሺህ አመት ይነግሣል:: ስለዚህ የክርስቶስ 1 ሺህ ዓመት ግዛት በአርማጌዶን ይኸች ዓለማችን ስትጠፋ የሚጀምረው ወዲያውኑ ነው:: ቀደም ብለን እንደአየነው ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ 48ሺህ በ1975 ዓ.ም. ይፈፀማል:: ክርስቶስ ከ1975 ዓ.ም. ጀምሮ ለ1000 ዓመት ይነግሣል፤ የራዕይ መፅሐፍ ምዕራፍ 20 ቁጥር 4 ትንቢት ያኔ ይፈፀማል:: ስለዚህ በክርስቶስ 1000 ዘመን ግዛት ውስጥ ሞት፣ መከራ፣ ድህነት፣ ጦርነት አይኖርም:: ስለሆነም የዓለማችን በ1975 ዓ.ም. መጥፋት የፈጣሪ ኘሮግራም እንደሆነ ማመን ተገቢ ነው ብለው በጉቻቸውን አሳመኑ::

<u>ስለዓለም በ1975 ዓ.ም. መጥፋት 3ኛ መረጃቻቸው ለእሥራኤል</u> ለሕዝብ የተሰጠ <u>የአስተዳደር መመሪያ ነው</u>

በዘሌዋውያን ምዕራፍ 25 ከቁጥር 1 እስከ ቁጥር 5 እንዲህ የሚነበብ ጥቅስ አለ:- «እኔ ወደምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ ምድሪቱ ለእግዚአብሔር ሰንበት ታድርግ:: ስድስት ዓመት እርሻህን ሥራ፣ ስድስት ዓመትም ወይንህን ቁረጥ፣ ፍሬዋንም አግባ:: በሰባተኛው ዓመት ግን ለምድሪቱ የእረፍት ሰንበት ነው:: ለእግዚአብሔር ሰንበት ይሁን፣ እርሻህን አትዝራ፣ ወይንህንም አትቁረጥ፣ የምድራችሁ የገቦ አትጨድ፣

ያልተቆረጠውንም የወይንህን ፍሬ አታከማች፡፡ በምድሪቱ የሰንበት እረፍት ይሁን፡፡»

በዚያን ዘመን እንደዛሬ የሕዝብ ብዛት አልነበረም፡፡ እንደዛሬ የዓለም አቀፍ ትሥሥር ተፈጥሮ ንግዱ አልተጧጧፈም፡፡ የትራንስፖርት ግንኙነት አልነበረም፡፡ ስለዚህ ጥቂት ሕዝብ በነበረበት ዘመን፣ ከሕዝብ ብዛትና ፍላጐት የተነሣ ደን ባል ተመነጠረበት ዘመን፣ ደን ስለአልተመነጠረ የመሬት አፈር መከላት ባልነበረበት ወቅት አለማዳበሪያ በቂ ምርት ይገኝ ነበር፡፡

ከላይ ከተዘረዘረው አንፃር 6 ዓመት በመደዳው ከታረሰ፣ ከተመረተ፣ 7ኛው ዓመት ላይ ባይመረት በቂ ምግብ ስለሚኖር መሬትን ማሳረፉ ተገቢ ነበር፡፡ በዛሬ ዓለምም የእርሻ ሣይንስ የሚደረገው መሬትን የመንከባከብ የአሠራር ዘዴ ነው፡፡ በዛሬ ዘመንም አንድ ዓመት ወይም ሁለት ዓመት መሬትን ማሳረፍ አስፈላጊነትን የእርሻ ሣይንስ ያስምሩበታል፡፡ ከመሬት ጥበት አንፃር ሣይታረስ ማሳረፍ የሚቻል መሬት ከሌለ ዘመናዊ ሣይንሣችን እያፈራራቁ መዝራትን ይመክራል፡፡ ለምሣሌ ሁልጊዜ ስንዴን ማሣ ላይ ስንዴን ብቻ ከመዝራንት አንድ ዓመት ገብስ ሌላ ዓመት አተር ወዘተረፈ እያፈራረቁ መዝራትን ሣይንሱ ይመክራል፡፡ የመሬት ጥበት ስለአለ፣ ፍላጐቱ ብዙ ስለሆነ፣ አቅርቦቱ እንዳያጥር መሬቱን ሣያሳርፉ በማዳበሪያ ሲገለገሉበት ይታያል፡፡ በቂ መሬት ኖሮ መሬትን ማሣረፍ ይመረጣል፡፡

ስለዚህ ከዚህ በላይ ከተመለከትነው አንፃር ለእስራኤል ልጆች የአስተራረስ ዘዴ ወይም ሕግ ነው፡፡ ይህንን



የአስተራረስ ዘዴ ሕግና ደንብን የይሖዋ ምስክሮች ለሙሴና አገልግሎት ለማዋል ፈልገው ልዩ ትርጉም በመስጠት የዓለም መጨረሻ ትንቢት አመልካች ነው ብለው ተረጐሙ፡፡ ይህንን ጥቅስ የፈለጉት 6 ዓመት እረስ በ7 ዓመት ላይ አትረስ የምትለውን ሐረጐች ስለፈለጓት ነው፡፡ ምክንያቱ 6 እና 7 ቁጥሮች ለሽብር ስብከታቸው እጅግ ጠቃሚ ስለሆኑ ነው፡፡ እስኪ ቀጥለን እንመልከት:-

በዘሌዋውያን 25 ቁጥር 8 ላይ ደግሞ እንደዚህ የሚነበብ የሕዝብ አስተዳደር ደንብ አለ፡፡ ይህ ደንብም ከፍልስፍና ቀመራቸው ስለሚሄድ እንደሚከተለው ተጠቅሞበታል፡፡ ጥቅሱ እንደዚህ ይነበባል፡፡ «ሰባት ጊዜ ሰባት አድርገህ የዓመታትን ሰንበት ቁጠር፣ የሰባት ዘመናትም ሰንበት ዘመን አርባ ዘጠኝ ትቆጥራለህ፡፡»

ይህ ደግሞ ሌላ ጠቃሚ የሆነ የአስተዳደር ሥርዓት ነው፡፡ በየሰባት ዓመት አንድ ጊዜ መሬትን ታሣርፋላችሁ፣ ስድስት ጊዜ መሬትዋን ካሣረፍክ በኋላ በ7ኛው የዕረፍት ወቅት ላይ ዝግጅት ታደርጋለህ ይለናል ከዚህ በላይ የተነበበው ጥቅስ፡፡ ይህ ማለት ሰባት ጊዜ ሰባት 49 0መት ነው፡፡ ስለዚህ በየ49ኛው ዓመት ላይ ከፍተኛ የበዓል ዝግጅት ይደረግ ነበር፡፡

በዘሌዋውያን ምዕራፍ 25 ቁጥር 9 ላይ እንደዚህ ይላል:- «ከዚያም በኋላ /49ኛው ዓመት ከባተ በኋላ/ በ7ኛው ወር በአሥረኛው ቀን በቀንደ መለከት ታውጃለህ፣ በማስተሰሪያ ቀን በምድራችሁ ሁሉ በቀንደ መለከት ታውጃላችሁ፡፡» ምን ብሎ ነው የሚያውጁት? ዓምሣ ዓመት ሲሞላ አምስት ወራት ሲቀር

ማለት 49 ዓመት ከሞላ በኋላ በ7ኛው ወር ላይ የማስተሰሪያ ወይም የነፃነት አዋጅ ይታወጃል:: ምን ተብሎ ይታወጃል?

በእሥራኤል ሕዝብ መካከል በባርነት የተገዛ፣ የሚከፍለው አጥቶ በዕዳ የተያዘ፣ በልዩ ልዩ ምክንያት በደል የተገዛ ሁሉ በ50ኛው የኢዮቤልዩ ዓመት በዓል ምክንያት ነፃ ይወጣል:: ከአምስት ወራት በፊት የሚታወጀውም ወደ አደገበት ወይም ወደተወለደበት አካባቢ ሄዶ በነፃነት የ50ኛውን ዓመት በዓል ለማክበር አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ነው:: ከዚህ በላይ በተገለፀው የአስተዳደር ደንብ ምስክሮቹ በፍልስፍናቸው በ1975 ዓ.ም. ዓለም ጠፍቶ የእኛ ከበሽታና ሞት ነፃ መውጣትን ያመለክታል ብሎ ተጠቀሙበት:: እንዲህም ብለው መግለጫ አወጡ:-

መግለጫ

48ኛው ሺህ የፍጥረት ዘመን የሚያልቀው በ1975 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ነው:: በ49ኛው ዓመት ውስጥ እሥራኤሎች ነፃ ወጥተው የ50ኛ ኢዮቤልዩ በዓላቸውን እንደሚያከብሩ ዓይነት እኛም 48ኛ ሺህ ዓመት ሲያልቅ በ1975 ዓ.ም. ነፃ ወጥተን እናከብራለን:: ስለዚህ ከ8 ዓመት በኋላ በ1975 ዓ.ም. ላይ ስንደርስ አርማንደን መጥቶ ይህችን ክፉ ዓለም አጥፍቶ ከሞት፣ ከድህነትና ከራብ ነፃ ያወጣናል ብለው ጆሌዎቻቸውን አታለሉ:: ከዚህ ዓይነቱ ስብከት በኋላ 50ኛ ዓመት ውስጥ የሚሆነውን መርሐ ግብር እንደሚከተለው አወጡ:-

ከ1975 ዓ.ም. በኋላ የሚጀመረው መርሐ ግብር

1ኛ. በ1975 ዓ.ም. ክርስቶስ ግዛቱን እንደሚጀምረው በራዕይ ምዕራፍ 14 ቁጥር 16 ላይ የተጠቀሰው ጦርነት ቀደም



ብሎ ወይም ልክ በ1975 ዓ.ም. በጥቅምት ወር አካባቢ ሊጀምር እንደሚችል

2ኛ. ከጦርነት በኋላ ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ሰይጣን ዲያቢሎስ በራዕይ 20 ቁጥር 1-2 መሠረት እንደሚታሠር

3ኛ. ሞት፣ በሽታ፣ ራብ፣ እርዛት፣ ሥራ ማጣት ጠፍትው የተሐድሶ ፕሮግራም ከምድር ዳር እስከምድር ዳር እንደሚዘረጋ

4ኛ. ከሁሉ ከሁሉ ከአዳም በወረስነው ሞት ምክንያት የሞቱት ፃድቃን ሁሉ ከመቃብር እንደሚነሱ፣ ይህ ሁሉ የሚፈፀመው በ1975 ዓ.ም. በሚጀምረው በኢየሱስ 1000 ዘመን ግዛት ውስጥ እንደሚሆን፣

5ኛ. ከታድሶ በኋላ ሽው ዓመት ሲያልቅ ሰይጣን ከእሥራቱ እንደሚፈታ

6ኛ. ሰይጣኑ ከተፈታ በኋላ የተሐድሶ ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን እንደሚፈትን

7ኛ. ፈተናውን ያላለፉት በራዕይ ምዕራፍ 20 ቁጥር 15 መሠረት እንደሚጠፉና ቀሪው የልበቢሱ የበግ ክፍል በዚህች ምድር ላይ ለዘላለም እንደሚኖር የሚገልጽ፣ ውሸትና ቅጥፈት የተሞላበት ፍልስፍናቸውን ዘረዘሩ:: ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በመጨረሻው ቁጥር 4 ስለዓለም ጥፋት ያቀረቡትን ማስረጃቸውን እንይ:-

ስለዓለም ጥፋት ከአዲስ ኪዳን የሚጠቅሱት መረጃ 4

ዓለም በ1975 ዓ.ም. ይጠፋል ለሚሉት ስብከታቸው እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡት ሌላ መረጃቸው በወንጌል ውስጥ ያሉት

ጥቅሶች ናቸው:: እነዚህን ጥቅሶች ቀጥለን አንድ በአንድ እንመለከታለን:-

1ኛ. ጥቅስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ከቁጥር 5-6 ያለው ሲሆን፣ እንደሚከተለው ይነበባል «አንድ አንዶቹም ስለመቅደስ በመልካም ድንጋይና በተሰጠው ሽልማት እንደ አጌጠ ሲነጋገሩ ሰማና ይህማ የሚታዩት ሁሉ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል አለ::» ይህ ታሪክ የተፈፀመው በቤተመቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው::

2ኛ. ጥቅስ ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ከቁጥር 1-3 ያለው ነው:: ይህም እንደሚከተለው ይነበባል:- «ኢየሱስ ከመቅደስ ወጥቶ ሔደ፣ ደቀመዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ:: እርሱ ግን መልሶ:- ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ፣ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሰይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው::» ማህበሩ ሰዓለም መጨረሻ መምጣት ስብከታቸው እንደ እውነተኛ ማስረጃ አድርገው ከሚያቀርቡት ነገሮች እነዚህ ሁለት ጥቅሶች በዋናናት ይገኛሉ::

እነዚህን መረጃዎቻቸውን ስንመለከት አንድ እርስበርሳቸው የሚቃረኑ ናቸው:: ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ ጻፉ ከተባለ ያ የመራቸው መንፈስ አንድ ዓይነት አለመሆኑን እንመለከታለን፣ ሉቃስን ያስፃፈው መንፈስ በቤተመቅደስ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቆመው የነበሩት ሰዎች የቤተመቅደሱን ሥራ ሲያደንቁ ኢየሱስ ሰምቶ የምታደንቁት ቤተ መቅደስ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሣይቀር ይፈርሳል እንዳላቸው ነው የምንመለከት::



ሌለኛው መንፈስ ደግሞ ማቴዎስን ያጻፈው መንፈስ ነው:- ይህኛው መንፈስ ደግሞ ኢየሱስ ከቤተመቅደስ ወጥቶ መሔድ እንደጀመረ ወይም እንደሄደ ይገልጻል:: ወጥቶ በመሔድ ላይ እያለ የገዛ ደቀመዛሙርቱ የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ:: በሌላ አባባል ከቤተመቅደሱ ወጥቶ ስለሔደ ተመልሶ የቤተመቅደስ ውበቱን እንዲመለከት የገዛ ደቀመዛሙርቱ እንደጠየቁት እንመለከታለን:: ከመሔዱ በፊት አያሳዩትም ነበር?

በዚህን ጊዜ ዞር ብሎ ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ ድነጋይ በድንጋይ ላይ ሳይቀር ይፈርሳል እንደአላቸው ነው:: ከእነዚህ ሁለት የታሪክ ዘጋቢዎች ከሁለቱ አንደኛው ዋሽተዋል ወይም ያስጻፈውም መንፈስ አንዱ የሌላው ተቃራኒ ሆኗል:: ስለዚህ ከመነሻው አንድ የጐደለ ነገር እንዳለ ግልፅ ነው::

ሉቃስ ምዕራፍ 21 ቁጥር 7 ኢየሱስ ግንቡን ላደነቁት ሰዎች ቤተመቅደሱ እንደሚፈርስ ሲናገር እዚያ ቤተመቅደስ ውስጥ ደቀመዛሙርቱ አብረውት ስለነበሩ እዚያ በዚያው «መምህር ሆይ እንግዲህ ይህ መቼ ይሆናል? ይህስ ይሆን ዘንድ እንዳለው ምልክቱስ ምንድን ነው?» ብለው እንደጠየቁት ተገልጾልናል::

ማቴዎስ ምዕራፍ 24 ቁጥር 3 ደግሞ እርሱ ከቤተመቅደስ ወጥቶ ከሔደ ፂኋላ ደብረዘይት በተለኘው ቦታ ተቀምጦ ሣለ «ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው? እንደ አሉት» ተጽፏል:: ከሁለቱ አንዱ ትክክል አይደለም::

ሉቃስ ከሁሉ የተሻለ የትምህርት ችሎታ እንደአለው ይነገራል። እንዲሁም የዘመኑን የባሕል መድኃኒት ስለሚያውቅ ሐኪም ተብሎም ይጠራ ነበር። ማቴዎስ ግን ትምህርቱ እጅግ ዝቅተኛ ነበር። ይህንን ችሎታቸውን ከአቀራረባቸው መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ በሉቀስ 21 ቁጥር 7 ላይ ይህ ቤተመቅደስ ይጠፋል እያልክ ነው፣ መቼ ነው የሚጠፋው? የመጥፋቱስ መቃረብ ምልክቱ ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ነበር ለኢየሱስ ያቀረበው።

ማቲዎስ ግን «ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው?» የሚሉትን ጥያቄዎች ነው የሚያቀርበው። ማቴ.24 ቁ. 3 ተመልከቱ። ኢየሱስ ስለዓለም መጨረሻ መናገሩን የሚገልፅ የለም? ኢየሱስ ይህ ቤተመቅደስ ይፈርሳል ነበር ያላቸው። በዓለም መጨረሻና በቤተመቅደሱስ መፍረስ መካከል ልዩነት አለ። ሉቃስ ስለ የዓለም መጨረሻ ጥያቄ አላነሳም፤ ስለዚህ አሁንም የአቀራረብ ልዩነት አለ፤ በትምህርት ገፍተው ባልተማሩት በተለይም ለማቲዎስ የቤተመቅደስ መጥፋትን እንደ የሞላው ዓለም መጥፋት የሚቆጠር ነው እንዴት?

<u>ስለዓለም መጨረሻ</u>

ኢየሱስ ስለዓለም መጨረሻ አንስቶ አልተናገረም ብለናል። ሉቃስም እንዲሁ ስለዓለም መጨረሻ አላነሳም። ማቴዎስ ግን ስለዓለም መጨረሻ አንስቷል። ዓለም የሚለው ቃል እንደየተጠቃሚው ሰዎች ሲጠቀሙበት እናያለን። «ዓለምሽ ዛሬ ነው ዛሬ» እንዲሉ ዓይነት ማለት ነው። አንድ ሰው እንዴት ነው? ሲሉት ጥሩ ነው። ዓለም ነው ይላል። የዘመናችን



ወጣቶችም እንዴት ይዞሃል? ሲባሉ ቆንጆ ነው። አሸዋይና ነው ይላሉ። ስለዚህ የግለሰብ ዓለም፣ የአንድ ሕዝብ ወይም ሥርዓት ማሕበር ዓለም፣ በጠቅላላው ደግሞ የድፍን ዓለም፣ ዓለም አለ። ስለዚህ በአንድ አንድ ነጥቦች ከማቴዎስ ወንጌላዊ ጋር ላለመስማማት ተስማምተን፣ በዚህ ዓለም በሚለው ቃሉ ለመስማማት እንሞክር:-

ኢየሱስ የአይሁድ ቤተመቅደስ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሣይቀር ይፈርሳል አላቸው እንጂ የዓለም መጨረሻ ይሆናል እንዳአላሰ ተመልክተናል። ይሁን እንጂ የአይሁድ ቤተመቅደስ ፈረሰ ማለት የአይሁድ ሕዝብ ወይም ማህበረሰብ ነፃነት፣ ደስታ፣ ባሕል እምነት ጠፋ ማለት ነው። የአንድ ሕዝብ የባሕል እሴት መጥፋት ደስታው ወይም ዓለሙ ጠፋ፣ ነፃነት አጣ ማለት ነው።

በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ የቤተመቅደሳቸው ታሪክ የሕዝባቸው ነፃነት ማጣት፣ ለባርነት መሸጥ፣ መበተን፣ መሆኑን በ607 ዓመተ ዓለም ቤተመቅደሳቸው በፈረሰ ጊዜ በቂ ትምህርት ያገኙ ይመስላል። ማቴዎሰ ደግሞ ይህንን ታሪካቸውን በደንብ ያውቃል። ስለዚህ የዓይሁድ ቤተመቅደስ መፍረስን ማቴዎስ የተገነዘበው የአይሁድ ሕዝብ ሥርዓተ ማሕበር ዓለም መጨረሻ መሆኑን ስለአመነ ደንግጦ የዚህ ሥርዓተ ማሕበር ወይም የዚህ የአይሁድ ሕዝቧ መጨረሻ አድርጐ እንደወሰደ አድርገን እንመለከታለን። እንዲህም ከሆነ የድፍን ዓለም መጨረሻ አለመሆኑን መገንዘቡ ቀላል ነው። ይህ የዓለም መጨረሻ የሚለው ቃል በአንድ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች ሥራ ላይ ዋለ እንጂ በብዙ የመጽሐፍ

ትርጓሜዎች የሥነሥርዓቱ መጨረሻ ምንድን ነው? ነው የተባለው። ስለዚህ የዓለም መጨረሻ የሚለው ቃል በዘመኑ የነበረ የአይሁድ ሥርዓተ ማሕበር መጨረሻ ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው:: እራሳቸው የይሖዋ ምስክሮች በተረጐሙት የአዲሱ ዓለም ትርጉም በተለኘው መጽሐፍ ቅዱስ የአይሁድ ሥርዓተ ማህበር እንጂ የሞላው ዓለም መጨረሻ አለመሆኑን በማሳየት እንደሚከተለው ተርጉመዋል:: «Tell us, when will these things be, and what will be the sign of your presence and of the conclusion of the system of things." የዚህ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትርጉም «ይህ መቼ ይሆናል? የመገኘትህና የሥርዓቱ ፍጻሜ መቼ ይሆናል?» የሚል ነው:: ስለዚህ የዓለም መጨረሻ የአይሁድ ሥርዓተ ማሕበር መጨረሻ እንደሆነ መመልከት ይቻላል::

ማቴዎስ ይህ መቼ ይሆናል ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ በማቴዎስ ምዕራፍ 24 ቁጥር 34 ላይ የሰጠው መልስ እንደዚህ የሚል ነበር:- «እውነት እላችኋለሁ ይህ ሁሉ እስኪሆን ይህ ትውልድ አያልፍም» ይህ የምትለው ቃል በኢየሱስ ዘመን የነበረውን ትውልድ የሚያመለክት ነው:: በተጨማሪም ያ የአይሁድ ቤተመቅደስ ከመጥፋቱ በፊት በዚያው ትውልድ አስቀድሞ የታዩ ምልክቶች እንደሚከሰቱ ገልጸዋል:: እስኪ ይህንን ተጨማሪ ምልክቶች ምን ምን እንደሆኑ ቀጥለን እንመልከታቸው:- እነዚህ ምልክቶች በሦስት የተከፈሉ ናቸው::

1ኛ. የአይሁድ ሥርዓተ ማሕበር መጥፋት መቃረብ የመጀመሪያ ምልክት፣ 2ኛ የአይሁድ ሥርዓተ ማሕበር መጥፋት



የመጀመሪያ መጨረሻ ምልክት 3ኛ. የአይሁድ ሥርዓተ ማህበር ከጠፋ በኋላ የሚተዩ ምልክቶች ናቸው::

<u>በኢየሱስ የተሰጡ የመጀመሪያ ምልክቶች</u>

እነዚህ የመጀመሪያ ክፍል ምልክቶች በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ከቁጥር 4-8 ያሉት ናቸው:- «በክርስቶስ ስም ሐሰተኞች ሰዎች መከሰት፣ ጦርና የጦር ወሬ መስማት፣ ጦርነቱ ከወሬ አልፎ ሕዝብ በሕዝብ ላይ እየተነሣ ጦርነት እንደሚተገበር፣ ጦርነቱን ተከትሎ ራብና ቸነፈር እንደሚሆን፣ የምድር መናወጦችም እንደሚደረግ፣ የሚሉ ምልክቶች ናቸው:: እነዚህ ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ምልክት ናቸው::

ከላይ እንዳየነው ኢየሱስ ስለአይሁድ ሥርዓተ ማሕበር አጠፋፍ ምልክት ነው የተናገረው:: ጦር የጦርንም ወሬ ትሰማላችሁ ይላል:: ይህ የአይሁድ ሥርዓተ ማሕበር በተአምር የሚጠፋ አይደለም:: የሚጠፋው በጦርነት ብቻ ነው:: ስለዚህ ለጦርነት መዘጋጀት ስለጦርነትም መስማት የግድ ይሆናል:: ይህ ጦርነት ከ500 ዘመናት በፊት በነቢዩ ዳንኤል የተተነበየ ጦርነት ነው:: ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 10 ቁጥር 1 ተመልከቱ:: የእስራኤል ሕዝብ የሮም መንግሥት አሰልክ ስለጨቆናቸው እራሳቸውን ነፃ ለማውጣት በልዩ ልዩ ፓርቲዎች ሥር ተደራጅተው የጦርነት ዝግጅት ያደርጉ ነበር:: አልፎ አልፎም በደፈጣ ውጊያ፣ አንድ አንዱ ፊት ለፊት እየገጠሙ የሮምን መንግሥት የቁም ስቃይ ማሣየት የጀመሩበት ወቅት ሆነ:: ሕዝቡ የተደራጀባቸው ፓርቲዎች የሚከተሉት ነበሩ:-

1ኛ. አሮጌ ፓርቲው የፈርሳውያን ድርጅት ፓርቲ

2ኛ. ሔሮዲያን የሚባል ፖርቲ። ይህ ፖርቲ ንጉሥ ሔሮድስ ከሞተ በኋላ ሮማውያን ከነገሰው ከልጁ ጋር ስለአልተስማሙ ሽረውት የራሳቸውን ሰው ስለሾሙ የሔሮድስ የገዥ መደብ ደጋፊዎች ያቋቋሙት ፖርቲ ነው።

3ኛ. በልዩ ልዩ ዘዴ የተደራጁ የዚሎትስ /Zealots/ ፖርቲ ነው። ይህ ፖርቲ ለሮም መንግሥት በሰላም ወዶ መገበር የአምላክን ሕግ መጣስ ነው እያለ ሕዝብን ይቀሰቅ የነበረ ፖርቲ ነው።

4ኛ. ኤሴኔራውያን የሚባል ፖርቲ ነው። ይህ ፖርቲ በሰላማዊ ትግል የቄሣርን መንግሥት መጣል ይቻላል ብሎ የሚያምን ነው። እነዚህና ሌሎችም ፖርቲዎች ግንባር ፈጥረው በድብቅ ወይም በሽምቅ ውጊያ የተሰለፉ፣ እና ለተሰለፉትም ሁለገብ እርዳታ ያደርጉላቸው የነበረበት ወቅት ነው። በማክሚላን ኩባኒያ፣ የታተመውን የሰው ሃይማኖት የሚለውን የ1967 ዓ.ም. እትም የታሪክ መጽሐፍ 562 ገፅ ተመልከቱ። ኢየሱስ ጦርንም፣ የጦርንም ወሬ ትሰማላችሁ፣ ነበር ያላቸው። ከላይ የተጠቀሱና ሌሎችም ምልክቶች ይከሰታሉ። ነገር ግን እነዚህን ሲታዩ የመጨረሻ እንደአልሆነ እወቁ አላቸው። ማቴዎስ 24.ቁ.6-7

<u>ማቴዎስ 24 ቁ. 14</u>

እንዲሁም ከመጀመሪያ ምልክቶቹ የሚደመር የወንጌል ስብከት በዚያን ዘመን ለነበረው ዓለም የመሰበክ ትንቢት ነው። በበዓለ አምሣ የኢየሱስ ተከታዮች በሙሉ ልዩ የሚያበረታ መንፈስ ፈሶላቸው ነበር። በዚሁ ዕለት ሌሎች 3000 አዳዲስ ተከታዮች ተጨምሮላቸዋል። በእነዚህም አዲስ በተጨመሩትና በነባሮቹ ላይ ያደረ መንፈስ በልዩ ልዩ ተአምራትና በድፍረት



እንዲሰብኩ ስለአደረጋቸው የዚያን ዘመን ዓለምን በወንጌል ስብከት አዳርሰዋታል። ወደ ኤሮፖ፣ ኤሺያ፣ አፍሪካ፣ አረቢያ፣ ሁሉ ተበትነው በሚገባ በከፍተኛ ድፍረት ሰብከዋል። በስብከቱም ምክንያት ስደት ደርሶባቸው ትንቢቱ ተፈፅሟል። እነዚህ የመጀመሪያ ሐዋርያት ይሰብኩት የነበረው የወንጌል ቃል ያልተበረዘና ያልተከለሰ ኦሪጅናል ነበር። ይህ ኦሪጅናል የመጥፋቱን ታሪክ ቀጥለን እንመልከት:-

<u>የዋናው ቅጅ መጥፋት</u>

ሀ. የመጀመሪያ የኢየሱስ ሐዋርያት ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ለወቅቱ እንደሚስማማ ተደርጐ ከዋና ቅጂው እየተገለበጠ መጻፍ ተጀመረ። ለምሳሌ በአደስ ኪዳን የመጽሐፍ ቅዱስ ስም በዚህ መልክ የተጻፉ 13ሺህ ቅጂዎች ተሠራጭተዋል። እንዲሁም በመጀመሪያ በሐዋርያት የተጻፉት የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ዋናው ጽሑፍ በዛሬ ጊዜ በፍጹም የለም።ኢን ሣይት ኦን ዘ ኢስክሪፕቸር የ1988 ዓ.ም. እትም ቮሊዩም አንድ ገፅ 443 ፖራግራፍ 4 እና 5 ተመልከቱ።

ለ. ዛሬ በሐዋርያት የተጻፉት ዋና ቅጂዎች በየትም ያልተገኙበት ዋና ምክንያት 1ኛ በ64 ዓ.ም. በመጀመሪያ ስደት በኔሩ ብዙ ክርስቲያኖች ተገዱ፣ ብዙ ጽሑፎቻቸውም ተቃጠሉ። 2ኛ. ከብዙ ዘመን በኋላ በ250 ዓ.ም. በአፄ ዴሲዮስ ክርስቲያኖችን በብዛት ያጠፉ፣ ጽሑፎቻቸውን በነቂስ እንዲቃጠል ያደረገ ስደት ተነሳ። 3ኛ. እና የመጨረሻው የክርስቲያኖችን ጽሑፎችና የክርስቲያን ጉባኤዎችን ያጠፉ ስደት ተነስቶ ይህ ነው የማይባል ጉዳት አድርሰዋል። ስለሰው ሃይማኖት የሚናገረውን የታሪክ

መጽሐፍ በጆን ቢኖስ ተዘጋጅቶ በማክሚላን ኩባኒያ በ1967 ዓ.ም. የታተመውን 626 ገፀ እና 635 ተመልከቱ:

ሐ. ክርስቲያኖችን ያስድዱት የነበሩት ሐሰተኞች ክርስቲያኖች ከፖለቲካ ባለስልጣናት ጋር በመመሳጠር፣ ባልተጠመቀው ንጉሥ ቆንጠስጥኖስ ሰብሳቢነት በመጀመሪያ ኒቂያ ጉባኤ በ325 ዓ.ም. ተሰብስበው መመሪያ አወጡ:: በመጨረሻም ከኒቂያ ጉባኤ ጋር የማይስማማ ማንኛውም የክርስቲያኖች ጽሑፎች እንዲጠፉ ተደረገ:: ለዚህም ነው ዛሬ ከ4 መቶ ክፍለ ዘመን በፊት የተጻፉትን ሙሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ የማይኖረው:: ከዚህም በላይ የክርስቲያን ሃይማኖትን ከወቅቱ የፖለቲካ መርሆ ጋር በማስማማት በየጊዜው ባደረጉት እንደንቂያ በነበሩት ጉባኤዎች ዛሬ የምንመራበት መጽሐፍ ቅዱስ ተዘጋጅቶ ቀረበ:: ከዚህም በላይ በተሐድሶ ዘመን የደረሰውን ከታሪክ መዘከር የሚቻል ነው:: በእነዚህና በመሳሰሉት ሁኔታዎች በመጣው ታሪካቸው ዛሬ ኢየሱስ ዓለምን አጠፋለሁ ብሎ ተናግሯል ብለው ምዕመናኖቻቸውን እያስፈራሩ ቢያጅጅሉ የሚገርም አይሆንም:: ለምን አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት ዓይነቃም እንደሚባለው ሆነና በኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ማሕበር በ1988 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የተጻፈ ኢን ሣይት ኦን ዘ ኢስክሪኘቸር በቮልዩም አንድ ገጽ 321 ላይ ጸሐፊዎቹ ማለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የመጀመሪያውን ዋና የወንጌል ቅጂን ሊበላሽ በሚችል ወረቀት ላይ ስለጻፉ ነው የተባለው፣ ምክንያታቸው ተጨባጨን እውነታ የሚያድበሰብስ ተልካሻ ምክንያት ነው:: ዞሮ ዞሮ ዋና ቅጂው መጥፋቱን ግን አምነዋል::



<u>ተጨማሪ ማስገንዘቢያ</u>

1. ስለ አዲስ ኪዳን በአጭሩ እንመልከት:: ኢየሱስ እራሱ በሕይዎት እያለ ተከታዩቹን በጽሑፍ አላስተማራቸውም:: ይህ አንዱ መሠረታዊ ችግር ነው::

2. ሰብስቦ ያስተማራቸው ተከታዮቹ ትምህርት የሌላቸው ወይም ያልተማሩ የቀን ኩሊዎች የነበሩ ናቸው:: 1ኛ. ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 26-31

3. ከረጅም ጊዜ በኋላ የኢየሱስን ታሪክና የክርስትና ፍልስፍናን በጽሑፍ ቀርጾ ማስቀረት ተገቢ መሆኑን ያመኑት የክርስትናን ፍልስፍና አድንቀው ወደ ድርጅቱ በተሳቡት በግሪክና በሮማውያን ምሑራን ረዳትነት ነው:: በእነዚህ ምሑራን ግፊት በጽሑፍ ቀርጾ የማስቀረት አስፈላጊነትን ከጊዜ በኋላ የተረዱት የክርስቶስ ተከታዮች የሚያስታውሱትን ያህል፣ እና የጌታቸውን ዝና ያጉላል ያሉትን ሁሉ እየጨመሩ ጻፉ:: ለምሳሌ ማቴዎስ የጻፈው በ41 ዓ.ም.፣ ሉቃስ የጻፈው በ56 ዓ.ም.፣ ማርቆስ የፃፈው በ65 ዓ.ም.፣ ዮሐንስ የፃፈው በ98 ዓ.ም. እንደነበር ታሪክ ይዘክረናል:: ይህም ሆኖ በእነዚህ የመጀመሪያ ሐዋርያት የተጻፉት የመጀመሪያ ቅጂዎች በስደት ምክንያቶች ጠፍተዋል:: አሁን በእጃችን ያለው የእርሱ ቅጂ ነው ተብለው፣ በየዘመኑ የነበሩት ሰዎች ከፖለቲካ አስተዳደር ጋር ተስማምተው ጽፈው ያቀረቡት እንደሆነ ይታመኗል:: እስከአሁን የተመለከትነው ኢየሱስ ስለአይሁድ ሥርዓተ ማሕበር መጥፋት መቃረብ የሚገልጹ የመጀመሪያ ክፍል ምልክቶች ናቸው:: የመጀመሪያ ክፍል መጨረሻ የሆኑትን ምልክቶች ቀጥለን በክፍል ሁለት እንመልከት:-

## የሁለተኛ ክፍል ምልክቶች

የሁለተኛ ክፍል ምልክቶች የተባሉት ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ከቁጥር 15-28 ያሉት ምልክቶች ናቸው:: እነዚህ ምልክቶች ናቸው የመጨረሻው ምልክቶች የሚባሉት:: እነዚህ የመጨረሻ ምልክቶች ስለጦር ወሬ፣ ስለጦርነት ዝግጅት፣ በየቦታው እዚህም እዚያም መገዳደል ወይም ውጊያ ሊከሰት እንደሚችል፣ ከተተነበዩት ከመጀመሪያው ክፍል ምልክቶች በፍጹም የተለዩ ናቸው::

በዚህ በሁለተኛ ምልክት መታየት ወቅት ስለጦርነት ዝግጅትና ስለጦር ወሬ ሣይሆን ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ጉራው ተለይቶ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት በጦር ሜዳ ውጊያውን ጀምር እስኪባሉ ትእዛዝ የሚጠባበቁበት ጊዜን የሚያመለክት ነው:: አንዱ ሌላውን ለማጥፋት የእጁ ጣት በቃተ ላንቃ ላይ ተቀምጦ ትእዛዝ ብቻ የመጠባበቅ ወቅትን የሚያመለክቱ ምልክቶች ናቸው:: እነዚህን ምልክቶች በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ከቁጥር 20 እስከ 24 በከፊል ቀጥለን እንመልከት:-

እንዲህ ይነበባል:- «ኢየሩሳሌም ግን በጭፍራ ተከባ ስታዩ በዚያን ጊዜ ጥፋትዋ እንደቀረበ እወቁ:: የዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራዎች ይሽሹ፤ በመካከልዋም ያሉ ከእርስዋ ፈቀቅ ይበሉ፣ በገጠር ያሉም ወደ እርስዋ አይግቡ:: የተጻፈው ሁሉ እንዲፈፀም ይህ የበቀል ጊዜ ነውና . . .» የተጻፈው ሁሉ እንዲፈፀም የሚለው ከ500 ዓመት በፊት በነቢዩ ዳንኤል የተተነበየ ትንቢት መኖሩን የሚያመለክት ነው::



ጌታ ኢየሱስ እንደነዚህ ያሉትን ምልክቶች ሲታዩ በሽሽት እራሳችሁን እድኑ ነበር ያላቸው:: እራሱ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ከቁጥር 15-28 የሉት የወሳኙ ጦርነት ምልክቶች መሆናቸውን ገልጸዋል:: በነቢዩ ዳንኤል የተነገረ ጦርነት መሆኑንም ገልጸዋል:: እንደዚህ ያሉት የመፋጠጥ ምልክቶች የታዩት በ66 ዓ.ም. ነበር:: በ66 ዓ.ም. ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት፣ የአይሁድን ሕዝብ ለመበተን የሮም ወታደሮች ኢየሩሳሌምን በወታደር ያጠሩበት ወቅት ነበር:: ይህ ምልክት በደንብ በተግባር ታይቷል:: ነገር ግን ቃታውን ስቦ ኢየሩሳሌምን ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሣይቀር ሊያጠፋት የነበረው ሠራዊት ከበባውን ትተው ተመለሰ:: ይህ ምልክት በደንብ ስለታየ ይህንን ምልክት ስታዩ እየሸሻችሁ ከኢየሩሳሌም ውጡ የተባለውን ትእዛዝ አስታውሰው የኢየሱስ ተከታዮች በሙሉ ከተማውን ጥለዋት ሸሹ:: ለዚህ ለሽሽት የተሰጠው ጊዜ 4 ዓመት ስለነበር የሮም ወታደሮች ከሽሽቱ በኋላ ተመልሰው በ70 ዓ.ም. ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሣይቀር ኢየሩሳሌምን በኢየሱስ ትንቢት መሠረት አጥፍተዋል:: የአይሁድ ሥርዓት ማህበር ወይም ዓለማቸው ጠፍተዋል:: በጆን ቢኖስ ተጽፎ በ1967 ዓ.ም. በማክሚላን ኩባኒያ የተጻፈውን የሰው ሃይማኖት የሚለውን የታሪክ መጽሐፍ ገጽ ከ564-565 እንብቡ::

## 3ኛው ምልክት

ይህ 3ኛ ምልክት በማቴዎስ ወንጌል 24 ቁ. 29 ላይ የምንአገኘው ነው:: ከመከራ በኋላ ወይም ከቤተመቅደሱ እና የአይሁድ ሥርዓት መጥፋት በኋላ ወዲያውኑ የሚከሰት

ምልክት ነው:: ይህንን ወዲያውኑ የሚከሰተውን ምልክት ቀጥለን በማቴዎስ 24 ቁጥር 29 ላይ የተባለውን እንመልከት:-

«ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፣ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፣ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፣ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ::»

በአሁኑ ዘመናችን ሣይንስ ፀሐይ የምትጨልምበት ወቅት፣ ጨርቃም፣ ብርሃንዋን የማትሰጥበት ወቅት በጥናት ተረጋግጠዋል:: በአስትሮኖሚ ሣይንስ እንዲህ ያለው ነገር የሉነር ወይም የፀሐይ ግርዶሽ እንዲሁም የጨረቃ ግርዶሽ እየተባለ የሚታወቀው ነው:: እነዚህ ነገሮች በየተወሰኑ ዓመታት ወይም ወራት የሚፈፀሙ ወይም የሚሆኑ ስለሆነ የዓለም ሣይንቲስቶች ክስተቱ ወደሚታይበት የዓለም አካባቢ እየሔዱ ይመለከቱታል፣ ያጠኑታል:: የአይሁድ ሥርዓት ከጠፋ በኋላ እንደዚህ ያሉት የተፈጥሮ ክስተቶች የሚታዩበት ወቅት እንደሚሆን የተነገረው ነገር ነው እንጂ ጠቅላላ ዓለማችን ትጠፋለች የሚለው ትንቢት አይደለም:: እነዚህ የዋች ታዎር ያንኪዎች መሥራቻቸው ሲቲ ራሴል ሚስቱን እንደአታለለ ሁሉ በአሁኑ ጊዜ ያሉትም እንደዚህ ባሉት በተፈጥሮ ክስተቶች መሆን ታሪክ ልበቢስ በጉቻቸውን እያታለሉ ነው::

ከዚህም በላይ ኮከቦችም ከሰማይ ይወድቃሉ የሚሉ ተወርዋሪ ኮከቦች በእንግሊዝኛ ሹቲንግ እስታርስ የሚባሉቱ ከዚያ ከአይሁድ ሥርዓት ጥፋት በኋላ በይበልጥ ሊከሰት የሚችል መሆኑን የሚገልጽ ነው:: እነዚህ ተወርዋሪ ኮከቦች ዛሬም እየወደቁና በአስትሮኖሚ ምሑራን እየተጠኑ ነው:: ከዚያ ጥፋት በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ የተፈጥሮ ክስተቶችን እንዲያውቁ



ኢየሱስ አስተማራቸው እንጂ ዓለማችን ትጠፋለች ብሎ እንዳላስተማረ ከበጉች ጭንቅላት በስተቀር የማይረዳ የለም:: እስኪ እነዚህ የተፈጥሮ ገሐዳዊ ክስተት ትርጉሙን ትተን ከመንፈሳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ትርጉም አንፃር እንመልከት:-

## ከመንፈሳዊ ትርጉም አንፃር

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ወይም አስተምሮ ከዋክብት በልዑላን ወይም በገዥዎች ይመሰላል:: በዘሁልቅ ምዕራፍ 24 ቁ. 17 ላይ ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል ይላል:: ይህ የተለመደ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች አነጋገር ነው:: ምን ማለት ነው? ግልፅ ነው:: ከያዕቆብ ዘር ገዥ የሚሆን ሰው ይወለዳል ማለት ነው:: ሌላ ትርጉም የለም::

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ሰማይ ከፍታን ያመለክታል:: ከፍታ ደግሞ ከዚህ አንፃር ከፍተኛ ስልጣን ወይም የአገረ ገዥ ቁንጮነትን የሚያሳይ ነው:: ምድር ደግሞ የተገዥ ዜጐች ምሳሌ ናት:: ነቢዩ ኢሳያስ የእስራኤል ሕዝብ ለናቡ ከደናጾር በባርነት ከተገዛ ከ70 ዓመት በኋላ ነፃነትን ስለአገኙ ይህንኑ አስመልክቶ በወቅቱ ለነበሩት ትምህርት ሰጥቷል:: ኢሳያስ በ607 ዓመተ ዓለም የተማረኩትን አሮጌ ሰማይና አሮጌ ምድር ናቸው:: እነዚህ ከ70 ዓመት በፊት ጀምሮ በባርነት ተገዝተው ያለፉ ስለሆነ ወደልብም አይገቡም:: ስለእነርሱ መቆጨትን ትታችሁ በአዲስ ተስፋ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ሆናችሁ ተንቀሳቀሱ ይላቸው ነበር::

በ537 ዓመተ ዓለም ነፃ ስለወጡት አዲስ ትውልድ ኢሳያስ ሲጽፍ እንደዚህ ብሏል:- «እነሆ አዲስ ሰማይና አዲስ

ምድር እፈጥራለሁ፣ የቀደሙት አይታሰቡም፣ ወደ ልብም አይገቡም።» ኢሳያስ ምዕራፍ 65 ቁጥር 17 ተመልከቱ። እነዚህ ከ70 ዓመት በኋላ ነፃነት ያገኙት የልጅ ልጆቻቸው አለቃና ምንዝር ሆነው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል። አለቆቹ አዲስ ሰማይ፣ ተገዢዎቹ አዲስ ምድር ተብለዋል። ስለሆነም እስከ አሁን እያየን የመጣናቸው ምልክቶች የአይሁድ ሥርዓተ ማሕበር በትንቢቱ መሠረት እንደሚጠፋ የተተነበዩና የተፈፀሙ ናቸው እንጂ ከዚያ ውጭ የሞላውን ዓለም ጥፋት የሚያመለክቱ አይደሉም።

ከዚህ መከራ በኋላ የፀሐይ ብርሃን አለመስጠት፣ የከዋክብቶች መውደቅ እና የመሰላሰሉት የኢየሱስ አነጋገሮች በዳንኤል ትንቢት መሠረት የተቀደሰው የዳንኤል ሕዝብ ከነመሪዎቻቸው ጋር ኃይላቸው መዳከሙን የሚያሳይ ነው። ከ70 ዓ.ም. በኋላ ጥሩ ጥሩ የሆኑ በፀሐይና በከዋክብት የተመሰሉ ባለስልጣናት ስልጣን አልባ ሆነው መበተናቸውን የሚገልፅ እንጂ የሞላው ዓለም ጥፋትን በምንም ተዓምር የሚያመለክቱ አይደለም። ተፈጥሮአዊ ሰማይ ስታስቡ ለምን ይጠፋል? ምድርስ ምን አደረገች? እነዚህ ተፈጥሮዎች ሥርዓታቸውን ጠብቀው ሙሐራቸውን ሣይለቁ እያገለገሉ ናቸው በሒደት በተፈጥሮ ባሕሪያቸው የመለወጥ ሁኔታ ቢኖርም ወይም መኖር ይችላል ቢባልም እንኳን ትንቢቱ የሚመለከተው እንዲህ ያለውን የገሐዳዊ ዓለም ጥፋትን የሚያመለክት አይደለም።

ከዚህ በላይ የተመለከትነው በዓለም መጨረሻ ስብከታቸው ምስክሮቹ ሕዝብን እንዴት እየረበሹ እንደበዘበዙ ነው። ነገር ግን ትንቢታቸው ሳይዝላቸው ቀርቶ ዓለም በ1975



ዓ.ም. ሣትጠፋ በቀረች ጊዜ ከምዕመናኖቻቸው ለምን? የሚል ጥያቄ መቅረብ ሲጀምር ምስክሮቹ አላልንም ብለው ካዱ። በዚህም የተነሳ ብዙ ተከታዮቻቸው ድርጅታቸውን ጥለው ወጥተዋል። ከእነዚህም አንዱ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ግለሰብ ነው። እውነት የይሖዋ ምስክሮች የዓለም መጨረሻ በ1975 ዓ.ም. እንደሚመጣ አልተነበዩም? መልሱ አዎንታዊ ነው

<u>በ1914 ዓ.ም. የትምህርተ ሃይማኖት ለውጥ</u>

ክርስቶስ በአካል መጥቶ ይወስደናል ብለው በተደጋጋሚ ስለከሸፈባቸውና ስለተነቃባቸው እንዲህ ያለውን የስብከት ትምህርት መለወጥና በትንሽ ቃላት ለውጥ በጎቻቸውን ለማታለል ፈለጉ። ስለዚህ ክርስቶስ በ1914 ዓ.ም. በሰማይ ነግሠዋል። በማይታይ መልኩም ግዛቱን በምድር ላይ ዘርግተዋል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በምድራዊ ጠላቶቹ ላይ እርምጃ ይወስዳል። ስለሆነም የዓለም መጨረሻ በ1914 ዓ.ም. ተጀምሯል። ይህ በ1914 ዓ.ም. የተጀመረ የዓለም መጨረሻ የአንድ ትውልድ ዘመን ሣያልፍ የሚፈፀም ይሆናል። ስለሆነም በ1914 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ መጀመር በማስተዋል ዓይን ያዩት ሰዎች በሕይወት እያሉ የዓለም መጥፋት ይከሰታል ብለው ወሰኑ። በኋላም ከላይ እንደተባለው የዓለም መጨረሻ በ1975 ዓ.ም. ይሆናል ብለው ሰብከው ሣይሆንላቸው በቀረ ጊዜ እንዲህ ብለን አልሰበክንም ብለው ካዱ። ይህንን የሰጎን ድብብቆሽ ከደታቸው እውነት አለመሆኑን ቀጥለን እንመልከት:-

<u>ከጽሑፋቸው የተጠቀሱ</u>

"Some of the generation that discerned the beginning of the time of the end in 1914 will still be alive on earth to witness

the end of this wicked system of things at the battle of Armageddon." May 1,1968 watch Tower issue page 272 የዚህ የእንግሊዝኛ ጽሑፍ ትርጉም ወደ አማርኛችን ሲመለስ የሚከተለውን ይመስላል:- «የዓለም መጨረሻ እ.ኤ.አ. በ1914 ዓ.ም. መጀመሩን በማስተዋል ያዩት የዚያ ትውልድ አባላት ይህ ክፉ ሥነሥርዓት በአርማጌዶን ጦርነት ዶግ አመድ ሲሆን ሣይሞቱ በምድር ላይ ሕያው ሆነው ለምስክርነት ይበቃሉ» የሚል ነው:: በአንድ ትውልድ ዘመን ውስጥ የሚፈፀም የዓለም መጨረሻ በ1914 ዓ.ም. ተጀመረ አላልንም ለሚለው ይህ አንዱ ማስረጃ ነው:: እ.ኤ.አ. ግንቦት 1 ቀን 1968 ዓ.ም. ያወጡትን የመጠበቂያ ማማ ጋዜጣ ገፅ 272 ተመልከቱ::

## 2ኛ አስረጅ

2ኛ አስረጅ ንቁ ጋዜጣቸው ላይ የወጣው ነው:: እንዲህ ይላል:- "The generation that saw the beginning of woes in 1914 would also see the end of Satan and his entire wicked system of things. Some who were alive then would still be alive when the end comes." October 8,1966 Awake page 18 ይህንንም ጽሑፍ ወደ አማርኛችን ከመለስን የሚከተለውን ሐሳብ እናገኛለን:- «እ.ኤ.አ. በ1914 ዓ.ም. የወዮታን መጀመር ያየ ትውልድ ሰይጣን ከእነ ክፉ ሥነሥርዓቱ ጋር ዶግ አመድ ሲሆንም በሕይወት ቆይተው ያዩታል::» እ.ኤ.አ. ጥቅምት 8 ቀን 1966 ዓ.ም. ንቁ ጋዜጣ ገጽ 18 ፖራግራፍ 5



## 3ኛ መረጃ እንዲህ ይላል

"Adam was created in the autumn of the year 4026 B.C. some time in that same year Eve would have been created, directly after which God's rest day commenced." The first 6000 years of man's existence and also the first 6000 years of God's rest day come to an end in 1975." Awake October 8,1966 Page 19.

ይህንኑም አሳባቸውን ወደ አማርኛችን መልሰን ከተመለከትን የሚከተለውን ይመስላል:- «አዳም በጥቢ ወራት በ4026 ዓመት ከልደት በፊት ተፈጥሯል:: በዚያው ዘመን ወዲያውኑ ሔዋን ከተፈጠረች በኋላ አምላክ እረፍቱን ጀምሯል:: ስለሆነም ሰው በምድር ላይ መኖር ከጀመረ 6 ሺህ ዓመትና እንዲሁም አምላክ እረፍቱን ከጀመረ 6ሺህ ዓመት የሚሞላው እ.ኤ.አ. በ1975 ዓ.ም. ነው::» ንቁ መፅሔት ጥቅምት 8 ቀን 1966 ዓ.ም. ገጽ 19:: ይህ ሁሉ ሀተታ ምን ለማለት እንደተፈለገ ግልፅ ነው:: በ1914 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የዓለም መጨረሻ ስለተጀመረ፣ ይህ የተጀመረ የዓለም መጨረሻ ደግሞ ከተጀመረበት ከ1914 ዓ.ም. ጀምሮ አንድ ትውልድ ከማለፉ በፊተ የዓለም መጨረሻ ስለሚሆን ቻል እንዳትሉ፤ ከጥፋቱ አምልጡ:: መጽሐፉ ቅዱስ እራሱ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ቁጥር 34 ላይ በ1914 ዓ.ም. እንደትውልድ የተቆጠረው ሕዝብ ከማለፉ በፊት የዓለም መጨረሻ እንደሚሆን ያስረዳል:: ስለዚህ የዓለም መጨረሻ ተቃርቧል እያሉ ሽብር መንዛታቸውን እንመለከታለን::

ይህንኑ ሐሳባቸውን እራሳቸው ከጻፉት ጽሑፍ እንደሚከተለው እንጠቅሳለን፡-

"This is worthy of notice particularly in view of the fact that the last day that began in 1914, and the physical facts of our day in fulfillment of prophecy mark this as the last generation of this wicked world, so, we can expect the immediate future to be filled with the thrilling events for those rest their faith in the God and his promises." Awake: October 8 page 19 paragraphs 20. የዚህ ትርጉም ሐሳብ የሚከተለውን ይመስላል።[፵፮] በተለይም ልብ ልንለው የሚገባው ነገር የዓለም መጨረሻ በ1914 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. መጀመሩንና የዚሁ ዓለም መጨረሻ መጀመር ትንቢት ምልክቶች መታየት ይህ ትውልዳችን የመጨረሻ ትውልድ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ በእግዚአብሔር እና እሱ በሰጠው ተስፋ እምነታቸውን ለጣሉት በቅርቡ የሚያስደስት ድንቅ ነገር ይከሰታል ብለን እንጠብቃለን፡[፵፯] ታዲያ ይህ ትንቢታቸው ለምን አልተፈፀመም? ምክንያቱ ምንድን ነው? መልሱን ቀጥለን እንመልከት።

<u>ትንቢቱ ለምን እንዳልተፈፀመ</u>

ይህ ትንቢት ያልተፈፀመበት ዋና ምክንያት ኢየሱስ ከተናገረው ትንቢት ውጭ ስለሆነ ብቻ ነው። ኢየሱስ የተናገረው ወይም የተነበየው ጥፋት የአይሁድን ሥርዓተ ዓለምና የዚያ የአይሁድ ሕዝብ ዘመን ትውልድን ብቻ የሚመለከት ስለነበረ፣ ትንቢቱ በ70 ዓ.ም. ትውልዱ ሣያልፍ ተፈፅሟል። ኢየሱስ ከ1914 ዓ.ም. ጀምሮ ስለአለው ትውልድ በፍጹም አልተነበየም።



ምስክሮቹ ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በጥቅሶች ቀርጦ ቀጥል ጥገና ፍልስፍናቸው ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን አምጥተው ልበቢስ በጉቻቸውን እያታለሉበት ነው። ይህ ራሱን ልባምና ታማኝ ባለአደራ መጋቢ ብሎ የሚጠራ የቅዱሳን ቅቡዓን ቀሪዎቻቸው ልበቢስ በጉችን ለማለብ የተጠቀሙበት ዘዴ ነው። ይህ ዘዴአቸው ሕፃን ልጅ ሲያለቅስ በአፉ ከሚከተተው የውሸት ጡጦ የተሻለ አይደለም። ይህ ትንቢት በማቴዎስ 24 ቁጥር 34 መሠረት ያ የኢየሱስ ዘመን ትውልድ ሣያልፍ በ70 ዓ.ም. ተፈፅሟል።

የዓለም መጨረሻ በ1914 ዓ.ም. ተጀመረ የሚለው ፍልስፍናቸው የተቀመረው በ1914 ዓ.ም. ክርስቶስ በሥጋ መጥቶ ወደሰማይ ይወስደናል ተብሎ በከሸፈው ትንቢታቸው ምትክ ነው። ስለዚህ የውሸት ትንቢት ስለሆነ ብቻ ሣይፈፀም ቀረ። ምስክሮቹ በ1914 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የተጀመረው የዓለም መጨረሻ የአንድ ትውልድ ዘመን ሣያልፍ ወይም ሣይሞላ ይፈጸማል ቢሉም ሣይፈፀም ትውልዱ አልፏል።

<u>የትውልዱ ማለፍ</u>

ምስክሮቹ የዓለም መጨረሻ በ1914 ዓ.ም. ሲጀመር በማስተዋል ዓይን ያዩ ሰዎች በሞት ከዚህ ዓለም ሣይለዩ የዓለም መጨረሻ ይሆናል ብለዋል። እንዲሁም በማስተዋል ዓይን ማየት የሚችል ቢያንስ አነስተኛ ዕድሜው 14 ዓመት የሞላው ሰው ነው በማለትም ሰብከዋል።[፵፰] ስለዚህ ትውልዱ ማለፉንና አለማለፉን እንደሚከተለው እንመልከታለን፡-

- በ1914 ዓ.ም. ዕድሜው 14 ዓመት የነበረ ሰው 14 ዓመት
- ከ1914 ዓ.ም. እስከ 1966 ዓ.ም. ያለው 52 ዓመት
- ከ1967 ዓ.ም. እስከ 1975 ዓ.ም. ያለው 08 ዓመት
- ከ1975 ዓ.ም. እስከ 2006 ዓ.ም. ያለው 31 ዓመት

ጠቅላላ 105 ዓመት

በአሁኑ ጊዜ በበለፀጉት አገሮች የአንድ ትውልድ ዕድሜ ማዕከላዊ ዓመት 69 ወይም 70 ዓመት ብቻ ነው፡፡ ኋላ ቀር በሆኑት አገሮች የሚኖረው ሕዝብ ትውልድ ዕድሜ ከ45 እንደማይበልጥ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ አሁንማ በኤድስና በሚከሰቱ ልዩ ልዩ በሽታዎች ወደ 35 ዓመት እንዳይወርድ ሥጋት አለ፡፡ ስለሆነም ትውልዱ ካለፈ 35 ዓመት ሆኗል፡፡ ምስክሮቹም ይኸንን አጥተውት ሣይሆን በዚህ መልኩ ሕዝብን በማሸበር ጥቅምን ለማግኘት የተነሱበት ዓላማቸው ስለሆነ ቀጥለውበታል፡፡

**ከ4004 ለምን 4026 ዓመተ ዓለም እንደተመረጠ**

ማህበሩ 4004 ትቶ 4026 ዓመተ ዓለምን የመረጠው ለመጣብህ መጣብሽ ስብከታቸው ጠቃሚ ሆኖ ስለአገኘው ነው፡፡ ከዚህ በፊት እንደአየነው ምስክሮቹ ዓለም ከተፈጠረ፣ ዘመን ከተቆጠረ 48 ሺህ ዓመት በ1975 ዓ.ም. ያልቃል ብለዋል፡፡ በ49ኛ ውም ሺህ የነፃነት መውጣት ተግባር ሥራ ላይ ይውላል ብለዋል፡፡ ይህ የሽብር ስብከት በይበልጥ ሕዝብን አሸብሮ ለድርጅቱ ሁለገብ አገልግሎት ለማበርከት የሚያስችለው 4004 ዓመተ ዓለም ሣይሆን 4026 ዓመተ ዓለም ከተመረጠ ብቻ ነው፡፡



የይሖዋ ምስክሮች የ1964 እና 1965 ዓ.ም. የዓመት /year book/ መጽሐፋቸው እንደተገለጸው ከሆነ ድርጅታቸው የመከሰር ቀስት አሳይቷል፡፡ ምዕመናኖቻቸው በጣም ተለላችተው የአባሎቻቸው ማሽቆልቆል ተስተውለዋል፡፡ ስለዚህ የበጐች የልብ ትርታ ቴርሞሜትር ተለክቶ ቤንዚን እንደሚያስፈልጋቸው ታመነ፡፡ ይህ ቤንዝን ቶሎ መሞላት አለበት፡፡ አለበለዚያ መኪናዋ ትቆማለች፡፡ ከላይ በተገለጸው የዓመት መጽሐፋቸው የቤንዚን ጌጁ ቤንዚን ማለቁን በሚገባ አሳይቷል፡፡ ስለዚህ ከ4004 ዓመተ ዓለም ይልቅ 4026 ዓመተ ዓለም የበለጠ በጥሩ ቤንዚንነት ሊያገለግልና መኪናዋም እንድትከንፍ ሊያደርግ ስለሚችል 4026 ዓመተ ዓለም ተመርጧል፡፡

በ4004 እና በ4026 ዓመተ ዓለም መካከል የ22 አመት ልዩነት አለ፡፡ ከዚህ ልዩነት አንፃር የዓለም መጨረሻ ሊመጣ 8 ዓመት ቀርቷል ከማለትና የለም 22 ዓመት ቀርቷል ከማለት መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ቀላል ነው፡፡ ለምሳሌ በ1967 ዓ.ም. ላይ 22 ዓመት ደምሮ የዓለም መጨረሻ በ1989 ዓ.ም. ይመጣል ከማለት ይልቅ በ1967 ዓ.ም. ላይ 8 ዓመት ደምሮ በ1975 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ይመጣል ማለት አጣዳፊነቱን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ማሕበሩ ለልበቢስ በጐቹ ማታለያ 4026 ዓመተ ዓለም እጅጉን በጣም ጠቃሚ ሆኖ ስለአገኘው 4026 ዓመተ ዓለምን መርጧል፡፡ ይህን ደግሞ የልበቢሶች በጐች ጭንቅላት ካልሆነ በስተቀር አስልቶ ከመጠቀም አንፃር ማንም የሚያደርገው ነው፡፡

## ምዕራፍ 8

## ከ1975 ዓ.ም. በፊት ይፈጸማሉ የተባሉት ሁለት ትንቢቶች

በ1975 ዓ.ም. የዓለም ጥፋት ከመሆኑ በፊት ሁለት ወሳኝ ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች እንደሚፈፀሙ ማሕበሩ እ.ኤ.አ. በ1966 ዓ.ም. መግለጫ አወጣ። ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1974 ዓ.ም. ድረስ ባሉት የ8 ዓመት ጊዜያት ውስጥ ትንቢቶቹ ይፈጸማሉ ማለት ነው። እነዚህ ትንቢቶች ምንድር ናቸው? እነዚህ ትንቢቶች አንዱ የደቡብ ንጉሥ እየተባለ በማሕበሩ የሚጠራው የሰሜኑ ንጉሥ ከሚባለው ንጉሥ ጋር ጦርነት ገጥሞ በአንደኛው የበላይነት ይደመደማል የሚል ትንቢት ነበር። እነዚህ ንጉሥ የተባሉት ተቃራኒ ነገሥታት ተራ የመንግሥት መሪዎች ሣይሆኑ ኃያላን ልዕለ መንግሥታት ናቸው። እነዚህ የዓለም ልዕለ ኃያላን ነገሥታት ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1974 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ባሉት ጊዜያት እርስ በርሳቸው ተዋግተው ድሉ በአንደኛው የበላይነት ይደመደማል ይላሉ። በዘመናችን ማለት ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1974 ዓ.ም. በዓለማችን የሰሜኑና የደቡብ ልዕለ ኃያላን መንግሥታት በፍጹም በዚህች ምድራችን ላይ በእውን አልነበሩም። ይህንን ዓይነቱን ፍልስፍና ልበቢስ በጒቻቸውን እያጃጃሉ ለማለብ ማሕበሩ የፈለሰፈው ልበወለድ ተረት ነው። በዚያም ሆነ በዚህ መፈፀም ካለባቸው ትንቢቶች አንዱ ከዚህ በላይ የተገለፀው የልዕለኃያላን ውጊያና በማጨረሻም የአንዱ በትንቢቱ መሠረት በአሸናፊነት መወጣት ነው።

ሁለተኛው ከ1966 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. እስከ 1974 ዓ.ም. መፈፀም አለበት የተባለው ትንቢት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢተ ሕዝቅኤል መሠረት ከይሖዋ ምስክሮች ድርጅት



በስተቀር የዚህ ዓለም ሃይማኖቶች በሙሉ በተባበሩት መንግሥት አመራር ሰጭነት ከምድረገጽ ይጠፋሉ የተባለው ትንቢት የሚፈፀምበት ወቅት ይሆናል፤ እነዚህን ሁለቱን ትንቢቶች ተራ በተራ በጥንቃቄ ቀጥለን እንመልከታቸው:-

### የመጀመሪያ ትንቢት

በምስክሮቹ እምነት እና ልዩ የጂኦግራፊ ተሰጥኦ የሰሜን ልዕለኃያል ወይም ንጉሥ የተባለው በሶቭየት ሕብረት ይመራ የነበረው የኮሚኒስት ጐራን የሚወክል ነው። የደቡብ ንጉሥ የተባለው ደግሞ በአንግሎ አሜሪካ የሚመራው የምዕራቡ ልዕለ ኃያል ጐራን የሚያመለክት ነው። ምስክሮቹ ይህንን ሐሳብ ያገኙት ከትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 11 ቁጥር 40 እና ቁጥር 43 ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ የሰሜንና የደቡብ የሚባሉ መንግሥታት ወይም ነገሥታት በዘመናችን በታሪክ አልታዩም። ቀዝቃዛ ጦርነት ከማክተሙ በፊት በዓለማችን የነበሩ ሁለት ልዕለ ኃያላን መንግሥታት ከምዕራብና ምሥራቅ ነበሩ እንጂ የሰሜንና የደቡብ ተብሎ በታሪክ የሚታወቅ የለም። ይህ በመሠረቱ እንዱ ውሸታቸው ነው።

እንደምስክሮቹ የጂኦፖለቲካል ትንተና የሰሜኑ የተባለው ቶታሊታሪያን እየተባለ ይጠራ የነበረው የኮሚኒስት ጐራ ሲሆን በአሸናፊነትም የሚወጣው ይኸው የኮሚኒስት ጐራ ነው ይላሉ። ይህም ውሸት ነው። እንኳን በአሜሪካን የሚመራውን የምዕራቡን ልዕለ ኃያል ማሸነፍ ቀርቶ እራሻቸው ፈራርሰው ወድቀዋል።

በዳንኤል ዘመን ከሰሜንና ከደቡብ አቅጣጫ በጦርነት የሚፈላለጉ ሁለት ነገሥታት እንደነበሩና የሰሜኑ የደቡቡን እንደሚያሸንፍ ዳንኤል በመገምገም ተንቢዮ ይሆናል። እነዚህ

ነገሥታት በዳንኤል ዘመን የነበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ነገሥታት ናቸው:: በመጨረሻው ዘመን የሚለውም የዳንኤል ትንቢት የእነዚያኑ በዘመኑ የነበሩ ነገሥታት የአገዛዛቸውን የመጨረሻ ፍጻሜ የሚያመለክት ትንቢት ነው:: የመጨረሻ ፍጻሜ የምትል ሐረግ ስለአለች ብቻ በጉቻቸውን በማሞኘት አመቺ ሆኖላቸው ተጠቀሙበት:: ስለዚህ ያንን ገና ድሮ ጥንት የተፈፀመውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ወደ 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በመሣብ ለሜኑን ከምሥራቁ የኮምኒስት ጐራ፣ ደቡብን ደግሞ ከምዕራቡ የዲሞክራቲክ ጐራ አቆራኝተው የማታለያ ትንቢታቸውን አወጁ:: ይህም ቢሆ እነርሱ በተነበዩት መሠረት ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1975 ዓ.ም. በነበረው ወቅት አልተፈጸመም፤ ለወደፊትም አይፈፀምም:: ይህንን የማታለያ ትንቢታቸውን በንቁ ጋዜጣቸው እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 8 ቀን 1966 ዓ.ም. እስከ 1974 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ይፈጸማሉ ከተባሉት ትንቢቶች አንዱን ብቻ ነው:: ሌላኛውን ትንቢት ደግሞ ቀጥለን እንመልከት:-

<u>ሁለተኛው ትንቢት</u>

ይህ ሁለተኛው ትንቢታቸው ከይሖዋ ምስክሮች በስተቀር ማንኛውም በዚህ ዓለም ላይ የሚገኝ ሃይማኖት ከ1966 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. እስከ 1974 ዓ.ም. ባሉት 8 ዓመታት ውስጥ ከገጸ ምድር ይጠፋሉ የሚል ነው:: ይህ ትንቢት በራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ 17 እና 18 ላይ የተመሠረተ ነው:: እንዴት እንደሆነ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን:-

<u>ታላቂቱ ባቢሎን</u>

እንደ የይሖዋ ምስክሮች እምነት ከእነርሱ ድርጅት ውጭ ያሉት የዓለም የሃይማኖት ድርጅቶች ሁሉ ታላቂቱ ባቢሎን



ተብለው ተሰይመዋል:: ይህም የሚያመለክተው በዓለም ላይ ያሉትን ሐሰተኞች የሃይማኖት ድርጅቶችን በሙሉ ነው ይላሉ:: እነዚህ ሐሰተኞች የሃይማኖት ድርጅቶች ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የሃይማኖት ትምህርት የሚያስተምሩ መሆናቸውን በመግለፅ ማሕበሩ እንደዚህ ብለዋል:-

«በምድር በሙሉ በሚገኙ በባቢሎናዊ መሠረተ ትምህርቶች በብዛት መኖራቸው፣ ይህ ድርጅት ከባቢሎን ምስጢሮች የመነጨች መሆንዋን ያመለክታል:: ለምሳሌ ያህል የሰው ነፍስ ዘላለማዊነት፣ የሲኦል ሲቃይና የአማልክት ሥላሴነት እምነት፣ በአብዛኞቹ የሩቅ ምሥራቅ ሃይማኖቶችም ሆነ በሕዝበ ክርስትና ሃይማኖቶች ውስጥ ይገኛሉ:: ከ4 ሺህ ዓመታት በፊት በጥንትዋ የባቢሎን ከተማ ውስጥ የተፀነሰው የሐሰት ሃይማኖት በጣም አድርጐ ትልቅ ድርጅት በመሆኑ ታላቂቱ ባቢሎን የሚል ስያሜ ማግኘት የተገባ ነው::» ታላቁ መደምደሚያ ደርሷል መጽሐፍ ገጽ 235 ፖራግራፍ 3 የ1993 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የአማርኛ እትም ተመልከቱ::

ይህ ከዚህ በላይ በምስክሮቹ የተጻፈው ሐሳብ የሰው ነፍስ አትሞትም፣ የሲኦል ስቃይ የመላእክትና የሥላሴዎች አምልኮት ወይም እነርሱን የሚያምኑ ሁሉ ሀሰተኞች የሃይማኖት ድርጅቶች ናቸው የሚል ነው:: በአብዛኛው የእሩቅ ምሥራቅ ሃይማኖቶች እና የሕዝበ ክርስቲያኖች መካከል እንደዚህ ያለ እምነት ስለአለ ታላቂቱ ባቢሎን የሚል ስም ይገባቸዋል:: ለምን ቢባል ሐሰተኞች የሃይማኖት ድርጅቶች ናቸውና እያለ የሚደመድም ሐሳብ ወይም መግለጫ መሆኑን እንረዳለን:: ይህንኑ በማጠናከር በዚሁ ታላቁ መደምደሚያው መጽሐፍ 1993

ዓ.ም. እትም ገጽ 208 በብራኬት ወይም ቅንፍ ውስጥ ከተጻፉት የመጀመሪያ ረድፍ ላይ እንዲህ ብለው ጽፈዋል፡- «ከታላቂቱ ባቢሎን ዋናኛ አባላት አንዷ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ነች፡፡» እንዴት? ቢባል መልሱ በሥላሴዎች፣ ነፍስ አትሞትም፣ መላእክት ያማልዳሉ ብላ ስለምታምን ነው፡፡ እነዚህ ትምህርቶች የጥንት ባቢሎን ሐሰተኛ የሃይማኖት ትምህርት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ መልኩ የሚያምኑ ሃይማኖቶች ሁሉ ሐሰተኞች ናቸው ይላሉ፡፡

**በ1986 ዓ.ም. እ.ኤ.አ.**

በ1986 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ዓለም ሰላም እንድትሆን፣ ቀዝቃዛ ጦርነቶች እንዲቆሙ፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰላም ዓመት ተብሎ እንዲሰየምና ሁሉም ስለዓለም ሰላም እንዲሠሩ ውሳኔ ተላልፎ ነበር፡፡ በዓለም ላይ ያሉት ታላላቅ የታወቁ የሃይማኖት ድርጅቶች በኢጣሊያ አሲዚ ውስጥ ተሰብስበው ይህንኑ የተባበሩት መንግሥታት የሰላም ዓመት እንዲሆን የተላለፈውን ጥሪ ደግፈውታል፡፡ ይህ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት እንደዚህ ያለውን መልካም ጥረት በማናናቅ እንደሚከተለው መግለጫ አወጣ፡-

« እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች የፀለዩት ለየትኛው አምላክ ነበር? እያንዳንዱን የሃይማኖት ቡድን ብትጠይቁ የተለያየ መልስ ይሰጣችኋል፡፡ በብዙ የተለያዩ መንገዶች ያቀረቡትን ፀሎቶች የሚሰሙ ይህን የሚያክል አማልክት አሉን? ከሥርዓተ ፀሎቱ ተካፋዮች መካከል ብዙዎቹ የሕዝበ ክርስትናን ሥላሴ የሚያመልኩ ናቸው፡፡» ይላል፡፡ ታላቁ መደምደሚያ መጽሐፍ ገጽ 240-250 ያሉትን እንብቡ፡፡



በስብሰባ ላይ ስለተካፈሉትም የሃይማኖት ድርጅቶች ማሕበሩ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ «በአጠቃለይ 12 የሃይማኖታዊ ድርጅቶች ቤተሰቦች ተሰብስበው ነበር፡፡ ሃይማኖታዊ ድርጅቶቻቸውን ወክለው ከተገኙት መካከል፡-

1. የእንግሊዙ የካንቴበሪ ሊቀጳጳስ
2. የቡድሂዚም ደላይ ለማ
3. የሩሺያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተጠሪ
4. የቶክዮ የሺንቶ ቤተ ፀሎቶች ማሕበር ኘሬዝዳንት
5. የአፍሪካ ጣኦት አምላኪዎች እና
6. በቀለማት ያሸበረቀ የራስ ጥምጥም ያደረጉት ሁለት የአሜሪካን ሕንዶች ይገኙበታል፡፡ ››

ታላቁ መደምደሚያ እ.ኤ.አ. 1993 ዓ.ም. የአማርኛ እትም መጽሐፍ ገጽ 250 ተመልከቱ፡፡ በማህበሩ እምነት እነዚህ የተሰበሰቡት የዓለም ኃይማኖት ድርጅቶች ሐሰተኞች ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር ከእነርሱ ድርጅት በስተቀር በዓለም ላይ ያሉት ሃይማኖቶች የተባሉት ሁሉ ሐሰተኞች ናቸው፡፡ ከእነርሱ ድርጅት አባላት በስተቀር የዚህ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ከምድረ ገጽ እነርሱ በቅርብ በቅርብ እየቀጠሩ በሚተነቢዩት የዓለም መጨረሻ ጥፋት ቀን ጠፊዎች ናቸው፡፡

**ይህ ሁሉ ሑተታ ለምን አስፈለገ?**

ይህ ሁሉ ሐተታ ያስፈለገው ከዚህ በላይ እንደተባለው ሞላው የዓለም ሃይማኖቶች ውሸታሞች ስለሆኑ አንድ የወል ወይም የጋራ መጠሪያ ስም አላቸው፡፡ ይህ የዓለም ሐሰተኞች ሃይማኖቶች የጋራ መጠሪያ ስም ታላቂቱ ባቢሎን የሚል ነው፡፡

ስለዚህ በምስክሮቹ እምነት ታላቂቱ ባቢሎን ከተባለ በዓለም ላይ ያሉት ሃይማኖቶች ሁሉ ውሸታሞች ናቸው ማለት ነው:: እንዲሁም የሰይጣን ካድሬዎች ናቸው ስለሚሉ ይህንኑ አባባላቸውን በደንብ ለመግለፅ ነው:: ስለዚህ እነርሱ ከጠቀሱት ጥቅስ አንፃር ታላቂቱ ባቢሎን ማን ናት? ከሚል አኳያ ጉዳዩን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመርምር:-



## ምዕራፍ 9

## ታላቂቱ በቢሎን

በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 18 ቁጥር 21 ላይ እንደዚህ የሚል ጥቅስ አለ:- «ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን እንዲህ ተገፍታ ትወድቃለች::» እንዲሁም ደግሞ በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 17 ቁጥር 1 ላይ «ታላቂቱ ጋለሞታ» የሚል አለ:: እንደምስክሮቹ ትርጉም ታላቂቱ ጋለሞታ ወይም ታላቂቱ ባቢሎን የዚህ ዓለም ሐሰተኞች የሃይማኖት ድርጅቶች የወል ስም ነው:: ስለዚህ ከራዕይ ምዕራፍ 17 ቁጥር 1 ጀምረን እውነት መሆኑንና አለመሆኑን እንመለከታለን:-

### ዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 17 ቁ. 1

«ሰባቱን ፅዋዎች ከያዙ ከሰባቱ መላዕክት አንዱ መጥቶ ና በብዙም ውሀዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ:: የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ፣ በምድርም የሚኖሩ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ሰከሩ ብሎ ተናገረኝ::» ከዚህ በላይ እንደተነበበው ከሆነ ታላቂቱ ጋለሞታ እንደአለች፣ ጋለሞታይቱ የተቀመጠችው በብዙ ውሀዎች ላይ እንደሆነ፣ ከዚህች ታላቂቱ ጋለሞታ ሴት ጋር የምድር ነገሥታት ሁሉ እንደሴሰኑት፣ የምድር ነገሥታት ብቻ ሣይሆኑ በምድር የሚኖር ሕዝብ ሁሉ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ እንደጠጡ የሚገልፅ ነው:: ስለዚህ ይህች ሴት ተከሣ ፍርድ ቤት ልትቀርብ ነው:: ለምን? ምን ስለአደረገች? ለምን እርስዋ ብቻ ተከሣ ፍርድ ቤት ትቀርባለች? ይህች ሴት ማን ናት? ወይስ ማንን ትወክላለች? ስለዚህች ሴት ሊያሳያት መልአኩ ዮሐንስን ይዞ ወደ በረሃ ስለሔደ ታሪኩን ቀጥለን እንመልከት:-

ራዕይ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 3-6 ደግሞ እንዲህ ይላል:- «በመንፈስም ወደ በረሀ ወሰደኝ፣ የስድብ ስሞች በሞሉበት፣ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ:: ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፋ፣ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በእንቁዎችም ተሸልማ ነበር:: በእጅዋም የሚያፀይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኵሰት የሞላበት የወርቅ ፅዋ ያዘች፣ በግንባርዋም ምስጢር የሆነ ስም:- ታላቂቱ ባቢሎን የጋለሞታዎችና የምድር ርኵሰት እናት ተብሎ ተጻፈ:: ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት::»

መልአኩ ወደ በረሀ ካደረሰው በኋላ ዮሐንስ ያየው ሰባት እራሶችና አሥር ቀንዶች ባሉት ቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ ነው:: ሴቲቷ የተቀመጠችበት ቀይ አውሬን በዚህ መጽሐፍ የውጭ ፊት ለፊቱ ገጽ ላይ ያለውን ስዕል በመመልከት መረዳት ይቻላል:: ቁምነገሩ የዚህች ሴት ስም ታላቂቱ ባቢሎን እንደተባለና ይህም ስሟ ሚስጢር እንደሆነ ነው:: ራዕይ 17 ቁጥር 5 ተመልከቱ:: ታዲያ ይህ ታላቂቱ ባቢሎን የሚለው ስም ምስጢር ነው ቢባልም የይሖዋ ምስክሮች እናውቃለን ብለዋል:: እንደ ምስክሮቹ ትርጉም ከሆነ ሴቲቷ የዚህች ዓለማችን የሐሰተኞች ሃይማኖቶች ድርጅቶች የወል ወይም የጋራ ስም ነው:: መልአኩ የስሙዋን ሚስጢር ተርጉሟል? ዮሐንስ ከመልአኩ የተረዳው ነገር አለ? እስከአሁን እንዳየነው ከሆነ ምንም ነገር የለም:: ዮሐንስ በበረሀ ደርሶ ይህንን ሁሉ ካየ በኋላ እጅጉን በጣም ተደነቀ:: የዮሐንስን መገረምና መደነቅ ያየው መልአክ ቀጥሎ እንዲህ አለው:-



ራዕይ ምዕራፍ 17 ቁጥር 7-8 «የምትደነቅ ስለምንድር ነው? የሴቱቱን ምስጢርና የሚሸከማትን ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉትን የአውሬውን ሚስጥር እኔ እነግርሃለሁ::» መልአኩ የሴቲቱን ምስጢርና የአውሬውን ምስጢር እኔ እነግርሃለሁ ብሎታል:: ለዮሐንስ ነግሮታል? መልአኩ የሴቲቷን ምስጢር እነግርሃለሁ ነበር ያለው:: በሴቲቱ ምስጢርና በስሙዋ ምስጢር መካከል ልዩነት ይኖር ይሆን? መልአኩ የሴቲቷን አድራጐትና አቋም ምስጢር ለዮሐንስ ነግሮት ይሆናል፤ ነገር ግን ምስጢር የሆነ ስም:- ታላቂቱ ባቢሎን» ምን ማለት እንደሆነ መልአኩ የገለፀላት አይመስልም:: ለማንኛውም ነገሩን በፅሞና እንከታተል:-

ዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 17 ቁ.8 የአውሬውን ምስጢር እንደሚከተለው አብራርቶታል:- «ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ፣ አሁንም የለም፣ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው፣ ወደ ጥፋትም ይሄዳል፣ ስሞቻቸወም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ አውሬው አስቀድሞ እንደነበረ፣ አሁን እንደሌለ፣ ነገር ግን እንዳለ ሲያዩ ያደንቃሉ ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው::»

ይህ አውሬ አንድ ብቻ ነው:: ነገር ግን ሰባት እራሶችና አሥር ቀንዶች አሉት:: ይኸው አንድ አውሬ ከሰባት እራሶች መካከል አንዱን በየተራው ብቻ እያደረገ የሚታይ መሆኑን እንመለከታለን:: በተወሰነ ወቅት ወይም ወቅቱ ሲደርስ ይታይ የነበረውን እራስ ሲቀይር አወሬው ጨርሶ የላላ ወይም የጠፋ ይመስልና በሌላኛው ቀንዱ ብቅ ብሎ እራሱን ያሳየል:: በዚህን ጊዜ ጨርሶ ጠፍቷል ብሎ የገመተው ምድረ ተመልካች

ሁሉእንደገና ሲያዩት ያደንቃሉ፤ ይለናል ዮሐንስ፡፡ ይህ አውሬ ምንድር ነው? የአውሬ ውስጠ ምስጢር ምንድን ነው? መልአኩ ለዮሐንስ ምን ብሎ እንዳለ ቀጥለን እንመልከት፡-

ዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 17 ከቁ. 9-11 ምስጢሩን እንደሚከተለው ይገልጻል፡- «ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች ናቸው፤ ሰባት ነገሥታት ደግሞ ናቸው፡፡ አምስቱ ወድቋል አንዱም አለ፣ የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል፡፡ የነበረውና የሌለው አውሬ ደግሞ ስምንተኛ ነው፡፡ ከሰባቱ አንዱ ነው፣ ወደ ጥፋትም ሄዷል፡፡» እንግዲህ ከአውሬው ምስጢር አንዱን ተመልከተናል፡፡ የሰባት እራሶች ትርጉም አግኝተናል፡፡ ዮሐንስ ተራራዎች ናቸው ይለናል፡፡ ተራራ ከፍተኛ ደረጃን የሚያመለክት ነው፡፡ በሌላ አባባል ከፍተኛ የመንግሥታት መዋቅር መስተዳድር መግለጫ ናቸው፡፡ ይህ አንዱ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ መልአኩ ሰባቱ ራሶች ሰባት ነገሥታት ደግሞ ናቸው ይለናል፡፡ ሰባቱን ተራራዎች ወይም ሰባቱን የመንግሥት መዋቅሮች የሚመራ መሪ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለእያንዳንዱ ተራራ ወይም ለእያንዳንዱ የመንግሥት መዋቅር አንድ መሪ ወይም እንደጥንቱ አንድ ንጉሥ ስለሚያስፈልግ ሰባቱ ራሶች የሰባት ነገሥታት ምሳሌ ናቸው ብሎም መልአኩ ተርጉሞልናል፡፡

ልብ በሉ ይህ አውሬ አንድ ብቻ ነው፡፡ ቀደም ብለን እንደአልነው ከሰባቱ ራሶች በቅደም ተከተል አንድ አንዱን እራስ ብቻ እያሳየ ወይም በየጊዜው አንድ አንድ ልዕለ ኃያል መንግሥት እያስነሳ የሚያስገዛ ወይም የሚያስተዳድር አውሬ



ነው፡፡ ዮሐንስ ይህንን ራዕይ ያይ በነበረበት ዘመን ይህ አውሬ ከሰባቱ ራሶች በአምስቱ ዓለምን ካስተዳደረ በኋላ እነዚያ አምስቱ የመስተዳድር ዘመናቸውን እንደፈፀሙ መልአኩ እንዲህ ሲል ገልጿል፡፡ «ሰባቱ ራሶች ሰባት ነገሥታት ናቸው፡፡ አምስቱ ወድቋል፣ አንዱም አለ፣ የቀረውም ገና አልመጣም» ራዕይ 17 ቁጥር 10፡፡ ነገሩ ግልፅ ነው፣ እነዚህ ዓለምን ገዝተው የወደቁት ልዕለ ኃያላን ነገሥታት እነማን ነበሩ? ከመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክም ሆነ ከሕብረተሰብ ታሪክ አንፃር ነገሮች ከተቃኙ የዓለም ልዕለ ኃያል ቀዳሚ የሆነችው ግብፅ ናት፡፡ ከግብፅ ቀጥሎ አሦሪያ፣ ባቢሎን፣ ሜዶፋሪስ፣ እና ግሪክ ነበሩ፡፡ እነዚህ አምስቱ ተራራዎች ወይም ልዕለ ኃያላን መንግሥታት ዮሐንስ ይህንን ራዕይ ሲያይ በነበረበት ዘመን ወድቋል፡፡ በዮሐንስ ዘመን የነበረው ልዕለ ኃያል መንግሥት የሮም መንግሥት ነበር፡፡ አንዱም አለ የተባለው ስለዚህ ነው፡፡ የሮም መንግሥት ከወደቀ በኋላ ሌላ ፀሐይ የማትጠልቅበት ልዕለ ኃያል መንግሥት ልክ እንደመልአኩ ቃል መጥቷል፡፡ ይህ 7ኛው ተራራ ወይም ልዕለ ኃያል መንግሥት መሆኑ ነው፡፡ ይህንን ሰባተኛውን የዓለም ልዕለ ኃያል መንግሥትን ማሕበሩ /Anglo-American's/ የእንግሊዝና የአሜሪካን ጥምር ወይም የመደጋገፍ አገዛዝ በማለት ይገልጻል፡፡ ይህ አውሬ እሱነቱን እየደበቀ በራሶቹ እንደራሴነት ዓለምን በተከታታይ ገዝቶ የመጨረሻ ራስ በሆነ ወኪሉ ላይ ደርሷል፡፡ አሁን ግዛቱን ለመቀጠል ከፈለገ ይህ አውሬ በእነዚህ ግዛታቸውን በጨረሱት ራሶች እንደገና መጠቀም አለበት፡፡ ምክንያቱም አውሬው ያለው 7 ራሶች ብቻ ናቸውና፡፡ እነርሱኑ እያፈራረቀ እንደገና እንዲጠቀምባቸው የግድ ይሆናል፡፡ ከ7ቱ

ራሶች ከነበሩት መካከል አንዱን መርጦ እንደገና መሾም መቻል አለበት። ለዚህም ነው መልአኩ በራዕይ 17 ቁጥር 11 ላይ «የነበረው የሌለውም አውሬ ራሱ ደግሞ ስምንተኛው ነው» ያለው፡- በአንድ ወቅት ይገዛ ነበር፣ ግዛቱን አቋርጦ ከቆየ በኋላ እንደገና ደግሞ ወደ ሥልጣኑ ተመለሰ ማለት ነው።

ሰባት ራሶች ከነበሩቱ አንዱ አሁን ተመልሶ 8ኛ የዓለም ገዥ ሆኖ ተሹሟል ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው። በማሕበሩ ትርጉም ይህ 8ኛው የሊግ ኦቭኔሽን ማለት የተባበሩት መንግሥታት ቃል ኪዳን ወይም የአሁኑ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ነው ብሎ ያምናል። እንደዮሐንስ አባባል «ወደ ጥፋትም ይሄዳል» ማለት ምን ማለት ነው? ግዛቱ ወይም ሥልጣኑ ይቋረጣል ወይም በሌላ ይተካል ማለት ነው። የስምንተኛው አገዛዝ ወቅት ከአበቃ አውሬው ከተቀሩት ቀንዶች አንዱን ባለተራ መርጦ 9ኛው ተራራ ወይም ገዥ ሊያደርገው ይችላል። ግን አውሬው እራሱ ማን ወይም ምንድን ነው? የአውሬውን የአገዛዝ ሥርዓትን እንጂ የአውሬውን ማንነት መልአኩ በግልፅ አላስቀመጠም። ምስጢር የሆነ የታላቂቱ ባቢሎንም ስም እስከአሁን አልገለፀልንም።

## አሥሩ ቀንዶች

ዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 12-13 እንዲህ ይነበባል፡- «ያየሃቸውም አሥሩ ቀንዶች ገና መንግሥታትን ያልተቀበሉ አሥር ነገሥታት ናቸው። ዳሩ ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት እንደ ነገሥታት ሥልጣን ይቀበላሉ። እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው፣ ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬ ይሰጣሉ።»



ይህ እንግዲህ ከሰባት ራሶች ቀጥሎ በአውሬው ላይ ስለበቀሉት አሥሩ ቀንዶች መልአኩ የሰጠው ትርጉም ነው። እነዚህ አሥር ቀንዶች በየተራ ዘመናቸው አውሬ ላስነሳቸው ራሶች ገባር የሆኑ /Vassal Tributary King/ ጃንጥላ መንግሥታት ናቸው። እነዚህ ከራስ ጋር እየተባበሩ በአንድነት ሆነው አውሬውን ያገለግላሉ። ይህ አውሬው ምንድን ነው? የዚህ ዓለም የአገዛዝ ሥርዓት ነው? የይሖዋ ምስክሮች አውሬው እራሱ ሰይጣን ዲያብሎስ ነው፣ እነዚህ የዓለም ልዕለ ኃያላኖች የነበሩና አሁንም ያሉት የሰይጣን ተወካዮች ናቸው ይላሉ። እነዚህ በየአገራቸው ያሉት ገባር ታናናሽ መንግሥታት ደግሞ በተግባር የተጣመሩ ስለሆነ በአርማጌዶን ጦርነት ሁሉም ይጠፋሉ ይላሉ።

እስከአሁን ያየነውና ያወቅነው በቀዩ አውሬ ላይ የበቀሉ ሰባት ራሶች የዓለም ልዕለ ኃያላት ነገሥታት እንደሆኑ፣ አሥሩ ቀንዶች (vassals tributary kings) በተዋረድ ያሉት እና ለልዕለ ኃያላን ገባር የሆኑ ታናናሽ መንግሥታት እንደሆኑም ተመልክተናል። ውሃዎች ደግሞ በሕዝብ፣ በወገኖች፣ በብዙ ሰዎች፣ በቋንቋዎችም የሚመሰል እንደሆነም መልአኩ ተርጉሞልናል። ጋለሞታይቱ ወይም ታላቂቱ ባቢሎን ደግሞ ግዛትዋን የዘረጋችው በውሃዎች በተመሰሉ በሕዝብ፣ በነገድ፣ በጐሣዎችና በቋንቋዎች ላይ እንደሆነም ግልጽ ሆኗል። ባቢሎን የሚለው ስሟ መልአኩ ምስጢር ነው ስለአለ ትርጉሙ ምን እንደሆነ መልአኩ አልገለፀም። እንዲሁም በላዩ ላይ 7 ራሶች፣ 10 ቀንዶች፣ እንዲሁም ታላቂቱ ጋለሞታይቱ ባቢሎንን የተሸከመው ወይም የበቀሉበት ቀዩ አውሬው ማንና ምን እንደሆነ መልአኩ አልገለፀም። መልአኩ ተግባራቸውን ብቻ

አብራርቶ ምንንና ማንን እንደሚወክሉ፣ የቀዩን አውሬውና የሴቲቱን ትርጉም ያልገለፀው ከአድራጐታቸው ተነስቶ ማንም በመገምገም ሊደርስበት ስለሚችል ቀላል ነው ብሎ በማሳብ ትቶት ይሆናል:: ስለዚህ ሴቲቱ ማንን እንደምትወክል፣ ቀዩ አውሬው ማንን እንደሚወክል የግድ ማሰብ አስፈላጊ ነው:: የይሖዋ ምስክሮች እስከአሁን እየተብራራ እንደመጣው ከሆነ ታላቂቷ ባቢሎን የዚህ ዓለም ሐሰተኞች ሃይማኖቶችን እንደምትወክል ገልጸዋል:: እንዲሁም ደግሞ ቀዩ አውሬው የሰይጣን ዲያቢሎስ ምሳሌ እንደሆነም አብራርቷል:: እውነት ነው? እንደዚህ መጽሐፍ ደራሲ አቋም ከሆነ በፍጹም እውነት አይደለም:: ፈሩን የሳተ ሊያስገኝ ከሚችል ጥቅም አንፃር የተቃኘ ትርጉም ነው:: ታዲያ እኛ ቀዩ አውሬውንና ታላቂቷ ባቢሎንን በማንና በምን እናስመስል? እስኪ ቀጥለን ስለዚሁ እንመልከት:-

<u>ከደራሲው አቋም አንፃር የአውሬው ትርጉም</u>

ከተፈጥሮ ሣይንስ አንፃር ይህ ቀይ አውሬ የጀርባ አከርካሪ አጥንት ካላቸው በሣይንስ ማማል ተብለው ከሚጠሩት እንስሳት ቤተሰብ ነው:: ሰው እራሱ ደግሞ በሣይንስ የዚሁ የማማልስ እንስሳት መደብ ክፍል መሆኑ ተረጋግጧል:: ይህ ከሣይንስ አንፃር ነው::

ከመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት አኳያም ካየን ሰው እንደ እንስሳ እራቁቱን የሚሄድ ፍጡር እንደነበርና ክፉና ደጉን የማያውቅ በደመነፍስ ይንቀሳቀስ እንደነበር ከሙሴ መጽሐፍ ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 25 እንረዳለን:: ነገር ግን ይህ አውሬ ከተንቀሳቀሰ በራሱ ሂደት ሁኔታዎችን መረዳትና ማወቅ የሚችል ኃይል በውስጡ አምቆ የያዘ ነበር:: ስለሆነም ከሚያደርገው



እንቅስቃሴ ነገሮችን እየተለማመደ እና እያወቀ ሄዶ ማሕበራዊ ሥርዓትንና ባሕልን ፈጥሮ ሰው ለመሆን የቻለ ነው:: ስለዚህ ይህ አውሬ ማንን የሚወክል ይመስላችኋል? በዚህ ዓለም ላይ ጥበበኛ፣ አዋቂ፣ ሁሉን አጠቃሎ ማዘዝ የሚችል አውሬ ወይም የጀርባ አከርካሪ አጥንት ካላቸው እንስሳት ከሰው የበለጠ የለም:: ስለሆነም ይህ አውሬ የራሱ የሰው ዘር ምሳሌ ነው:: ይህ አወሬ ለሌሎች ማለት ለሰባት ራሶች ሥልጣን ሰጥቶ ዓለምን ሲያስተዳድር ተመልክተናል:: እነዚህ ሰባት ራሶች በዚህ ዓለማችን በየወቅቱ የተቋቋሙና ዓለምን የገዙት 7 ልዕለ ኃያላን መንግሥታት እንደነበሩና እንደሆኑም ተመልክተናል:: ሌላው ቀርቶ የአስተዳደር መዋቅሩን እስከታች በመዘርጋት በአሥር ቀንዶች የተመሰሉ 10 ትናናሽ ገባር ነገሥታትን ፈጥሮ እያስተዳደረ ነው:: ስለዚህ ይህንን አውሬ ከሰው ዘር ሌላ በምድራችን ማንም ሌላ ፍጡር ሊወክል እንደማይችል እንመለከታለን:: ስለሆነም ቀዩ አውሬው የሰው ዘር ምሳሌ ነው::

<u>ሴቷስ</u>

ሴቷ ደግሞ የሰው ዘር የማስተዳደር ብልሃት ወይም ጥበብ ምሳሌ ናት:: ሴትዋ በብዙ ውሃዎች፣ በአሕዛብና በቋንቋዎች ሁሉ ላይ ተቀምጣለች በሌላ አባባል የሰው ዘር አካባቢውን የማስተዳደር ብልሃት ወይም ጥበብ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት በጐሣዎች በብዙ ሰዎች፣ በሕዝብ፣ በአሕዛብና በቋንቋዎች ሁሉ ላይ የሚገለፅ ነው:: ይህን የአስተዳደር ብልሃትና ጥበብ የሰው ዘር ሁሉ እውቀት መተግበር እንደአለበት የሚጠቁመን ነው:: ስለዚህ ሴቲቱ የሰው ዘር የፈጠረውና ሁሉም እንደ ሕግ ተቀብሎ የሚተዳደርበት የአሠራር ባሕል ምሳሌ

ናት፡፡ በዚህ ዓለም ያሉት የሰው ዘሮች ሁሉ በያሉበት የአሠራርና የአንዋኖር ሕግ፣ ባሕል፣ ልማድ የሌላቸው የሉም፡፡ እንደዚህ ያለው የአሠራር ባህልና ልምድ በሁሉ የሰው ዘሮች የሚተገበርና የሚገለፅም ነው፡፡ ስለሆነም በልዩ ልዩ መልኩ በሕዝብ ላይ የሚታየው የአኗኗር ባሕል በታላቂቱ ባቢሎን ሴት ይመስላል፡፡ እንዲህ ያለው የአሠራር ባሕል በሰው ዘሮች ሁሉ ላይ ነግሷል፡፡

ከዮሐንስ ዘመን በፊት በጋርዮሽ ወቅት የአኗኗር ባሕል ወይም ማሕበራዊ የአኗኗር ዘዴዎች እንደነበሩ ከሕዝብ ታሪክ እንረዳለን፡፡ እንዲሁም በባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት ማሕበሩም የአሠራር፣ የአበላል፣ የመተባበር፣ በጠቅላላው የተመሠረተ ሥርዓት ነበራቸው፣ ሕግም ነበራቸው፡፡

ዮሐንስ በነበረበት ዘመን ማለት ከ2000 ዘመን በፊት የአስተዳደር ሥርዓት ፊውዳላዊ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ ይህ የፊውዳል ሥርዓት ከጋርዮሽና ከባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት እጅጉን እድገት ያሳየና የተሻለ ነበር፡፡ አውሬም ቢሆን በዚህ ዓይነቱ የአስተዳደርና የአሠራር ባሕል ተጠቅሞ ሰባቱ ራሶችን እና አሥሩ ቀንዶችን ያስተዳድራል፡፡ አሁን በዚህ የአስተዳደር ብልሃትና ጥበብ፣ ከጥንት ጀምሮ በማሻሻል እየተሠራበት ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ላይ በ7ኛው የዓለም ልዕለ ኃያል መንግሥት ዘመን እንዲህ ያለው የጥንቱ አሠራር መቅረት እንደአለበት ስለታመነ፣ ይህንን የአሠራር ብልሃት ጨርሶውኑ እንደሚያስወግዱት መልአኩ ለዮሐንስ ወንጌላዊ አስረዳው፡፡ ይህ በሴት የተመሰለው የአሰራር፣ የአስተዳደር ጥበብና ብልሃት በአውሬ በጉፊቃድ፣ በአሥር ቀንዶች በተመሰሉት በምድር ነገሥታት ሁሉ ተባባሪነት እንዲጠፋ ተወስኗል፤ ወይም



ጠፍተው በሌላ አዲስ የአሰራር ብልሃት እንደሚተካ የሚገልፅ ትንቢት ነው፡፡ ይህ አዲሱ አሠራር የዘመናችን ተራማጁ ሊብራል ዲሞክራሲ አሠራር ነው፡፡ ሕዝብ በዚያ በጥንቱ የአስተዳደር ብልሃትና ጥበብ ተሰቃይተዋል፡፡ ግልፅነትና መብት የለም የግለሰብ ነፃነት አይኖርም፣ አልነበረምም፡፡ ስለዚህ በሲብራል ዲሞክራሲ የጥንቱ አሣሪ እና ጉታች ኋላቀር አሠራር እንደሚወገድ የሚያመላክት ትንቢት ነው፡፡ የሴቲቱ በአሥሩ ቀንዶች መጣልና ተቃጥሎ መጥፋት የዲሞክራሲ መስፍንን አመልካች ነው፡፡ ሴቲቷ በእጅዋ የያዘችው ፅዋ ብልሹ ኢዲሞክራሲ አሠራርን ያመለክታል፡፡ በዚህ ፍትሕ አልባኢዲሞክራሲ አሠራር የዮሐንስ ወንድሞች እና የክርስቶስ ተከታዮች ጭምር እንደተሰቃዩም መልአኩ ገልጿል፡፡

ይህንን የጥንቱን ግልፅነት አልባ፣ ዲሞክራሲ አልባ፣ ጨቋኝ የአሠራር ጥበብ ተብዬን 7ኛው ራስ ወይም 7ኛው የዓለም ልዕለ ኃያል መንግሥት በብዙ መልኩ ለውጦታል፡፡ በአገሩ ብቻ ሣይሆን በየዓለማቱ የዲሞክራሲን የአሠራር ዘመንና ግልፅነትን ለማስፈን እየተጣራ ነው፡፡ ከሞላ ጎደል ሴቲቷ ተጥላለች፡፡ ከሰባተኛው እራስ አንዱ እንደገና ተራ ደርሶት 8ኛ የዓለም አገዛዝ ሥርዓት ዘርጊ፣ ወይም አመራር ሰጭ እንዲሆን የተመሠረተ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም በ7ኛው ራስ የተጀመረው ሴቲቱን የማጥፋት ዘመቻን በማፋፋምና በመደገፍም ላይ ነው፡፡ በመጨረሻው የ7ኛው ራስ የአገዛዝ ፍጻሜ በሚሆንበት ወቅት ላይ ስንደርስ ይህ ከሰባቱ አንዱ የነበረና እንደገና እንደ 8ኛ ተቆጥሮ በተባበሩት መንግሥታት ስም የተመሠረተው ድርጅት እድገቱን ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋግሮት ዓለም አቀፉ ትሥሥርን

በይበልጥ ያጠናክር ይሆናል:: በሁሉ መልኩ የዓለም የአሠራር ዘይቤ ወይም ጥበብ በየጊዜው እያደር እያደገ በመጣው ቴክኖሎጂ እና ኮሙኒኬሽን የተነሣ ይህች ዓለማችን በአንድ ራስ ብቻ ወይም በአንድ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ሥር ብቻ የሚተዳደርበት ወቅት ሊፈጠር ይችል ይሆናል::

በዚህ መልኩ በዳንኤል ምዕራፍ 7 ቁጥር 27 ላይ የተጻፈው ትንቢት እውን ሊሆን ይችል ይሆናል ተብሎም ይታሰባል:: በዚያም ሆነ በዚህ ይህች ታላቂቱ ጋለሞታ ሴት የሰውን መበት በሚጋፋ ብልሹ አስተዳደር ወይም አሠራር ምሳሌ ናት ብለን መደምደሙ ይሻላል:: ከግል ጥቅም አንፃር ተቃራኒ ወይም አንድ አመለካከት ስለሌላቸው ብቻ በሃይማኖት ድርጅቶች ስለምትመስል ሃይማኖቶች ሁሉ ከእኛ ድርጅት በስተቀር ጠፊ ናቸው ማለት ውሸት ነው ከዚህ በላይ ስለቀዩ አውሬውና ስለ ጋለሞታየቱ ከተገለፀልን' አንፃር በመገምገም የራሱን አስተየየት የሰጠው የመጽሐፉ ደራሲ ነው::

ሰባት ራሶች ወይም ሰባት የዓለማችን ልዕለ ኃያላን መንግሥታት በዚህ ዓለማችን መታየታቸውን ተመልክተናል:: እነዚህ ሰባት የታሪክ ልዕለ ኃያላን መንግሥታትን ቀዩ አውሬው ወይም የሰው ዘር እንዴት አድርጐ እያንዳንዳቸውን ከየት እስከ የት ባሉት ጊዜያት ሥልጣን ላይ እንዳወጣቸው እንመልከት:-



| <u>የዓለም ኃያላን የገዥ መደቦች ስም</u> | | <u>የገዙበት ዘመን</u> |
|---|---|---|
| 1ኛ. ግብፅ | ከልደት በፊት | ከ1600-740 ዓመት |
| 2ኛ. አሶሪያ | ከልደት በፊት | ከ740-625 ዓመት |
| 3ኛ. ባቢሎን | ከልደት በፊት | ከ625-539 ዓመት |
| 4ኛ. ሜዳፋርስ | ከልደት በፊት | ከ539-332 ዓመት |
| 5ኛ. ግሪክ | ከልደት በፊት | ከ332-63 ዓመት |
| 6ኛ. የሮም መንግሥት | ከልደት በፊት | ከ63 - 1763 ዓመት |
| 7ኛ. ታላቋ ብሪታኒያ | ከልደት በኋላ | ከ1763 - 1920 ዓ.ም. |
| 8ኛ. የተባበሩት መንግሥታት | ከልደት በኋላ | ከ1920 - 1975 ዓ.ም. |

ይህ ከዚህ በላይ የዓለም ልዕለ ኃያላን የቅደም ተከተል አገዛዝ መግለጫ እ.ኤ.አ. በ1966 ዓ.ም. ማሕበሩ ጽፎ ያወጣው ነው:: ከዚህ በላይ በተገለፀው መሠረት የመንግሥታቱ የአገዛዝ ዘመን እስከ 1975 ዓ.ም. ብቻ እንደሚቆይና ከዚያ በኋላ እንደሚቋረጥም ነበር የለበኩት::

ከዚህም በላይ ታላቂቱ ጋለሞታይቱን እነዚያ ከሥሩ ታናናሽ ገባር መንግሥታት በሚሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት እንዴት አድርገው ጥሉአት እንደሚያጠፉአት የሚያሣይ ምስል ቀርቧል:: መጪው ጊዜ ብሩሃን ነው:: መጪው ጊዜ ተስፋ ነው:: ብልሹ አሠራር ቀርቶ የሰው ልጅ እጅግ ወደተሻሻለው ሕይወትና ማሕበራዊ ኑሮ የሚሸጋገሩበት ወቅት እየመጣ ነው::

ነገር ግን ከዚህ ከተፈጥሮ ሁኔታ ውጭ በሐሳብ እየቃዡ ወይም ደግሞ በርዕዮት ዓለምም ሆነ ከልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች የተነሣ ከማይጣጣሙት ተቋም አንፃር ትርጉም መስጠት

እውነታን አያመለክትም:: እውነት ቢሆን ኖሮ በ1975 ዓ.ም. እና ከዚያም በፊት ባደረጉት ትንቢቶች ሐቁ ይገለጥ ነበር::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የዓለም ታላላቅ ልዕለ ኃያላን ነገሥታት በየተነሡበት ተራ ዘመናቸው የየራሳቸውን በ10 ቀንዶች የተመሰሉ ተራ ገባር ነገሥታትን ፈጥረዋል:: እነዚህ ታናናሽ ነገሥታት በየጊዜው ለተነሱት ለዓለም ልዕለ ኃያላን የሚገብሩ /Tributary kings/ ገባር ነገሥታት ናቸው:: ሥልጣናቸውም የሚመነጨው ከአውሬው እንደሆነ መልአኩ ገልጸዋል::

ለአውሬው የማይገብሩ ከሆነ ግን አውሬው ከሰባቱ እራሶች አንደየዘመናቸው ወቅት በአንዱ እራስ ተጠቅሞ እንደሚያጠፋቸው ወይም ከሥልጣን እንደሚያባርራቸው ግልፅ ነው::

ይሁን እንጅ እያንዳንዱ የዓለም መሪ በአንድ ዲያብሎስ ይመራል የሚሉት ስብከታቸው ስሕተት ነው:: ፈቃድ በምድር ትሁን መጽሐፍ ገጽ 221 ተመልከቱ::





## ምዕራፍ 10

## በማህበሩ የሽብር ስብከት ያልተሸበሩም ነበሩ

በ1975 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ይሆናል የሚለው አዋጅ ከወጣ በኋላ ሽር ጉድ በዛ:: ይህንን መንታ ትርጉም ባዘለው ጽሑፋቸው የጻፉትን በይበልጥ በየጉባኤ እየዞሩ በቃላት ለማብራራት፣ ጥያቄዎችን ለመመለስና የጊዜ ሁኔታ እንዴት ቾል ማለት እንደማይገባ ድስኩር ማድረግ ጀመሩ:: የዞን፣ የክልልና የጉባኤዎች ዞሮ ጎብኚዎች የሚባሉ ሹማምንቶቻቸው በዓለም ላይ ተሰማሩ:: በእነዚህ ዞሮ ጐብኚ ሹማምንቶች አማካኝነት «የቁርጡ ቀን መጣ፣ እራሳችሁን አድኑ፣ በኖህ መርከብ በምትመሰለው ወደ ደህንነት መርከብ ማለት ወደ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት ተሰብሰባችሁ በተግባር የመዳን ዋስትናን ምናልባት ካገኛችሁ ትጉ::» በተባሉት ርእሶች ተደሰኮረ:: ነባር የሆኑ አባላት ጊዜ ስለቀረበ ለዓለማዊ ድርጅት በወፍራም ደመወዝ ከማገልገል የአምላክን ድርጅት በሚሰጠን መመሪያ መሠረት በነፃ እናገልግል እየተባለ ከሥራ መሰናበት ተዘወተረ:: ሀብታም ከሆኑ ለ8 ዓመታት የሚበቃውን ገንዘብ ብቻ ከያዙ በኋላ የተረፈውን ድርጅቱ እንዲሠራበት፣ እራሳቸውም ድርጅቱ በሚመድባቸው ቦታ በነፃ እንዲያገለግሉ ብዙዎች ወስነው ተሰማሩ:: ሞላው ዓለም እንዲጠፋ እነርሱ ግን እንዲድኑ የዘወትር ፀሎት ሆነ:: ኔ

በየአገሩ እየዞረ በዚህ መልኩ ከሚሰብከው አንዱ አማኑኤል ፖታራኪ የሚባል የግሪክ ተወላጅ ሰው ነበር:: ይህ ግለሰብ ይህንኑ ቅስቀሳና ስብከት ለማሰማት ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ ኃላፊ ስለነበርኩ ኤርፖርት ሔጄ ተቀበልኩት::

ስለሥራው ጉዳይ ብዙ ከተነጋገርን በኋላ እንደዚህ አለኝ:- «አንተ በዚህ ድርጅት ውስጥ ለብዙ ዓመታት የቆየህ ወንድም ነህ:: አሁን ሁላችን እንደምናውቀው የዓለም መጨረሻው መከሰቻ በጣት የሚቆጠር ዘመን ነው የቀረው፣ እንዲሁ ከእጆች ጣቶች ያነሰ በቁጥር 8 ዓመት ነው ብለን እናስባለን:: እንዲሁም ከዚህ ከተባለው 8 ዓመት ወዲህ እንኳን ምን እንደሚፈጸም የሚያውቀው ይሖዋ ነው:: ምን ይመስልሃል? ማሕበሩ ትንሽ ቢሮ ተከራይቶልህ በይበልጥ ሙሉ ጊዜህን በዚህ በአገልግሎት ሥራ ላይ ብታውል?» አለኝ::

ያኔ በብዙ መልኩ የዚህ ድርጅት እውነተኝነት ጥርጣሬ እየበላኝ ወይም እየገዘገዘኝና ሁሉንም ከጥርጣሬ አንፃር ጭምር እከታተል ስለነበር እና በዚህ በስብከታቸው መሠረት ዓለም ምንም እንደማትሆን የጠነከረ ሐሳብ ስለነበረኝ ምክንያት ደርድሬ ለዚህ ስብከት ሙሉ ጊዜዬን እንዳሳልፍ የቀረበልኝ ሃሳብ አጠፍኩ:: በዚሁ በእምነቴ መላላት ምክንያት የተነሣ እና ነገ ዓለም በ8 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደማትጠፋ ስለአመንኩ የቤት ግንባታ ይገፔ ወይም ጀምሬ ነበር:: በዚሁ በቤት ግንባታ ሥራ ምክንያት ለሌሎች በጣም መጥፎ አርአያ ሆነሃል፣ ነገ ማዘጋጃ ቤት የሚያፈርሰውን ቤት ወንድም አበበ እያደሰ ነው፣ እየተባለም መተረቻ ሆኜ ነበር:: አንዳንዶቹም እየቀረቡኝ እስኪ አሁን ወንድም ምን አለፋህ? ነገ ነፃ ልንሆን? እያሉ ይሉኝ ነበር:: እኔም ጊዜ ከቀረበና አርማጌዶን ከመጣ ምንም ካላጠፋሁ ከቤቴ ጋር ቤተሰቦቼ ጭምር እድናለሁ ከማለት በስተቀር የከረረ ክርክር ውስጥ ከእነርሱ ጋር መግባት አልፈለኩም ነበር:: ምንም እንኳን በአንድ አንድ የድርጅቱ ስሕተቶች የተደናበርኩና ከፍተኛ



ጥርጣሬ ያደረብኝ የነበርኩ ቢሆንም ለድርጅቱ የነበረኝ አክብሮት፣ የእግዚአብሔር የሚታየው ምድራዊ ድርጅት ነው የሚለው ጨርሶ ከጭንቅላቴ አልወጣም ነበር:: አጥፊዎቹ በድርጅቱ ውሰጥ ያሉት አንድ አንድ ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ድርጅቱ ግን የአምላክ ድርጅት ሊሆን ይችላል፣ ፈራጅ እግዚአብሔር ስለሆነ እስኪ ዝም ብዬ ልቆይ የሚል አመለካከት ነበረኝ:: በአንድ አንድ ነገሮች ተላስቼም ሆነ ሣላምንበት ቀርቼ እንደሚገባ ዲሲፒሊናቸውን እንደድሮው ጠብቄ መራመድ ባልችልም፣ በዚሁ ምክንያት ከይሖዋ ምስክሮች አባልነት ተወግደሃል ቢባልም፣ በአብዛኛው ባሕርዬ የይሖዋ ምስክሮችን አቋም እንዳንፀባረቀ ለብዙ ዓመታት ቄይቼአለሁ:: እነርሱ ከዳር እስከዳር አኩርፈውኝ ሳለ እንኳን በእነርሱ ላይ የሚሰነዘረውን መጥፎ አመለካከት ባለኝ አቅም እከላከል ነበር:: በተለይም በ1973 ዓ.ም. እ.ኢ.አ. የቀበሌ ሊቀመንበር በነበርኩ ጊዜ እና ቀደም ተብሎም በሰራተኛ ማሕበር ሊቀመንበርነትና በመኢሠማ ምክር ቤት በአባልነት እሠራ በነበርኩበት ወቅት ሁሉ በእኔ ኃላፊነት መስመር በኩል በእነርሱ ላይ እንዲወሰድ የታቀደውን እርምጃ ሁሉ በዘዴ ተከላክዬላቸዋለሁ:: ይህን ያደረኩት የእነርሱ ቤሳ ቤስቲን ለመልቀም ሣይሆን ወይም ወደማህበራቸው እንደገና ለመመለስ ሣይሆን ምንም ባላደረጉና ባላወቁት፣ በእምነት የተጃጃሉ ስለሆኑ፣ የሚያደርጉትን ነገሮች ሁሉ ስሕተትም ቢሆን በቅንነት ስለሚያደርጉት፣ በደርግ ጡንቻ ማስነካቱ ትክክል ነው ብዬ ስላላመንኩ ብቻ ነው:: አሁንም ቢሆን በእነዚህ የተጃጃሉት በጐች ላይ በፍጹም የግል ጥላቻ የለኝም::

ነገር ግን 34 ዓመት ካገለገልኩት መሥሪያ ቤት ለቅቄ አንድ አንድ የራሴን የኑሮ እንቅስቃሴ ላለፉት 11 ዓመታት እመራ ስለነበር፣ የተሻለ ጊዜም ስለነበረኝና ስላለኝም አንድ አንድ የይሖዋ ምስክሮችን ጽሑፍ ማንበብ ጀመርኩ:: አሁን ባለኝ የአእምሮ ግንዛቤና ያኔ ድሮ በነበረኝ ግንዛቤ መካከል ልዩነቱ እየተከሰተልኝ ስለመጣ በይበልጥ ማንበብ ጀመርኩ፣ በይበልጥ ሣነብ በይበልጥ ፍጹም ተሳስቼ እንደነበር ተገነዘብኩ:: ስለዚህ ማንንም ለመጉዳት ወይም ለመጥቀም ወይም በምቀኝነት ሣይሆን የስሕተቱ ምንጭ እነማን እንደሆኑም ስለገባኝ ይኽንኑ አቋሜን ለመግለፅ በመጽሐፍ መልኩ ማቅረብ ፈለኩ፤ ተሞኝቼ እንደነበርም ገባኝ::

<u>ያልተሞኙት እነማን እንደነበሩ</u>

የዚህ ምዕራፍ ርእስ ያልተሞኙም ነበሩ ይላል:: እነዚህ በዚህ ድርጅት እየኖሩ ነገር ግን ያልተሞኙ እነማን ናቸው? እነዚህ ያልተሞኙት ከኤርትራ የመጡ ጥቂት ወንድሞች ናቸው:: እነዚህ ከኤርትራ ከመጡት መካከል ጥቂት ወንድሞች ድርጅቱን ለፖለቲካ አቋማቸው ሊጠቀሙበት ስለፈለጉ ወይም ድርጅቱን ሽፋን ለማድረግ ወደ ድርጅቱ የተጠጉ ነበሩ:: እነዚህ እንደመሐል አገር እና የደቡብ ወንድሞች በማሕበሩ ስብከት ርእዮት ያልተጃጃሉ፣ ምላጮች ነበሩ:: ትግላቸውም በድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ አመራር ከያዙ በኋላ ለዓለማቸው ድርጅቱን ሽፋን ለማድረግ የተነሱ ተንቀሳቃሾች ነበሩ:: ያኔ ነገሩ በደንብ ባይገባኝም አድራጐታቸው ይገርመኝ ነበር::

ምናልባት ለምን ተገረምክ? ከተባልኩ በማሕበሩ ሕግ መሠረት ከፈቀደ ወይም መስሎ ከታየው ለሐላፊነት



የሚመርጠው ማሕበሩ ነው እንጂ ግለሰብ እራሱን ለሹመት ለማቅረብ አይጣጣርም:: የፈለገውን ያህል እወቀት ኖሮት የተማረ ቢሆንም እንደዚህ የሚያደርግ ወይም እንደዚህ የሥልጣን ጉጉት የሚያሳይ ካለ ማሕበሩ ጨርሰው ከተራ አስፋፊ በላይ ሥልጣን አይሰጠውም:: በማሕበሩ እንደዚህ ያለ አድራጐት እንደ ትልቅ ነውር ይቆጠራል:: አሁን ግን እንደሚገባኝ ተንኮላቸው እንዳይነቀባቸው የመነሣሣት መንፈስ ያላቸውን ስለሚፈሩ ነው:: ለዚህም የሚያቀርቡትን ምክንያት የቴኦክራቲክ አመራር የተባለውን አለመከተል ነው:: የቴኦክራቲክ አመራር አለመቀበል የአምላክን ሕግ መጣስ ነው:: ምንም እንኳን ይህን ሕግ ማሕበሩ ለራሱ ጥቅም ማስጠበቂያ የደነገገና በጐቹን ያሳመነ ቢሆንም አምነው በተካተሉት አባላት ዘንድ ተቀባይነት ስለአገኘ ሕጉን አለማክበር እንደጠያፍ ነገር ይቆጠራል:: ማሕበሩ ኘሬዝዳንቱን እግዚአብሔር እንደሾመ፣ በኘ ሬዝዴንቱም መመሪያ መሠረት ሌሎች እስከ የበታች ሹማምንት እንደሚሾሙ ያምናል:: ከድርጅቱ ሰውን ለማባረርም ሆነ ለመሻር በመዋቅሩ አማካኝነት በኘሬዝዳንቱ ይፀድቃል:: ኘሬዝዳንቱን ግን የሚሾመውም ሆነ የሚሽረው ሰው ሣይሆን እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ያ እግዚአብሔር ግን ስንቱን ሞላጫ ኘሬዝዳንቶችን ሣያስወግድ እስከዛሬ አለ? ያም ሆነ ይህ እነዚያ የሰሜኑ ቆቆች ግን ስልጣን ላይ ወጥተው ድርጅቱን ለመቆጣጠር በፈለጉ ጊዜ እኔ ደንቃራ ሆንኩባቸው::

እኔ የማሕበሩ ተወካይ ሆኜ በቀጥታ ኒዮርክ ካለው ዋና ቢሮም ሆነ አፍሪካ ውስጥ ካለው ከናይሮቢ ቅርንጫፍ ጋር ግንኙነት የማድረግ መብት ስለነበረኝ የእኔን ከዚህ ቦታ ለመሻር

ከፍተኛ ትግል አደረጉ:: በቀጥታ በጉን ወደ ማሕበሩ ደብዳቤ ቢጽፉም ማሕበሩ መልሶ ወደ እኔው ይልከው ጀመር:: ሕጉን ማሳየትና ማስተማር የተገባ መሆኑን ዞሮ ጉብኚዎች ያሳስቡኝ ነበር:: ምክንያቱም እራስን አሳልፌው ከሰጡት ወንድሞች ይህ የማይጠበቅ ስለሆነ እንዴት የጉለመሱ ወንድሞች እንደዚህ ያደርጋሉ እየተባለ እንወቀስም ነበር:: ከማሕበሩ ጋር እንደዚህ አድርጉ ግንኙነት ለመፍጠር ሲታገሉ በሌላ በኩል ደግሞ በአገር ውስጥ ባለው ድርጅት ውስጥ ለመግባት ወይም የሐላፊነት ቦታ ለመያዝ እጅግ በጣም ጥረት ያደርጉ ነበር:: በተቻለ መጠን ምክንያት እየፈጠሩ ከአዝመራ የመጡት እንደነ ገብረየሱስ ያሉት ለምን ስልጣን አይሰጣቸውም? ለምን የመጠበቂያ ጽሑፍን አይተረጉምም? በማለት በቀጥታ ቁልፍ ቦታ የሆኑ አንድ አንድ የኃላፊነት ቦታዎችን ለመያዝ ዞሮ ጉብኛቸው በሆነው ወንድም ምናሴ በሚባለው ሰው አማካኝነት ጥያቄ አቀረቡልኝ:: ይህንን ጥያቄ ያቀረበልኝ ወንድም ምናሴ ከመቶ አለቃ እስጢፋኖስ ደምሳስ ጋር ሆነው ነበር:: ሁለቱም ኤርትራውያን ናቸው:: ላቀረቡልኝ ጥያቄ የቅን መልስ ባለመስጠቴ የመቶ አለቃው ተበሳጭቶ በመውደቅ ተንደፋድፈዋል:: ነገሩን ለማጣራት እንደሞከርኩት ከሆነ ንዴት በተሰማው ጊዜ ማለት በከፍተኛ ደረጃ ሲበሳጭ ንዴት አንቀጥቅጦት እንደሚጥለው ነው የተነገረኝ:: ይህ ዓይነቱ ጠባይ በፍጹም ከምስክሮቹ ዲሲፒሊን የራቀ፣ ለእምነት ሣይሆን ለልዩ ዓይነት ፍላጐት ለማስመሰል ይሠሩ እንደነበር ግልፅ ቢሆንም አጉል ጠባይ የተጠናወታቸው ስዶች ይመስሉኝ ነበር እንጂ የፖለቲካ ንክኪ ይኖራቸዋል ብዬ አልጠራጠርም ነበር:: ስለሆነም እኔ ሣይገባኝ ለዓላማቸው



እንቅፋት መሆኔን የተረዳሁት ከጊዜ በኋላ ነው:: ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ከማሕበሩ ዲሲፒሊናዊ ባሕርይ ውጭ ይንቀሳቀሱ የነበሩት::

1. ወንድም ገብረኢየሱስ የሚባል ከሚስቱ ጋር
2. ስብሃቱ የሚባል የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኛ የነበረ
3. ወልደ ማርያም ጊላማርያም የሚባል
4. አብረሃም የሚባል ከዚህ ዓለም በመኪና አደጋ በሞት የተለየ፣
5. ተክሌ የሚባል ግለሰቦች ነበሩ::

እነዚህ ከዚህ በላይ ከ1-5 የተጠቀሱት በቅርብ የማውቃቸው በድርጅቱም ኃላፊነት እያላቸው፣ ነገረ ግን የምስክሮቹ ጠባይ የራቃቸው ግለሰቦች ነበሩ:: ለምሳሌ ገብረኢየሱስ የተባለው ግለሰብ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚሠራ ሲሆን ሚስቱ ነርስ ነች:: በዚያን ጊዜ ኢትዮ ሲውዲሽ የሰሜን ክፍል እየተባለ ይጠራ በነበረው ክሊኒክ ውስጥ ታገለግል ነበር፤ ሁለት ልጆችን ወልደዋል:: ነገር ግን እንደወለደች ነርስ አዜብ ልጆችዋን በቤትዋ አታቆይም፣ በቤታቸው ልጆቻቸው አያድጉም:: ይህ ነገር ይገርመኝ ስለነበር ለምንድን ነው? ብዬ ብጠይቃቸው ለአገልግሎታችን ማለት ለስብከታችን ሥራ አገልግሎት እንቅፋት ስለሚሆኑብን ለዚሁ ሲረዱን ለተዘጋጁ ዘመዶቻችን እንዲያሳድጉ እያደረግን ነው:: ማንኛውንም ወጪ እኛ እንችላለን:: አሣዳጊ ወላጆቻችን የእኛ እምነት ተከታዮች ስለሆኑ ችግር የለም:: ከዚህም በላይ እኛም በጥብቅ እየተከታተልን የምንረዳቸው ይሆናል የሚል መልስ ሰጡኝ:: ሠራተኛ ለልጆች ተቀጥሮ

የምታገለግል ከሆነ ምስጢራቸው እንዳይጋለጥ ለመደበቅ እንደሆነ ደርግ ደርሶባቸው ሊይዛቸው ሲል ጠፍተው ከሔዱ በኋላ ነገሩ ግልፅ ሆነልኝ:: ደርግ ስለላ ሲያደርግ ደርሶባቸው ሊይዛቸው ሲል ባቻኔሎቻቸው አደጋ መኖሩን ተረድተው ጠፍተው ከአገር ወጡ:: ታህሣሥ 5 ቀን 1997 ዓ.ም. መኮንን ግዛቸው የሚባል ወንድም ከሌላ ወንድም ጋር ሊያፅናናኝ በመጣ ጊዜ ይኸንኑ አንስቼለት፣ ያኔ እርሱ ምፅዋ እንደነበር አስታውሶኝ በዚያን ጊዜ ይህ ገብረኢየሱስ የተባለው ወንድም ተብዬው በምፅዋ አድርጐ ወደሻቢያ ከገባ በኋላ ወደ ጀርመን መሻገሩን ገልጾልኛል:: ደርግም ከሚፈለጉ ጋር ፎቶግራፎቻቸውን በአደባባይ ለጥፎ ነበር:: በድርጅቱ ውስጥ ቁልፍ የሐላፊነት ቦታ ለመያዝ ይንሰፈሰፉ የነበረው ለዚህ ዓላማቸው መሆኑ ግልጽ ሆነልኝ::

## <u>የይሖዋ ምስክሮች ሥራ በኢትዮጵያ</u>

የይሖዋ ምስክሮች ሥራ በግልጽ እንዳይካሄድ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1949 ዓ.ም. ጀምሮ የታገደ ሆኖ ነበር:: ስለዚህ በትንንሽ ቡድኖች እየሆኑ መሰብሰብና በተናጥል እየዞሩ ላገኙት ሰው ስለእምነታቸው ከመመሥከር በስተቀር በግልጽ የሚሠራ ሥራ አልነበረም:: ሥራ ሁሉ የሚሠራ በየሐላፊዎችና እጅግ ምስጢር ጠባቂ በሆኑ ወንድሞች ቤት ነበር:: ከማሕበሩም ጋር ግንኙነት የሚደረገው በኮድ እና በልዩ ዘዴ በሚቀነባበር የደብዳቤ አፃፃፍ ነው:: ከተለመደው ኮድ ውጭ መጻጻፍ ክልክል ነው:: ለዚህም ግንኙነት የሚመደብ አንድ ሰው ብቻ ነው:: ደብዳቤ ለማህበሩ መድረሱን፣ የማሕበሩም ለጉባኤ መድረሱን ወይም አለመድረሱን በኮድ ነበር ክትትሉ:: በዚህ መልኩ ነጮች



ከሔዱና ካሣሁን ገብረጊዮርጊስ የሚባል ድርጅቱን ከተወው በኋላ ሬኢግልስን የሚባለውም ካናዳዊ በ1950 ዓ.ም. ያንክ ኢስቴዲየም በተደረገ የዓለም አቀፍ ስብሰባ እነ አብርሃም ከመቃብር መነሣታቸው እውን ባለመሆኑ ድርጅቱን ማገልገል ስለተወው፣ በአገሩ የተሻለ እኔው ሆኜ ስለተገኘሁ፣ ለዚሁ ሥራ መደቡኝ::

አሁን በዚሁ መልክ ግንኙነቱ ቀጥሎ ሣለ አንድ ጊዜ ልዩ ደብዳቤ ደረሰኝ:: ይህ ደብዳቤ ከተባለው የኮድ አፃፃፍ ውጭ የመጣ ነው:: ከማሕበሩም አሠራር መስመር ውጭ ነው:: አደጋ ወይም ክትትል መኖሩን ፍንጭ የሚሰጥም ሊሆን ስለሚችል ተቀብዬ ምንም መልስ ሣልሰጥ ዝም አልኩ:: ምናልባት ክትትል ካለ በዚህ ወይም በሌላ መልኩ አንድ ነገር ይከሰታል እያልኩ ስጠባበቅ ሳለሁ ከእለታት አንድ ቀን ወንድም ገብረኢየሱስ በመጀመያ ተራ ቁጥር ላይ የተፃፈ ወንድም መሆኑ ነው፣ እለኮድ ደርሶኝ የነበረውን ደብዳቤ ግልባጭ ይዞ ቤቴ መጣ:: ደብዳቤውንም አሳይቶኝ ይህ ደብዳቤ አልደረሰህም? አለኝ:: መልሴ አልደረሰኝም የሚል ነበር:: በደብዳቤው ላይ 571.45 የኢትዮጵያ ብር ለገብረኢየሱስ እንድከፍለው የሚያዝ ነው:: በዛሬ ምንዛሬ ሂሳብ ስሌት 2280 የኢትዮጵያ ብር ያላነሰ ይመስለኛል:: ኮድ ይዞ ስለአልመጣ፣ ከማሕበሩ የአሠራር ደንብ ውጭ የማሕበሩን ገንዘብ ወጪ እንዳደርግ የሚያዝም ስለነበር፣ ሉገብረኢየሱስም፣ ለማሕበሩም ጧንም መልስ ሣልሰጥ ዝም ብዬ ስለነበር ነው በቀጥታ ሊጠይቀኝ የመጣው:: በተቻለኝ መጠን ሁኔታውን እንዲያስረዳኝ ለማወጣጣት ሞከርኩ:: በደብዳቤው ላይ ከተገለፀው ሐሳብ በስተቀር የሰጠኝ ፍንጭ አልነበረም::

ለካ እዚያ የይሖዋ ምስክር ነኝ የሚለው አንዱ ሞላጫ ነጭ ከአንድ የሻቢያ አባል ጋር ተግባብቶ እዚያ ናይሮቢ በሽልንግ ወይም በኬኒያ ገንዘብ ከተከፈለው በኋላ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው አባላቸው ለአቶ ገብረኢየሱስ በኢትዮጵያ ብር 571.45 ተከፍሎ እንዲሠራበት የታሰበ ነበር:: ወይም ደግሞ በኢትዮጵያ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት ውስጥ ሠርገው እንደገቡ እዚያም ናይሮቢ ሠርገው ይገቡና ነጮችን የጠመዘዘ አንድ ሻቢያ ኖሮ ሊሆን ይችላል:: በኋላም ገንዘቡን እንዲከፍለው ሥርዓት ባለው መልኩ ስለአልመጣና እራሴንም ከጉዳት ለማዳን ምንም እንዳልደረሰኝ ገልጬ ዘጋሁት:: ከማሕበሩ አለመሆኑ የሚታወቀው ኮድን የተከተለ ሌላ የእርምት ደብዳቤ እንዲላክ አለመደረጉ ነው:: ብቻ እነዚህና የመሳሰሉት መቀላጠፍ፣ እነዚያ ነጮቹም እራሳቸው ከማህበሩ ሥርዓት ይልቅ የእነርሱን ሥርዓት አልበኝነት የመደገፍ አዝማሚያ ስለአሳዩኝ ሁኔታዎቹ አስጠሉኝ:: ይህንን ሕገወጥ ደብዳቤ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ አያይዤአለሁ::

## በ1968 ዓ.ም: የናይሮቢ ስብሰባ

በ1968 ዓ.ም. ዲስትሪክት ስብሰባ ስለነበር በዚህ ስብሰባ ላይ ለመገኘት ወደ ናይሮቢ ሄጄ ነበር:: በ4ኛው ተራ ቁጥር ስሙ አብርሃም ተብሎ የተጠቀሰው ኤርትራዊ ወንድም ከማሕበሩ ሥርዓት ውጭ ያው የተለመደ ጠባዩን ማንፀባረቅ ተያያዘው:: በደንቡ መሠረት የልዑካን መሪ የሆነ ሰው ከየት እንደመጣ፣ ከመጣበት አገር ስለ ሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል:: ይህንን አይነቱን ሪፖርት በተሰጠኝ መመሪያ መሠረት አድርጌያለሁ:: ሪፖርቱ ኤርትራንም በኢትዮጵያ ስም



የሚያጠቃልል ነበር:: ወንድም አብርሃም ግን ለብቻ ኤርትራ ለምን ሪፖርት አታቀርብም ብሉ ከተወሰኑ ነጮች ጋር ከተነጋገረ በኋላ ኤርትራን በተመለከተ ሪፖርት ተነስቶ አቀረበ:: ኤርትራ በካርታ ላይ የት እንደምትገኝ ሁሉ ዘረዘረ:: ማሕበሩ እራሱ እኛን በመሳሰሉት ሥርዓት ጠባቂዎች ላይ በይበልጥ ሕግ ሲጥል በጣም ንቃት ያላቸው ኤርትራውያኖችን ዝም እንደሚላቸው ነው የተረዳሁት፤ ስለዚህ አሁን ሁኔታው ማሕበሩ በሃይማኖትም ሆነ በአገር እያከፋፈሉ ቢመሩ ግድ የሌላቸውና ለዚህ ነገር ግፊትም እንደሚሰጠው ነው የሚገባኝ:: የእኔ ሪፖርት በኢትዮጵያ ስም ነበር የቀረበው:: ይህ ነበር አብርሃምን አበሳጭቶት መድረክ ላይ ያወጣውና ከኤርትራ መምጣቱንና ዘሩም ኤርትራዊ መሆኑን ያስለፈለፈው:: በዚህን ጊዜ አንድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቴክኒሽያን የነበረው ፀጋዬ የሚባል ሰው እርሱ ፖለቲከኛ ነው ብዬ አጋልጣለሁ ብሎ በተነሣ ጊዜ አስፈላጊ አለመሆኑን ገልጬለት ከእንካስላንታ፣ አንጃግራንጃ ውስጥ ከመግባት ዳንን:: ይህን ነገር እግዚአብሔር አይፈቅድም በሚሉት የደቡቡ በጐችና በሰሜኑ ቆቆች መካከል ምን ያህል የጮሌነትና የንቃት ልዩነት እንዳለ መገንዘቡ ቀላል ነው::

እንደነ ኃይሉ የምሩ፣ ወንድም አደራ፣ አሸቱ ምንዳ፣ ከአውራጐዳና፣ ሌሎችም የይሖዋ ምስክሮች የውይይት ክበብ ገብተን ፖለቲካን አንማርም፣ ሲያድባሬ ይውደም አንልም ብለው በደርግ በዘኔዎች በጥይት ተደብድበው በታማኝነት ሲሞቱ፣ የሰሜኑ አራዶች እምነት እና ብልጠት ግን ከዚህ የተለየ መሆኑን እናያለን:: እነዚህ የይሖዋ ምስክሮች ነን እያሉ ነገር ግን የድርጅቱ የሃይማኖት ትምህርት እስረኞች ያልሆኑት፣ በጐችን

አግልሰው ድርጅቱን በበላይነት እየተቆጣጠሩ ነው:: አሁን እንደዚህ ይህን ታሪክ የፃፍኩት የነበረውን ሁነታ ለመግለፅ ያህል ነው እንጂ አገራችሁን አትውደዱ፣ በፖለቲካ አትካፈሉ፣ የዚህ ዓለም ፖለቲካ የሰይጣን ኘሮፖጋንዳ መግለጫ ነው:: ስለዚህ እኛ የይሖዋ ምስክሮች ፖለቲካንም ሆነ ፖለቲከኞችን እንደግፍም:: የእኛ አቋም የአምላክን መንግሥትና የአምላክ ምድራዊ ድርጅትን መደገፍ ብቻ ነው የሚለውን የይሖዋ ምስክሮችን አቋም ለማንፀባረቅ ፈልጌና አምኜም አለመሆኑን እገልፃለሁ::

<u>ሌላ የኤርትራውያኖች አለመጻጻል ምሳሌ</u>

አንድ ኢትዮ ግሪክ ኮቶን ኘሮሴስ የሚባል ኩባንያ የሚሠራ ወንድም ነበር:: ይህ ወንድም ከማሕበሩ የግብረገብ ሥርዓት ውጭ ሲሠራ መታየቱን የሚያመላክት ሪፖርት ደረሰኝ:: በማሕበሩ ደንብ አንድ ወንድም፣ በጣም አስጠያፊ ሕገ ወጥ ሥራ ሲሠራ ሌላ ወንድም ካየው፣ ስለዚሁ ወንድም ለጉባኤው ሐላፊ ሪፖርት ማድረጉ የተለመደና ለድረጅቱም ተቆርቋሪነትን ስለሚያሳይ የሚደገፍ ነው:: ስለዚህ ምስክር ባይኖርም የጉባኤ ሐላፊዎች ከ3 ያላነሱ ሆነው ጠርተው ያነጋግሩታል:: ካላመነ እንደሁኔታው በጥበቃ ላይ ሆኖ ይመከራል፣ ይበረታታል፣ እንደነዚህ ያሉት አጉል አመልካች ጣቶች ወደ አንተ እየቀሰሩ ስለሆነ ተጠንቀቅ ተብሎ በዓይነ ቁራኛ ይጠበቃል::

ክትትሉ የማይቀር ይሆናል:: ያመነው ከሆነ ግን ለተወሰነ ጊዜ በጉባኤው ውስጥ ሐላፊነት በቶሎ አይሰጠውም:: ስለዚህ እነዚህን ሁኔታዎችን ለማጣራት ሁለት የኤርትራ ወንድሞችና አንድ የመቀሌን ወንድም ይዤ ይህንን በድለዋል የተባለውን



ወንድም ጠርቼ በጋራ አነጋገርነው:: በመጀመሪያ ጊዜ ይህ ወንድም በቅንነት ጥፋት መሥራቱን አመነ:: ጥፋቱንም ስለአመነ ምን አይነት የቅጣት ውሳኔ መስጠት እንደሚቻለን ተነጋግረን ለመወሰን ለሣምንት ተቀጣጠርን:: እርስ በርሳችን ስለማንጠራጠርና እንደ ደንቡ አንዱ ሌላውን ማታለል ወይም መዋሸት ወይም መካድ ኃጢአት ስለሆነ፣ ከምንም በላይ መተማመን አለ:: በተለይም በድብቅ ስለምንሠራ እና በሕግ ያልተፈቀደልን ስለሆነ፣ ቃለ ጉባኤን መያዝ የተለመደ አልነበረም:: ቃለጉባኤ የሚያዘው የመጨረሻ ውሳኔ በተላለፈበት ጊዜ ብቻ እንጂ ሂደቱን በቃለ ጉባኤ እየያዝን እና እየፈረምንም አንከታተለውም ነበር:: ስለዚህ ቃለጉባኤን ሣንይዝ ዝም ብለን ለሣምንትቀጠሮ ተስማምተን ተለያየን::

ለካስ ከሰበሰበ በኋላ አገር ታምሶ ኖሯል፤ ለምን አመንክ? በጉባኤ ሹመት ያገኘህ መሰለህ? በቶሎ ሐላፊነት እንደማይሰጥህ እንዴት አታውቅም? እየተባለ ተዶለተ:: እኔ ሞኙ ግን ይህንን ሴራቸውን ስላላወኩ፣ በቀጠሮ በተገናኘን ጊዜ ሣምንት ምን ምን ተባብለን እንደነበር ጠቃቅሼ ወደ ዋናው ጉዳይ ገብተን እንድንወያይ መድረኩን ከፍት አደረኩ:: በዚህን ጊዜ ሣምንት አምኖ የነበረው ተከሳሹ ግለሰብ በቁጣ ምን እያልክ ነው? ለምንድን ነው ስሜን የምታጠፋው? እኔ መቼ እንደዚህ ብዬ አመንኩ? ብሎ ቡራ ከረዩ አለ:: ለዚህ ምስክርነት ወደ ሦስቱ ወንድሞች ፊቴን ባዞር እንደዚህ ብሎ ማመኑን እኛ አልሰማንም ብለው በአንድ ቃል ካዱኝ:: ድሮም የማሕበሩን ድክመት መገንዘብ ጀምሬ ስለነበር፣ አሁን ደግሞ በምን ዓይነት ሰዎች እንደተከበብኩ ተረዳሁ:: ይህንን ሁኔታ ለማሕበሩ ብገልፅም

ነጮች በአፈጮሌነት እየተደለሉ ስለአስቸገሩኝ ምንም ለማላገኝ እና በትክክል በእምነቴ መሠረት መሥራት ለማልችለው ነገሮች እራሴን ማስገዛት ተውኩ:: እውነት በብዙ መልኩ አንፃራዊ ሆነችብኝ:: ውሸቴን ከሆነ እነ ማሞ ብርሃኔና የመቶ አለቃ አስጢፋኖስ ደምሳስ ሕሊናቸው ይመስክር::

## ከደቡብም ብልጦች አልጠፉም

ከደቡብም ቢሆን አንድ አንድ እራሳቸውን ማዳን የቻሉ ብልጦች አልጠፉም:: ለምሳሌ እንደነ ሻምበል ኃይለ ኢየሱስ ዋና፣ ተስፋዬ በጅጋ፣ እህት ልክየለሽ፣ አበበ የሚባለው ባልዋ እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል:: ከእለታት አንድ ቀን ከላይ የተጠቀሱትን ወንድሞችና ሌሎችንም፣ የታጠቁ የደርግ የቀበሌ ቦዘኔ አባላት በስብሰባቸው ላይ ሳሉ ከብበው ይይዟቸዋል:: ወደ ቀበሌም ከተወሰዱ በኋላ ሁለተኛ እንደዚህ ያለውን ሥራ አንሠም ወይም አንሰበስብም ብለው ስለፈረሙ እንደሌሎቹ ወንድሞች ችክ ብለው ከመረሸን ዳኑ:: እነዚህ ትንሽ ጭንቅላታቸውን አሰርተው ከመረሸን ድነዋል:: ይህንኑ ጉዳይ በ15/5/1990 ዓ.ም. እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ማለት ነው ከቀኑ 5 ሰዓት ተኩል በሆነ ጊዜ መሥሪያ ቤቱ ሔጄ ወንድም ተስፋዬ በጅጋን አነጋግሬአለሁ:: ተስፋዬ ግን የአልሸሹም ዞር አሉ መልስ ሰጠኝ:: ተስፋዬ ማፈሩ በፊቱ ላይ እየተነበበ እንዲህ አለኝ «እኛ እኮ ጨርሶ አንሰበስብም ብለን ሣይሆን በዚህ አካባቢ ወይም በዚህ ቀበሌ አንሰበስብም ብለን ነው የፈረምነው» ብሎ መልስ ሰጠኝ:: ስለድርጅቱ መጽሐፍ በመጻፍ ላይ መሆኔንም ገለጥኩለት:: ተስፋዬ ግን «ከዚህ ድርጅት የተሻለ እወነትን የያዘ ስለሌለ እውነትን ተቃውሞ መጽሐፍ መጻፍ ጥሩ አይደለም» ብሎኛል::



እነዚህ ጥቂቶች የደቡብ ብልጦች መንግሥት ጠርቶአቸው ባሉት ቀበሌ ሣይሆን ጨርሶ በኢትዮጵያ ውስጥ አትሰበኩ ቢላቸውም እንደሚፈርሙ የተረጋገጠ ነው:: ከላይ ከተዘረዘረው አንፃር እንድጽፍ ያነሣሣኝ ከአስመራ ብልጦችም ሆነ ከደቡብ በጐች ልዩ ቅራኔ ኖሮኝ ሣይሆን የሃይማኖት እስረኛ በመሆንና ባለመሆን መካከል ልዩነታቸው ምን ያህል እንደሆነ ለማሳየት ነው::

አሁን ድርጅቱን በበላይት የሚቆጣጠሩ የኤርትራ ወንድሞች የሆኑበት አንዱ ምክንያት ኤርትራዊ የሆነ ዞሮ ጉብኚ በፈረንጆቹ ስለተሾመና በዚህ ሰው አማካኝነት ደቡቦቹ እየተገፉ ስለሄዱ፣ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ለወገኖቹ ለማስረከብ ችለዋል:: ደቡቦችም እኛ እውነትን ፍለጋ እንጂ ምንቸገረን እያሉ ሌላ ልዩ አላማ ስለሌላቸውና እንደበግ ስለሚነዱ ነው:: ዛሬም ቢሆን ማለት በኢሕአዴግ ዘመን በሁለቱ የቀድሞ ወዳጆች መካከል ጥል ስለተፈጠረ አንዱ ሌላውን ከአገር የማባረሩ ጉዳይ ተከስቷል:: በዚህ መልኩ የይሖዋ ምስክሮችን ድርጅተ ሽፋን ያደረጉ ምላጮች ከኢትዮጵያ መባረራቸውን የጀመርን ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ ከቀኑ 11 ሰዓት እስከ ለ12 እሩብ ጉዳይ በሚያደርገው የዜና እወጃው ከአስመራ ወኪላቸው አቶ ጉይቶምን በመጥቀስ ግንቦት 11 ቀን 1991 ዓ.ም. ገልጸዋል:: ምን ያህሉ ከእነዚህ እንደተባረሩ አላውቅም:: ለማወቅም አልሞከርኩም::

## ነጮቹ ቢሞኙም ማጠፊያ አላቸው

ቀደም ተብሎ እንደተገለፀው በ1975 የዓለም መጨረሻ ይመጣል ተብሎ ሥራ የፈቱት ኤሮፖውያኖች ተጐድተውም አይጐዱም:: አንደኛ ፖርት ተይም መሥራት ይችላሉ::

ለመሥራት ከፈለጉ እንደገና ምን ጊዜም ሥራ አያጡም:: እንዲሁም ባይሠሩም ከማሕበራዊ ዋስትና በየወሩ ገንዘብ ሊያገኙ ይችላሉ:: ቢሞኙም የሁልጊዜ ወይም ዘላቂ ጉዳት አይደርስባቸውም:: የእኛው አገር በጐች ግን ሲወልዱ ቢታይ እንደሚባል አይነት ነው የሆኑት::

ለምሳሌ በአውራ ጐዳና ጥሩ ሥራ የነበረው ሰው ነበር:: ሚስቱ የኮሜርስ ምሩቅ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሠራተኛ ናት:: ሁለቱም የይሖዋ ምስክሮች ናቸው:: ሁለቱም ጥሩ ደመወዝ አላቸው ለማለት ይቻላል:: በእዚያ ዘመን በዚያን ወቅት ማሕበሩ በ1975 ዓ.ም. የዓለም መጨረሻ ይመጣል ስለአለ፣ ለዚህች ለቀረችው ጥቂት ዘመን ሁለተችን እየሠራን ጊዜአችንን ከምናአሳልፍ አንዳችን ሥራችንን ትተን ልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚ እንሁን ተባባሉና ከሥራ የመውጣት እጣ የአቶ ባል ይሆናል:: ከጊዜ በኋላ ሚስቱ በንግድ ባንክ ከከተማ ውጭ ትመደባለች:: እርስዋ እየሠራች እርሱ በአካባቢው እየሰበከ ኑሮአቸውን እንደቀጠሉ አጅሬ ደርግ መንግሥቱን ይዞ ከተፍ ይላል:: ከ1966-1970 ባለው ጊዜ ውስጥ አሰቃቂ ሁኔታዎች ስለነበሩ፣ በዚህ በተቃራኒ ርዕዮቱ አቶ ባል በቀበሌው ተደብድቦ ሞቷል ተብሎ ይጣላል:: ሳይሞት ይቀርና እንደምንም ተነስቶ ወደ ቤቱ ከተመለሰ በኋላ ሸሽተው አዲስ አበባ ይመለሳሉ:: አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ እመት ሚስት ባለሥራ፣ አቶ ባል ቦዘኔ፣ እንዳይሰብክ አስቸጋሪ ይሆንበታል:: ኑሮም እየከበደ ሄደ፣ ልጆችም እያደጉ ሄደው ለገብረማርያም ትምህርት ቤት ለብዙ ልጆች ክፍሎ ማስተማሩ አስቸጋሪ ሆነ:: የሚጠባበቁት የዓለም ሕዝብ አልቆ የእነርሱ የመዳን ዋስትና ፋና ጠፋ:: ስለዚህ በሁሉ



መልኩ ጫና ስለበዛ አቶ ባል አሮጌ ታክሲ ገዝቶ ማንከራከስ ጀመረ:: ከሚስትም መጣላት መጣና እንዲሁም መለየት ተከሰተ:: ስጊዜው ሚስቱ አውራሪስ ሆቴል ልጆችን አስታቅፋ ገባች:: በኋላ የቤት ችግር ስላለ ቤቱን ለሁለት ተካፍለው እንዲኖሩ ለሚስቲቱ ስለተፈረደ፣ በዚሁ ንዴት በአስም ታንቆ ከዚህ ዓለም በሞት ተሰናብቷል:: ሌሎች እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ከመሳሰሉት ሥራቸውን ትተው የተሞኙ ብዙዎች ናቸው::

## ምዕራፍ 11

## የይሖ ምስክሮች የነቢዩ ዳንኤልን ትንቢት መቃማት

ነቢዩ ዳንኤል ማን ነው? ነቢዩ ዳንኤል የአይሁዳዊ ዘር የሆነ ምሑር የነበረ ሰው ነው። ይህ ምሑር ወይም ነቢይ ወይም ደግሞ የአምላክ ሰው ገና እድሜው 16 ዓመት እንደሞላ በ3ኛው የዓለም ልዕለ ኃያል መንግሥት መሪ በናቡከደናጾር ከሌሎች ሦስት ጓደኞቹ ጋር ወደባቢሎን ቶወስደው እንዲማሩ እስኮላርሺፕ ከተሰጣቸው ወጣቶች አንዱ የነበረው ነው። ዳንኤል ምዕራፍ 1 ቁጥር 1-7 ተመልከቱ። ወጣቱ ዳንኤል ከጓደኞቹ ሁሉ የተሻለ ብሩህ ጭንቅላት ስለነበረው በተሰጠው የመማር እድል ተጠቅሞ ታላቅ ምሑር ሆነ። የናቡከደናጾር መንግሥትም እስከተገለበጠበት ዘመን ድረስ ከከፍተኛ ባለስልጣኖች አንዱ ሆኖ የባቢሎንን መንግሥት አገልግለዋል። ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 1 ቁጥር 21 ተመልከቱ።

የባቢሎን ልዕለ ኃያል መንግሥት ወድቆ በቦታው የሜዶ ፋሪስ 4ኛ ልዕለ ኃያል መንግሥት በተተካ ጊዜም ዳንኤል በምሑርነቱና በፖለቲካ ችሎታው ተመርጦ አገልግሎቱን ስመቀጠል ችለዋል። ከናቡከደናጾር ዘመነ መንግሥት የበለጠ ፈተና ቢደርስበትም ፈተናውን በብልሃትና በፅናት ተቋቁሞ የበለጠ ስልጣን ተጎናጽፈዋል። ዳንኤል ምዕራፍ 6 ቁጥር 28

ይህ ታላቅ ምሑር ዘሮቹ በሆነው በእሥራኤል ሕዝብ ላይ በ607 ዓመተ ዓለም በባቢሎን ንጉሥ በናቡ ከደናጾር የደረሰበትን ማከራ እያሰበ ይተክዝ ነበር። ትንሽም ዕረፍት ባገኘ ቁጥር ስለሕዝቡ የሚያወራውን የታሪክ መጽሐፍ እየፈለገ ያነብ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ይህ ሕዝቡ በ607 ዓመተ ዓለም



ከመማረኩ በፊት ኤርምያስ በተባለው ነቢይ የተነገረውን ትንቢት ያነባቸው ከነበረው ከሕዝብ ታሪክ ገጽ አገኘ። ይህ ያገኘው ታሪካዊ ትንቢት የእሥራኤል ሕዝብ በ607 ዓመተ ዓለም በናቡከደናጾር ተመርኮ ለ70 ዓመታት በባርነት ከተሰቃየ በኋላ፣ ሰባው ዓመት ሲፈፀም ግን ነፃነትን እንደሚጎናጸፉ የሚገልፅ ነበር። ዳንኤል ይህንን ታሪካዊ ትንቢት ያነበበው በ535 ዓመተ ዓለም አካባቢ ነበር። ዳንኤል ያነበበው የተጻፉ ትንቢት እንደዚህ ይል ነበር:-«ይህች ምድር ሁሉ ባድማና መደነቂያ ትሆናለች። እነዚህ አሕዛብ ለባቢሎን ንጉሥ ሰባ /70/ ዓመት ይገዛሉ። ሰባው ዓመትም በተፈፀመ ጊዜ የባቢሎንን ንጉሥና ያንን ሕዝብ ስለኃጢአታቸው እቀጣለሁ።» ኤርምያስ ምዕራፍ 25 ቁጥር 11-12

ይህንን ታሪካዊ ትንቢት ባነበበ ጊዜ ዳንኤል ወደ ዓመት መቁጠር ገባና በትንቢቱ መሠረት 70 ዓመት ሊሞላ ምንም ያህል እንዳልቀረ ተገነዘበ። በዚህን ጊዜ በአንድ በኩል ስለወገኖቹ ነፃነት መቀረብ እጅግ ሲያስደስተው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሐዘንና ፍርሃት ተሰማው። እንደዚህ ያለው ፍርሃትና ሃዘን የተቀላቀለበት በአንድ በኩል ተሰምቶት በሌላ በኩል ደግሞ ሰው ደስታ እንደሚሰማው በመግለፅ ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል እንደሚከተለው ጽፎ ነበር:- «እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነገር ባየ ጊዜ ደስታውን ትታ ዙር ወደ ትካዜ።» ነቢዩ ዳንኤልም የሕዝቡ ነፃነት መቃረብ ካነበበው ታሪካዊ ትንቢት በተገነዘበ ጊዜ ያደረገው ልክ እንደዚሁ ነበር።

ይህንን መልካም የምስራች ለማደናቀፍ ምቀኛ ወይም ምቀኞች ተከስተው እንቅፋት መሆን ስለሚችሉ የጥንቃቄን

አስፈላጊነት ዳንኤል ተገነዘበ:: የዳንኤል ጉልበት፣ ብልሃትና ጥንቃቄ ፈጣሪውን በፀሎት መማፀን ስለሆነ ለፀሎት ሱባኤ መግባቱን እንደሚከተለው ገልጾልናል:- «በቃሉ ለነቢዩ ኤርምያስ የተናገረውን የዓመቱን ቁጥር በመጽሐፍ አስተዋልሁ:: ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ ሰዶም እፀልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደ አምላክ አቀናሁ:ኝ» ትንቢተ ዳንኤል 9 ከቁ. 2-3:: በዚህ ሱባኤ መጨረሻ ለዳንኤል የተሰጠውን መልስ ቀጥለን እንመልከት:-

## ለዳንኤል ፀሎት የተሰጠ መልስ

ለዚህ ታላቅ ምሑርና ነቢይ ፈጣሪ ለፀሎቱ የሰጠውን ትንቢታዊ ምላሽ ከትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 9 ከቁጥር 24 እስከ 27 የተፃፉትን ቁጥር በቁጥር በአንክሮ እንከታተል:-

1ኛ ዳንኤል 9 ቁጥር 24 «ዓመፃን ይጨርስ፣ ኃጢአትንም ይፈፅም፣ በደልንም ያስተሰርይ፣ የዘላለምን ፅድቅ ያገባ፣ ራእይንና ትንቢትን ያትም፣ ቅዱስ ቅዱሳኑንም ይቀባ ዘንድ በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባኤ ተቀጥሮአል::»

ከዚህ በላይ «በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ» የሚለውን ኃይለ ቃል ልብ በሉ:: ዳንኤል ፈጣሪውን ሱባኤ በመግባት በልመና ያስቸገረው ስለሕዝቡ እና ስለቅድስቲትዋ ከተማው ነበር:: የዳንኤል ሕዝብና የዳንኤል ከተማ ደግሞ የእሥራኤል ሕዝብና የኢየሩሳሌም ከተማ እንደሆነች የሚታወቅ ነው:: ስለዚህ የፈለገ ነገር ቢሆን በዚህ በዳንኤል ሕዘብና በዳንኤል ሕዝብ ከተማ በኢየሩሳሌም ላይ የማይቀር ቀጠሮ ተይዞላቸዋል:: የተያዘውም ቀጠሮ ሰባ ሱባኤ ወይም ሰባ ሳምንታት ናቸው:: እነዚህ ሰባ ሱባኤዎች 490 ዓመታትን የሚወክሉ ናቸው



እንዴት? እንዲህ ነው:- የጥንት ሰዎች 30 ቀኖችን ነው አንድ ወር የሚሉት በጁሊያስ የቀን አቆጣጠር መሠረት ማለት ነው:: ኢትዮጵያም ጥንታዊት አገር ስለነበረች ይህንን የጥንቷን የጁሊያስ ዘመን አቆጣጠር ተቀብላ እስከ አሁን እየሠራችባቸው ነው:: ከጊዜ በኋላ በጊሬጎሪያስ ዘመን አቆጣጠር የጁሊያስ ከላንደር በተተካ ጊዜ፣ ኤሮፓዎች የዓመትዋን ትርፍ ቀኖች ለአንድ አንድ የዓመቱ ወራት ሲያደላድሉ ኢትዮጵያም ጳጉሜን እንደ የዓመቱ የትርፍ ቀናት ወይም እንደ ትንሽዋ 13ኛዋ ወር ወስዳለች:: ይህ ትክክል ይመስለኛል:: ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው አንፃር የዳንኤል ትንቢት በተጻፈ ጊዜ የዘመኑ የቀን አቆጣጠር አንድን ወር 30 ቀን አድርጐ የሚወስድ ነበር:: ስለዚህ አንድ ሳምንት ወይም አንድ ሱባኤ ሰባት ቀን ነው:: ዳንኤልም ስለሰባ ሱባኤ ሲተነበይ ከዚህ አንፃር ነበር::

ወደ ሰባ ሱባኤ እንመለስና በዳንኤል ሕዝብ ላይ የተቀጠረው ይህ ሰባ ሱባኤ ወደ ቀን ሲለወጥ /70×7=490 ቀናት/ አራት መቶ ዘጠና ቀናት ይሆናሉ:: እነዚህ 490 ቀናት አራት መቶ ዘጠና ዓመታትን የሚወክሉ ናቸው:: ምክንያቱ ትንቢቱ ከተነገረበት ዕለት አንስተን ስንቆጥር እስከ ተፈፀመበት ጊዜ ድረስ 490 ዓመታትን ስለፈጀ ነው:: ስለዚህ ሰባ ሱባኤ ስንል 490 ዓመታት ማለታችን መሆኑን አንባቢው እንዲገነዘብ ነው:: የአቆጣጠሩን ትክክለኝነት መቀበልም ሆነ ከአለመቀበል አንፃር ሣይሆን የታሪኩ ሂደት እንደዚህ መሆኑን በመረዳት ታሪኩን መከታተል አስፈላጊ ነው:: ስለዚህ ታሪኩን ቀጥለን እንከታተል::

## <u>ሰባ ሱባኤ መቆጠር የጀመረበት ወቅት</u>

በዳንኤል ሕዝብና በዳንኤል ከተማ ላይ የ70 ሱባኤ ወይም የ490 ዓመታት ቀጠሮ ተይዞላቸዋል:: ይህም ማለት ሀ ተብሎ የ490 ዓመታት ጊዜ መቆጠር ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ የዳንኤል ሕዝብ ምንም አይሆንም:: ነገር ግን ሀ ተብሎ ተቆጥሮ 490 ከተፈጸመ በኋላ ወይም ፸ ሱባኤ ከሞላ በኋላ በዳንኤል ሕዝብ ላይ በተያዘው ቀጠሮ መሠረት የሚደርስ ነገር አለ:: ስለዚህ ጥያቄው ይህ በዳንኤል ሕዝብ ላይ የተያዘው የ70 ሱባኤ ቀጠሮ መቆጠር የጀመረው መቼ ነው? ወይም መቼ ነበር? የሚል ይሆናል:: ይህ ትንቢት መቆጠር የጀመረበትን ወቅት ካወቅን የዳንኤል ሕዝብ በቀጠሮ መሠረት የሚጠየቅበትን ወቅት አወቅን ማለት ነው:: ስለዚህ ቀጥለን ከዚህ አንፃር እንመልከት:-

### <u>2ኛ ዳንኤል 9 ቁጥር 25</u>

ለዳንኤል ፀሎት ምላሽ ለመስጠት የመጣው ቅዱስ ገብርኤል /ዳንኤል 9 ቁጥር 21 ተመልከቱ/ የትንቢቱ ወይም የሰባ ሱባኤ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ እንደሚከተለው ነግሮታል:- «ስለዚህ እወቅ፣ አስተውልም፣ ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሲሕ ድረስ ሰባት ሱባኤና ስድሳ ሁለት /7+62=69/ ሱባኤ ይሆናል::» ዳንኤል ምዕራፍ 9 ቁጥር 25 ኢየሩሳሌም አለ ሰው ለ70 ዓመታት ስለቆየች፣ በትንቢቱ መሠረት ነፃ ወጥቶ በ537 ዓመተ ዓለም ከልደት በፊት ወደ አገራቸው በተመለሱ ጊዜ ሁሉ ነገር ፈርሶ ነበር ያገኙት:: ስለዚህ እንደ ጥንቱ ተመልሳ እንድትሠራ ከዓለም ሕዝብ፣ እና ነፃ እንዲወጡ ከፈቀደላቸው ከዘመኑ ባለስልጣናት፣ በተለይም ከመዘኑ ንጉስ ፈቃድና ትእዛዝ



ማግኘት ነበረባቸው:: ይህ ትእዛዝ አስፈላጊ ነበር:: እንዲህ ያለው ትእዛዝ እንዴት እንደወጣ ቀጥለን እንመልከት:- «በሀያኛው ዓመት በከሴሉ ወር እንዲህ ሆነ፣ እኔ ሱሳ ግንብ ሳለሁ፣ ከወንድሞቼ አንዱ አናኒ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሰዎች ከይሁዳ መጡ:: እኔም የዳኑትን ከምርኮ የተረፉትን፣ የአይሁድን ነገር ጠየቁአቸው:: እነርሱም፣ በዚያ ሥፍራ ያሉት ከምርኮ የተረፉት ቅሬታዎች በታላቅ መከራና ስድብ አሉ:: የኢየሩሳሌምም ቅጥር ፈርሷል፣ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋል አሉኝ::» ነህምያ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1-3

ከዚህ በላይ የተነገረው ታሪክ የእስራኤል ሕዝብ ከስደት በ537 ዓመተ ዓለም ወደ አገራቸው ቢመለሱም፣ ይህ ወደ አገሩ የተመለሰው ስደተኛ ሕዝብ ማንም እንደማይረዳው፣ በትልቅ መከራ ውስጥ እንደአሉ፣ የኢየሩሳሌምም ቅጥር እንደፈረሰ መሆኑን፣ በሮችዋ በእሳት እንደተቃጠሉና ያው እንደፈረሰች ያለች መሆኑን ተመልሶ ከመጡት ሰዎች ነህምያ ወሬ መስማቱን የሚገልጽልን ነው:: በነገራችን ላይ ይህ ነህምያ በዚያን ዘመን ካሉት ከአገሩ ንጉሥ ባለሙያዎች አንዱ የሆነ ትልቅ ባለስልጣን የነበረ ነው:: ይህ ትልቅ ባለስልጣን እኔን ከደላኝ ምንቸገረኝ የሚል ዓይነት ሰው ስላልሆነ እጅጉን ስለሕዝቡ ተጨነቀ:: ከባቢሎን ባርነት ነፃነት ቢያገኙም አለአንዳች እርዳታ በመከራ ላይ እንዳሉ ሰማ ስለዚህ ነህሚያ እንዲህ ሲል ይገልፅልናል:: « ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቅሳለሁ፣ አያሌ ቀንም አዝን ነበር፤ በሰማይ አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር::» ነህምያ ምዕራፍ 1 ቁጥር 4:: ይህ ታላቅ ሰው የዘመኑ ንጉሥ አርጤክስስ የጠጅ አሳላፊ ነበር:: ከላይ እንደተመለከትነው በሐዘን

እንደጠወለገ የሥራ ግዴታ ስለነበረበት ንጉሡ ፊት ቀም ጠጁን ለማሳለፍ ወደሥራው ገባ:: ለንጉሡ ጠጅ ቀድቶ ሲሰጥ ሲል ንጉሡ በነህምያ ፊት ላይ የሐዘን ድባብ አስተዋለበትና እንዲህ ሲል ጠየቀው:- «ማትታመም ፊትህ ለምን አዘነ? ይህ የልብህ ሐን ነው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም አለኝ::» ይለናል ካህኑ ነህምያ ነህምያ ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 ተመልከቱ::

በዚህን ጊዜ በዚህ አጋጣሚ ተጠቅሞ ነህምያ ለንጉሡ አርጤክስስ እንዲህ ሲል መለሰለት:- «ንጉሡ ሺህ አመት ይንገሥ፣ የአባቶቼ መቃብር ያለበት ከተማ ተፈትታለችና፣ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋልና ፊቴ ስለምን አይዘን? አልሁት:: ንጉሡም ምን ትለምነኛለህ? አለኝ:: እኔም ወደ ሰማይ አምላክ ፀለይሁ::» ነህምያ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3-4:: ልብ በሉ እግዚአብሔር ከመቅፅበት ፀሎትን መስማት ይችላል:: ከዚህ በኋላ ንጉሡ ለሰባ አመታት ባድማ የነበረች ኢየሩሳሌም እንድትሠራ፣ ቅጥርዋም እንዲጠገን፣ ሕዝብ ሁሉ ገንዘብ ጭምር እያዋጣ እንዲረዳ፣ ከንጉሡም ግምጃ ቤት በጀት እንዲታዘዝለት፣ ማንም ይህንን ኘሮጀክት እንዳይቃወም የንጉሡ ትእዛዝ መሆኑን በማስመልክት በነህምያ አማካኝነት ለሚመለከተው ሁሉ ትእዛዝ በማስተላለፍ ፈቀደለት:: ይህንኑ ታሪክ በነህምያ መጽሐፍ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 8 እስከ ምዕራፍ 3 ቁጥር 32 ማንበብ ይቻላል:: በዳንኤል ምዕራፍ 9 ቁጥር 25 ላይ ኢየሩሳሌምን ለማደስ ትእዛዝ ይወጣል፣ ይህም ሰባ ሱባኤ መቆጠር የሚጀምረው ያን ጊዜ ይሆናል የተባለውን ትንቢት ተፈፀመ:: በመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር ታሪክም ሆነ በሕዝብ ታሪክ ንጉሥ አርቴክሳስ ይህንን ትእዛዝ የሰጡት በ455 ዓመተ ዓለም ክልደት



በፊት ነበር:: ስለዚህ ሰባ ዓመት መቆጠር የጀመረው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መሆኑን መገንዘቡ ቀላል ነው:: ይህም ማለት በ537 ከባቢሎን ነፃ ከወጡ ከ80 ዓመታት በኋላ መሆኑ ነው:: ይህ ትእዛዝ ከወጣበት ከ455 ዓመተ ዓለም ጀምሮ እየሱስ ክርስቶስ በመሲሕ ደረጃ እስከመጣበት 29 ዓ.ም. መጨረሻ ወይም እስከ 30 ዓ.ም. መጀመሪያ ድረስ 70 ሱባኤ መቆጠር ከጀመረ 69 ሱባኤ ሆኖታል:: በዳንኤል ምዕራፍ 9 ቁጥር 25 ላይ «እስከ አለቃው እስከ መሢሕ ድረስ ሰባት ሱባኤና ስድሣ ሁለት ሱባኤ ይሆናል» ስለተባለ አቆጠጠሩን ቀጥለን እንመለከታለን:-

7×(ሱባኤ) + (62 ሱባኤ)×7

= 7×7 = 49 + 62×7= 434

= 49+434 = 483 ዓመት

ወይም ደግሞ በዳንኤል አቆጣጠር 62+7=69 ሱባኤ ማለት ነው::

ስለሆነም ኢየሱስ በ30 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ 70 ሱባኤ መቆጠር ከጀመረ 69 ሱባኤ ሆኗል:: ሰባ ሱባኤ ሲሞላ አንዲት ሱባኤ ብቻ ቀርታለች:: ስለዚህ ከ69 ሱባኤ በኋላ የሚሆነውን ነገር ከነቢዩ ዳንኤል እንስማ:-

<u>3ኛ ዳንኤል 9 ቁጥር 26-27</u>

በዚህች በቀረችው አንድ ሱባኤ ወይም 7 ዓመት ውስጥ መስሒ ብዙ ነገሮችን መፈፀም አለበት:: ምንድን ናቸው መሲሕ በቀረችው አንድ ሱባኤ ውስጥ መፈፀም የነበረበትና የፈፀመው? ቀጥለን እንመልከት:-

በዳንኤል ምዕራፍ 9 ቁጥር 26 «ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሢሕ ይገደላል::» ይህ እንግዲህ በ33 ዓመት

ተኩል ላይ የኢየሱስ የቤዛ መስዋእት መከፈልን የሚያመለክት ትንቢት ነው። መስዋእት መሆን ያስፈለገበትንም ምክንያት ሲዘረዝር ነቢዩ ዳንኤል እንደዚህ ይለናል፡-

ዳንኤል 9 ቁጥር 27 «ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባኤ ያደርጋል። በሱባኤውም እኩሌታ መስዋእቱንና ቁርባኑን ያስቀራል።»

ሀ. በዚያች በቀረችው አንዲቷ ሱባኤ ወቅት የእራሱን ተከታዮች አፍርተው፣ ለእነርሱ እንደማይተዋቸው ቃል እንደሚገባላቸው የሚገልፅ ትንቢት ነው። ይህንንም ከ30 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 33 ዓ.ም. ተኩል ድረስ ፈፅመዋል።

ለ. ልክ በ33 ዓ.ም. ተኩል ላይ ወይም በዳንኤል አገላለፅ በአንዲቷ ቀሪ ሱባኤ እኩሌታው ላይ የኦሪትን ሕግ መስዋእትና ቁርባን ሊያስቀር የሚችለውን መስዋእት በመሆን ዋጋ ከፍለዋል።

ሐ. ምንም እንኳን በሱባኤው እኩሌታው ላይ የሙሴን የኦሪት ሕግ ለማስቀረት እራሱን መስዋእት አድርጎ ቢያቀርብም ወይም ቢሞትም፣ ከሙታን ተነስቶ በቀረችውም የሱባኤ እኩሌታው ውስጥ ለተከታዮቹ ቃል ኪዳን የማፅናት ተግባሩን ቀጥሎበታል። ምክንያቱም ቃል ኪዳን የማፅናት ወይም ቃልኪዳን የማስገባት ተግባር የሚተገበረው በዳንኤል ትንቢት መሠረት ለአንድ ሱባኤ ነውና። ስለዚህ ይህንንም በልዩ ልዩ ዘዴ ከሙታን ከተነሣም በኋላ እስከ 36 ዓ.ም. ፈፅሞታል። ከዚህ በኋላ በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት መመሪያን ተቀብለው መሥራት የኢየሱስ ተከታዮች ፈንታ ነው። ነገር ግን በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት የሙሴ ሕግ ከ33 ዓ.ም. ተኩል ጀምሮ



ቀርቷል የሚለውን ትምህርት የኢየሱስ ተከታዮች በብዙ መልኩ ላለመቀበል እምቢተኞች ሆኑ። ለምን? በምን ምክንያት? ምክንያቱን ቀጥለን እንመልከት፡-

<u>የሙሴ ሕግ ይሻራል የሚል እምነት አልነበራቸውም</u>

የኢየሱስ በሱባኤው እኩሌታ መገደል የሙሴን ሕግ ሽሮ ሕዝብን ነፃ ለማውጣት የሚችል መሆኑን ስለአልተረዱ ነው። እንዴት? እንዲህ ነው፡-

1ኛ ኢየሱስ እራሱ ደቀመዛሙርቱ የሙሴን የኦሪት ሕግ በደንብ እንዲያከብሩ እንጂ እንዲሽሩ አላስተማራቸውም። እንዲህም ይላቸው ነበር፡-«ጻፎችና ፈርሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ፣ ጠብቁትም።» ማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ቁ. 2-3

2ኛ እራሱ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ቁጥር 17 ላይ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፣ ልፈፅም እንጂ ለመሻር አልመጣሁ።» እያለ አስተምሮአቸዋል። እሥራኤላዊ ሆኖ በሙሴው ሕግ መሠረት ፋሲካን፣ የዳምንታት በዓልና የዳስ በዓል የተባሉትን የማያከብር ወንድ ልጅ ይገደል ነበር። ዘሑልቅ 9 ቁጥር 13፣ ዘዳግም 16 ቁጥር 16 ተመልከቱ። ኢየሱስም ወንድ ስለነበር ይህንን በዓል ማክበሩ ስለማይቀር በዚህ በዓል ላይ ይዘነው እንገድለዋለን በማለት አይሁዶች እንደአሴሩበት ወንጌላዊ ዮሐንስ በምዕራፍ 7 ላይ ይገልፃል። እነዚህ ጠላቶቹ የማያምኑ የገዛ ወንድሞቹን እንደሰላይ በመጠቀም በበዓሉ ላይ በግልፅ ሥልጣኑን እያወጀ፣ በደቀመዛሙርቱ ታጅቦ እንዲገኝ መከሩት። እርሱ ግን ሃሳባቸውን ስለአወቀ በመጨረሻ ሰዓት ላይ በል ተነስ ሲሉት እኔ

ከእነጭራሹ ዛሬ በዚህ በዓል ላይ መገኘት አልፈልግም ብሎአቸው በቤቱ ቁጭ አለ:: እነርሱ ግን ተነስተው ወደ በዓሉ ከወጡና ከዓይኑ እይታ ከተሠወሩ በኋላ ተደብቆ ወደ በዓሉ ወጥቶ አከበረ:: ይህን ያህል እየፈራ ተደብቆ ሄዶ ማክበር ያደረሰው የአሪትን ሕግ ማክበር አስፈላጊነት እና ግዴታውም ስለነበር ነው:: ደቀመዛሙርቱን በቃል አሪትን አክብሩ ብሎ ያስተማራቸውን በተግባር አሳያቸው:: ይህ አንዱ ነጥብ ነው:: ሌላኛው ነጥብ መልካም ለመሥራት ወይም እራስን ለማዳን መዋሸት ይቻችኋል ይህ ነው:: ይህንን ታሪክ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ከቁጥር 2-10 ተመልከቱ::

3ኛ ሌላ ኢየሱስ ክርስቶስ የኦሪትን ሕግ በተግባር እየፈፀመ ሌሎችም እንዲፈፅሙት አርአያ በመሆን ሠርተዋል:: ተከታዮቹ ኦሪተን እንዲያቃልሉ፣ እንዲተው ወይም እንዲሽሩ ምንም አይነት እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ፍንጭ አልሰጣቸውም:: ስለዚህ በሱባኤው እኩሌታው በየዘወትር ቁርባን ፈንታ እራሱን ሰውቶ፣ የዘወትር ቁርባን እንዲቀር ዋጋውን በ33 ዓመት ተኩል ላይ ከከፈለ በኋላ እንኳን ተከታዮቹ በሙሉ ኦሪትን ያከብሩ ነበር:: መከበርም እንደአለበት ያምኑም ነበር:: ስለዚህ በዳንኤል ትንቢት ምዕራፍ 9 ቁጥር 26፣27 በሱባኤውም እኩሌታ መሲሕ ሕይወቱን በመሠዋት የዘወትር ቁርባኑን ያስቀራል የሚለው ትንቢት የሚያመላክተው ወዲያውኑ በዕለቱ የዘወትር ቁርባን በተግባር መቅረቱን የሚያሣይ አይደለም:: በተግባር የሚቆመው ወይም እንዲቆም የሚደረገው በብዙ መልኩ ትምህርት ከተሰጠ በኋላ እንደሚሆን ግልፅ ነው::



4ኛ ሌላ ቀርቶ የኦሪትን የዘረኝነት ሕግ ወይም የእነሱን ባሕል የማይከተሉትን እንደ እርኩስ የመጠየፍና እንደዚህ ላሉት ዘሮች ምንም አይነት እርዳታ ያለማድረግን ሕግ ጌታ ኢየሱስ አክብረዋል:: አንዲት የግሪክ ዜጋ የሆነች የሲሮፊኒቃዊት ዘር ሴት ኢየሱስ በሽታን ሁሉ ከአይሁድ ልጆች ላይ እየፈወሰ መሆኑን በአየችው ጊዜ፣አጋንንት የያዛቸውን ልጆችዋን እንዲፈውስላት እግሩ ላይ ተደፍታ ለመነችው:: እርሱ ግን ተይኝ ወግጂልኝ አላት:: ምክንያቱንም ሲነግራት የልጆችን ምግብ ለቡችሎች መስጠት አይገባም አላት:: በሌላ አባባል አንቺ ውሻ ልጆችሽ ቡችሎች ናቸው ማለት ነው::

እርሷ ግን ሆደ ባሻ ስለአልነበረች «አዎን ጌታዬ ሆይ፣ ቡችሎች እንኳን ከማዕድ በታች ሆነው የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ» የሚል መልስ ሰጠችው:: አሁን ይህች ሴት ከኦሪት ሕግ አንፃር እራስዋ ውሻ ልጆችዋም ቡችሎች እንደሆኑና የእሥራኤል ሕዝብ ግን የጌቶች ልጆች ወይም የአምላክ ልጆች እንደሆኑ የማመን ፍንጭ ሰጥታለች:: በሌላ አባባል በዚህ በእሥራኤል ሕዝብ ባሕልና ሕግ አምና የበታችነትዋን ተቀብላለች ማለት ነው:: ይህንን የሴትዮዋን አቋም ከአረጋገጠ በኋላ ብቻ ነበር እንዲህ ያላት:- «ስለዚህ ቃልሽ ሂጂ ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቷል አላት::» በኦሪት ሕግ ደንብ የእሥራኤልን ሕዝብ የበላይነት የተቀበሉትንና ሕጋቸውን የሚያከብሩትን ይረዳሉ፣ አብሮም በቤተመቅደሳቸው ይሰግዳሉ:: ስለዚህ የግሪክትዋ ሴት ልጆች ከዚህ አንፃር እንደረዳት መገንዘቡ ቀላል ነው:: ታሪኩን በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ቁጥር 25-30 ተመልከቱ::

የኢትዮጵያ ሕዝብ አይሁዶች አይደሉም። ነገር ግን የአይሁድን አምላክ እንደ አምላካቸው፣ የአምላካቸውንም ሕግ እንደ አምላካቸው ሕግ አድርገው ስለሚቀበሉት አምላካቸው ይሖዋ ከእሥራኤል ሕዝብ ለይቶ እንደማያያቸው በአሞፅ ምዕራፍ 9 ቁጥር 7 ላይ ተገልጿል። የአይሁድ መቅደስ በሰባ ዓ.ም. ከመጥፋቱ በፊት ኢትዮጵያውያኖች አየሩሳሌም እየሔዱ ከእነርሱ ጋር በመቅደሳቸው ይሰግዱ እንደነበር በሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 26 ጀምሮ ታሪኩን ማንበብ ይቻላል። ስለዚህ የኦሪትን ሕግና ሥርዓት አምና ከመቀበልዋ አንፃር ተመልክቶ ነው ጌታ የሴትዮዋን ልጆች ያዳናቸው። እስከአሁን እያየን እንደመጣነው ኢየሱስ ኦሪትን ሙሉ በሙሉ ይፈፅምና ያስፈፅምም እንደነበር ነው። በዚህ መልኩ እየፈፀመ ሣለ በቀረችው ሣምንት እኩሌታ ላይ የዘወትር መስዋእቱን ሊያስቀር የሚችል ዋጋውን ከፈለ። ከዚህ በኋላ የሚቀረው ሥራ የኦሪት ሕግ የሚያስቀር ዋጋ ተከፍሏል ብሎ እንደገና ተከታዮቹን ማስተማር የግድ ሆነ። ይህ የማስተማሩና የማሳመኑ ሥራ ሰባ ሱባኤ ካበቃ በኋላ ከ36 ዓ.ም. ጀምሮ በስፋት የሔዱበት ተግባር እንደነበር ቀጥለን እንመለከታለን፡-

## 4. የሙሴ የኦሪት ሕግ ማሻሩን ማብሰር

እስከ አሁን እያየን እንደመጣን ሁሉ የኢየሱስ ተከታዮችና እራሱ ኢየሱስ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ የኦሪትን ሕግ ያከብር እንደነበር ነው። ነገር ግን የኦሪትን ሕግ ለማስቀረት የሚችል ዋጋ የተከፈለው በ33 ዓምተ ምሕረት ተኩል ላይ በኢየሱስ መስዋትነት ነው። ኢየሱስ እራሱን መስዋእት በማድረግ ከኦሪት ሕግ ነፃ ሊያወጣ የሚችለውን ቼክ ቆርጦ ለተጠቃሚዎቹ ሰጠ።



ይህንን የእርሱን ቤዛነት ያመነ ሁሉ ከኦሪት ሕግ ነፃ እንደሚወጣ ተረጋገጠ። አሁን ቁም ነገሩ ይህ ከኦሪት ሕግ ነፃ እንድያወጣኝ የተጻፈልኝ ቼክ ወይም የተከፈለልኝ ቤዛ በእውነት ነፃ ያወጣኛል ብሎ አምኖ የመቀበል ጉዳይ ብቻ ነው። አምኖ እንዲቀበሉ ደግሞ ስለዚሁ መስበክ፣ ማስረዳትና ማስተማር አስፈላጊ ነው። ይህ ደግሞ ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑ የማያጠያይቅ ጉዳይ ነው። ስለዚህ በምድር ላይ ሥጋ ለብሶ ያላስተማራቸውን አዲስ ትምህርት ለተከታዮቹ ማስተማር ግድ ሆነበት። ለኦሪት ሕግ አስፈላጊው ተፈጽሞ ዋጋ በሙሉ ስለተከፈለ ከዛሬ ጀምሮ የኦሪትን ሕግ የማክበር ግዴታ የለባቸውም ብሎ የማስተማር ሰፊ ኘሮጀክት ተከፈተ። እንዴት? እንዴት እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥለን እንመልከት፡-

### ትምህርት

ኢየሱስ ሞቶ ከተነሣ በኋላ የኦሪትን ሕግ ከእንግዲህ ማክበር አስፈላጊ አይደለም የሚለውን ትምህርት ለተከታዮቹ ማስተማር ጀመረ። ኢየሱስ በመንፈስ ሁለት ቦታ በአንድ ጊዜ በመገኘት፣ ወይም ሁለት መልአኮቹን በተመሣሣይ ወቅት ሁለት ቦታ ተገኝተው ስለኦሪት መቅረት እንዲያስተምሩ እንዴት እንደአደረገ ቀጥለን እንመልከት፡-

በአንድ በኩል ለጴጥሮስ እንዲህ የሚለው ትምህርት ይሰጥ ነበር፡- «ሰማይም ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ። በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ፣ አራዊትም፣ በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት። ጴጥሮስ ሆይ ተነሣና አርደህ ብላ የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ። ጴጥሮስ

ግን ጌታ ሆይ፣ አይሆንም፣ እንዳች ርኩስ የሚያፀይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ:: ደግሞም እግዚአብሔረ ያነፃውን አንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ:: ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ ወዲያው ዕቃው ወደ ሰማይ ተመለሰ::» የሐዋርያት ሥራ 10 ቁጥር 11-16 ተመልከቱ::

በኦሪት ሕግ ያልተሰነጠቅ ሼኮና ያላቸው ለመብላት ያልተፈቀዱ ነበር- እንደነዚህ ያሉት በኦሪት ሕግ የተከለከሉት አራዊቶችን በራዕይ ለጴጥሮስ ካሣየ በኋላ ተነስተህ አርደህ ብላ ብሎ እንደአዘዘው እንመለከታለን:: እግዚአብሔር ቀድሶዋልና ከዛሬ ጀምሮ እርኩስ ናቸው አትበል፣ አርደህ ብላ እያለ በመደጋገም አረጋግጦለታል:: ቀደም ብለን እንደአየነው አይሁዳዊያን ያልሆነ ሕዝብ ደግሞ እንደ ርኩስና እንደውሾችም ይቆጠሩ ነበር፤እነዚህ ባሕሎች ሁሉ መሻሩንም ጌታ ለጴጥሮስን አስተማረው:: በሌላ በኩል ደግሞ ልክ በዚያው ሰዓትና ቀን እንደ እርኩስ ከሚቆጠሩት አሕዛብ ጋር ግንኙት ፈጥሮ የሚከተለውን ትእዛዝና መመሪየ እንደሰጠ ቀጥለን እንመልከት:-

<u>ለአሕዛቡ ለመቶ አለቃ ቆርኔልዎስ የተሰጠ መመሪያ</u>

እንዲህ እናነባለን:- «ቆርኔሌዎስ ሆይ፣ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራዕይ በግልጥ አየው:: እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ ጌታ ሆይ ምንድን ነው? አለ:: መልአኩም አሁን ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምኦንን አስመጣ አለው::» የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1-23 ታሪኩን አንብቡ::

ይህ ሁሉ ጥረት በምድር ላይ ሥጋ ለብሶ ሣለ ያላስተማረውን አዲስ ትምህርት ማብሰሩን እንመለከታለን:: ከላይ



እንደተመለከትነው ኢየሱስ በመልአኮቹ የአሕዛብ የሕዝብ አለቃ የሆነውን የመቶ አለቃ ቆርኔልዎስን ጴጥሮስ የሚባለውን ፈልገህ አግኝ ተብሎ መታዘዙን እናያለን:: በሌላ በኩል ደግሞ ጴጥሮስ የአሕዛቡን አለቃ እሺ ብሎ ተቀብሎ ወደ ቤቱ እንዲሄድ በራዕይ አስፈላጊውን የትምህርት ግንዛቤ ሰጥቶታል:: በመጨረሻም ቆርኔልዎስ ጴጥሮስን አግኝቶ ወደ ቤቱ እንዲገባ በጋበዘ ጊዜ፣ ጴጥሮስ ወደ አሕዛብ ቤት ገብቶ፣ አብሮ መብላት የተከለከለ ነው የሚለውን የኦሪትን ሕግ ጥሶ ወደቤቱ ገብቶ አብረው በልተዋል:: ይህ እንግዲህ የኢየሱስ በመላእክቱ አማካኝነት ያደረገው የማስተማር ውጤት ነው::

እንደዚህ ያለው ትምህርት ገና ያልደረሳቸው ወይም ያልተሰጣቸው ሌሎች የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ጴጥሮስ ወደአልተገረዘ አሕዛብ ቤት ገብቶ አብሮ መብላቱን በተመለከቱ ጊዜ እጅጉን ነቀፋት:: የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 11 ቁጥር 1-3:: የኦሪት ሕግ አሁን ጌታ ኢየሱስ ሽሯል፤ የሚል ትምህርት ቢሰጥም እርሱ በምድር ላይ እያለ ያላስተማረንን አሁን እናንተ የምታምኑትን ነገር እንቀበልም የሚል ተከራካሪ በዛ:: የሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 6-29 ታሪኩን አንበቡ:: ይህ ክርክር እስከ 56 ዓ.ም. አካባቢ ቆይቷል:: በ56 ዓ.ም. አካባቢ የክርስቲያኖች ጉባኤ ኃላፊዎች በጠሩት ትልቅ ስብሰባ ላይ የኦሪት ሕግን መጠበቅ አስፈላጊ አለመሆኑ ታምኖ በውሳኔ ተረጋገጠ:: ስለዚህ በተግባር ምላሽ ተገኝቶ የዘወትር ቁባን የቀረው በ66 ዓ.ም. አካባቢ እንደሆነ መገመት ይቻላል:: ምክንያቱም በዚያ ዘመን ትራንስፖርት ችግር በዚህ ላይ ስደት

ሥር ሆኖ ለዚያ ዓለም ዘመን ሕዝብ ማዳረሱ ጊዜን የሚጠይቅ ሆነ።

አሁን በ66 ዓ.ም. ላይ በዳንኤል የተነገረው ሰባ ሱባኤ ከተፈፀመ 30 ዓመት ሆኗል። የተወሰኑ የዳንኤል ትንቢቶች በአብዛኛው 490 ዓመታት ወይም 70 ሱባኤ ከማለቃቸው በፊት የተፈፀሙ ነበሩ። ነገር ግን ከሰባ ሱባኤ ወይም ከ490 ዘመናት በኋላ የሚፈፀሙ ወይም በተግባር የሚገለፁ ትንቢቶች እንደቀሩ መገንዘቡ ቀላል ነው። እነዚህ ትንቢቶች ምንድን ናቸው?

<u>ከ70 ሱባኤ በኋላ የተፈፀሙ ትንቢት</u>

ሀ. በዳንኤል ምዕራፍ 9 ቁጥር 27 መሠረት ከ70 ሱባኤ በኋላ የተፈፀሙት 1ኛ የአሪት ሕግ መሻሩን የማስተማር ሐላፊነትና ትምህርት ማሠጠቱ የትንቢቱ አካል ናቸው። ከ36 ዓ.ም. በኋላ እንዲህ ያለ ትምህርት ተሰጥቶ ከአሕዛብ ሕዝብም ጋር ቃልኪዳኑን አፅንተዋል።

ለ. በእርኩሰት ጫፍ ላይ አጥፊ ይመጣል ስለተባለ ዳንኤል ለ2ኛ ጊዜ ስለሕዝቡና ቅድስቲቱዋ ከተማ ሱባኤ የገባው በዚህ ርኩሰት ጫፍ ላይ የሚመጣው አጥፊው ዘሮቹን ጨርሶ ከገፀ ምድር እንዳያጠፋቸው ብሎ እንደነበር የሚታወስ ነው። ለዚህ ፀሎቱ ለዳንኤል የተሰጠውን መልስ ቀጥለን እንመለከታለን:-

<u>ዳንኤል ለ2ኛ ጊዜ ሱባኤ ገብቶ ያገኘው መልስ</u>

በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 11 ላይ የዓለም ልዕለ ኃያላን ነገሥታት መነሳትና መውደቅ ቅደም ተከተል ነግሮት ሲያበቃ በዳንኤል ሕዝብ ላይ ከቶ የማይቀር መከራ እንደሚወርድባቸው ለዳንኤል ተነገረው። ቀጥሎም ምንም እንኳን እጅግ ታላቅ



መከራ የሚወርድባቸው ቢሆንም ዘሮችህ ከምድር ገጽ ጨርሶ አይጠፉም ተብሎም ለዳንኤል ማረጋገጫ ተሰጥቶታል። ይህ ማረጋገጫ የተሰጠው በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 1 ላይ ነው።ታላቁ ሚካኤል ለሕዝብህ ስለሚቆም ጨርሶ አይጠፉም ተብሏል።

የዳንኤል ሕዝብ ከሚደርስባቸው መከራና ፈተና ጨርሶ ከምድረ ገፅ ግይጠፉ ይተርፋሉ ብሎ አንዱ መልአክ ለዳንኤል እየነገረው ባለበት ወቀት ሌላው መልአክ ራቅ ብሎ ያደምጥ ነበር። ይህ ሲያደምጥ የነበረው መልአክ ዳንኤልን ያነጋግር ለነበረው መልአክ የሚከተለውን ጥያቄ አቀረበ:- «የዚህ ድንቅ ፍጻሜ እስከ መቼ ነው?»

ዳንኤልን ያነጋግር የነበረው መልአክ ለጠያቂው መልአክ እንዲህ ሲል መለሰለት:- «ለዘመንና ለዘመናት፣ ለዘመንም እኩሌታ ነው።» ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 5-7 ተመልከቱ።

ሁለቱ መላእክት በዚህ ጉዳይ ላይ ሲነጋገሩ በአንክሮ ይከታተል የነበረው ዳንኤል አልገባኝም፣ ነገሩን በግልፅ ንገሩኝ በማለት ጥያቄ አቀረበላቸው። በዳንኤል አንደበት የተጠየቀው ጥያቄ እንደዚህ ይነበባል:- «ሰማሁም ነገር ግን አላስተዋልሁም የዚያን ጊዜም ጌታዬ ሆይ፣ የዚህ ሁሉ ፍጻሜ ምንድር ነው? አልሁ።» ዳንኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 8። ተመሳሳይ ጥያቄ ዳንኤልን ያነጋግር ለነበረው ሌላ መልአክ ጠይቆ መልስ ተሰጥቶታል። መልአኩ ገብቶት ዝም ብለዋል። ዳንኤል ግን አልገባ ስለአለው እንደገና ከላይ ያየነውን ጥያቄ ደግሞ ለመጠየቅ

ተገድደዋል:: ምን መልስ ተሰጥቶት ይሆን? ቀጥለን እንመልከት:-

## ለዳንኤል የተሰጠው መልስ

ዳንኤል «ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኩሌታ ነው::» ተብሎ የተሰጠውን መልስ አልገባኝም፣ አብራሩልኝ? ምን ማለት ነው? ብሎ መጠየቁን በዳንኤል ምዕራፍ 9 ቁጥር 8 ላይ ተመልክተናል:: ይህ ዓይነቱ አነጋገር አልገባኝም ስለአለ መልአኩ በሚገባው ቋንቋ እንዲህ ሲል ገልጾለታል:-

«የዘወትሩ መስዋእት ከቀረ ጀምሮ፣ የጥፋትም ርኩሰት ከቆመ ጀምሮ 1290 ቀን ነው::» ዳንኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 11 ተመልከቱ:: ይህ ለዳንኤል ጥያቄ የተሰጠ መልስ ነው:: በዚህ በዳንኤል ሕዝብ ላይ ይወርዳል የተባለው ቅጣት የሚፈፀመው መቼ ነው? ብሎ መልአኩ ጠይቆ ከገኘው መልስ ጋር ትርጉሙ አንድ ነው:: ዳንኤል ግን «ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኩሌታ ነው» የሚለው የመልአኩ አነጋገር አልገባ ስለአለው በቀላል መልኩ ተገልጾለታል:: ስለዚህ ቀጥለን ጉዳዩን በዝርዝር መቼ እንደነበር እንመልከት:-

1ኛ. በዳንኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 11 ላይ «የዘወትሩ መስዋእትም ከቀረ ጀምሮ፣ የጥፋትም ርኩሰት ከቆመ ጀምሮ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ቀን ይሆናል::» ይላል:: ስለዚህ ጥያቄው:-

ሀ. የዘወትር መስዋእቱ የቀረው መቼ ነበር?

ለ. የጥፋቱ ርኩሰት የቆመ መቼ ነበር?

ሐ. የጥፋቱ ርኩሰት ከቆመና የዘወትር መስዋእትም ከቀረ ጀምሮ 1290 ቀን ነው ተብሏል:: ከመቼ እስከመቼ መሆኑ ነው?



መ. እየሱስ እራሱ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ይህ በዳንኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 11 የተተነበየው ገና አለመፈጸሙን በማመልከት በትንቢቱ መሠረት የተባለው የጥፋት ርኩሰት ይቆማልና መቆሙን ስታዩ እየሩሳሌምን ለቃችሁ ሽሹ ብሎአቸዋል:: ማቴዎስ 24 ቁጥር 15 ተመልከቱ:: ከመቼ እስከመቼ ነበር የተፈፀመው?

## መልስ

1. የዘወትር መስዋእት የቀረው እያየን እንደመጣነው የእየሱስ ተከታዮች የአሪትን ሕግ ማክበር አስፈላጊ አለመሆኑን ከዳር እስከዳር ተገንዝበው ማክበሩን ባቋረጡ ጊዜ ነው:: ከዳር እስከዳር አሪትን ማክበር የተውት በ66 ዓ.ም. ነበር::

2. የጥፋትም ርኩሰት የቆመው እ.ኤ.አ. በ66 ዓ.ም. ተኩል ላይ የሮም ወታደሮች እየሩሳሌምን ለማጥፋት ዙሪያውን በከበቡ ወቅት ነበር:: ይህ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በሕዝብ ታሪክ የተረጋገጠ ሆኗል:: ሉቃስ ምዕራፍ 21 ቁጥር 20 ተመልከቱ::

3. 1290 ቀኖች ማለት 3 ዓመት ተኩል እንደሆነ በሂሳብ ቀመር ለማረጋገጥ ይቻላል::

4. እየሩሳሌም በወታደሮች ስትከበብ ወይም በጥፋት ርኩሰት የተመሰሉ የሮም ወታደሮች ሲከቧት ስታዩ በዳንኤል ትንቢት መሠረት የሚፈፀመም ስለሆነ ከእርስዋ እየወጣችሁ ሽሹ፤ በተባለው መሠረት ይህ ሽሽት የተፈፀመው ከ66 ዓመት ተኩል ከበባ በኋላ እስከ 70 ዓ.ም. መቃረቢያ ወቅት በነበረው ጊዜ ነው::

ስለዚህ ከላይ እያየን እንደመጣነው ሁሉ በ66 ዓ.ም. ተኩል ላይ ቆመን ካሰላነው የዳንኤል ሕዝብና ቅድስቲቷ ከተማ

ሊጠፉ የ3 ዓመት ተኩል ዕድሜ ብቻ ቀርቷአቸው እንደነበር ማስተዋሉ ቀላል ነው:: ስለሆነም የመስዋእቱ ቁርባን በ66 ዓ.ም. በተግባር ከቆመ በኋላ የዳንኤል ሕዝብ በ1290 ቀናት ውስጥ እንደሚጠፉ ለዳንኤል መልስ ተሰጥቶታል:: መልአኩም አሁን ይህ ነገር ባይገባህም ሰወደፊት ሰዘመኑ ትውልድ ስለሚገባቸው ዝም ብለህ ትንቢቱን አትም ስለተባለ ትንቢቱን ጽፏል:: ሐቁ ይህ ነው፤ ይህ ትንቢት ከ500 ዓመታት ላላነሰ ጊዜ ከቆየ በኋላ በ70 ዓ.ም. ተፈፅሟል::

## የይሖዋ ምስክሮች ቅጥፈት

የይሖዋ ምስክሮች ግን ይኸንን ሐቁን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እያጣመሙ ለእኛ ለዎች ታዎር ባለሥልጣናት ተተንብዮ በእኛው ላይ የተፈፀመ ትንቢት ነው ይላሉ:: ይህ ትንቢት እ.ኤ.አ. በ1918 ዓ.ም. የማሕበሩ ኘሬዝዳንት የነበረ ጄ.ኤፍ ራዘር ፎርድን ጨምሮ ሌሎች በአመራር ቦታ ላይ የነበሩ የማሕበሩ አባላት በተከሰሱ ጊዜ የደረሰባቸውን ሁኔታ የሚገልጽ ነው ይላሉ:: የዳንኤል ትንቢት በትኩረት እንከታተል በሚለው የ1999 ዓ.ም. እትም የአማርኛ መጽሐፋቸው ገጽ 296 ተመልከቱ:: ገና ድሮ ተፈፅሞ ያበቃውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት አይናቸውን በጨው አጥበው ለእኛ የተነገረ ነው ይላሉ:: ይህ መቼም ሰውን እናሞኛለን እያሉ መንፈሳዊ ትንቢትን አሰቦታው በማዋል እየተሳደቡ ነው:: ይህ ራዘር ፎርድ የተባለው ኘሬዝዳንታቸው ሁለቱን መሐን ባልና ሚስት በማስታረቅ ፈንታ እንዲፋቱ በማድረግና በተንኮል የራሴልን ሚስት ኩባንያ ያስቀማ ግለሰብ ነው:: አሁን ደግሞ የማርያን ኩባንያ የቀሙት እንኳቸው ዳንኤል ለእሥራኤል ሕዝብ ተንብዮ የተፈፀመውን ትንቢት



በድፍረት እየቀሙ ነው:: በተንኮል እምነት በተጻጻሉት በምዕመናን ስሜት በመጠቀም እነአብርሐም ይስሐቅና ያዕቆብ በቅርቡ በጉባኤያችን ከሙታን ተነስተው ይታያሉና እነርሱን ሰምንአሳርፍበት ቤት መሥሪያ ገንዘብ አዋጡ ብሎ ሕዝብን በመዝረፍ ሙስና የፈጸሙ ቁጭ በሉ ድርጅት ነው:: በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 55 እንደገና ታሪኩን መመልከት ይቻላል::

ከዚህ በላይ እንዳየነው

ሀ. ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ያላስተማራቸውን ከሞት ከተነሳ በኋላ እንዴት እንዳስተማራቸው::

ለ. የጥፋት ርኩሰትና የዘወትር መሰዋዕት የቀረው በ66 ዓ.ም መሆኑ

ሐ. ከዚህ በኋላ 1290 ቀናት ውስጥ ወይም በ3 አመት ተኩል ጊዜ ውስጥ በዳንኤል ሕዝብ ላይ በትንቢቱ መሠረት መከራ እንደደረሰባቸው ነው::

## ምዕራፍ 12

## አሕዛብ

አሕዛብ የሚለው የአማርኛችን ቃል በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ጄንታይል /Gentile/ የሚል ቃል ነው:: እንደ Thorn dike century Junior dictionary ትርጉም አይሁዳዊ ያልሆነ ሰው ማለት ነው:: (Oxford advanced dictionary) አድቫንስድ ኦክስፎርድ ዲክሽነሪም ቢሆን የሚሰጠው ትርጉም ተመሳሳይ ነው:: ስለሆነም የአሕዛብ ትርጉም የእስራኤል ሕዝብ ዘር ያልሆነ ሕዝብ ማለት እንደሆነ ሁለቱም የቃላት መፍቻ መጻሕፍት ያስምሩበታል::

ይህ የእሥራኤል ሕዝብ ያልሆነ ዘር ማለት ማንኛውም በዚህ ዓለም ላይ ያለው ሰው ሆኖ ግን የእሥራኤልን ባህል የማይከተል ማለት ነው:: እሥራኤሎች በጣሙን የሚጠየፉት ባሕላቸውን የማይከተለውን ሕዝብ ነው:: እሥራኤላዊ ባይሆንም የእሥራኤልን ሕዝብ ባህልና ሥርዓትን የሚከተል ሕዝብ ከሆነ ግን ያንን ሕዝብ እንደ አሕዛብ አይቆጥሩም ወይም አይጠየፉትም ነበር:: የእነርሱ ባሕልና እምነት የሚከተል፣ የእሥራኤል ሕዝብ ያልሆነ ሕዝብ በአምላካቸውም ሆነ በእራሳቸው በሥጋዊ እሥራኤሎች ዘንድ እንደ እሥራኤል ይቆጠራል:: በመጽሐፍ ቅዱስ አሞፅ በተባለው መጽሐፍ ምዕራፍ ዘጠኝ ቁጥር ሰባት ላይ ምንም እንኳን በሥጋ እስራኤላዊ ባይሆንም የያኔው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ እሥራኤል ይቆጠር እንደነበር ይገልጻል:: እራሱ አምላካቸው ያሐዌ ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ «የእሥራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል



እግዚአብሔር» በማለት አረጋግጧል:: ስለዚህ በዚያን ዘመን የነበሩ ኢትዮጵያውያኖች የእሥራኤል ባሕል ተከትለው ልክ እንደ እሥራኤል በይሖዋ ቤተመቅደስ ይሰግዱ ነበር::

### የአንድ ሕዝብ የእሥራኤል ባሕል የመከተሉ ምልክት

በዘዳግም ምዕራፍ 23 ቁጥር አንድ ላይ እንደዚህ የሚል መመሪያ ነበራቸው:- «ቁላ የተቀጠቀጠ፣ ብልቱም የተቆረጠ ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አይገባም::» እንዲሁም በዘፀአት 12 ቁጥር 48 ላይ «እንግዳ ሰውም በመካከላችሁ ቢቀመጥ፣ ለእግዚአብሔርም ፋሲካን ሊያደርግ ቢወድድ አስቀድሞ ወንድ ሁሉ ይገረዝ::» ይላል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ በልዩ ልዩ ምሑራን ከተጻፉት ታሪክ እንደምንረዳው ከሆነ ኢትዮጵያኖች ይህንን የእሥራኤልን ባሕል ተቀብለው በቤተመቅደሳቸውም ከእነርሱ እኩል ይሰግዱ እንደነበር ነው ይምንረዳው:: ከዚሁ የትካሣ ኢትዮጵያውኖች በእሥራኤል መንግሥት ውስጥ ጭምር የሥልጣን ቦታ እንደነበራቸው አይሁዳዊ ኤርምያስ መጽሐፈ ኤርምያስ ምዕራፍ 38 ላይ ይገልጻል::

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ኤርምያስ ነቢይ ወይም አስተዋይ የፖለቲካ አማካሪ ሰው ነበር:: በዚያን ዘመን የዓለም ልዕለ ኃያል ከነበረው አከባቢሎን መንግሥት ጋር የእሥራኤል ሕዝብ ቅራኔ ውስጥ ገባ:: የዚያ ዘመን የዓለም ልዕለ ኃያል መንግሥት የዛሬይቱ ኢራቅ የሣደም አገር መሆንዋ ነው:: ይህንን ያወቀው አማካሪው ነቢዩ ኤርምያስ ከልዕለ ኃያሉ የባቢሎን መንግሥት ጋር ጦርነት እንዳትገጥሙ:: እነርሱ እንደአሉ ተስማሙ ብሎ ይመክራቸው ነበር:: ይህንን

ምክሩን ቁንጮ ባለስልጣናት ለመቀበል ፈቃደኛ ስለአልሆኑ፣ ሕዝቡ እንዳያልቅ አስቀድሞ ወደ ባቢሎን ጭምር እንዲሰደድ ይመክር ጀመር።

ይህንን አድራጐቱን የሕዝብ ደህንነት ስለደረሰበት እንደሚከተለው ለበላይ አካላቸው ሪፖርት አቀረበ። «የሕዝብን ሁሉ ልብ ያደክማል፣ ሕዝቡ ለአገሩ ተሰልፎ እንዳይዋጋ አትዋጉ እያለ ይሰብካል ብለው ከሰሱት። የበላይ ክፍተኞች ባለስልጣናትም ወደ ንጉሡ ቀርበው የኤርምያስን በደል ከዘረዘሩ በኋላ የሞት ፍርድ እንዲያፀድቅላቸው ንጉሡን ለመኑት። ንጉሡም ስለፈቀደላቸው መልክያ በተባለው ጉድጓው ውስጥ ጣሉት። ጉድጓዱም እጅግ ጥልቅና በሚያሰምጥ ጭቃ የተሞላ ነበር። እንደዚህ ባለው ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ እንዲሞት አሥረው በገመድ አወረዱት።

ይህንን የመኳንንትን አድራጐት የሰማው፣ በእሥራኤል መንግሥት ውስጥ ባጅሮንድ የነበረው አንድ ኢትዮጵያዊ ሰው ነበር። ይህ ኢትዮጵያዊ በሥልጣኑ ተጠቅሞ ይህንን ነቢይ ለማዳን ወሰነ። ወደ ንጉሡ ቀርቦ ሁሉን ካስረዳ በኋላ የንጉሡን አሳብ ለመለወጥ ቻለ። ስለዚህ ለመኳንንቶቹ ፈቅዶ የነበረውን ትዛዝ ንጉሡን አሽሮ ኤርምያስ ከጉድጓድ እንዲወጣ ተደረገ። ይህ ሰው አቤ ሜልክ ይባላል። ኤርምያስ ምዕራፍ 38 ቁጥር 8-13። ይህ የሚያመለክተው ኢትዮጵያውያኖች በቤተ መቅደሳቸው እንደ እሥራኤሎች ይሰግዱ እንደነበርና በፖለቲካቸውም ተካፋዮች እንደነበሩ ያሳያል።

ኢትዮጵያውያኖች የአይሁድ ቤተመቅደስ በሮማውያኖች በ70 ዓ.ም. እስከ ጠፋበት ድረስ ወደ አይሁድ ቤተመቅደስ



እየሄዱ ይሰግዱ እንደነበር የንግሥት ሕዳኬ ጆንደረባ ወይም ባጅሮንድ አንዱ መረጃችን ነው። የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 27 ተመልከቱ። ጃንደረባ የሚለውን አንዱን ነጠላ ትርጉም ብቻ በመመልከት እንዴት ስልብ ወደ አይሁድ ቤተመቅደስ ገብቶ ይሰግዳል? የሚሉ ሰዎች አሉ። አቤ ሜልክም ሆነ የንግሥት ሕዳኬ ጃንደረቦች፣ ብልተ ቆራጦች አልነበሩም። እንደዚህማ ቢሆን ኖሮ በዘዳግም 23 ቁጠር 1 መሠረት ለስግደት ወደ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ አይሄዱም ነበር። የጃንደረባ ትርጉም ባጅሮንድ መሆኑን እንጂ ስልብነትን ብቻ የሚያመለክት አለመሆኑን /Aid to Bible Understanding/ መጽሐፍ ቅዱስን ለማወቅ የሚረዳ በተባለው መጽሐፋቸው የ1969 ዓ.ም. እትም ገጽ 535 ላይ የዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ድርጅት ጃንደረባ ባጅሮንድ መሆኑን ይገልጻል። ይህንን ባሕላቸውን ያልተቀበለው ሌላ አሕዛብ ወይም ሕዝብ እንኳን ቤተመቅደሳቸው ገብቶ ሊሰግድ የቤተመቅደሱንም አጥር መንካት አይችልም ነበር። በአሁኑ ጊዜ ሻሮን በፊሊስጤም ስግደት ቦታ በመሔዱ የተፈጠረው መተላለቅ አይነት ያኔም ይፈጠር እንደነበር መረዳት ቀላል ነው። ስለዚህ እስራኤሎች ባህላቸውን ያልተቀበለውን ሕዝብ እንደ ጥንብ አንሣ ይቆጥሩ እንደነበር ዘዳግም 14 ቁጥር 21 ላይ አንተ የተቀደስክ ስለሆንክ የበከተውን አትብላ። ነገር ግን ለአሕዛብ ስጠው በሚል ዘይቤ ይገልፃል። ኢየሱስም በምድር ላይ በነበረ ጊዜ የእሥራኤልን ባሕል ያልተቀበሉት ሰዎች እንደውሾች ይቆጥር እንደነበር በማርቆስ 7 ከቁጥር 25-28 ተገልጸዋል። ነገር ግን ኢትዮጵያውያኖችን እንኳን እንደዚህ ተጠይፎ ማራቅ እራሱ መሪያቸው ሙሴ ከኢትዮጵያ

ቆነጃጅት መርጦ ሚስት እንዳአገባ ዘሁልቅ ምዕራፍ 12 ቁ. 1 ይገልፃል:: ከእነዚህ ሁሉ አንፃር አሕዛብ ማለት እንደእኔ፣ ትክክለኛው ትርጉም የእሥራኤልን ባሕል ያልተቀበለው ሕዝብ ማለት ይመስላል::

ከጥንት ዓለም ሥልጡኖች አንዷ ኢትዮጵያ እንደነበረች ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከቕብረተሰብ ታሪክ እንረዳለን:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አንፃርም ከተመለከትን ኢትዮጵያ ከ1473 ዓመተ ዓለም /BC/ በፊት እንደ አገርና እንደመንግሥተ የውጭ አገር መሪዎችን ተቀብላ ታስተናግድ እንደነበር የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 68 ቁጥር 31 ይገልፃል:: «መኳንንት ከግብፅ ይወጣሉ፣ ኢትዮጵያም እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች::» በሚለው መፈክር መሠረት ኢትዮጵያ እጆችዋን ዘርግታ ከተቀበለችው የአምላክ እንደራሴዎች አንዱ ልዑል ሙሴ ነበር:: ሙሴ የግብፅ ፈርኦን የልጅ ልጅ ሆኖ በግብፅ ጥበብ ሁሉ የሰለጠነ የዘመኑ ታላቅ ሰው ነበር:: ኢትዮጵያ ይህን ታላቅ ሰው ተቀብላ ማስተናገድዋን ግራም ሐንኮክ የሚባል ጸሐፊ ዘሣይን ኤንድ ዘሲል መጽሐፍ ገጽ 450 ላይ የፊላቪስ ጆሴፍስ /Flavis Josephus/ ታሪክ በማጣቀስ ነቢዩ ሙሴ ከ40 እስከ 80ዓመት በነበረው እድሜው ወደ ኢትዮጵያ መጠቶ እንደነበር ይገልፃል:: ቀደም ብሰን በዘሁልቅ ምዕራፍ 12 ቁጠር 1 ላይ የነቢዩ ሙሴ ሚስት ኢትዮጵያዊት እንደነበረች የተጠቀሰው ለዚህ ነው::

<u>የትኛዋ ኢትዮጵያ?</u>

አንድ አንድ ዘመን አመጣሽ ምሑራን ኢትዮጵያ ይባል የነበረው አገር የዛሬይቱ ኢትዮጵያችን እንደማይመለከት ያስምሩበታል:: እንደ እነዚህ ምሑራን ከሆነ ኢትዮጵያ ከላይ



እንደተባለው ረጅም ታሪክ የሌላትና ከውጭ አገር ሕዝቦች ጋር ግንኙነት ማድረግ የጀመረችው ቅርብ ጊዜ እንደሆነ ይተርካሉ:: ያኔ ኢትዮጵያ የሚባለው ድፍን ጥቁር የአፈሪካ ሕዝብን ነው ይላሉ:: ይህንኑ በማስመልከት ግራም ሐንኮክ የተባለው ሰው በተጠቀሰው ዘሣይን ኤንድ ዘሲል መጽሐፉ በገጽ 130 እና 150 ኢትዮጵያ የምትባለው የዛሬዋ አገራችን ከአይሁድ ሕዝብ ጋር ግንኙነት እንዳልነበራትና ግንኙነቷን የመሠረተችው ከ70 ዓ.ም. በኋላ ከሮም ወታደራዊ ጥፋት በሽሽት ለመጀመሪያ ጊዜ በየመን አድርጐ አይሁዶች ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውን የአገራችን ታሪክ አዋቂ እራሳቸው ዶክተር ሪቻርድ ፓንክረስት እንደሚያምኑበት ይገልፃል:: ግን እወነት ነውን?

እንደ ግራም ሐንኮክ ከሆነ እውነት አይደለም:: ግራም ሐንኮክ በእራሱ አነሳሽነት ተነሣሥቶ አደረኩት ወይም ደረስኩበት እንደሚለው ማስረጃ ከሆነ ኢትዮጵየ ጥንታዊት አገር መሆንዋን፣ ከማንኛውም ሕዝብ ቀደም ብላ ከእሥራኤል ሕዝብና መንግሥት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላት፣ ባሕላቸውንም የተቀበለች አገር መሆንዋን ያስምርበታል:: ቀደም ብላ ወዳጅነትን ኢትዮጵያ ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር መሥርታ ስለነበር፤ በ606 ከልደት በፊት ቤተመቅደሳቸው በዘመኑ ልዕለ ኃያል መንግሥት በናቡ ከዳናጾር ጠፍቶ ስለነበር ለወደፊትም ተመሳሳይ ሁኔታ ካጋጠማቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሸሹ ኢሳያስ መክሯቸው ነበር:: ስለዚህ ወገኑ የሆነው የእሥራኤል ሕዝብ እንደዚህ ያለ አደጋ በመጣ ጊዜ ቀደም ብለው በጊዜ ኢትዮጵያ ወደምትባል አገር እንዲሸሹ እንደመከራቸው ኢሳያይስ ምዕራፍ 18 ቁጥር 1-

3 በመጥቀስ ግራም ሐንኮክ ይከራከራል። ይህ ጥቅስ እንደዚህ ይነበባል፡-

«እናንተ ፈጣኖች መልእክተኞች ሆይ ወደ ረጅምና ወደ ለሰለሰ ሕዝብ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ወደ ሆነ ወገን፣ ወደሚሰፍርና ወደሚረግጥ፣ ወንዞችም ምድራቸውን ወደሚከፍሉት ሕዝብ ሄዱ።» እንደ የእንግሊዘኛው አዲስቱ ዓለም ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ /Whose Land the Rivers have washed away/ ምድራቸውን ወንዞች የሚጠራርግባቸው ሕዝብ ሂዱ ይላል።

እንደ ግራም ክርክር ወንዞች የምድቸውን አፈር የሚጠራርግባቸው ከኢትዮጵያ በቀር ሌላ እንደሌለ ያመለክታል። በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ግዛት እስከ የመን ጭምር የተዘረጋም እንደነበር ተገልጿዋል። ይህ የግራም ሐንኮክ አመለካከት ነው።

እንዲሁም ይኸንኑ የኢትዮጵያ የረጅም ታሪክ ባለቤትነት በመደገፍ ዶክተር ላጺሶ ህዳር 1994 ዓ.ም. ፊት ለፊት የሚባል ኘሮግራም ቀርቦ የኢትዮጵያን ማንነትና ጥንታዊነት የሚመሰክሩና ኢትዮጵያ ታሪክ አልባ አለመሆንዋን የሚያስረዱ የተጠናከረ መረጃ መኖሩን ገልጸዋል። ስለዚህ ከተጠናቀረው መረጃ አንፃር የኢትዮጵያ ታሪክ በአዲስ መልክ እንደሚፃፍም ገልጸዋል። በዚህም ሆነ በዚያ ምሑራን ተስማምተው አንድ ውጤት ላይ ቢደርሱ ይመረጣል።

የኢትዮጵያ ታሪክ በቤተክርስቲያንና በቤተመንግሥት ባለስልጣናት እጅ ብቻ ተቀምጦ፣ ሠፊው ሕዝብ ግን በቃል ብቻ በጆሮ ከሚሰማው ትረካ ውጭ የሚያውቅበት ዘዴም ሆነ እድል አልነበረውም። ክቡር ዶክተር ደጃዝማች ዘውዴ በዚሁ ፊት



ለፊት በተባለው ኘሮግራም ቀርበው የንጉሡ ዙፋን ከክርስቶስ የተገኘ ነው የተባለው ነገር እስከጠቀመ ድረስ ችግር የለውም ያሉት የእወነት አብነት አለው። ብቻ ሕዝብን እስከ አረጋጋ ውሸትም ቢሆን ስለሚጠቅም የየዘመናቱ የኢትዮጵያ ገዥዎች ግድ እንዳልነበራቸው እንረዳለን። ይህ የፖለቲካ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ለመመራመረ እና ሐቁን ለማውጣት ሙያም ሆነ አቅም ስለሌለኝ እንደዚህ ያለው ጉዳይ ለሚመለከታቸው ምሑራን ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ለአቤቱታ መልስ በአፋጣኝ ይገኛል ተብሎ ባይታሰብም በአቤቱታ መልክ እተወዋለሁ። አንድ ጊዜ አቶ ከበደ እዮ የሚባል ሰው በኢትእጵ መፅሔት ቅፅ 2 ቁጥር 02/92 ገፅ 21 ላይ ለእግዚአብሔር እንደዚህ ብሎ አቤቱታ አቅርቦ ነበር፡-

<u>አለኝ ቅሬታ ይላል ርዕሱ</u>

«አለኝ ጥያቄ ደግሞም አቤቱታ፣
ታድዬ ካገኘሁ ዕድሉን ለአንዳፍታ።
ካልሆነ እወቁ ነቢያት ፃድቃኖች፣
አድርሱልኝ እንኩ ፧
ለእግዜር ጥያቄዎች ።
ስለዚህ እንደእኔ የግሌ አቤቱታ፣
አንድ ነገር አለኝ ፧
አድምጡኝ በእርጋታ።
ፈጣሪ ተናዶ ሞትን ከፈጠረ፣
ዕድሜን መተመን ይገባው ነበር።
ቀነሰ ቀነሰ አድርጎ ከትንንሾቹ፣
መጨመር ይገባል ለጥበበኞቹ።»

ሕዝብ የራሱ ዘመን እንደአለውም ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን:: ይህ ዘመን «የአሕዛብ ዘመን» ይባላል:: ምን ማለት ነው? በዚህ የአሕዛብ ዘመን እየተጠቀሙ ለዓለም መጨረሻ ማስረጃቸው የይሖዋ ምስክሮች እንዴት ልበቢስ በጐቻቸውን እንደሚያታልሉ ቀጥለን እንመለከታለን:-



## ምዕራፍ 13

## የአሕዛብ ዘመን

አሕዛብ የተባለውን የቃል ትርጉም በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 12 አይተናል:: አሁን ደግሞ የአሕዛብ ዘመን ስለተባለው ነገር እንመለከታለን:: የአሕዛብ ዘመን ማለት የእሥራኤልን ሕዝብ ባሕል የማይከተል፣ የእሥራኤል ዘር ያልሆነ ሕዝብ ዘመን ማለት ነው:: ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ዘሮቹ የሆነ የእሥራኤል ሕዝብ በአሕዛብ የሚሸነፍበትና እራሱን በራሱ ማስተዳደር የማይችልበት ዘመን ይመጣል ሲል የተናገረው ቃል ነው:: በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ቁ. 24 ከ70 ዓ.ም. ጀምሮ የሚሆነውን ሲያመለክት ኢየሱስ ያለውን ቃል እንዲህ እናነባለን:- «በዚህ ሕዝብ ላይ ቁጣ ይሆናል፣ በሴፍ ስለትም ይወድቃሉ፣ ወደ አሕዛብ ሁሉም ይማረካሉ፣ የአሕዛብ ዘመን እስኪፈፀም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች::» ከላይ ያነበብነው የጌታ ቃል በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ጦርነት እንደሚከፈት፣ ብዙዎቹም በሴፍ ስለት በጦርነቱ እንደሚያልቁ፣ ከጦርነቱ በሕይወት የተረፉት ደግሞ ሁሉም እንደሚማረኩና በዓለም ላይ እንደሚበተኑ የሚገልፅ ነው:: ከዚህ በኋላ እሥራኤላዊ ያልሆነ ሕዝብ ኢየሩሳሌምን ረግጦ ይገዛል ይሰናል:: ይህ የአይሁድ ዘር ያልሆነ አሕዛብ ኢየሩሳሌም ረግጦ የሚገዛበት ዘመን የአሕዛብ ዘመን ይባላል:: ይህ የአሕዛብ ዘመን የሚያበቃበት ዘመን መኖሩን ሲያመለክት ጌታ ኢየሱስ «የአሕዛብ ዘመን እስኪፈፀም ድረስ » በሚል ኃይለ ቃል ተጠቅመዋል:: ይህ የአሕዛብ ዘመን በኢየሱስ ዘመን ገና ያልተጀመረ መሆኑን ሲያመለክት «በዚህ ሕዝብ ላይ ቁጣ ይሆናል፣ በሴፍ ስለትም

ይወድቃሉ፣ ወደ አሕዛብ ሁሉም ይማረካሉ።» በማለት ገና ወደፊት የሚፈፀም ነገር መሆኑን አሳይተዋል። በሌላ አባባል ይህ የአሕዛብ ዘመን የሚጀመረው የእሥራኤል ሕዝብ በጦርነት ተሸንፎ ሁሉም ወደ አሕዛብ ከተማረኩ በኋላ ነው። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በሰላም እራሳቸውን በራሳቸው ኢያስተዳደሩ፣ ነገር ግን ሮም ልዕለ ኃያል መንግሥት እንደማንኛውም ታናናሽ ገባር መንግሥታት እየገበሩ የሚኖሩበት ጊዜ ነበር።

የማሳያ አስረጃችን ኢየሱስ በዚሁ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ከቁጥር 5-6 የተናገረው ቃል ነው። ቀጥለን እንመልከት:-«አንድ አንዶቹም ስለ መቅደስ በመልካም ድንጋይና በተሰጠው ሽልማት እንደአጌጠ ሲነጋገሩ:- ይህማ የምታዩት ሁሉ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል አለ።» ይህም የጌታ አባባል ኢየሩሳሌም ገና ተረግጣ መገዛት እንደአልጀመረች፣ ነገር ግን ተረግጣ የምትገዛበት ዘመን እንደሚመጣ የሚያረጋግጥ ነው። ስለሆነም የአሕዛብ ዘመን የተጀመረው መቼ ነው? የሚለው ትልቁ ጥያቄአችን ነው። የይሖዋ ምስክሮች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እያምታቱ ሞደፊክ በመሥራትና አለቦታው ትርጉም በመስጠት የአሕዛብ ዘመን የተጀመረው በ607 ዓመተ ዓለም ነው ይላሉ። እንደምስክሮቹ ልብወለድ መነሻቸው 607 ዓመተ ዓለም፣ ማስረጃቸው ናቡ ከደናጾር የተባለው የባቢሎን ንጉሥ ነው። ጥቅሳቸውም ዳንኤል ምዕራፍ 4 ከቁጥር 4-37 ያለው ነው። በዚህ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፈ 4 ከቁጥር 4-37 ባሉት ቁጥሮች ምስክሮቹ እንዴት ሞደፊክ እንደሠሩ እንመለከታለን። ለእነዚህ



ጥቅሶች ነቢዩ ዳንኤል ምን እንደአለና ምን ብሎ እንደተረጐመ፣ የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ ምን ምን እያሉ እንደሚተረጉሙ እንመለከታለን። በመጀመሪያ ዳንኤል 4 ከቁጥር ከ4-18 ያለውን እንመልከት:-

<u>የጥቅሱ ምንባብ</u>

«እኔ ናቡ ከደናጾር በቤቴ ደስ ብሎኝ በአዳራሼም ተመችቶኝ ነበር። ሕልም አለምሁ፣ እርስዋም አስፈራችኝ፣ በአልጋዬም ላይ የነበረው አሳቤና የእራሴ ራዕይ አስጨነቀኝ። ስለዚህ የሕልሙን ፍቺ እንዲያስታውቁኝ የባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ወደ እኔ ይገቡ ዘንድ አዘዝሁ። የዚያን ጊዜም የሕልም ተርጓሚዎቹና አስማተኞቹ ከላዳውያኑና ቃላተኞቹ ገቡ፣ ሕልሙንም በፊታቸው ተናገርሁ፤ ፍቺውን ግን አላስታወቁኝም። በመጨረሻም የቅዱሳን አማልክት መንፈስ ያለበት እንደ አምላኬ ስም ብልጣሶር የሚባለው ዳንኤል በፊቴ ገባ፣ እኔም ሕልሙን ነገርኩት፣ እንዲህም አልኩት:- የሕልም ተርጓሚዎች አለቃ ብልጣሶር ሆይ፣ የቅዱሳን አማልክት መንፈስ በአንተ ወስጥ እንዳለ ከምስጢርም ሁሉ የሚያስቸግርህ እንደሌለ አውቁአለሁና ያለምኩትን የሕልሜን ራዕይ ፍቺውን ንገረኝ፣ የራሴ ራዕይ በአልጋዬ ላይ ይህ ነበረ:-

«እነሆ በምድር መካከል ዛፍ አየሁ፣ ቁመቱ እጅግ ረጅም ነበረ። ዛፉም ትልቅ ሆነ፣ በረታም፣ ቁመቱም እስከ ሰማይ ድረሰ መልኩም እስከ ምድር ዳርቻ ድረሰ ታየ። ቅጠሉም የተዋበ ነበረ፣ ፍሬዋም ብዙ ነበረ፣ ለሁሉም መብል ነበረበት፣ ከጥላውም በታች የምድር አራዊት ያርፉበት ነበር፣ በቅርንጫፎቹም ውስጥ የሰማይ ወፎች ይቀመጡ ነበር። ሥጋ ለባሹም ሁሉ ከእርሱ

ይበላ ነበር:: በአልጋዬም ላይ የእራሴ ራዕይ አየሁ፣ እነሆ፣ አንድ ቅዱስ ጠባቂ ከሰማይ ወረደ:: በታላቅ ድምፅም እየጮኸ እንዲህ አለ:- ዛፉን ቁረጡ፣ ቅርንጫፎቹንም ጨፍጭፉ፣ ቅጠሎችንም አራግፉ፣ ፍሬውንም በትኑ፣ አራዊቱንም ከበታቹ፣ ወፎችም ከቅርንጫፉ ይሸሹ:: ነገር ግን ጉቶውን በምድር ውስጥ ታውት፣ በመስክም ውስጥ በብረትና በናስ ማሠሪያ ታስሮ ይቆይ:: በሰማይም ጠል ይረሰርስ፤ ዕድል ፈንታውም በምድር ሣር ውስጥ ከአራዊት ጋር ይሁን:: ልቡም ከሰው ልብ ይለወጥ፣ የአወሬውም ልብ ይሰጠው፣ ሰባት ዘመናትም ይለፍበት:: ልዑል በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሰለጥን፣ ለወደደውም እንዲሰጠው፣ ከሰውም የተዋረደውን እንዲሾምበት ሕያዋን ያውቁ ዘንድ ይህ ነገር የጠባቂዎች ትእዛዝ፣ ይህም ፍርድ የቅዱሳን ቃል ነው:: እኔ ንጉሥ ናቡ ከደናጾር ይህን ሕልም አልሜአለሁ፣ አንተም ብልጣሶር ፍቺውን አስታውቀኝ፣ የመንግሥቴ ጠቢባን ሁሉ ፍቺውን ያስታውቁኝ ዘንድ አይችሉምና፣ ነገር ግን የቅዱሳን አማልክት መንፈስ በአንተ ውስጥ አለና አንተ ትችላለህ::» ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 4 ቁጥር 4–18:: ትርጉሙን ከመመልከታችን በፊት በጥቅሱ ውስጥ የተጠቀሱትን ወይም የተነገሩት አንኳር አንኳር ነገሮችን እንመልከት::

1ኛ. አንድ ትልቅ ዛፍ አለ:: ይህ ዛፍ ቁመቱ ሰማይ የደረሰ፣ የሁሉ ፍጥረታት መጠለያና ምግብ የሆነ ነው::

2ኛ. የዛፉ መቆረጥ እና የዛፉ ጉቶ በሜዳ ውስጥ ሣይነቀል በናስ ታስሮ እስከ 7 ዓመት እንዲቆይ መወሰን በተመለከተ

3ኛ. የንጉሥ በበሽታ መቀጣት



4ኛ. የንጉሡ ከ7 ዓመት በኋላ ወደ ዙፋኑ መመለስ ስተባሉት ሐረጎች ነቢዩ ዳንኤል ምን ብሎ ትርጉም እንደሰጣቸው፣ የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ እንዴት እንደሚተረጉሙ እንመልከት:: መጀመሪያ የዳንኤልን ትርጉም፣ ቀጥሎ የይሖዋ ምስክሮችን ትርጉም ተራ በተራ ቀጥለን እንመለከታለን::

## በመጀመሪያ የዳንኤል ትርጉም

ዳንኤል የዛፉን ፍቺ እንዲህ ብሎ አብራራ:- «ትልቅ የነበረ፣ የበረታውም፣ ቁመቱም እስከሰማይ የደረሰው፣ መልኩም እስከ ምድር ሁሉ ድረስ የታየው፣ ቅጠሉም አምሮ የነበረው፣ ፍሬውም የበዛው፣ ለሁሉም መብል የነበረበት፣ በበታቹም የምድር አራዊት የተቀመጡበት፣ በቅርንጫፎቹም የሰማይ ወፎችም ያደሩበት ያየኸው ዛፍ ንጉሥ ሆይ፣ እርሱ ታላቅና ብርቱ የሆንክ አንተ ነህ፣ ታላቅነትህ በዝቶአል፣ እስከ ሰማይም ግዛትህም እስከ ምድር ዳርቻ ነው::» ዳንኤል 4 ቁጥር 20-22 ተመልከቱ::

ከዚህ በላይ ያነበብነው ነቢዩ ዳንኤል ለንጉሡ ስለአየው ዛፍ ትርጉም የሰጠው መግለጫ ነው:: የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ ፈጽሞ በጥቅሱ ውስጥም ሆነ ባለሕልሙ ንጉሡ ካየው ስዕል ውጭ አሳብ አመንጭተው እንደሚከተለው ተረጉሙ:-

## የምስክሮቹ ትርጉም

ቁ.1. ይህ እስከሰማይ የደረሰው ዛፍ በተሰይም ከምድራችን ጋር ባለው ግንኙነት ሁሉን ፍጥረታት የሚመግበውን የአምላክ የበላይ ገዥነትን ያመለክታል ብለው

ተረጉሙ:: እ.ኤ.አ. በ1991 ዓ.ም. የታተመውን፣ በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ የተባለው መጽሐፋቸውን ገፅ 139 ተመልከቱ:: ዳንኤል ግን የዛፉ ትርጉም የእራሱ የናቡከደናጾር ምሳሌ እንደሆነ ነው የተረጐመው:: ይህ ስለዛፉ የሰጡት አንዱ ትርጉማቸው ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ለዛፉ ያኼኪዎቹ የሰጡት ትርጉም ደግሞ ይህ የሰማይ አምላክ የእራሱን እገዛዝ ለተወሰኑት ጊዜያት በእሥራኤል ሕዝብ ላይ አቋቁሞት በነበረው መንግሥት አማካኝነት ተገልጾ ነበር:: ስለዚህ ዛፉ የይሖዋ አምላክ በእሥራኤል ሕዝብ ላይ በአቋቋመው መንግሥትም ይመስላል ሲሉም ተረጉሙ:: ስለዚህ እሉ:- የእሥራኤል መንግሥት በ607 ከዘመናችን አቆጣጠር በፊት በናቡ ከደናጾር በጠፋ ጊዜ በምድር ላይ የነበረ የአምላክ ግዛት ተቋረጠ የሚል ትርጉም ይሰጡታል:: አሁንም ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን መጸሐፍ ገፅ 139 ላይ አንብቡ::

ይህንን ሁለተኛውን ትርጉም ደግሞ ለምን እንደአመጡ ልብ በሉ:: በመጀመሪያ የአምላክ የበላይ ገዥነትን ያመለክታል አሉ:: በ2ኛ. የእሥራኤልን ሕዝብ መንግሥት ያመለክታል አሉ:: እንዴት ሲባል፣ በእጅ አዙር የእሥራኤል ሕዝብን ይገዛ የነበረው የሰማዩ አምላክ ስለሆነ ነው ይላሉ:: ሁሉም ትርጉሞች ከዳንኤል ትርጉም ጋር ሆድና ጀርባ ናቸው:: አይገናኙም:: ሁለተኛው ትርጉም ለምን አስፈለገ? ለሚለው ጥያቄ ይህንን የዛፉን ትርጉም የጥንት የእሥራኤልን ሕዝብ ይመለከታል ካሉ በኋላ፣ አሁን ግን የእሥራኤል ሕዝብ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ከአምላክ ሕዝብነት ደረጃ ስለወጣ እነርሱን አይመለከትም:: አሁን ይህ



የዛፉ ትርጉም የሚመለከተው መንፈሳዊ እሥራኤልን ነው።። እነዚህም መንፈሳዊ እሥራኤሎች በአሁኑ ዘመን ቅቡአን ቀሪዎች ናቸው እያሉ በጉቻቸው ለማጃጃልና እራሳቸውን ፃድቃን ለማስመሰል ነው::

## 2ኛው የዳንኤል ፍቺው

2ኛው የእንኤል የሕልሙ ፍቺ «ንጉሥ ሆይ ከሰማይ የወረደውንና ዛፉን ቁረጡ፣ አጥፉትም ነገር ግን ጉቶውን በምድር ውስጥ ተውት፣ በብረትና በናስ ማሣሪያ ታስሮ በመስክ ውስጥ ይቆይ፣ በሰማይም ጠል ይረስርስ፣ ሰባት ዘመናትም እስኪያልፍበት ድረስ ዕድል ፈንታው ከምድር እራዊት ጋር ይሁን ያለውን ቅዱስ ጠባቂ ማየቱን ንጉሥ ሆይ ፍቺው ይህ ነው:: በጌታዬ በንጉሡ ላይ የወረደው የልዑል ትእዛዝ ነው:: ልዑሉም በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሠለጥን፣ ለሚወደውም እንዲሰጠው እስከታወቅ ድረስ ከሰዎች ተለይተህ ትሰደዳለህ፣ መኖሪያህም ከምድር አራዊት ጋር ይሆናል፣ እንደበሬም ሣር ትበላ ዘንድ ትገደዳለህ፣ በሰማይም ጠል ትረሰርሳለህ፣ ሰባት ዘመናትም ያልፍብሃል:: የዛፉንም ጉቶ ይተውት ዘንድ ማዘዙ ስልጣን ከሰማያት እንደሆነ ካወቅህ በኋላ መንግሥትህ ይቆይልሃል::» ዳንኤል ምዕራፍ 4 ቁ.23-26

ከዚህ ከዳንኤል ትርጉም የምንረዳው የዛፉ መቆረጥ የንጉሡ ከሥልጣን መባረር እንደሆነ፣ ከሥልጣን ከተባረረ በኋላ የንጉሥ በእብደት በሽታ አእምሮውን ስቶ እንደ እንስሳ መሆን፣ በምድር መስክ ውስጥ እንዲቀርና እንዳይነቀል በብረት ናስ እስከ ሰባት ዓመት ታሥሮ እንዲቆይ የተደረገው ጉቶ፣ ንጉሡ ከሰባት ዓመት በኋላ ሲድን ወደ ዙፋኑ ወይም ሥልጣኑ እንደሚመለስ፣

መንግሥቱ እንደምትቆይለት የሚያመለክት ነው። በዳንኤል ትርጉም ሥልጣን ከሰማይ መሆኑ ንጉሡ ካወቀ በኋላ በ7ኛው ዓመት መጨረሻ ስልጣኑ እንደሚመለስለት መተርጐሙን መረዳት ከባድ አይደለም። ይህ ሁሉ በዳንኤል የሕልም ትርጉም መሠረት በትክክል ቃል በቃል በናቡ ከደናጾር ላይ ደርሰዋል። ይህም የሆነው 7ኛው ዓመት ከተፈፀመ በኋላ ነው። ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 4 ከቁጥር 28-37 ተመልከቱ።

ሰባቱ ዓመት ንጉሡ የተቀጣበት ወይም የሚቀጣበት ዘመን መሆኑን ነው የተረጐመው ዳንኤል። ዳንኤል ይህ ሰባት ዓመት 2520 ዘመናት ናቸው አላለም። ምስክሮቹ ግን ይህንን ሰባት ዓመት በ360 ቀኖች ካባዙ በኋላ 2520 ቀናትን አገኙ። ይህንን 2520 ቀናትን ዓመታት ናቸው ብለው ተረጐሙ። ከዚህ በፊት በዚሁ መጽሐፍ እንደአየነው በአንድ ሺህ የፍጥረት ቀናት ላይ 6 ሺህ የፍጥረት ቀናት ደምረው አንዱን የፍጥረት ቀን ወደ 7 ሺህ ዘመናት እንደአሳደጉ ዓይነት የጥቅስ ቆርጦ ቀጥል ሥራ ነው። ለምን እንዲህ አደረጉ?

የአምላክ ምድራዊ ግዛት በ607 ዓመተ ዓለም ተቋርጠዋል። ይህ የተቋረጠበት ዘመን እንደቀድሞ ወይም እንደበፊቱ የሚመለሰበት ዘመን ይመጣል። ይህ ዘመን የሚመጣው ከ607 ዓመተ ዓለም እስከ 1914 ዓ.ም. ከቆየ በኋላ ነው። ስለዚህ ከ607 ዓመተ ዓለም ጀምሮ እስከ 1914 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜን ያመለክታል። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ ግዛት የሚመለስላቸው ለእሥራኤል ሕዝብ ሣይሆን ለእኛ ለቅቡዓን ቀሪዎች ነው። በመሆኑም ይህ ርዝመት ከ607 ዓመተ ዓለም እስከ 1914 ዓ.ም. ያለው 2520 ዘመናት በእኛው ላይ ፍጻሜን



አግኝቷል። በ1914 ዓ.ም. የእግዚአብሔር መንግሥት በሰማይ ተቋቁማ በእኛ አማካኝነትም ምድርን በመግዛት ላይ ናት። እኛ የክርስቶስ ወኪሎች ነን፣ ድርጅቱም የሚታየው የአምላክ ምድራዊ ድርጅት ነው ለማለት ነው። ይህ ትምህርታቸው ከነቢዩ ዳንኤል ትርጉም ውጭ መሆኑ ማንም አሳቢ አእምሮ የሚስተው ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን እውነት ምስክሮቹ እንደሚሉት እሥራኤል ያልሆነ ሕዝብ ወይም አሕዛብ ኢየሩሳሌምን ከ607 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ እስከ 1914 ዓ.ም. ረግጠው ገዝተዋል? ኢየሩሳሌም በአሕዛብ ተረግጣ መገዛት የጀመረችው መቼ ነው? ክ607 ዓመት ዓለም ጀምሮ ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ከመስጠታችን በፊት ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክና ከእሥራኤል ሕዝብ መንግሥታት አገዛዝ ታሪክ አንፃር ነገሮችን መቃኘት የግድ ይላል። ስለዚህ ነገሮችን በአንክሮ እንከታተል።

## <u>የይሖዋ (SUPPERMACY) የበላይነት</u>

የይሖዋ ምስክሮች የአሕዛብ ዘመን በ607 ዓመተ ዓለም ነው የተጀመረው የሚከሉት አንዱና ዋና ምክንያታቸው የይሖዋ የበላይነት መስተዳድር የተቋረጠው በ607 ዓመት ከልደት በፊት ስለሆነ ነው ይላሉ። እንዴት ከተባሉ ከዚያን ዘመን ጀምሮ የእሥራኤል ሕዝብ የተገዛና ሲገብርም የኖረው በየጊዜው ለተነሱት ለአሕዛብ ነገሥታት ነበር። ከ607 ዓ.ም. በፊት ግን በቀጥታ ለይሖዋ ብቻ እየተገዙና እየገባሩ፣ ይኖሩ ስለነበር የይሖዋ (Supremacy) የበላይነት አልተደፈረም ነበር። ስለሆነም ጥያቄው የበላይነት መዳፈርና አለመዳፈርን የሚመለከት ስለሆነ እንዲህ ያለው ድፍረት የተከሰተው በ607 ዓመተ ዓለም

ናቡከደናጾር ቤተመቅደሳቸውን አፍርሶ፣ የዓምልኮት ሥርዓት ፕሮግራማቸውን እንዲቋረጥ አድርጐ፣ በባርነት በአጋዛቸው ጊዜ ብቻ ነበር:: ስለሆነም የአሕዛብ ዘመን አገዛዝ በ607 ዓመተ ዓለም ተጀመረ:: ከዚያ በኋላ እንደዚህ ያለው ሥርዓት እንደገና አልተከሰተም ይላሉ:: እውነት ነው?

ሀ. ከ607 ዓመተ ዓለም በፊት የእሥራኤል ሕዝብ መዋቅር ወይም አደረጃጀት እንዴት ነበር?

ለ. ይህ አደረጃጀታቸው ምን ይመስል ነበር?

ሐ. ይህን አደረጃጀት የፈጠረላቸው ማን ነበር?

መ. ይህ አደረጃጀታቸው የይሖዋ የበላይነት መገለጫ ነበር?

ሠ. እንዲህ ያለው አደረጃጀት በ607 ዓመተ ዓለም ከተቋረጠ በኋላ እንደገና አልተመለሰም ነበር?

ለእነዚህ ጥያቄዎች ከሚሰጠው መልሶች አንፃር የይሖዋ የበላይነት በ607 መቋረጡንና አለመቋረጡን እንመለከታለን:-

<u>የይሖዋ የበላይነቱ መገለጫ</u>

የይሖዋ የበላይነቱ መገለጫ እያመለኩት እንዲጠብቁ የሰጣቸው የኦሪት ሕግጋት ነበሩ:: በሙሴ አማካይነት ሕጉን በቃል ኪዳን ደም እናከብራለን በማለት ተቀበሉት:: ዘፀአት ምዕራፍ 24 ከቁጥር 6 እስከ ቁጥር 11 ተመልከቱ:: ስለዚሁ ጉዳይ ሲመሰክር ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብራውያን ምዕራፍ 9 እንደዚህ ይላል:- «ሙሴም ትእዛዛትን ሁሉ እንደ ሕጉ ለሕዝብ ሁሉ ከተናገረ በኋላ፣ የጥጆችንና የፍየሎችን ደም ከውኃና ከቀይ የበግ ጠጉር፣ ከሂሶጵም ጋር ይዞ:- እግዚአብሔር ያዘዘላችሁ የኪዳን ደም ይህ ነው።፡ ብሎ በመጽሐፉና በሕዝቡ ሁሉ ላይ



ረጨው፣ እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነፃል::» ዕብራ 9 ከቁጥር 19-22:: እነዚህ የይሖዋ (Suppermay) የበላይነት መገለጫዎች የሆኑ ሕጎች በመጀመሪያ ደረጃ በአሥርቱ ትእዛዛትና ከዚያም በኋላ በሙሴ አማካኝነት የተሰጣቸው ከ600 ያላነሱ የኦሪት ሕጐች ናቸው:: ከእነዚህም ሕዝቡ እንታዘዛለን፣ እናከብራለን ብለው በደም ቃልኪዳን ከገቡት መካከል ለናሙናነት የተወሰኑትን እንመለከታለን:: ኦሪት የቴኦክራቲክ (Theocratic) አገዛዝ መገለጫ ነበረች:: ቴኦክራቲክ የመለኮታዊ አገዛዝ የሆነ ፍጹማዊ ሥርዓት ነው:: ይህ ፍጹማዊና አሐዳዊ ሥርዓት ፍጹማዊ ሳልሆኑ ሕዝብ ተሰጠና ፈጹም ያልሆነ ሕዝብ ሕጉን መጠበቅ ከአቅሙ በላይ ስለሆነበት በኃጢአት ሥርየት እንዲታለፉ ይደረግ ነበር:: ስለሆነም ያ ሥርዓት እንደሥርዓት የይሖዋ የበላይነት መገለጫ ሥርዓት ነበር::

1ኛ. ነቢዩ ኢሳያስ በምዕራፈ 33 ቁጥር 22 ላይ «እግዚአብሔር ፈራጃችን ነው፣ እግዚአብሔር ሕግን ሰጪያችን ነው፣ እግዚአብሔር ንጉሣችን ነው» ብሎ በገለፀው መሠረት የይሖዋን (Supremacy) ሉዓላዊነትን አምነው በደሙ ቃል ኪዳን መቀበላቸው አንዱ ነው:: ይህ አገዛዝ ከሕዝብ ሥርዓት በፍጹም የተለየ ነው:: ይህ ዓይነቱ አገዛዝ በእሥራኤል የመለኮታዊ አገዛዝ (Theocratic) ይባላል:: ስለዚህ እንደሌሎች ሕዝብ ወይም ሕዝቦች ሕግ• አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈፃሚ የመንግሥት መዋቅር አልነበራቸውም:: የተቀሩት የመንግሥት ባለሥልጣናት ሁሉ በአንድ የበላይ አካል ብቻ የሚሾሙ

ይሆናል:: ሕዝብ መርጦት በድምፅ ብልጫ ብሎ ነገር የለም፤አልነበረምም::

2ኛ በዚሁ የአገዛዝ ደንብ መሠረት ይሖዋ የሰጣቸውን ሕግ አክብሮ የሚያስከብሩ ከ12 ነገደ እሥራኤል አንዱን የሌዊ ወገን መርጦ በሊቀካህንነት ሾመዋል:: ከሌዊ ወገን የተመረጠው ሰው ልጆች የሊቀካህን ምክትሎች ወይም የበታች ካህናት እንዲሆኑ ሲመረጡ፣ የዳኝነት ጉዳይም ከሌዊው ወገን በሊቀካህኑ ለሚሾሙት ተሰጥተዋል:: ይህ ከዋና መዋቅሮች አንዱ ነው:: የቴኦክራቲክን ሕግ የማያከብር ቢኖር ቅጣቱን ተግባራዊ የሚያደርጉት ሕግ አስፈፃሚዎችም ነበሩ:: እነዚህ የሕግ አስፈጻሚዎቹም ቢሆኑ የሚሾሙት በሕዝብ ድምፅ አልነበረም:: ስለ ሕግ ጉዳይ አደራ የተሰጣቸው ለለዊ ወገኖች ስለነበሩ ሕግ አስከባሪዎችም ከሌዊ ወገኖች የተውጣጡ ነበሩ:: እንዲሁም ካስፈለገ ንጉሦችም እንደዳኛ ሆነው እንዲፈርዱም ይፈቀድላቸው ነበር::

በ3ኛ ደረጃ ሕግ ሰጪአቸው ይሖዋ የሰጣቸውን ሕጐች ሁሉ ሕዝቡ የማክበር ግዴታ ስለአለበት ባለሥልጣናቱ ሕዝቡ ሕጉን ማክበራቸውና አለማክበራቸውን መቆጣጠርና የማያከብር ከተገኘ በሕጉ ትእዛዝ መሠረት መቅጣትና ማስቀጣት ነበር:: እነዚህ ሦስት ነገሮች ማለት ከ1-3 እየተመለከትን የመጣነው ነገሮች የይሖዋ የበላይነት (Supremacy) በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የተዘረጋው ልዓላዊነት አገዛዙን የሚያመለክቱ ናቸው:: በተግባርም ሲገለጥ የሚቃጠል መስዋእት፣ የዘወትር ቁርባን፣ የቁርባን መስዋእት ወይም የሰላም መስዋእት የሚባሉ መስዋእቶች፣ የበደል መስዋእት፣ የኃጢአት መስዋእት፣ የእህል



ቁርባን፣ የመጠጥ ቁርባን፣ የሚወዛወዝ ቁርባን የሚባሉት ሁሉ ሣይቋረጡ መፈፀም ነበረባቸው:: እነዚህ ነገሮች የይሖዋን የበላይነት አውቆ የመታዘዝ ምልክቶች ስለሆኑ የማይታለፍ እና እንደታዘዘው መፈፀም ያለባቸው ናቸው:: ኢ.ን.ሣይት.ኦን.እስክሪኘቸር 2ኛ ቮልዩም የ1988 እትም ከገጽ 525-528 ዝርዝሩን ተመልከቱ:: ስለዚህ የይሖዋ ሱፐር መሲ ወይም የበላይነት ተጣሰ፣ ተደፈረ፣ ተቋረጠ የሚባለው የእሥራኤል ሕዝብ እነዚህን የየሖዋን የአገዛዝ ሕጐች ሣይተገብሩ ወይም ሣይፈፅሙ መቅረት ከተከሰተ ብቻ ነው:: እንደዚህ ያለውን የይሖዋ ሕግን የእሥራኤል ሕዝብ ሣይፈፅም በሚቀርበት ጊዜ ሁሉ ይሖዋ እራሱ የየዘመኑን ልዕለ ኃያላን መንግሥታት እየተጠቀመ የእሥራኤልን ሕዝብ ይቀጣ ነበር:: አንድ አንዴም ለይሖዋ ብቻ ሣይሆን በየዘመኑም ለነበሩት ለዓለም ልዕለ መንግሥታት የእሥራኤል ሕዝብ አለአቅሙ እየተንጠራራ አንገብርም የሚልበትም ጊዜ ብዙ ነበር::

## ለዓለም ልዕለ ኃያላን መገበር የይሖዋን የበላይነት አይሽርም

ለዓለም ልዕለ ኃያላን የእሥራኤል ሕዝብ መገበር ወይም የቄሣርን ለቄሣር መስጠት የይሖዋን የሉዓላዊነትን ሕግ የሚጥስ ወይም የሚደፍር አይደለም:: የዓለሙ ልዕለ ኃያል መንግሥት እስከ አሁን እየተገለፀ የመጣው የይሖዋ የበላይነት መገለጫ የሆነው የሃይማኖታቸውን ሕግ ካልከለከለ በስተቀር የእሥራኤል ሕዝብ እንዲገብሩለት መጠየቅ የይሖዋን ሉዓላዊነት መቃወም አይደለም:: ስለዚህ እሥራኤሎች የይሖዋን የበላይነት መገለጫ የሆነ ሕጋቸውን እያከበሩ ለዓለሙ ልዕለ ኃያላን

መንግሥት እንደማንኛውም የምድር ታናናሽ ነገሥታት ይገብሩ ነበር:: እንዲህም ስለአደረጉ የይሖዋን ሕግ ጣሱ አይባልም:: ይሖዋም የራሱን የበላይነት መገለጫ የሆነውና የነበረውን የእሥራኤልን ሕዝብ ሕግ እንዲሻር ወይም እንዲቀር እስከአላደረጉ ወይም ሕጋቸውን እስካልተቃወሙ ድረስ ለዓለም ልዕለ ኃያላን መንግሥታት እንደማንኛውም የዘመኑ ገባር መንግሥታት እንዲገብሩ ያዛቸውም ነበር:: ለምን ቢባል በእሥራኤል አለመገበር ይሖዋ በእነርሱ ላይ ያቋቋመው የእራሱ የበላይነት መገለጫ የሆነው ሥርዓቱ እንዳይፈርስበት ነው::

በ607 ዓመተ ዓለም የእሥራኤል ሕዝብ እንደሚገባ ለዓለሙ ልዕለ ኃያል ንጉሥ ለናቡከደናዶር ግብር አንገብርም፣ አሻፈረኝ ባሉ ጊዜ፣ ይሖዋ በእነርሱ ላይ ዘርግቶ የነበረው የበላይነት መገለጫ የሆነው የአሪት የአገዛዝ ሕጉ እንዳይፈርስበት ሲል በነቢዩ ኤርምያስ አማካኝነት እንደሚከተለው አዝዞአቸው ነበር:- «በባቢሎን መንግሥት ቀንበር በታች አንገቱን ዝቅ የማያደርገውን ሕዝብና መንግሥት፣ ያን ሕዝብ በእጁ እስካጠፋው ድረስ በሴፍና በራብ፣ በቸነፈርም እቀጣለሁ ይላል እግዚአብሔር::» ትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 27 ቁጥር 8::

ከላይ ከተመከትነው አኳያ የእሥራኤል ሕዝብ ለኃያሉ ልዕለ መንግሥት ወይም ንጉሥ ለናቡከደናጾር በሰላም ቢገብሩ ኖሮ ይሖዋ በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ዘርግቶ የነበረው የራሱ የአስተዳደር ሥርዓት በ607 ዓመተ ዓለም አይፈርስም ነበር:: ነገር ግን በነገሥታት ዜና መዋእል ካልእ ምዕራፍ 24 እና ምዕራፍ 25 እንደምንአነበው ይሖዋ በእሥራኤል ላይ ዘረግቶ የነበረው የአገዛዝ ሥርዓቱ የእሥራኤል ለልዕለ ኃያል



መንግሥት አለመገበር የተነሣ በ607 ዓመተ ዓለም ለጊዜው ተቋረጠ:: አንድ አንድ የይሖዋ ምስክር ነኝ ባዮች የእሥራኤል ሕዝብ ከ607 ዓ.ም. በፊት ለማንኛውም ሌላ ልዕለ ኃያል መንግሥት አይገብሩም ነበር የሚለው የግለሰቦች የተሳሳተ አመለካከት ነው::

እንዲሁም የግብፅ መንግሥት ከ607 ዓመተ ዓለም በፊት ይሖዋ አምላካቸው የበላይ ገዥአቸው ሆኖ ሣለ እሥራኤሎችን ያስገብር ነበር፣ እንዲሁም አንገብርም የሚለውን መሪ፣ ራሱ የግብፅ መንግሥት ከሥልጣን እያወረደ በምትኩ ሌላ ንጉሥ ይሾም ነበር:: ይሖዋም ቢሆን አምልኮቱ እንዳይነካበት ለልዕለ ኃያላን ነገሥታት እንዲገብሩ ያዛቸው ነበር:: ስለዚሁ ታሪኩን ቀጥለን እናነባለን:- «ፈርኦን ኒካዑም የኢዮሲያስን ልጅ ኤልያቄምን በአባቱ በኢዮሲያስ ፈንታ አነገሠ፣ ስሙንም ኢዮአቄም ብሎ ለወጠው:: ኢዮአክሲንም ወስዶ ወደግብፅ አፈለሰው::» መጽሐፈ ነገሥት ካልእ ምዕራፍ 23 ቁጥር 34-35:: ይህ የግብፅ ንጉሥ የይሖዋን የአምልኮት (Supremacy) የበላይነት ሥርዓትን አልነካም፣ ግን አልገብርም ያለውን ንጉሥ ከሥልጣኑ አውርዶ እንዴት እንዳጋዘው እንረዳለን:: ይህ ታሪክ ከ607 ዓመተ ዓለም በፊት ነበር የተፈፀመው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ 3ኛው የዓለም ልዕለ ኃያል ንጉሥ ናቡ ከደናጾር የግብፅ መንግሥት ያስገብር የነበረውን ግዛቱን ነጥቆ ለራሱ እንዲገብሩ እንዴት እንዳአደረገ በመጽሐፈ ነገሥት ዜና መዋእል ምዕራፍ 24 ቁጥር 6-7 ተመልከቱ::

በጥንቱ ዘመንም ሆነ ዛሬም ቢሆን በረቀቀ መልኩ ልዕለ ኃያል በመሆን አካባቢውን በቁጥጥሩ ሥር የሚያደርግ አሸናፊ

መንግሥት ያሸነፉትን የአካባቢ ታናናሽ መንግሥታትን ገባር እንደሚያደርጋቸው ከታሪክ እንረዳለን። በተለይ በጥንት ጊዜ እነዚህ ልዕለ ኃያላን የነበሩ ነገሥታት ገባር ካደረጉአቸው ከሕዝቡ መሪዎች የበለጠ ለሕዝብ ቀረቤታ እንዳልነበራቸው ግልፅ ነው። ስለዚህ የተወሰነ ግብር በዓመት እየገበሩ የራሳቸወን ሕዝብ እንዲያስተዳድሩ ያደርጉ ነበር እንጂ እራሳቸው ጣልቃ ገብተው ባሕላቸውንና አንዋኖር ዝይቤአቸውን አያጠፉም ነበር። እንዲህ ያለውን እርምጃ የሚወስዱት የየአካባቢ ተሸናፊ ገባር ነገሥታት ሕዝብን ቀስቅሰው ለልዕለ ኃያሉ መንግሥት አንገብርም በሚሉት ጊዜ ብቻ እንደነበር እንመለከታለን። ስለዚህ የእሥራኤል ሕዝብ በ607 ዓመተ ዓለም በናቡ ከደናጾር መጥፋት የመሪዎች የእሥራኤልን ሕዝብ አሣምፀው አለመገበር ውጤት ነበር። አምላካቸው ይሖዋ የበላይነት ሥርዓተ አምልኮቱ እንዳይፈርስ ለባቢሎን ንጉሥ እንዲገብሩ ቢያዛቸውም እምቢ አሉ። ስለዚህ ያ የይሖዋ አምልኮት የተቋረጠው በናቡ ከደናጾር ጥፋት አልነበረም። ወይም ናቡከደናጾር ከዛሬ ጀምሮ የይሖዋን ሕግ አታክብሩ፣ ሥርዓቱንም አትፈፅሙ ብሎ ስለአዘዛቸውም አይደለም። በዚህ መልኩ በ607 ተቋርጦ የነበረው የይሖዋ የበላይነት መገለጫ የሆነው የኦሪት ሥርዓት ሕግ በ537 ዓመተ ዓለም ነፃ ከወጡ በኋላ ተመልሶ እንደተመሠረተና ይሖዋም እንደተቀበለ እንረዳለን።

<u>የዳግም ቤተመቅደስ ምሥረታ</u>

ከዚህ በላይ እንዳየነው በ607 ዓመተ ዓለም በናቡ ከደናጾር ጥፋት ሣይሆን፣ ወይም ደግሞ በራሱ በይሖዋ፥ በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የበላይነቱን ማንገሥ ፍላጐት ማጣት ሣይሆን፣



በእሥራአል ሕዝብ መሪዎችና በእሥራኤል ሕዝብ ፍላጐት ማጣት የተነሣ ከ607 ዓመተ ዓለም ጀምሮ የይሖዋ የኦሪት ሕግ ሥርዓት ፈረሰ። የይሖዋ የኦሪት ሕግ ሥርዓት ፈረሰ ማለት ይሖዋ በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ዘርግቶ የነበረው የበላይነት መገለጫ ሥርዓቱ ቀረ ማለት ነው። ታዲያ የኦሪት ሕግ ሥርዓት ከ607 ዓመተ ዓለም ጀምሮ ተቋርጧል ለማለት የሚያስችለን ምክንያት አለን? በፍጹም የለንም። ምክንያቱም ይህ ይሖዋ በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ዘርግቶ የነበረው የበላይነቱ መገለጫ የሆነውን ሥርዓት የእሥራኤል ሕዝብ ለልዕለ ኃያላን ነገሥታት ካለመገዛት ወይም አለመገበር ውጭ ለሁልጊዜ እንዲፈርስ ወይም ፈርሶ እንዲቀር ያደረገውና የሚያደርገውም ኃይል እስከ 70 ዓ.ም. ስለአልተነሣ ነው። ስለዚህ የእሥራኤል ሕዝብ በየዘመኑ ለሚነሡት ልዕለ ኃያላን መንግሥት እየገበሩ፣ እራሳቸውን ለይሖዋ ሥርዓት ካስገዙ ይሖዋ ሥርዓቴ በእናንተ ላይ እንደገና አይዘረጋም ስለአላለና ስለማይልም ነው። ስለዚህ ፈርሶ የነበረው የይሖዋ የበላይነት (Supremacy) መገለጫ የሆነው የኦሪት ሕግ እሥራኤል ከስደት በ537 ዓመተ ዓለም ወደ አገራቸው ተመልሰው ቤተመቅደሳቸውን እንደገና ሠርተው፣ ሥርዓቱን ማካሄድ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ እስከ 70 ዓ.ም. ድረስ እንደገና ተዘርግቶ ነበር። ኢየሱስም ቢሆን ያንን ሥርዓት አክብሯል። እንግዲህ እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባን ነገር ቢኖር በልዕለ ኃያላን ጣልቃ ገብነት የእሥራኤልን ሕዝብ እንዲገብርላቸው ማስደረግ የይሖዋን የበላይ አገዛዙን ወይም ሉዓላዊነቱን የሚያስቀር ቢሆን ኖሮ የበላይነቱ ገና ድሮ ከ607 ዓመተ ዓለም በፊት ይቋረጥ ነበር። በዚህ ሐሳብ ላይ

ያተኮርኩበት ምክንያት ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ ወንድም ፋሲል እና ወንድም በየነ የተባሉ ምስክሮች ሊያነጋግሩኝ ቤቴ መጥተው በውይይታችን ወቅት እሥራኤሎች እስከ 607 ዓመተ ዓለም ለማንኛው ምድራዊ ልዕለ ኃያል መንግሥታት አይገብሩም ነበር ብለው ስለአሉ ነው:: ነገር ግን ከ607 ዓመተ ዓለም በፊት የእሥራኤል ሕዝብ በየጊዜያቱ ለነበሩት ልዕለ ኃያላን ነገሥታት ይገብሩ እንደነበሩ ተሸክሞ ከሚዞሩት መጽሐፍ ቅዱሳቸው ሐቁን እንዲገነዘቡ ለማሳሰብም ነው::

ከዚህም በላይ በ607 ዓመተ ዓለም ተቋርጦ የነበረው የይሖዋ (Supremacy) የበላይነት ከ537 ዓመተ ዓለም በኋላ እንደገና ተመልሶ መዘርጋቱን የሚገልፅ ማስረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን:: ይህም ማለት በ607 ዓመተ ዓለም ተቋርጦ የነበረው የይሖዋ የበላይነት መገለጫ የአገዛዝ ሥርዓት 2520 ዓመታት ከቆየ በኋላ በ1914 ዓ.ም. ተመሠረተ የሚሰው የምስክሮቹ ትምህርተ ሃይማኖት ውሸት መሆኑን የሚገልጽ ነው:: እንዲህ እናነባለን:-

«ከዚህ ሥፍራ ወደ ከለዳውያን ምድር የሰደድሁትን የይሁዳን ምርኮ ለበጐነት እመለከተዋለሁ:: ዓይኔንም ለበጐነት በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ፣ ወዲዚህችም ምድር እመልሳቸዋለሁ፤ እተክላቸዋለሁ እንጂ አልነቅላቸውም:: እኔም እግዚአብሔር /ይሖዋ/ እንደሆንሁ የሚያውቅ ልብ እሰጣቸዋለሁ:: በፍጹም ልባቸውም ወደ እኔ እመለሳሉና፣ ሕዝብ ይሆኑኛል፣ እኔም አምላካቸው እሆናቸዋለሁ::» ኤርምያስ ምዕራፍ 24 ቁጥር 4-7

ልክ በኤርምያስ 25 ቁጥር 10-12 በተነገረው ትንቢት መሠረት 70 ዓመት ከተፈፀመ በኋላ በ537 ዓመተ ዓለም ወደ



አገራቸው ተመልሰው በዘሩባቤል መሪአቸው እየተመሩ የይሖዋን መለኮታዊ አገዛዝ ሥርዓት እንደገና ገንብተዋል:: እርሱም እንደገና አምላካቸው ሆነዋል:: ከታሪክም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አንፃር በተገለፁት እውነታዎች ሁሉ ምክንያት የይሖዋ መለኮታዊ አገዛዝ ከ537 ዓመተ ዓለም እስከ 70 ዓ.ም. ድረስ አልተቋረጠም ነበር:: ስለዚህ የይሖዋ የበላይነት በ537 ከተመሠረተ በኋላ ሳይቋረጥ ለ607 ዓመታት ቆይተዋል:: ከ607 ዓመተ ዓለም በፊት በየጊዜ ለነበሩት ልዕለ ኃያላን ነገሥታት ግብር እየገበሩ፣ ነገር ግን የይሖዋ መለኮታዊ ሕግ (Theocratic law) እየጠበቁ ኖረዋል:: ይህም ማለት የይሖዋ የበላይ (Supremacy) ሉዓላዊነቱን አከብረዋል ማለት ነው:: የራሳቸውን የውስጥ አስተዳደር ሣንሐድሪን በተሰኘው ፍርድ ቤታቸው እራሳቸውን በራሳቸው እየዳኙ፣ የሙሴን ሕግና ሥርዓት አስፈጻሚ ባለስልጣናት ሁሉ ከላይ እስከታች እራሳቸው ሾመው፣ ከ600 ባላነሠ ሕጋቸው እየተመሩ ኖረዋል:: በዚህ መልኩ የበላይ አምላካቸው የነበረ ይሖዋም፣ ከስደት በኋላ ማለት ከ537 ዓመተ ዓለም በኋላም ተመልሶ የበላይ አካል አምላካቸው ሆነዋል:: ይህንን የይሖዋ ልዓላዊነት መገለጫ የሆነውን ሥርዓታቸውን ከ537 ዓመተ ዓለም ጀምሮ እስከ 70 ዓ.ም. ድረስ ማንም አልከለከላቸውም ነበር:: ይህ ታሪካዊ ሐቅ ነው፤ እርግጥ ከ607 ዓመተ ዓለም ጀምሮ እስከ 537 ዓመተ ዓለም ባለው ጊዜ ውስጥ ለ70 ዓመታት በራሳቸው በእሥራኤል ሕዝብ ጥፋት የይሖዋ የበላይነት መገለጫ የነበረ ሥርዓታቸው ፈርሶ ነበር:: በእነዚህ ሥርዓቱ በፈረሰባቸው 70 ዓመታት ውስጥም ቢሆን ኢየሩሳሌም ሕዝብ አልባ፣ እንዲሁም ሰው አልባ ነበረች እንጂ ማንም ረግጦ

የገዛት ምድራዊ ኃይል አልነበረም:: ነገር ግን ከላይ እንደተመለከትነው በ607 ዓመተ ዓለም ጠፍቶ የነበረው የይሖዋ የበላይነት መገለጫ የነበረው ሥርዓት እንደገና በ537 ዓመተ ዓለም ተመሥርቶ እስከ 70 ዓ.ም. ከቆየ በኋላ በሮም ወታደሮች ጠፍተዋል:: ከዚያ በኋላ ኢየሩሳሌምን አሕዛብ እየረገጠ መግዛት ጀመረ:: ስለዚህ ኢየሩሳሌምን ኧሕዛብ እየረገጣት መግዛት የጀመረው ከ607 ዓመተ ዓለም. ሣይሆን ከ70 ዓመተ ምሕረት ጊዜ ጀምሮ ነው:: እስከመቼ? ወይም ለስንት ዘመናት ኢየሩሳሌም በአሕዛብ ተረገጠች? ለዚህ ጥያቄ መልሱ ከ70 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1948 ወይም 1967 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ድረስ ነው:: በሌላ አነጋገር በትንቢቱ መሠረት እሥራኤል ወደ አገሩ በተመለሰ ጊዜ ነው:: ወይም ደግሞ በኢሳያስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 11 የተጻፈው ትንቢት መፈፀም በጀመረ ጊዜ ነው:: ይህ ትንቢት ምን እንደሚል ቀጥለን እንመልከት:- «በዚያም እንዲህ ይሆናል:- የቀረውን የሕዝቡን ቅሬታ ከአሦር፣ ከግብፅ፣ ከጳትሮሲና ከኢትዮጵያ፣ ከኤላምና ከሰኦር፣ ከሐማትም፣ ከባሕርም ደሴቶች፣ ይመለስ ዘንድ ጌታ እንደገና እጁን ይገልጣል» ትንቢተ ኢሳይያስ 11 ቁጥር 11 በዚህ ትንቢት መሠረት ወቅቱ በደረሰ ጊዜ በትንቢቱ መሠረት ከአገራችን ከኢትዮጵያም በዘመቻ ጊዲዮን የፈላሻዎች ወደ እሥራኤል መመለስ የሚዘነጋ አይደለም:: ከሁሉ የሚያሳዝነው እውነታን እያወቁ በጉቻቸውን ለማሞኘት ሲሉ ብቻ የይሖዋ ምስክሮች በኢንሣይት ኦን ኢስክርፕቸው የመጀመሪያ ቮሊዩም ገፅ 134 እንዲህ ያሉት ነገር ነው:-



«All of this gives strong reason for **believing that the** lengthy vision and its interpretation were included in the book of Daniel because of their revealing the duration of appointed times of the nations and the time for the establishment of God's kingdom by his Christ." Insight on the scriptures first volume page 134. ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ሣይኖር ቃላትን በማሳመር ብቻ በናቡከደናጾር ላይ የተጣለው የቅጣት ገደብን የአምላክ መንግሥት የምትመሠረትበት ጊዜ የሚያመለክት ነው ማለት አሣዛኝ ነው:: ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ከኢሳየያስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 11 ትንቢት አንፃር እሥራኤል እንዴት ወደ አገሩ ሊመለስ ቻለ? ትንቢቱስ እንዴት ተፈፀመ? የአሕዛብ ዘመን ርዝመት በእርግጥ 2520 ዘመን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመለከተውን መረጃ ቀጥለን እንመልከት:-

<u>የትንቢቱ መፈፀም</u>

ከዚህ በላይ እየተነጋገርን እንደመጣነው የአሕዛብ ዘመን የሚያበቃት ጊዜ መጣ ወይም እሥራኤላዊ ያልሆነ ዘር ኢየሩሳሌምን የማይገዛበት ዘመን መጣ:: የአሕዛብ ዘመን የተጀመረው በ70 ዓ.ም. ነበር:: አሁን ደግሞ ይህ የአሕዛብ ዘመን ግዛት የሚያበቃበት ዘመን መጣ:: ወቅቱ ደረሰ::

<u>የትንቢቱ መፈፀም</u>

እሥራኤል በትንቢቱ መሠረት ወደ ትውልድ ሀገሩ የሚመለስበት ዘመን መጣ፤ የትንቢቱ መፈጸም ዋዜማ ተከሰተ:: እንዴት? በ1882 ዓ.ም. በራሺያ በሚኖሩት የአይሁድ ሕዝብ ላይ በጣም ከፍተኛ ስቃይ ደረሰ:: እንዲሁም እንደዚህ ያለ

በሩማኒያም በሌሎችም አገሮች ባሉት እሥራኤሎች ላይ ሥቃይ በረከተ:: በጣም መኖር ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ ከያሉበት በተለይም ከራሺያ በሆነ መልኩ እያመለጡ ወደ ትውልድ አገራቸው መመለስ ጀመሩ:: እነዚህ ወደ አገራቸው ለመመለስ የቻሉት አይሁዶች ወደተመለሱበት አገር ከሚኖሩት አረቦች ሕዝብ በጥሩ ገንዘብ መሬት እየገዙ መስፈር ጀመሩ:: በመጨረሻም በቁጥር በርከቶው አንድ ጉራ ሕዝብ ከመሆናቸውም በላይ ቀደም ብለው በአካባቢው ይኖሩ ከነበሩት አረቦች ሁሉ በሁለገብ እንቅስቃሴአቸው እየተሻሉ መጡ:: አይሁዶች በዘመናዊ እርሻ ጭምር እየበለፀጉ ሲሔዱ መሬት ሻጮቹ አረቦች በኢኮኖሚ ከስደት ከተመለሱ አይሁዶች በታች መሆን ጀመሩ::

ስለዚህ ይህንን ሁኔታ የተመለከቱት የአረብ ከበርቴዎች በዚያን ዘመን ኢየሩሳሌምን ለሚያስተዳድረው ለኦትማን መንግሥት እሥራኤል ከሌላ አገር እየተሰደደ ወደ ፖለስታየንና ኢየሩሳሌም እንዳይገቡ ይከለከል ዘንድ አቤቱታ አቀረቡ:: ይህ አቤቱታ የቀረበው በ1891 ዓ.ም. ነበር:: የቱርክ ኦትማን መንግሥት ከ1500 ዓ.ም. እስከ 1914 ዓ.ም. ድረስ አካባቢውን ይቆጣጠር ስለነበር ነው አቤቱታው የቀረበለት::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአውስትሪያ እውቅ ጋዜጠኛ የነበረው (Theodor Hezl) ቴኦዶር ሔርዝል አይሁዶች ወደ አገራቸው እንዳይመለሱ መከልከል የለባቸውም:: አሁን በዓለም ላይ የሚታየው የአይሁዶች ችግር ሊፈታ የሚችለው አይሁዶች ወደፖሊስቲና ተመልሰው ወይም ሌላ አገር ለብቻቸው



ተሰጥቶአቸው መንግሥት ካቋቋሙ ብቻ ነው እያለ ከ1896 ዓ.ም. ጀምሮ በጋዜጣወ ላይ እየጻፈ ያሰራጭ ጀመር::

ይህ የቴኦደር ሔዜል አቤቱታ በዚህ ላይ እንዳለ በ1914 ዓ.ም. 1ኛው የዓለም ጦርነት ተነሣ:: በጦርቱም የቱርክ መንግሥት ተሸንፎ አካባቢውን የእንግሊዝ መንግሥት በበላይነት ማስተዳደር ጀመረ:: በዚህ መልኩ የኦትማን መንግሥት ቦታውን ከለቀቀ በኋላ በ1917 ዓ.ም. የእንግሊዝ መንግሥት ለእሥራኤል ሕዝብ መንግሥታቸውን የሚያቋቁሙበት ቦታ ያስፈልጋቸዋል ብሎ መግለጫ አወጣ::

በአዲሱም የእንግሊዝ አስተዳደር ሥር የእሥራኤል ሕዝብ ወደ ፖሊስታይን መጉረፉን ቀጠለ:: አሁንም አረቦች የእንግሊዝ መንግሥት አይሁዶች እንዳይመለሱ መከላከል መቻል ነበረበት:: ዝም ብሎ ለምን ያስገባቸዋል በሚል ረብሻ አነሱ:: በመሐሉ 2ኛው የዓለም ጦርነት ተነስቶ በይበልጥ አይሁዶች በየቦታ እየተሰደዱ ተገደሉ:: የጀርመኑ ሂትለር ብቻ 6 ሚሊዮን አይሁዶችን ፈጀ:: በትንቢቱ መሠረት ተሳክቶላቸው ወደ ትውልድ አገራቸው ከመመለሳቸው በፊት የመጨረሻው የበቀል ቅጣት (The last dose of their punishment) መቀበል ነበረባቸው:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት ተዳክሞ ቅኝ ግዛቶቹን በተለይም ረብሻ የሚበዛበትን አካባቢ ማስተዳደር ስለተሳነው ፖሊሲታይን ለሁለት ተከፍላ በግማሹ መንግሥታቸውን እንዲያቋቁሙበት ለእሥራኤል ሕዝብ ይሰጥ ብሎ ለተባበሩት መንግሥታት ማመልከቻ ፃፈ:: የተባበሩት መንግሥታትም በእንግሊዝ መንግሥት የቀረበውን ሐሳብ በ1947 ዓ.ም. ተቀብሎ አፀደቀ:: እሥራኤልም በ1948 ዓ.ም. በተሰጡት

አካባቢ የራስዋን መንግሥት መሠረተች። ይህንን ያዩ የአረብ መንግሥታት ጦርነት ቢከፍቱባትም አሸነፈቻቸው። ከጊዜ በኋላ በጀማል አብዱል ናስር አስተባባሪነት ከ7 ያላነሱ የአረብ አገሮች በ1967 በእሥራኤል ላይ ጦርነት ከፈቱ። ይህ የ6 ቀን ጦርነት ተብሎ የሚታወቀው ነው። በዚህ ጦርነት እሥራኤል አንፀባራቂ ድል ተጎናጽፋ ሲና ፔኒሱላን ከግብፅ፣ ከሶሪያ ጎላን ሐይት የተባለውን አካባቢ፣ ከዮርዳኖስ ደግሞ ዌስት ባንክን ነጠቀች። በዚህ መልኩ እና በትንቢቱ መሠረት እሥራኤል ተወለደች። ይህም በራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ 12 ላይ ዮሐንስ የእሥራኤልን መንግሥት መወለድ በአንዲት እርጉዝ ሴት በማስመሰል እንደዚህ ብሎ ጽፈዋል።

«ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ፣ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ አሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች። (ዮሐንስ 12 ከዋክብት ሲል 12ቱን የእስራኤል ነገዶችን ሲያመለክት ነው) እርስዋም ፀንሳ ነበር። በምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች። ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፣ እነሆ ታላቅ ቀይ ዘንዶ ሰባት እራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩበት፣ ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደችው ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባለች ሴት ፊት ቆመ።» ራዕይ 12 ከቁጥር 1-6። ይህ የእሥራኤል ሕዝብ ወደ አገራቸው ሲመለሱ ምን እንደሚገጥማቸው በምሳሌአዊ አነጋገር የተነገረ ትንቢታዊ ንግርት ነው። ቀጥለን እንመልከት:- አይሁዳዊ የሆነው ባለራዕይው ዮሐንስ ለወደፊት በስደት ላይ ባሉት ዘሮቹ ላይ ምን ዓይነት ችግር እንደሚደርስ የተነበየው ትንቢት ነው። የይሖዋ ምስክሮች ግን ይህ ትንቢት የሚናገረው



ስለድርጅታችን ነው ይላሉ። እንደዚህ ባለመልኩ ትምህርት አልባ፣ የሃይማኖት ልምድ አልባ የሆኑ እና ማጣፊያ ያጠራቸው ልበቢስ በጉቻቸውን ያታልሉበታል። ዮሐንስ ባለራዕይው ስለወገኑ በተነበየው በዚህ ትንቢት የእሥራኤልን ሕዝብ በእርጉዝ ሴት ያስመስላል። ይህ በሴት የተመሰለው የእሥራኤል ሕዝብ መንግሥታቸውን ለማቋቋም በ1948 ዓ.ም. በተነሱ ጊዜ ይህንን ዓለማቸውን ወይም ሐሳባቸውን ለማጨናገፍ ዮሐንስ በአውሬ በመሰላቸው የአካበቢ መንግሥታት ችግር ደረሰባቸው። ዮሐንስ ባለራዕይው ወንድ ልጅዋን በመውለድ በምጥ ጣር በተያዘችው ሴት የመሰላቸውም ከዚሁ ታሪካዊ ነገር የተነሣ ነው። ሴቲቷን የምጥ ጣር የያዛት ወንድ ልጅን እንድትወልድ ብላ ነበር። ይህች ሴት የምትወልደውን ወንድ ልጅ ዮሐንስ ባለራዕይው በእሥራኤል መንግሥት አስመስሏል። ስለዚህ ወንዱ ልጅ በ1948 ዓ.ም. ያቋቋሙት መንግስታቸው ምሳሌ ነው። ወላዲቷ ሴት ደግሞ የእሥራኤል ሕዝብ ምሳሌ ናት። ይህ የእሥራኤል ሕዝብ ወይም የምትወልደው ሴቲቷ እጅግ በጣም ተጨንቃ ጮኸቷን እንደአሰማች ባለራዕይው ዮሐንስ ይገልፃል። ምክንያቱም ገና ሀ ብሎ መንግሥታቸውን ማቋቋም እንደጀመሩ ዮሐንስ በቀይ ዘንዶ የመሰላቸው የአካባቢው መንግሥታት ይህ የእሥራኤል ሕዝብ የመሠረተውን መንግሥት ለማጥፋት ስለተነሱ ነው። በዮሐንስ አገላለጥ «ሴቲቷ የወለደችውን ወንድ ልጅ ለመብላት ተነሱ።» በዚህ ትንቢት መሠረት የአካባቢ መንግሥታት ጦርነት በከፈቱባቸው ጊዜ የእሥራኤል ሕዝብ አሸነፈ።

ይህንን በ1948 ዓ.ም. የተቋቋመ በወንድ ልጅ የተመሰለው መንግሥታቸውን የእሥራኤል ሕዝብ ጠብቆ የማቆየት ብቃታቸወን ሲገልጽ ባለራዕዩው ዮሐንስ እንደዚህ ይለናል:- «ለሕዛብን ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ ወለደች:: ልጅዋም ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ተነጠቀ::» ራዕይ ምዕራፍ 12 ቁጥር 5ኛ ተመልከቱ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ገዢዎች በጨረቃ፣ በፀሐይ፤ ብለማይ፣ በአጠቃላይ በከፍተኛ የተፈጥሮ ነገሮች ይመስላሉ:: ተራራዎች በነገሥታትም እንደሚመሰሉ ቀደም ብለን በዚሁ መጽሐፍ ተመልክተናል:: በጥንት ዘመን ደግሞ ገዢዎች የሆኑ ባለስልጣናት እራሳቸውን እግዚአብሔር ብለው ይጠሩ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ እንረዳለን:: ለምሳሌ በሙሴ መጽሐፍ ዘፍጥረት ምዕራፍ 4 ቁጥር 26 ላይ እነዚህ ገዢዎች «እግዚአብሔር እየተባሉ ወይም በእግዚአብሔር ስም መጠራት የጀመሩትን ወቅት ይጠቁመናል:: በዚያም ሆነ በዚህ ይህ በራዕይ ምዕራፍ 12 ቁጥር 5 ላይ ያለው የዮሐንስ አገላለጥ የእሥራኤል ሕዝብ የሚያቋቁመው መንግሥት የማይበገር ጠንካራ መንግሥት እንደሚሆን የሚገልጽ ነው::

የይሖዋ ምስክሮች ከጥቅም አንፃር ከተቃኘው አተረጓጎማቸው በመነሣት እርጉዟ ሴት የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት ነው፣ ወንድ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ የበላይነት የሚመራ የ144 ሺህ በ1914 ዓ.ም. ትንሣኤ አግኝተው በሰማይ ላይ የመንገሥ ትንቢት ነው:: ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት የማይበገር ስለሆነ ለወደፊት በአርማጌዶን የምድር ነገሥታትን ሁሉ የሚያጠፋ ይሆናል ይላሉ:: ይህ በፍጹም፣



በፍጹም ውሸት ነው:: የጥቅሶችን ከዚያም ከዚህም እያምታቱ ወይም እያጋጩ ሞደሌክ መሥራት ተግባር ነው:: እንደገና እየደገምን አንድ እውነትን በጋራ እንመልከት:-

1ኛ ኢየሩሳሌም በ607 ዓመተ ዓለም በናቡከደናጾር የጠፋች መሆኑ የታሪክ ሐቅ ቢሆንም እሥራኤሎች በ537 ዓመተ ዓለም ወደአገራቸው ተመልሰው የድሮ አምልኮአቸውን እንደድሮ አስከመሠረቱበት ዘመን ድረስ ለ70 ዓመታት በሕዝቅኤል ትንቢት ምዕራፍ 21 ቁጥር 27 መሠረት ኢየሩሳሌም ባድማ ወይም ሰው አልባ ነበረች:: ስለዚህ በአሕዛብ ተረግጣ አልተስተዳደረችም:: በመጽሐፈ ነገሥት ካልእ ምዕራፍ 25 ቁጥር 26 ላይ እንደምንአነበው ከሆነ ከ607 ዓመተ ዓለም በኋላ ናቡከደናጾር እንደገና መጥቶ ያጠፋናል በሚል ፍራቻ የእሥራኤል ሕዝብ ከሕፃን እስከ ታላቁ ድረስ ሕዝቡ ሁሉ አገሪቱን ትተው ወደ ግብፅ አንደተሰደዱ እንዘከራለን፡ ስለዚህ ኢየሩሳሌም ሰው አልባ ሆነ መሪና ተማሪ ባልነበረበት ለ70 ዓመታት ቆየች እንጂ በእሥራኤልም ሆነ እሥራኤል ባልሆነ ሕዝብ አልተገዛችም ነበር:: ኢየሱስም ቢሆን በሉቃስ 21 ከቁጥር 20-24 ስለ ኢየሩሳሌም ጥፋት በተነበየው ትንቢት ላይ ለወደፊት የሚሆን መሆኑን በማመልከት ወደ አሕዛብ ሁሉም እንደሚማረኩ፣ ከዚያ በኋላ ኢየሩሳሌምን አሕዛብ ረግጦ እንደሚገዛትና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአሕዛብ ግዛት እስከአበቃ ወይም እስከተፈፀመ ድረስ እሥራኤላዊ ባለሥልጣን ኢየሩሳሌምን የማይገዛ መሆኑን መግለጡን ወይም ማስተማሩን እንገነዘባለን::

2ኛ. የኢየሩሳሌም ለመጀመሪያ ጊዜ አይሁድ ባልሆነ ሕዝብ መገዛት በትንቢቱ መሠረት የተጀመረው በ607 ዓመተ ዓለም ሣይሆን በ70 ዓመተ ምህረት እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም ሆነ ከሕዝበ ዓለም ታሪክ እንረዳለን።

3ኛ. ይህ በ70 ዓ.ም. የተጀመረው የአሕዛብ ዘመን የእሥራኤል ሕዝብ በትንቢተ ኢሳያስ 11 መሠረት ወደ አገራቸው ከያሉበት ተሰብስበው ከተመለሱና በወንድ ልጅ የተመሰለ መንግሥታቸውን እስከ መሠረቱት ዘመን እስከ 1948 ዓ.ም. የነበረው ጊዜን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።

4ኛ. ስለዚህ የአሕዛብ ዘመን ምስክሮቹ እንደሚሉት 2520 ዘመናት ርዝመት ያለው ሣይሆን ከ1878 ወይም ከ1897 ዓመታት ርዝመት የማይበልጥ ነው። በሣይንሣዊ የጅኦግራፊ ጥናት ላይ ያልተመሠረተ የዓመቱ ቀኖችን እንደ እነርሱ በ30 ቀናት ሒሳብ እንኳን እንቀበል ብንል ውሸትን እያወቅን መቀበላችን ነው። የዓመቱ ቀኖች 364½ኛ ነው። በዚህ ሂሳብ ስሌትም ቢሆን 2520 ዘመን ሣይሆን 2549 ዓመታት ይሆን ነበር። ስለዚህ አቆጣጠራቸውም ስሕተት ፍልስፍናቸውም ውሸት ነው።



## ምዕራፍ 14

## እንዴት ወደዚህ ድርጅት እንደገባሁ

በእኛ አቆጣጠር ከ1945 እስከ 1946 ዓ.ም. ድረስ ሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤት እየተማርኩ ከእህቴ ጋር ፖፖላሬ የሚባለው ሰፈር እኖር ነበር። አቶ ከበደ ተሰማ የሚባል የእህቴ ጐረቤት ሰው ነበር። ይህ ሰው ከይሖዋ ምስክሮች አንዱ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን በቁም ነገር ጠርተውኝ ከተማርክ በኋላ በምን ዓይነት ሥራ መሰማራት ትፈልጋለህ? አሉኝ። አባባላቸው ምን አይነትን ሙያ ለማጥናት ትፈልጋለህ? ማለታቸው እንደሆነ ገባኝና እጩ የክብር ዘበኛ ካዴት ገብቼ እስከመጨረሻ በሚሊተሪ ሣይንስ ሙያ መካን እፈልጋለሁ አልኩአቸው። ከዚህ በኋላ ምንም ሣይጠይቁኝ በዚሁ ተለያየን። ያኔ የሚሊተሪ መኮንኖችና እጩ የካዴት ምሩቃን ተማሪዎች በሠፈራችን በብዛት ስለነበሩ፣ እንደነርሱ ለመሆን ምኞት ነበረኝ። የትምህርት ቤት ባልንጀሮቼም የኰሎኔል ልጆች ነበሩ። ለምሳሌ ኰሎኔል ወርቁ የሚባሉ መኮንን ልጆች ነበራቸው። አንዱ ቀፀላ ወርቁ ሌላው ሽፈራው ወርቁ ይባላሉ። የእነርሱም የእኔው ዓይነቱ ምኞት ነበር። እነዚህ ሁለቱ ባልንጀሮቼ ምኞታቸው ተሳክቶላቸው እስከ ኰሎኔል ከፍተኛ የሚሊተሪ ማዕረግ ደረጃ ላይ ነበሩ። አሁን ይህንን መጽሐፍ ስጽፍ በሕይወት ይኑሩ አይኑሩ የማውቀው ነገር የለም። ነገር ግን ይህንን ያነሳሁት የዚያን ጊዜ ምኞቴ በአካባቢው ሁኔታ እንዴት ተስቤ እንደነበር እና ግን በምኞቴ ሣልገፋበት የቀረሁበትን ምክንያት ለመግለፅ ነው። እንዲሁም ደግሞ አባቴ ከማጨው ጦርነት በፊት ዛሬ ፖሊስ እንደሚባለው ዓይነት አገልግሎት የሚሰጥ የአራዳ ዘበኛ ሆኖ ያገለግል ነበር።

እነካርል ማርክስ በኮሚኒስት ማኒፌስቶው የጠራጊ ልጅ ጠራጊ የዘበኛ ልጅ ዘበኛ እንደአለው ዓይነት ሆነና እኔም የክብር ዘበኛ የመሆን ምኞቴ ከፍተኛ ነበር።

የእህቴ ጉረቤት በተባለው በአቶ ከበደ ተሰማ ቤት በሣምንት አንድ ጊዜ እየመጣ ሰዎችን ሰብስቦ የሚሰብክ አንድ ፈረንጅ (FRANK OR FERENJI)ሰው ነበር። ከእለታት አንድ ቀን አቶ ከበደ አለወትሮው ወደ ቤት ጠሩኝ። እኔም ጥሪአቸውን አክብሬ ወደ ቤታቸው ሔድኩ። ቤቱ ውስጥ ስገባ ብዙ ሕዝብ ተሰብስበዋል። ከላይ እንደተባለው ፈረንጁ አለ። አቶ ከበደ ከሁሉ በፊት ከፈረንጁ ጋር አስተዋወቁኝ። ይህ አሜሪካዊ ፈረንጅ ለተወሰነ ደቂቃ በእንግሊዝኛ አወራኝ። በኋላ እንደገባኝ እንግሊዝኛ መቻሌንና አለመቻሌን ለማረጋገጥ ነበር። ከስብሰባ በኋላ አነጋግርሃለሁ ብሎ ስብሰባውን ለመምራት አንዲት ትንሽ አትሮኖስ አጠገብ ሔዶ ፊት ለፊታችን ተቀመጠ። በአማርኛ ቋንቋ መናገር ጀመረ። አማርኛው የሚገባ ቢሆንም የፈረንጅ አማርኛ አነጋገር ነበር።

ከስብሰባ በኋላ ተገናኝተን ከዚህ በፊት አቶ ከበደ ጠይቆኝ የነበረውን ተመሳሳይ ጥያቄ በመጨረሻ ላይ ጠየቀኝ። እኔም ለአቶ ከበደ የሰጠሁትን ተመሳሳይ መልስ ሰጠሁት። እርሱም እኔም ይህንን ጥያቄ የጠየኩህ ቀደም ብሎ ስለዚሁ አቶ ከበደ ስለነገረኝ ነው አለኝ። ቀጥሎ ያቀረበልኝ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስን ታምናለህ? የሚል ነበር። እኔ ያደኩበት ቤት ወይም ቤተሰብ አመለካከት መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ መኮትለክ ነው። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን ከሚሲዮኖች ጋር ማጥናት ፀረ ማርያምነት



ነው። ትንሽ በትምህርት ከመግፋቴ በፊት የእኔም እምነት እንደዚያው ቤተሰቦቼ ነበር።

ከጊዜ በኋላ ግን ከትምህርት ቤት ጓደኞቼ ጋር እሁድ እሁድ ሱዳን ኢንተርየር ሚሽን የሚባለው ድርጅት ውስጥ ሚስተር ኮልማን የሚባል ካናዳዊ ግለሰብ መጽሐፍ ቅዱስን በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያስተምር ስለነበር፣ ልጆች ሁሉ የእንግሊዝኛ ቋንቋችንን እናሻሽል እያሉ እየሔዱ ስብከቱን ይሰሙ ስለነበር፣ እኔም ከእነርሱ ጋር መሔድ ጀመርኩ። እንዲሁም ሞዝቮልድ እየተባለ ይጠራ በነበረው ድርጅት አካባቢ በአንድ ቤት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ዲስኩር /ሌክቸር/ በሣምንት አንድ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ወጣት በሆኑት ኢትዮጵያውያኖችና ፈረንጆች ይሰጥ ነበር። እኔም እንደነዚያ ወጣት ኢትዮጵያውያኖች የእንግሊዝኛ ቋንቋዬን አሻሽዬ ሌክቸር መስጠት እመኝ ነበር። ስለዚህ እንደነዚህ ካሉት ስብሰባዎች ፍጹም አልቀርም ነበር።

በዚያን ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ልክ እንደፈረንጆቹ ንግግር ያደርግ የነበረው የያኔ ወጣት የአሁኑ ዶክተር ኃይሌ እንደነበሩ አስታውሳለሁ። ዶክተር ኃይሌ ከብዙ ጊዜ በኋላ በኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ወቅት ባለስልጣን ሆነው በቴሌቪዥን መስኮት አይቻቸዋለሁ። እንደዚህ ባለመለኩ ብዙ ክትትል ካደረኩ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ፀረ ማርያም አለመሆኑንም እግረ መንገዱን ስለተረዳሁ ሚስተር ውዲ መጽሐፍ ቅዱስን ታምናለህን? ብሎ ለጠየቀኝ ጥያቄ መልሴ አዎንታዊ ሆነ። እንደ ዱሮ ቢሆን ኖሮ መልሴ አሉታዊ እንደነበር አልጠራጠርም።

## ከይሖዋ ምድራዊ ድርጅት ማገልገል ውጭ ዓላማ እንደማይኖር

ሰው ከእንስሳት የሚለየው በተሻለ መልኩ ማሰብ በመቻሉ ነው:: ሰው በዚህ የትግል ዓለም ሲኖር እራሱን ፈልጐ ማግኘትና በዓላማ ላይ የተመሠረተ ኑሮን መኖር መቻል አለበት:: በይሖዋ ምስክሮች እራስን ፈልጐ ማግኘትና በዓላማ መኖር ማለት የሚታየው የይሖዋ አምላክ ምድራዊ ድርጅት በሚሰጠው መመሪያ ብቻ እየተመሩ ይሖዋ አምላክን ማገልገል ነው:: ከዚህ ውጭ እራስን ፈልጐ ማግኘትና ለተሻለ ኑሮ በዓላማና እቅድ መመራት በዓለም ውስጥ ትልቅ ደረጃ ላይ ለመድረስ መመኘት ነው:: ይህ ደግሞ ዓለሙም ምኞቱም ስለሚያልፉ በዓለም ውስጥ ትልቅ ደረጃ ለመድረስ በትጋት መሥራት አይገባም ይላሉ:: ለጠየቀኝ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስን እንደማምን ከተረዳ በኋላ ወንድም ውዲ (Brother Woody) እንደሚከተለው ለበከኝ:-

ይህ የአንተ ምኞት በዚህች ዓለም ላይ ዝነኛ ለመሆንና ከዓለማዊ ድርጅቶች ጋር ለመራመድ የታቀደ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስን አምናለሁ ካልክ ግን የእግዚአብሔር ቃል እንደዚህ ያለውን የዓለማዊ ሥራን መምረጥን አይመክረንም:: በመጀመሪያ የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት ምዕራፍ 2 እንዲህ እናነባለን:- «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም:: ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል::» 1ኛ የዮሐንስ መልእክት ምዕራፍ 2 ቁጥር 15-17 እንዲሁም ከሌሎች ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጥቅሶችን እየጠቀሰ ይህች ዓለማችን በቅርቡ በዘመናችን ስለምትጠፋ፣ የዓለምን ዝና፣ የዓለምን ትምህርት ወድዶ ከምድራዊ የአምላክ ድርጅት መመሪያ ሥርዓት ውጭ መቆየት ውጤቱ በቅቡ በአርማጌዶን ጦርነት መጥፋት ነው አለኝ:: አንተ አባላቸው እሆናለሁ የምትለው፣ ይህ እርስበርሱ ለመጠፋፋት ጦርነትን የሚማረው የወታደር ክፍል በቅርቡ በአርማጌዶን ጦርነት እንደሚጠፋ በራዕይ ምዕራፍ 16 ቁጥር 12-16 ያለውን ተንትኖ አስረዳኝ::



ምንም እንኳን በተነገረኝ ስብከት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ያመንኩ ቢሆንም፣ እንዲሁም የተማሩት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሰዎችን ጠይቄ የመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃልነት እውነታን አረጋግጨው ስለነበር፣ ከዚህም እንደ ኘሮቴስታንቶችና ካቶሊኮች ያሉት ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔረ እውነተኛ ቃል እንደሆነ እንደሚያምኑም አውቅ ስለነበር፤ ነገር ግን ከተነገረኝ ትምህትርና ስብከት ውጭ ይኸንኑ እራሴ የማረጋገጥ ሃሳብም ሆነ ችሎታ ስለአልነበረኝ፣ በሚስተር ውዲ የተገለጠልኝ እውነት እንደሆነ አሜን ብሎ ከመቀበል ውጭ ለጊዜው የታየኝ ምንም ነገር አልነበረም::

ከዚህ በኋላ በሣምንት አንድ ጊዜ እየተገናኘን እንደሚያስጠናኝ ነገሮኝ በሣምንት በሣምንት እራሱ እየመጣ በመኪና እየወሰደኝ ያስጠናኝ ጀመር:: ከጊዜ በኋላ በባዶ ጭንቅላቴ አስፈላጊውን እጥበት አድርጐ በይበልጥ ባዶ እንዲሆን ካደረገ በኋላ በይሖዋ ምስክሮች ትምህርት እንዲሞላ አደረገ:: አንድ ዓመት ተኩል ካስጠናኝ በኋላ በሙሉ ጊዜ አቅኚነት

እንድሠራ ተደረኩ:: ሙሉ ጊዜ አቅኚ ማለት (General Pioneer) ምንም ሣይከፈለው በትርፍ ጊዜው ከ90 ሰዓቶች ያላነሰ እየሠራ በማሕበሩ የስብከት ሥራ ተሠማርቶ የሚያገለግል ሰው ነው:: ሰልጥኖ በዚህ መልኩ ማገልገል መቻል እንደትልቅ በረከትና ማዕረግም ይቆጠራል:: ከዩኒቨርሲቲ በቢኤ እንደመመረቅ ነው:: እንዲሁም በዚህ መልኩ ከሚያገለግሉት መካከል የማሕበሩን መመዘኛ የሚያሟላ ደግሞ ወደ ልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚ (Special Pioneer) ያድጋል:: ይህ ደግሞ በኤምኤ እንደመመረቅ የሚቆጠር ነው:: በእነርሱ ዘንድ ልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚ ከመሆኔ በፊት ጄኔራል ፓይኔር በሚባለው ደረጃ ላይ ሆኜ እናቴ ከተማ ውስጥ እንድማር ከቤት ኪራይ በፈቀደችልኝ 20 ብር የወር ቀለቤ አለምንም ክፍያ ለብዙ ጊዜ በነፃ አገለገልኩ:: ከጊዜ በኋላ በየጠቅላይ ግዛት ትኩስ ኃይልና ብርቱ ታታሪ ሰባኪ ለመላክ ስለፈለጉ ልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚ ሆነህ እንድትሠራ ፈቅደንልሃል የሚል ደብዳቤ ደረሰኝ:: ሚስተር ዲን ሆፕት (Dean haupt) የሚባል ዞሮ ጉብኝ ፈረንጅ ጉባኤያችንን በጉበኘ ጊዜ በዚህ ደረጃ መሥራት ይገባዋል ብሎ ሪፖርት በማድረጉ እንደሆነ ከጊዜ በኋላ ገባኝ:: በዚህ ማዕረግ የሚሠራ ሰው 150 ሰዓቶች በወር የስብከት ሥራ ላይ ማሳለፉ ከተረጋገጠ 65 የኢትዮጵያ ብር በወር እንደ እርዳታ የሚሰጠው ሰው ነው:: ከዚህ በኋላ ለእኔም 65 የኢትዮጵያ ብር ይሰጠኝ ጀመር:: በዚሁ ምክንያት ትምህርቴን ትቼ በእነርሱ የስብከት ሥራ ላይ ተሠማራሁ:: ቤተሰቦቼ በዚህ መልኩ ትምህርቴን እንደተውኩ በሰሙ ጊዜ ካቶሊክ ሆኗል ብለውኝ እጅጉን ጠሉኝ:: የስብከቱና የጉባኤ ስብሰባ ሥራ ከምሽቱ 2-3 ሰዓት አንድ አንዴ ያቆየን ስለነበር



እዚያው ካቶሊኮችህ ጋር እደር እንጂ አምሽተህ እንዳትመጣ ተባልኩ:: በዚሁ ምክንያት የጉባኤ ወንበሮችን አንዱን ከአንድ ጋር አጋድሜ የኖርኩበት ወቅትም ነበር:: በዚሁ ምክንያት አባቴ እስከ እለተ ሞቱ በአንድ ገበታ ከእኔ ጋር ሳይበላ አልፏል::

የበለጠ ችሎታን እንድንአዳብር ጠዋት ጠዋት ወደ ስብከት ሥራ ከመሰማራታችን በፊት ለ6ወሮች ያህል ከጠዋቱ 2 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት በየቀኑ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ልዩ ስልጠና ይሰጠን ነበር:: በዚህ ልዩ ስብሰባ ቡድን አባል ከነበሩት አንድ አንዶቹ ወንድም ወርቁ ካሣ፣ በኋላ የአውራ ጐዳና መሐንዲስ የነበረ፣ ወንድም ካሣሁን ገብረጊዮርጊስ በኋላ የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ኮሚሽን ፀሐፊ የነበረ፣ ወንድም አስመላሽ ገብሬ በኋላ የጥርስ ሐኪም የሆነ ወዘተ ይገኙበት ነበር:: ለትምህርት ጉጉት ስለነበረኝ ውዲ የሚባለውን አስፈቅጄ ማታ ማታ የንግድ ሂሳብ አያያዝና የእንግሊዝኛ ቋንቋን ያስተምሩ ስለነበር በነፃ እማር ነበር:: ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚ ስለሆንኩ ወኪላቸው አድርጉኝ ወደጠቅላይ ግዛት ትምህርቴን ከመጨረሴ በፊት እንዳይልኩኝ ስጋት ነበረኝ:: የፈራሁት ደረሰና ትምህርቴን ለመጨረስ 6 ወር ያህል ሲቀረኝ ህዳር 1949 ዓ.ም. ወደ ደሴ ላኩኝ:: ትምህርቴ በመቋረጡ ባዝንም በሌላ በኩል ድርጅቱን ወክሎ ሌሎች የይሖዋ ምስክሮች ወደሌሉበት መላክ እራሱ ትልቅ ክብርና የመዳንም ዋስትና እንደመጨበጥ ስለመሰለኝ ድልድሉን በደስታ ተቀብዬ ሄድኩ:: የተመደብኩት አፈወርቅ ከሚባል የጐንደር ልጅ ጋር ነበር:: ያኔ እድሜዬ 18 ዓመት ነበር:: አፈወርቅ ግን እድሜው ከ30 በላይ የነበረ ሰው ስለሆነ ብቸኝነቴም በእርሱ እየተፅናና በሃይማኖቱ ምክንያት

ከሚጠሉኝ ዘመዶቼ አካባቢ ተለይቼ ደሴ ገባሁ:: ያቸው 65 ብር ብቻ ናት እንጂ አበል አልነበረንም:: በዚህ መልኩ ደሴ ጠቅላይ ግዛት ለ8 ወራት ያህል እንዳአገለገልን የይሖዋ ምስክሮች ሥራ በኢትዮጵያ መንግሥት ታግዶ ቢሮአቸው ተዘጋ:: በግልህ እምነት በመሰለህ ዘዴ ስብከትህን አታቋርጥ፣ ወደ አዲስ አበባ የምትመለስ ከሆነ የትራንስፖርትህን እንከፍልሃለን፣ በተረፈ «ከዛሬ ጀመሮ ማህበሩ ከአገር ተባርሯል» የሚል ደብዳቤ ደረሰኝ:: ምርጫ ስለአልነበረኝ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩና ሥራ ፈት ሆንኩ:: እንዴት እሆናለሁ? እንዴትስ እኖራለሁ? የሚል ጥያቄ ለመጀመሪያ ጊዜ በአእምሮዬ አቃጨለ:: ከደሴ መጥቼ ከአውቶብስ ስወርድ የምገባበት ቤት አጣሁ:: ወደ ቢሮ ብሔድ ቢሮው ታሽጓአል:: እነርሱ ከአገር ወጥተዋል:: ማንም አልነበረም:: ከትምህርት በትምህርቴ ሣልገፉ አቋረጥኩ፤ ከዘመዶቼ ባሕል ወጥቼ እነርሱም ከቤት አባርረውኛል:: አባቴም በዚሁ በሃይማኖቴ ምክንያት ከእኔ ጋር በአንድ ማዕድ እንደማይበላ የታወቀ ነው:: አሁን ደግሞ እንደዚህ ያለ ነገር ሲገጥመኝ እንደገና ወደ እነርሱ ቤት ተመልሼ መሄዱ ሞት መስሎ ታየኝ:: እናቴና አባቴ ተለየይተዋል:: እናቴ ለብቻዋ ነው የምትኖረው፡ ምንም ቢሆን ምን እርስዋ ክፉ ስለማትናገረኝ የሌሎችንና የአባቴት ቤት ትቼ በመጨረሻ ላይ ወደ እናቴ ቤት ለመሄድ ማሰላሰል ጀመርኩ:: መቼም ከፍታ የማትከፋ እምዬ ስለሆነችና ማጣፊያም ስለአጠረኝ በመጨረሻ ላይ ወደ እናቴ ቤት ለመሄድ ወሰንኩ:: እናቴ ቤት ስደርስ ከምሽቱ 3 ሰዓት ገደማ ነው:: እንደመተኛት ብላ ነበር፤ በሩንም አንኳኩቼ ማንነቴን ስታወቅ በሞትኩ ብላ በእንባ ተቀበለችኝ:: እናቴ ዘንድ አድሬ



በማግስቱ ምናልባት የማውቃቸውን ሰዎች ለማግኘት ወደ ባቡር መንገድ ወጣሁ:: በዚያን ዘመን እውነተኛ ወንድም የሚባለው ወይም ደንበኛ አባል የሆኑት በጣም ጥቂት ስለነበሩ እና እነርሱም በየቦታው ስለተበታተኑ አጣኋቸው:: አስመላሽ ገብራይ ቀደም ብሎ አሥመራ ተመድበዋል፣ ወርቁ ካሣ አውራ ጐዳና ሥራ አግኝቶ ሄዷል:: ታደሰ በየነ የሚባልም አስቀድሞ ሥራ አግኝቶ ወደ አሰብ ሄዷል:: ተራ አስፋፊዎቹ ተደናግጠው ተበትነዋል፣ አድራሻቸው አይታወቅም የሚል ወሬ ገና ከአንድ መልካም ፈቃደ ካለው ሰው አፍ ሰማሁ:: መልካም ፈቃድ ያለው ሰው ማለት የይሖዋ ምስክሮችን የማይጠላ ከእነርሱም ጋር መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ፈቃደኛ የሆነ ሰው ማለት ነው:: አውራ ጐዳና ብዙ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚችሉ ካቦዎችን ይቀጥራል፣ ወርቁም የሄደው በዚሁ መንገድ ነው ስለተባለ፣ እኔም ስራ ፍለጋ ተነስቼ ወደ አውራ ጐዳና ሄድኩ:: ፈተናን ለሚያልፍም ሰው የቅየሣ ሥልጠና እንደሚሰጥም አረጋገጥኩ:: የአውራ ጐዳና ፔርሶኔል ክፍል ገብቼ ፎርም ለመሙት መምጣቴንና ሥራ ፈላጊ መሆኔን ነገርኩአቸው:: ፔርሶኔሉ የኢትዮጵያዊ ሰው ነበሩ፣ ለጊዜው ግን የሉም አለችኝ ፀሐፊዋ:: ነገር ግን አንድ አሜሪካዊ ብድግ ብሎ ይኸንን ፎርም ሙሉ ብሎ ሰጠኝ፡ ፎርሙን ሞላሁ:: ያኔ አውራ ጐዳናን የሚያስተዳድሩት አሜሪካኖች ነበሩ:: ከአውራ ጐዳና ስወጣ እጅግ እያዘንኩ እንባዬ መጥቶ ዐይኔን ጋረደው:: ሰው በማያየኝ መልኩ ወደ አንድ ጥግ ሄጄ እየፀለይኩ አለቀስኩ፣ እያለቀስኩም ፀለይኩና ስሜቴን ካረገብኩ በኋላ ፊቴን ጠራርጌ መሄድ ጀመርኩ:: ድንገት በመንገድ ላይ ስሄድ ተሾመ የሚባል ልዩ ሙሉ ጊዜ አገልጋይ

አቅኚ የነበረ ሰው አገኘሁ። እጅግ በጣም ደስ አለኝ። እግዚአብሔርም ፀሎቴን እንደሰማ ቆጠርኩ። ስለሁኔታው ስጠይቅ ሁለት ነጮች ሬኢግልሰን ሬየስ ኢንጅነሪንግ የሚሠራ 2ኛ ጆርጅ ቡሩሚሊን የሚባል የፖሊስ ሬዲዮ መገናኛ አሰልጣኝ፣ እነዚህ ሁለቱ ብቻ ቀርተዋል። ሥራውንም የሚመሩ እነርሱ ስለሆኑ እጅግ በጣም በድብቅ እና በጥንቃቄ ውስጥ ለውስጥ መሥራት አለባችሁ ብለው አዝዞናል። አለበለዚያ መንግሥት እኛንም ከአገር ያስወጣናል እያሉ ይፈራሉ ብሎ አጫወተኝ። ታዲያ አሁን ስብሰባ ወደየት ነው? ብለው ማታ በ12 ሰዓት ተኩል እቴጌ መስክ እንገናኝና አብረን እንሄዳለን ብሎኝ በቀጠሮ ተለያየን። ማታ ስብሰባ ላይ ሄጄ በቅርቡ የማውቃቸውን አላገኘሁም። ግን አንድ ወንድም ወደ እኔ ጠጋ ብሎ ሬኢግልሰን የሚባል ወንድም ይፈልግሃል አለኝ። ታዲያ የት አገኟለሁ አልኩት። በምልክት ቤቱን ስለነገረኝ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን አጠገብ ወደ ነበረው ቤቱ ሄድኩ። እርሱም በኋላ ወደ ካሣሁን ላክኝ ፤ ፈረንጆች በነበሩ ጊዜ በቢሮ ውስጥ እየሠራ የሚያገለግል፣ መጻሕፍትንና መጽሔቶችን የሚተረጉምና የቤቴል አገልጋይ የሚባል ማዕረግ አይነት ስለነበረው፣ከኢትዮጵያዊያኖች ጋር ግንኙነት እያደረገ ሥራውን እንዲቆጣጠር ሾመውት ስለነበር፣ መመሪያውን ከነጮቹ እየተቀበለ የሚያሰራጭ፣ የኢትዮጵያዊያኖችንም ወንድሞች እንቅስቃሴ ለነጮች ሪፖርት የሚያደርግ አገናኝ መኮንን ሆኖ ይሠራ ነበር። ትንሽ ቤት ተከራይቶለት ከዋና ጉምሩክ ቢሮ አካባቢ ይኖር ነበር። በኋላ በትእዛዙ መሠረት የወንድም ካሣሁንን ቤት ፈልጌ አገኘሁ። ለእርሱም ስለእኔ አስቀድሞ



ተነግሮት ስለነበር ገና እንደ አየኝ ኤኝ አለኝ። በቀልድ ስም ኤኝ እያለ ይጠራኝ ስለነበር። ኤኝ አለኝ ኣንደገና ደገመና። ምነው? ስም አለኝ እኮ ለመሆኑ ደህና ነህ? አልኩት። ትንሽ እንደተወያየን ምን ይመስልሃል በልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚነትህ ብትቀጥል? አለኝ። ምንም መልስ ከመስጠቴ በፊት እንባዬ በዓይኖቼ ግጥም አለ። እንደምንም አጉንብሼ እንዳይፈስ መልሼ ከዋጥኩት በኋላ ቀና ብዬ እኔ ገና ድሮ ነው ፈቃዴን የሰጠሁት። ዛሬ እንደ አዲስ እንዴት ትጠይቀኛለህ? አልኩ። ምንም መልስ ሣይሰጠኝ ወደ መስኮት ሄዶ ውጭ ውጪን ሲመለከት ከቆየ በኋላ ወደ እኔው ዞር አለና በል እንግዲህ ከዛሬ ጀምረህ በልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚነትህ ቀጥል፣ የቸርቸር ጉዳና የጉባኤ አገልጋይም ሆነህ ታገለግላለህ አለኝና ወንበሩ ላይ ተቀመጠ። ንግግራችን በዚሁ አበቃ። እኔም ወደ አገልግሎቴ ሄድኩ፣ እርሱም ሥራውን ቀጠለ። ይህ የሆነው በእኛ አቆጣጠር በነሐሴ ወር መጨረሻ በ1949 ዓ.ም. ነው። በዚሁ የቃል ትእዛዝ በልዩ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት እስከ ነሐሴ 12 ቀን 1951 ዓ.ም. ሠራሁ። ልክ ነሐሴ 12 ቀን 1951 ዓ.ም. በኮሎኔል ገበየሁ ወርቅነህ ትእዛዝ በፖሊስ ተይዤ የሕዝብ ደህንነት መሥሪያ ቤት ተወሰድኩ። የያዘኝ የመቶ አለቃ አያና ይባላል። በደርግ ዘመን ሙሉ ኮሎኔል ደርሰው አይቼአቸዋለሁ። ሌላኛው የመቶ አለቃ ተስፋዬ የሚባል ነበር። ከእኔ ጋር የታሠሩት የተወሰኑ ወንድሞችም ነበሩ። አንዱ ባዬ ባለድ፣ ሌላው ታደሰ ጉርሜሣ የሚባሉ እንደበር ትዝ ይለኛል። ከዚያም ቤቴ ተበርብሮ ምንም የዘውዱን መንግሥት የሚቃወም ነገር ስለአልተገኘ በማስጠንቀቂያ ተለቀቅን። ይህንን መታሠራችንን የሰሙት ሁለቱ

ነጮች እኛ በእነርሱ ምክንያት ከአገር እንባረራለንና ሥራቸውን ማለት የልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኝነታቸውን ያቁሙ ብለው ትእዛዝ አስተላለፉ:: እነርሱ ከሥራ እንዳይወጡ በእኛ ጉሮር ላይ ፈረዱ:: የልዩ መሉ ጊዜ አቅኚ የሚባለው 150 ሰዓት በወር ከሠራ 65 የኢትዮጵያ ብር የሚከፈለው ሰው ነው ብለናል:: ይህችው 65 ብር በዚሁ ምክንያት ቀረችና ሥራ ፈት ሆንኩ:: ከባለቤቴ ጋር ተጋብተን አንድ ልጅ ወልደን ስለነበር በዚችሁ 65 ብር መቅረት የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ:: ዓላማችን ገንዘብ ለማግኘ ት ሣሆን ዓለም ከዛሬ ነገ ስለምትጠፋ በድርጅቱ ውስጥ ሆነን ለመዳን ነው:: ስለዚህ የዕለት ሽሮ አስከተገኘ ስለሌላ ግድ አልነበረንም:: በእምነቴማ ነገ ይች ዓለም ስለምትጠፋ የወደፊቱ የምድሪቱ ሐላፊ እሆናለሁ ነው ሙሉ ተስፋዬ:: እምነት ሰውን ያሞኛል የሚባለው እንደዚህ ካለውና ከመሳሰለው አንፃር ነው:: የሕይወቴ ገጠመኞች ብዙ ስለሆኑ እድሜና ጊዜ ከፈቀደ በሌላ መጽሐፍ እመለስበታለሁ:: ያም ሆነ ይህ ዛሬ እንደዚህ እየተቸሁ የምነቅፈው ድርጅት ያኔ ግን ሕይወቴን መስዋእት ማድረግ ቢያስፈልግ እንኳን ለመስዋት ቆርጬ አባል የሆንኩት ከዚህ በላይ በተብራራው መሠረት እንደነበር ለመግለፅ ያህል ነው:: እምነታችን ለነገ እንድናስብ አያስችለንም ነበር:: ለነገሩማ ለነገ አታስቡ ተብሎ የለም!

በ4ኛው ደረጃ ሰዎች ወደ ድርጅታቸው ገብተው ቶሎ በተንኮላቸው ሣይነቁ እንዲቆዩ እና ለመንቃት ረጅም ጊዜ ያውም ከነቁ የሚወስድባቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋምን ገብቶ መማር በብርቱ ስለሚነቀፍ ተምሮ እራስን የማወቅ ዕድል የለም:: ለእምነት የማያንፀው፣ ለዘላለም ሕይወት ለማያዘጋጅ፣



እያሉ ከፍተኛ ት/ቤትን ገብቶ መማርን ይነቅፋሉ:: ወጣቶች የእነርሱን የፕሮፖጋንዳ መጽሐፎች፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች እየዞሩ መሸጥ የበለጠ ወጤት እንዳለው ይሰብካሉ:: እርግጥ ለማሕበሩ ውጤት አለው፣ ለሻጩ ግን ምንም ጠብ የሚልለት የለም:: ነገ አርሜጌዶን መጥቶ ከሚያጠፋው የዓለማዊ ድርጅትን መንገድ ወይም የእነርሱን ዓላማ ተቀብሎ እንደ እነርሱ መሆን አብሮ መጥፋት ስለሆነ የድርጅቱን ዓላማ ይዞ የዘላለም ሕይወት ዋስትናን መጨበጡ ይመረጣል እያሉ የሚጃጃሉ ብዙ ወጣቶች አሉአቸው:: ከውጭ አዲስ ገቢ አባልን በዚሁ መልክ እየሰበኩ፣ የራሳቸው ልጆችን ደግሞ 12ኛ ከጨረሱ በኋላ አገልጋይ እንዲሆኑ ስለሚገፋፏቸው ወደ ድርጅቱ አገልገሎት ይሰማራሉ:: ስለዚህ ይህ ድርጅት ከውስጥ እራሱን እንደዚህ እያጠናከረ፣ ከውጭም አዳዲስ አባላት እየሰበኩ እጅጉን ተግቶ ይሰራል:: ሰው ተምሮ አመለካከቱ የላቀ እንዳይሆን፣ ተምሮም ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዳይደርስ እንዴት የስነ ልቦና ሰለባ እንደሚያካሂዱ ሐምሌ 2005 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ያወጡትን ንቁ. ጋዜጣ ገፅ 24 ላይ የጻፉትን ተመልከቱ በዚህ መልኩ በጎቻቸውን ያልባሉ!

አሁን እንደዚህ እየተቸሁ በመጻፌ ታማኝና ልባሙ መጋቢ በጎችን ባልብ ምን አገባህ? ይለኝ ይሆናል:: እስኪ ይህን ነገር በምሳሌ አንዴ እንመልከት፣ አንድ ሰው በእጁ ጮጮ ይዞ አህያን ሰንክሎ ወይም እግርዋን አስሮ ለማለብ ሲዘጋጅ አንድ ሰዉ እንደ አጋጣሚ ያየውና እንዳላየ ሆኖ ያልፋል:: ቤቱ ከገባ በኋላ ለሚስቱ አይ ዛሬ ያየሁት ጉድ፣ ይላል:: ሚስቲቱም ለወሬ ሰፍ ብላ ምን አየህ ፍቅሬ? ትለዋለች:: በመጨረሻ ላይ አቶ ባል አቶ እገሌ እኮ አህያ ሲያልብ አየሁት ብሎአት አረፍ:: ሴትዮዋም

አበሰ ገበርኩ አበስ ገበርኩ እያለች ወሬውን ለመንደሩ ሁሉ አዳረሰች:: በመጨረሻም አቶ እገሌ አህያ አላቢ ተብሎ ለሰውዬው ስም ወጣለት ይባላል:: አሁን እዚህ ላይ አጥፊው ማን ነው? አህያ አላቢ ነው? ወይም አህያ አላቢው አህያውን ሲያልብ አይቶ ያወራ ሰው ነው? አህያዋ መቼም ለምን እታሰባለሁ ብላ ስለማትከራከር ከቁጥር አትገባም:: ምናልባት በአህያ መገልገል ምን ችግር አለ? በአህያ ለምን ተገለገልክ? አህያንስ ለምን ታልባለህ? እያለ ያወራው ነው ጥፋተኛ የሚል ሰው አይጠፋም:: ለ3ሺ ዘመናት ስንገለገልባት ከቆየን በኋላ የአህያ ሴሚናር በደብረዘይት ተካሔዶ የለም እንዴ/ እኛ እኮ አህዮችን በደንብ ጠብቀን ልንገለገልበት ስለአልቻልን ወይም ስላልፈለግን ይሆን ይሆናል ሴሚናሩ እንዲካሔድ ተፈቅዶ የተካሔደው:: እኛ «አይጣል የአህያ በሽታ ቆዳ አይሸጥ ሥጋው አይበላ» እያልን ነው:: አሁን አሁን ግን በአህዮች መጠቀምን የጀመርን ይመስላል::

ይህ ድርጅት እንደሌሎች ሚስዮኖች ትምህርት ቤት ሣይከፍት፣ ክሊኒክ ሣይከፍት፣ ምንም ዓይነት የአገልግሎት ሰጭ ድርጅት ሣያቋቁም፣ በሰው ብቻ እየነገደ፣ ቀረጥ ሣይከፍል እጅግ በጣም ብዙ ትርፍ ገቢ የሚያገኝ ድርጅት ነው:: ለሠራተኞችም የሚያወጣ ወይም የሚከፈል ደመወዝ የለም:: ብቻ በሰው ጭንቅላት ላይ እየተጫወተ የአእምሮ የስነልቦና ሰለባ እያካሄደ፣ ቁጭ ብሎ ትርፍ ማጋበስ ብቻ ነው:: እንኳን ለሕዝብ የሚጠቅም የአገልግሎት ድርጅት መክፈት ቀርቶ በሌሎች ሚሲዮኖች ትምህርት ቤትና ክሊኒክ ምርጫ ካላጣችሁ በስተቀር እንዳትጠቀሙ እያሉ የሚሰብኩ ናቸው:: ለምሳሌ በሚሲዮኖች



ትምህርት ቤት፣ በሆስፒታል ክሊኒክ ወዘተ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ገብታችሁ አትሥሩ ይላሉ:: ከዚህ በፊት እንዳየነው የ1844፣ 1864፣ 1874፣ 1878፣ 1907፣ 1914 እና 1925 ዓመተ ምህረቶች በተደጋጋሚ የጥፋት ዘመናት መጥቷል እያሉ ሕዝብን አታልለዋል:: ዛሬም እንደዚህ የተወሰነ ዓመትን እያጠቀሱ ማወናበዳቸውን አልተውም:: የይሖዋ ምስክሮችን አባላት በጉርፍ ማስመሰል ይቻላል:: ጉርፉ ኃላፊ ነው:: ጉርፉ የሚጉርፍበት ወንዙ ግን ቋሚ ነው:: በጉርፍ የተመሰሉ ተሰባኪ ምእመናኖቻቸው ወይም በጉቻቸው የዓለም ጥፋት ይመጣል እያለ ድርጅቱ ዓመተ ምህረቱን ወስኖ በሚሰብክበት ጊዜ ወደ ድርጅቱ እየጐረፉ ሁለገብ እርዳታ በመስጠት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ ወንዙ ይሞላል:: ያ ቀን ደርሶ የዓለም ጥፋት የማይከበት ከሆነ ግን ጉርፍ እንደሚያልፍ ሁሉ ሕዝቡም ይህንን ድርጅት ጥለውት ይወጣል:: ጉርፍ ወንዙን ጥለው እንደሚሄደው ሁሉ እነዚህም ድርጅቱን የሚተው በጉች ናቸው:: እንደገና ድርጅቱ ስብከቱን በማስተባበሉ እየቀጠለ፣ በማረጋጋት ሲበረታ ደግሞ ሌላ በአዲስ ጉርፍ የሚመሰሉ አዳዲስ ተሰባኪዎች ወይም ምስክሮች ይመጣሉ:: ጉርፉ የሚጎርፍበት ወንዝ ወይም ድርጅቱ ግን ያው ነው፣ ዓላማውም ያው ነው አይለወጥም::

እንዲሁ ጉርፍ ሲያልፍ ወይም ድርጅቱ በሰዎች እጥረት የከሰረ በሚመስለው ጊዜ አዲስ የፍልስፍና ዘዴ ቀምሮ ጉርፍን በማጉረፍ ዘዴ ታማኙና ልባሙ መጋቢ የተካነ ነው:: ብዙ ዘመናት ዝም ብሎ ከቆዩ በኋላ በ1975 ዓ.ም. ዓለም ይጠፋል ብሎ ያወጁትም ካለፈው የተሞክሮ ታሪካቸው እየተነሱ ነው::

አንድ ትንፋሽ ብቻ ማሕበሩ ዓለም ሲጠፋ ነው ብሎ ከተነፈሰ ብዙ ምድረ በግ በንቃት ወደ ድርጅታቸው እንደሚጉርፍ አውቀውታል::

አንተም ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ስለነበርክ ታዲያ እንዴት ልትሞኝ ቻልክ የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል? እኔም ሆንኩ ማንኛውም ወደዚህ ድርጅት የሚገባ ሰው ስለሃይማኖት ጥልቅ እውቀት የሌለው ነው:: ከቶስማራብት የግል ሥራ ሌላ ስለሃይማኖት አመጣጥ እና ስለሃይማኖት ታሪክ አስቀድሞ የሚያገኘው የይሖዋ ሰባኪ ከሚነግረው በስተቀር ምንም የማያውቀው ሰው ነው በእነርሱ የሚታለሰው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተገኘ፣ ምንም የማያውቁ ሰዎች ናቸው እነርሱን አሜን ብለው የሚቀበሉት:: ይህ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የምእመናኖቻቸው እውነተኛው ገጽታ ነው:: እኔም ቢሆን እንደነዚህ ካሉት ሰዎች በጣሙን እጅግ ነጠላ ሐሳብ ብቻ የነበረኝ ሰው ስለነበርኩ ነው፡ይህ አንደኛ ምክንያት ነው::

ሁለተኛው ሌላ ምክንያት የድርጅቱ አባላት በማሕበሩ እየታተሙ ከሚቀርቡት መጽሐፎች፣ መጽሔቶችና በወር ሁለት ጊዜ እየታተሙ ከሚወጡት ጋዜጦች በስተቀር የውጭ ድርጅት ጽሑፎችን እንዳያነቡ ስለሚከለከሉ ነው:: ለዚህም ክልከላቸው የሚያቀርቡት ምክንያት በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ቁጥር 42 ላይ የተጻፈውን ጥቅስ ነው:: ጥቅሱም እንደዚህ ይነበባል:- «እንኪያስ ምግባቸውን በየጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተሰቦቹ ላይ የሚሾመው ታማኝና ልባም መጋቢ ማን ነው?» እዚህ ላይ ምግባቸው የተባለው ማሕበሩ እያሳተመ የሚያሰራጫቸው ጽሑፎች ናቸው:: አዘጋጆችም እነ ራሴልና



በኋላም የራሴል ወራሾች ናቸው:: ከዚህ በፊት እንደአየነው ታማኝነታቸውን ለኘሬዝዴንቱ እስከአረጋገጡ ድረስ ሰባት ሰዎች ለዚሁ ሥራ ተመድበው እየሠሩ ያሠራሉ:: ከኘሬዝዳንቱ ጋር ሆነው ታማኝና ልባም መጋቢ የተባሉት እነዚህ ሲሆኑ የተዘጋጀውን መና ተመጋቢዎች በጐች ናቸው:: ስለዚህ በጐቹ ታማኝና ልባም መጋቢ ከሚያዘጋጁት ጽሑፍ ውጭ እንዳያነቡ ወይም እንዳይመገቡ ይከለከላሉ:: ካነበቡም ነውር ነው! በምንም መልኩ ያልተበረዘና ያልተከለሰ ወይም ያልተመረዘ ምግብ ታማኝና ልባም መጋቢ የሚያዘጋጁት መጽሐፎች፣ ጽሑፎችና ጋዜጦች ብቻ ናቸው ብለው ያምናሉ:: በዚህ መልኩ አእምሮአቸው በደንብ ታጥበዋል:: እኔም ቢሆን ከዚህ የተለየ ዓላማ ወይም አመለካከት አልነበረኝም:: እጅግ ነጠላ ሐሳብ ብቻ የነበረኝ ሰው ነበርኩ ብዬ በመጀመሪያውኑ የገለጽኩት ስለዚህ ነው:: እጅግ ነጠላ ሐሳብ ብቻ ነበረኝ የሚለውን አመለካከቴን ለመግለፅ እንዲያመቸኝ ስለሕይወቴ ታሪክ ትንሽ ልጥቀስላችሁ::

እኔ የተወለድኩት ታህሣሥ 9 ቀን በ1928 ዓ.ም. እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ዕለተ ሐሙስ ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ነው:: አባቴ አቶ በዛብህ ቸኮል ዘብሔረ ጉጃም ሲሆን እናቴ መንዲዳ ከሚባለው ሰሜን ሸዋ ወደ አሮሞ ክልል ወረድ ብሎ ልዩ ቀበሌ አቢቹ አብደል ማግል የሚባል አጥቢያ ሥፍራ ተወላጅ ናት:: ድርና ማጉዋም አሮሞ ናት:: እናቴ ከአንድ ከተማ ተቀማጭ ሰው ጋር በ15 አመትዋ ኮብልላ አዲስ አበባ ከገባች በኋላ ከአስኮብላዩ ስለአልተስማማች አቶ በዛብህን ማለት አባቴን አገባች:: አባቴ በዘመኑ አገልግሎት ከሚያበረክቱት ከአራዳ

ዘበኞች አንዱ ነበር:: አቶ በዛብህ ከእናቴ አበባዬ በዛብህ የምትባለውን እህቴንና እኔን ብቻ ነው የወለደው::

እኔ ከተወለድኩ በኋላ እንደ አገሩ ልማድ ቅቤ ሊያውጡኝ እንደሞከሩ፣ እኔም በምንም ተአምር ቅቤን ለመላስ አፌን አላላውስ እንደአልኩ እናቴ አጫውታኛለች:: ቅቤም ሣልልስ፣ ጡትንም ሣልጠባ ከሐሙስ ዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ ሙሉ ቀን አርብ ዋልኩ:: እየታገልን እንደው ለዓመል ከምራቅ ጋር ገብቶ ካልሆነ በስተቀር ምንም አልቀመስኩም ትለኛለች እናቴ:: በመጨረሻም አርብ ምሽት ጨርሶ አፌን መክፈት ስለአቃተኝ አባቴ አቶ በዛብህ ይህ መቼም ሰው አይሆንም፣ አንቺኑ እንኳን ለቀቀ፣ ትተሺው እዚያ አስተኚው፣ ከሞተም ነገ ይቀበራል ብሎ አለኝ ትላለች የእኔ እናት:: እኔም ሁኔታህን ሣይ የምትተርፍ ስለአልመሰለኝ ለብቻህ በጨርቅ ጠቅልዬ ግርግዳ ጥግ አኖርኩህና ተኛሁ:: በኋላ ተኝቼ በሕልሜ ከትከሻህ ላይ ሐረግ እሬሣ እንደጉድ በቅሎብህ አየሁ:: ይኸኔ በዛብህ? በዛብህ? በዛብህ? ብዬ ተጣራሁ:: እርሱም ዎዬ! ምን ሆንሽ የእኔ ወርቅ አለ? ብዙ ጊዜ የእኔ ወርቅ ብሎ መጥራት ይቀናው ስለነበር:: እኔም በል መብራት አብራልኝ፣ ልጄ አይሞትም፣ ሕልም አይቻለሁ ብዬ አልኩት:: እርሱም ኩራዝ ስለአበራልኝ አንስቼህ ጡቴን ብሰጥህ ጠባህልኝ አለችኝ እናቴ:: ይህንን አጫውታኛለች::

በመጨረሻም እድገቴ ቀጥሎ በሚያዝያ 28 ዓ.ም. ጣሊያን አዲስ አበባ ገብቶ በገባው በዓመቱ ሕዝብን ፈጅቶ ቤቶችን ስለአቃጠለ፣ እናቴ እኔን ይዛ ወደ ትውልድ አካባቢዋ ሄደች:: እዚያ ኦሮሞ አገር ለአያቴ ሰጥታኝ ወደ አዲስ አበባ ስትመለስ የ10 ወር ልጅ እንደነበርኩ ተተርኮልኛል:: ዘመኑ ክፉ ስለነበርና



ላሞችም ስለነጠፉ በራብ ሣለቅስ አያቴ ደረቅ ጡትዋን ሰጥታኝ በየጊዜው ስስብ ወተት ወጥቶልኝ ከእርስዋ ደረቅ ጡት በወጣው ወተት ነፍሴ ተረፈች ተብዬአለሁ::

እስከ 7 ዓመት ተሞላቅቄ በቤት አደኩ:: መሞላቀቅ ከተባለ የገጠር ሞልቃቃ እስኪ ይታያችሁ! በ7ኛው አመቴ ወንድ አያቴ ሞቱ:: በዚሁ ዓመት እረኝነት እንዲወጣ አጐቴ አስገደደኝ ከ7 እስከ 12 ዓመት ደንበኛ እረኛ፣ ከ12 እስከ 16 ዓመቴ በሥራ ቀን ጋይ የሚባል አፈር እየሰበሰቡ በእሳት ማቃጠልና በኋላ መልሰው የመበተን ሥራን፣ እንዲሁም ማረስ፣ በበዓል ቀን እረኝነት፣ ከብት ማገድ ግዴታ ሆነብኝ:: ይህንን ድካም አሁን በምሬት አስታውሳለሁ:: የከተማዋ እናቴ አገር ትንሽ እንደመረጋጋት ካለ በኋላ በየዓመቱ እየተመላለሰች ብታየኝም እስከ 16 ዓመቴ ድረስ ስንገላታ እያዘነች በዝምታ ትመለከት እንደነበር ከጊዜ በኋላ አጫውታኛለች:: ለምን አልረዳሽኝም ነበር ታዲያ? ብዬ ብላት እርግማን ፈርቼ ልጄ፣ እርግማን ፈርቼ ትለኛለች:: የምን እርግማን እማማ ስላት ደረቅ ጡትዋን እጥብታ ያሳደገችህ አያትህን እርግማን ትለኛለች::

ምንም እንኳን ገጠር ባድግም የኦሮሞችን ባሕል በደንብ የመመራመርና በደንብ የመገንዘብ የላቀ ችሎታ አልነበረኝም:: ሆኖም ዋቃን አውቃለሁ:: ዋቃ ለእኔ ይመስለኝ የነበረው በዓመት አንድ ጊዜ በሰኔ ወር ወዳጆ ሲታድር አያቴን የሚያስጨፍራት ነገር ይመስለኝ ነበር:: ወዳጆ ስታደር ከብት ይታረዳል፣ በየዓይነቱ ዝግጅት አለ፣ ዋቃ ይወርዳል:: ድግስ ነው ደስታ ነው:: ለእኔ ግን ያው በእርሻ ቀን እያረስኩ እንደዚህ ባለው የበዓል ቀን ደግሞ ውጭ ከብት እንድጠብቅ ስለምታዘዝ ከበዓሉ

የመካፈል ዕድል አልነበረኝም። ከእነርሱ ጋር ለመሆን እጅግ ጉጉት ቢኖረኝም እንዳልካፈል አጐቴ እኔን ከብት እያስጠበቀኝ የራሱን ልጆች ግን ከበዓሉ እነዲካፈሉ ይፈቅድ ነበር። ይህንንና የመሳሰሉ ጉዳቶቼን ነበር እናቴ እያየች ዝም ያለችው። ከጊዜ በኋላ ግን የእኔን ጉዳት እንዴትስ አድሎ እንደሚደረግብኝ በለዘብታ እናቴ ለአያቴ ማጫወት ጀመረች። ዝም ብላ እንዳትወስደኝ የአያቴ ዋቃ እንዳይገድለኝ ትፈራ ነበርና ነው ጉዳቴን ለአያቴ እያለዘበች መንገር የጀመረችው።

አያቴም ሁኔታውን እንደምታውቅ፣ ምንም ማድረግ ግን እንዳልቻለች፣ ጉልበት እንደአጣች፣ ሥራ ወይም እንግልቱ የአገር ባሕል ስለሆነ ባልከፋ ግን አድሎውን ተገንዝቤአለሁ። እኔ ከመትከ የባሰ ያደርጉታል። ስለዚህ በሕይወቴ እያለሁ መርቄልሽአለሁ ውሰጅው ብላ አለች። በዚህን ጊዜ እናቴ ተነስታ የዋቃን የፀሎት ቦታ ሳመች። የአያቴንም እግር ሳመች። ልብስ ማለት አዲስ ልብስ ገዝታ አልብሳት በዘጠኝ ሠርዶ ሣር ላይ ቅቤ ቀብቶ እንትፍትፍ ብላ መርቃኝ ለእናቴ መለሰችኝ። ከእናቴ ጋር ወደ አዲስ አበባ እንድመጣ ፈቀደችላት፡ ይህ የኦሮሞ ባሕል ነው።

አዲስ አበባ ስገባ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተማ የሚባለውን እንደ ጉድ አየሁ። የኤሌክትሪክ መብራት በየመንገዱ ሣየው ይገርመኝ ነበር። የአማርኛን ቋንቋ አንድ ቃል እንኳን አላውቅም ነበር። እንደገባን በማግሥቱ ከጐላ ሚካኤል በታች አቶ አድማሱ ግቢ /የዶክተር ዮናስ አባት ናቸው/ የኔታ ቅሩብ የሚባለው መምህር ዘንድ ትምህርት አስገባችኝ። እጅግ በጣም ሁሉ ነገር ግራ ስለሚያጋባ ከእኔ ያነሱ ትንንሽ ልጆች ፊደሎችን



ሲያቀላጥፉ በጣም እናደድና እቆጭ ነበር። ሌት ተቀን ተግቼ አጠና ስለነበር የአማርኛ ቋንቋ ፊደሎችን ማጥናት ቀጥዬ በአንድ ዓመት ውስጥ ዳዊት ደገምኩ። በ1944 ዓ.ም. ውስጥ ማለት ነው። ከዚያም በ1945 ዓ.ም. ሺመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤት እናቴ አስገባችኝ። አቶ ሀብቴ ለሚባል የትምህርት ቤት ዘበኛ እኔን ለማስገባት ወይም እንዲያስገባኝ 3 ብር ጉቦ መክፈልዋ ትዝ ይለኛል። እዚያም ገብቼ በጣም እያጠናሁ 1ኛ በመውጣት በዓመት ሁለት ጊዜ የክፍል ዝውውር /ኘሮሞሽን/ አገኝ ነበር።

ይሁን እንጂ አሁንም በጣም ለትምህርት የዘገየሁ መሆኔ እየተሰማኝ እያጠናሁ እንግሊዝኛዬንም አሻሻልኩ፣ የአራዳነት ወይም የከተማነት ብልጠት ግን አልነበረኝም። እንዲህ ባለመልክ እና አቋም እያለሁ ነው ከይሖዋ ምስክሮች ጋር ተዋውቄ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የጀመርኩ። እንደዚህ ባለው ባዶ ጭንቅላት ነው የበለጠውኑ ባዶ ለማድረግ የዎች ታዎር ባለስልጣኖች እጥበት ያካሄዱብኝ። ምንም እንኳን ያኔ እንግሊዝኛ ቋንቋን በመናገር ከፈረንጆች ጋር መግባባት ብችልም የከተሜዎችን የኑሮ ኢሴት /ዋጋ/ ለእኔ ምኑም አልነበሩም። አንድ ጥሩ ቦላሌ ለብሶ ክራባትና ጥሩ ጫማ ያደረገው የከተማ ወጣት ከእኔ ከባለ ቁምጣና ከመጫማ አልባ እግሮች ወይም የእኔ አለጫማ ተጓዥ ምንም የሚሻል መስሎ አይታየኝም ነበር። እንዲሁም የእኔው የሚቀል የሚመችና የሚያምርም ይመስለኝ ነበር። ስለዚህ የመበላለጥ ደረጃ በእኔ አመለካከት በትምህርት ልቆ ከመገኘት አንፃር ብቻ ነበር የምመለከተው። ይህ ነገር በመሠረቱ እውነት ቢሆንም ከእኔ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሰው ከእኔ ከመናጢ ባዶ እግር ተጓዥ ኪስ ሣንቲም

አልባ አይሻልም ብሎ ዋጋ የማሳጣት ግምቴ ግን ልክ አይመስለኝም:: የነገሮችን እሴት ወይም ቫልዩ አለመገንዘብ ነው:: ከዚህም በላይ ሁላችን ወንድማማችና እኩል ነን አንዱ የሁላይ አንዳችን የበታች አይደለንም የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ሲታከልበት የባሰውኑ ተጃጃልኩ:: የኢኮኖሚ እኩልነት ከሌላ እኩልነት ምኑ ላይ ነው? ከእውን ግን በመካከላችን ያለው ትልቁ የኑሮ ልዩነት አይታዩኝም ነበር:: ስለዚህ በምኖርባት ባለኩራዝ መብራት ቤቴ ፈረንጆችን ግብዣ የጠራሁት ከዚሁ ግንዛቤ ጉድለት እና በእውነት በእኩልነቴ ማመን የተነሣ ነው:: ከሁሉ የባሠ ነጠላ አመለካከት ነበረኝ ያልኩት ይኸው ነው:: በእራሴ መተማመኑ ግን ምንም ቢሆን ምን አሁንም በስሜታዊነት አኮራብታለሁ:: ስለዚህ እንደዚህ ባለው ዝቅተኛ የግንዛቤ እወቀት ያለው ሰው ድርጅቱ ካሣተመው ጽሑፍ ውጭ ማንበብ ከሰይጣን ማዕድ እንደመመገብ ነው የሚለውን ትምህርት በቀላሉ ይቀበላል:: ማሕበሩ ያሳሳታማቸው ዓለማዊ ጽሑፎች ሁሉ ለመንፈሳዊ አቋም መርዞች ናቸው:: ስለሆነም ከሰይጣን ድርጅት የፖለቲካ መግለጫዎች እኛ ምስክሮቹ አንድነት የለንም እያሉ የአባሎቻቸውን አእምሮ በደንብ ስለሚያጥቡ ማንም እንደዚህ ያለውን መመሪየ ለመጣስ አይፈልግም:: መመሪያውን ለመጣስ ከደፈረም በሌሎች ዓይኖች እንደጉድ ይታያል:: ስለዚህ ትእዛዙን ማክበር አለበት ወይም ድርጅቱን መተው መቻል ነው:: አብዛኞቹ ግን እየደነገጡ ከድርጅቱ ጽሑፍ ውጭ ማንበብን ያቆማሉ::

ከሁሉ የሚገርመው ግን እነዚህ ታማኝና ልባም መጋቢየተባሉት በዓለም ላይ አሉ የሚባሉትን ምርጥ



መጽሐፎችን ሁሉ፣ የጠንቋዮችና የኦካልቲስቶች ሣይቀር እየገዙ በጥንቃቄ ያነባሉ:: ለእነርሱ የስብከት ፕሮፖጋንዳ ጠቃሚ መስሎ የታያቸውን ሁሉ እየለቀሙ በወር ሁለት ጊዜ በሚታትመው ጋዜጦቻቸው በማተም ይጠቀሙበታል:: ለምሳሌ ዶክተር ቲ ሎስፐንግ ራምፖ የሚባል አንድ የቲቤት ኦካልቲስት ነኝ የሚል ሰው ነበር:: ይህ ሰው ከ12 መጽሐፎች በላይ ጽፏዋል:: ልዩ ችሎታ አለኝ የሚል ሰው ነው:: እራሱን ዶክተር ብሎ ይጠራል:: ይህ ዶክተር ከጻፈው የሕይወት ምዕራፍ ከተባለው መጽሐፍ በገጽ 24 በመጀመሪያ ረድፍ ላይ ያለውን የባቡርና የተሳፋሪዎችን ምሳሌ ቃል በቃል ገልብጠው በመጠበቂያ ጽሑፋቸው ላይ አውጥተዋል:: የሚያሳዝነው ግን ሐሳቡን ያገኙበትን መጽሐፍም ሆነ ደራሲውን አለመጥቀሳቸው ነው:: አለመጥቀሱን የመረጡት እነርሱም ለካ ከጠንቋይ መጽሐፎች ያነባሉ እንዳይባሉና ተከታዮቻቸውም የእነርሱን አርአያ እንዳይከተሉ ነው:: አባሎቻቸው ግን ተራ ጋዜጣ እንኳን እንዲያነቡ አይፈቀድላቸውም:: ከጊዜ በኋላ ማንበብ የማይፈቀደው ለምንድን ነው? ብዬ ጠየኩ:: መልሱ መንፈሳዊ ሞትን ስለሚያስከትል ነው የሚል ሆነ። እንደዚህ እንደመልሱማ ቢሆን ኖሮ ታማኝና ልባም መጋቢእቸው ወይም የአስተዳደር የበላይ አካላቸው አሥር ጊዜ ገና ድሮ በሞቱ ነበር:: ምስክሮቹ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በመንፈስ ሞቶ፣ ለሥጋ ጥቅም ብቻ የሚንቀሳቀሱ ናቸው ብንል የምንሳሳት አይመስልም:: ከላይ እንደተመለከትነው ማህበሩ እንዳያነቡ ለተከለከሉ አባሎቻቸው ከጠንቋዮች መጽሐፎች ሣይቀር እያነበበ ለድርጅቱ ጥቅም ማስጠበቂያ ይጠቅማል ብሎ ያመነበትን ሐሳብ

እያሳተመ ያድላቸዋል:: በዚህም ምእመናኖቻቸው እየተደነቁ ማሕበሩ እንዴት ሐሳብ አያልቅበትም? የእግዚአብሔር መንፈስ ነው እኮ እንደዚህ የሚረዳቸው እያሉ ይጃጃላሉ::

በሦስተኛ ደረጃ በዚህ ድርጅት ስሕተትና ተንኮል በቶሎ መንቃት የሚያስቸግር ነገር ቢኖር የድርጅቱ አባሎቻቸው ቆሞ ብለው የማሰብ ጊዜን ማሳጣት ነው:: ምስክሮቹ እርስበርስ ሐሳብ ስሐሳብ እንዳይለዋወጡ፣ ከግል አመለካከት አንፃር አንዱ ስለሌላው የማወቅና በግል ደረጃ የመወያየት ብሎ ነገር እንዳይኖር አባሎቻቸው በሥራ እንዲጠመዱ ማድረግ ነው:: ሲገናኙም የሚጫወቱት ማሕበሩ ባወጣው ኘሮግራም መሠረት ስለሥራ ወይም ስለስብከታቸው ብቻ ይሆናል:- ማሕበሩ አባሎቻቸውን እንዴት ውጥረት ወስጥ እንደሚከቱአቸው ቀጥለን እንመልከት:-

1ኛ እያንዳንዱ ወንደ ላጤ፣ ሴተ ላጤ እና የተጋቡት ቤተሰብ ከድርጅቱ ጽሑፎች ወይም በተለይ በቅርብ ከወጡት ጽሑፎች አስቀድመው በቤታቸው በግል ማጥናትና መረዳት እንደአለባቸው መመሪያ አለ። እንዲሁም የይሖዋ ምስክሮች የዓመት መጽሐፍ ተብሎ በየዓመቱ ከሚተተመውም መጽሐፍ በወጣው ኘሮግራም መሠረት የዕለት ጥቅስን አንብቦ መወያየትና መረዳዳት አንዱ ነው::

2ኛ. ከሰኞ እስከ አርብ ያሉት የሣምንቱ ቀናት በኘ ሮግራም የተያዙ ናቸው:: ለምሳሌ በቡድን የመጽሐፍ ጥናት ቀን፣ የቴኦክራቲክ ትምህርት ቤት ቀን፣ የአገልግሎት ትምህርት ቤት የስብሰባ ቀን፣ የመጠበቂያ ጥናት ስብሰባ ቀን፣ የተባሉት ኘሮግራሞች ላይ መገኘት በመልካም አቋም ላይ



የመገኘት ምልክቶች ናቸው:: እነዚህ ስብሰባዎች በሙሉ ከአንድ ሰዓት ያላነሰ ጊዜ የሚፈጁ ናቸው:: ከእነዚህ ስብሰባዎች የሚተርፍ ጊዜ ቢኖር የደከሙ ወንድሞችን እየዞሩ ማፅናናት ነው:: የደከሙ ወንድሞች የሚባሉት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ስብሰባዎች ላይ ብቅ ጥልቅ የሚሉና ጨርሶም የማይገኙ አባላት ናቸው:: ከዚሁ በላይ ደግሞ የግል ሥራና የበተሰብ ኃላፊነት ሲታከልበት ምስክሮቹ ምንም የሚተርፋቸው፣ ቆም ብለው ማሰብ የሚችሉበት ጊዜ አይኖራቸውም:: ይህ እውነት ነው::

የሰንበት ቀንም ቢሆን ከቤት ወደ ቤት በቡድን በቡድን እየሆኑ ለስብከት መሠማራት አለ: ከዚህም በላይ በዚሁ በሰንበት ቀን የሕዝብ ንግግር የሚሉት ነገር አላቸው:: አፈጮማ ካድሬዎች ወይም ወንድሞች ወይም በፈለጋችሁ ስም ጥሩአቸው ቢያንስ ለአንድ ሰዓት በተመረጠ ርዕስ ንግግር ስለሚያደርጉ ማንኛውም የይሖዋ ምስክር ቤተሰብ ታናናሽ ልጆች ሣይቀሩ የማዳመጥ ግዴታ አለባቸው:: ከዚህም በላይ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር ስለይሖዋ ባለበት ሁሉ መስበክ ስለአለበት ሰብኮ ለማጥናት ፈቃደኛ የሆነውን ሰው በሳምንት አንድ ጊዜ የማስጠናት ግዴታም አለ:: እነዚህና እነዚህን በመሳሰሉት ምክንያቶች ምስክሮቹ ጊዜ አይኖራቸውም።ስለዚህ ቶሎ በዚህ ድርጅት ተንኮል ከማይነቃበት ምክንያቶች አንዱ ይኸው ነው:: የይሖዋ ምስክሮች ሕዝብን በዚህ መልኩ የሚበዘብዙት በእምነት እያሞኙአቸው ሲሆን ሌላ ሰዎች ከፍተኛ ትምህርት ቤት ገብተው እንደማይማሩ በልዩ ልዩ ዘዴ እያናናቁ በማጥላላት ነው:: ስለዚሁ ለመረዳት በቅርቡ እ.ኤ.አ. ሐምሌ ወር 2005 የወጣውን ንቁ (Awake) ከገጽ 24-25 በጥሞና አንብቡ::

የይሖዋ ምስክሮች ከፍተኛ ትምህርት ቤት ገብቶ መማርን ከመከልከላቸውም በላይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ገብቶ መሥራት ከአውሬው ምልክቶች አንዱን ወድደው መቀበል ነው፤ ስለሚሉ ይከለክላሉ:: በዚሁ ምክንያት በኢትዮጵያ ኢሴኤ (ECA) ለመመሥረት በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ትንሽ ቢሮ ተሰጥቶአቸው ለድርጅቱ ሠራተኛን እየመለመሉ የሚቀጠሩበት ወቅት ነበር:: እኔም ከሌላ ሰው ጋር ለመቀጠር ሔጄ ተመዝግቤ ነበር:: በተመዘገቡት መሠረት ፈተና ተቀብለው ግማሹ ለጸሐፊነት፣ ግማሹ ለዘበኝነት፣ ግማሹ ለጽዳት፣ ግማሹ ለተላላኪነት ይቀጠሩ ነበር:: አብረን ከተመዘገብን አንዱ እንደገና ተመልሶ ፈተናውን ወስዶ ለተላላኪነት ሲቀጠር እኔ ግን ማሕበሩ እዚያ መቀጠር ክልክል ነው ስለአለኝ ተውኩት:: ያ በተላላኪነት የተቀጠረ ግለሰብ እራሱን አሻሽሎ የአንድ ክፍል ኃላፊ፣ ባለብዙ ሺ ብር ደመወዝ፣ በመጨረሻም ወፍራም ጡረታ ይዞ እንደወጣ አውቃለሁ:: ይህ ከበደሎቼ አንዱ ነው:: እኔ ግን ምንም ለማላገኝበት ከምሽቱ 2 ሰዓት ከግሌ ሥራዬ እየወጣሁ እስከ መሽቱ 6 ሰዓት ድረስ ቁጭ ብዬ በየቀኑ የመጠበቂያ ማማ ጋዜጣቸውን ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ እየተረጐምኩ፣ በእስቴንስል ታትሞ ለወንድሞች ወይም አባላት እንዲሰራጭ ይደረግ ነበር:: ይህ ሁሉ አገልግሎት የሚሠራው በደስታና በነፃ ነበር፡ አባሎቻቸው በፈቃደኝነት በሙሉ ልብ ስለሚሠሩ ደስተኞች ናቸው:: ይህ ደስተኝነት ብቻ ይመስለኛል ጥቅማቸው:: ደስተኝነታቸው ግን በውሸት ላይ የተመሠረተ ነው:: ይህንን በውሸት ላይ የተመሠረተውን



ተስፋቸውና ደስታቸው መሠረት ስለሌላው አንድ አንድ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚባንኑ አሉ::

ለምሳሌ አንድ እንግሊዛዊ ወጣት በዚህ አትማሩ በሚለው ፕሮፖጋንዳ ሰብከታቸው ተታልሎ ከካቢሪጅ ዩኒቨርስቲ የዓለም መጨረሻ ስለደረሰ መማር አያስፈልግም ብሎ ይወጣና የእነርሱ ልዩ ሙሉ ጊዜ ሰባኪ በመሆን ለአያሌ ዘመን ያገለግላል:: ትምህርቱን አልማርም ብሎ በመተው ጉዳት እንደደረሰበት፣ ትምህርታቸውን የተማሩት ግን የትና የት እንደደረሱ፣ ይህ ድርጅት በዚህ ውሸት ሰብከታቸው ዕድሉን እንደአኰላሹት ይረዳል:: ትምህርታቸውን የጨረሱት ወፍራም ደመወዝ እየተከፈላቸው በደስታ ሲኖሩ እርሱ ግን በዚህ በረቀቀ የውሸት ሰብከታቸው ተራ የመጽሐፎቻቸው ሻጭ ሉቅ በደረቴ እንደአደረጉት ይገነዘበዋል:: ስለዚህ ሌሎች የሚታለሉትን በጐች እየሰበከ ወደ ድርጅታቸው ማምጣትን ማቆም አማራጭ የማይገኝለት ውሳኔ መሆኑን ተረድቶ የሚሽኔሪሥራቸውን ይተዋል:: እንደ ኢስትቬንሶን አባባል ከበጐች አለመሻል ነው:: ብዙ በጐችን በአንድነት ወደ አንድ ገደል ወይም ወንዝ ለማሻገር ብትመሩ እሺህ ብሎ አይሻገሩም-በቂጣቸው ወደ ኋላ ይጋፋሉ:: ነገር ግን አንድዋን በግ ነጥሎ እንድትዘል ወይም እንድትሻገር ከወረወሯት ሁሉም በጐች እርስዋን ተከትለው እየዘለሉ ይገባሉ:: ይህ የበጐች ጠባይ ነው:: ስለዚህ ጉዳይ የበግ እረኞች የበለጠ ያውቃሉ:: እነዚህ በበግ የተመሰሉ የዋች ታዎር ምዕመናኖችም እንዲሁ ናቸው ይላል ኢስቲፈንሶን፡ ይህ ግለሰብ በዚህ መልኩ የተማረረ ስለነበር ማሕበሩ በ1975 ዓ.ም. የዚህ ዓለም እልቅት ሆኖ የእኛ ድርጅት ብቻ እሬሣዎች መካከል ቆሞ ይቀራል

የሚለው ከንቱ ስብከታቸውን በ1966 ዓ.ም. ባወጡ ጊዜ በመረረ መልኩ ተቃወማቸው:: ተቃውሞውንም የ1975 ዓ.ም. ጥፋት (The doom of 1975) በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ ጽፎ ሕዝቡ እንዳይሣሣት አስጠንቅቆአቸው ነበር:: ያኔ ይህንን መጽሐፍ በአንክሮ ካነበብኩ በኋላ የተሻለ አመለካከት አለው ብዬ ለገመትኩት አንድ ኤርትራዊ፣ ሰለሞን ዘረማርያም ለሚባል ሰጠሁት:: ሰለሞን ገና ኦርእስቱን እንደአየ መጽሐፉን ወረወረብኝ:: በኋላ የያዝኩት ሃይማኖቴ እያስደሰተኝ ስለሆነ ውሸትም ቢሆን ለመመራመር አልፈልግም ብሎ አረፈ:: እንግዲህ ፊደል በመጠኑ ቆጠሩ የተባሉት 12ኛን የጨረሱት እንዲህ ሲሆኑ፣ አብዛኛው አባሎቻቸው መሐይሞች ስለሆኑ ከተነገራቸው ውጭ ማሰብ የማይሹም አሉ ማለት ነው::

ከጥቂት ዓመታት በፊት እነዚህ እራሳቸውን ልባሞች ብለው የሚጠሩ፣ የዋች ታዎር መሪዎች ልበቢስ በጐቻቸውን የበለጠ ልብ እንዲያጡ ለማድረግ «የሰው ዘር አምላክን ሲሻ» በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ አሣትሞ ነበር:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ምርጥ ምርጥ የዓለም ፀሐፊዎች በምርምር የደረሱበትን እየጠቃቀሱ ከጻፉ በኋላ ከ6 የማያንስ የዓለም ታላላቅ የሃይማኖት ትምህርቶችን እጅግ በጣም እየነቀፉ ጽፈዋል:: እነዚህ የሃይማኖት ድርጅቶች ያረሙአቸውን የትምህርት አይነቶች ጭምር እያነሱ፣ አሁንም ገና እንደአላረሙ በመቁጠር ክፉኛ ከተቹአቸው በኋላ የእነርሱ ድርጅት ብቻ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ እውነተኛ እንደሆነም በድፍረት ገልጸዋል:: ከሁሉ ከሁሉ በጣም የገረመኝ ካለሥርዓታቸው በውሸት ወሬ እኔን ማስወገዳቸው ነው::



## ታሪኩ እንዲህ ነው

እኔ በዚህ ድርጅት እውነተኛነት በብዙ መልኩ ስለተጠራጠርኩ በ1975 ዓ.ም. ዓለም ይጠፋል የሚለው ስብከታቸውን መስበክ ተውኩ:: እንዲሁም የሠራተኛ ማሕበር አባልና የቀበሌ ሊቀመንበርም ሆኜ ተመረጥኩ:: በዚህን ጊዜ ድርጅቱ በፖለቲካ ውነተኞች የይሖዋ ምስክሮች አይካፈሉም ብሎ ስለሚያምን እኔን አስወገዱኝ:: ይህ የእነርሱ ሕግ ስለሆነ ምንም ችግር የለም፣ ተቀብዬአለሁ::

ከጊዜ በኋላ ቀበሌንም ተውኩ፣ የሠራተኛ ማህበር አባል መሆንንም ተውኩ፣ እንዲሁም የኢሠፖ አባልም ስለአልነበርኩ እኔን ሣያነጋግሩኝ ስለአስወገዱኝ ከጊዜ በኋላ ሕሊናቸውን ፀፀቷቸው ይሆን ይሆናል እኔ በማላውቀው አንድ አንዶቹ እየቀረቡኝ ወደ ድርጅቱ እንድመለስ ፍንጭ ይሰጡኝ ጀመር:: ከዚህ ሁኔታ የተነሣ እኔም እንደዛሬው ተመራምሬ ጉዴን በሚገባ የተረዳሁ ስለአልመሰለኝ ወደድርጅታቸው ተመልሼ እንድንቀሳቀስ ፈቀዱልኝ:: እዚያው ጐረቤቴ የነበረ ወንድም ማሞ ብርሃኔ የሚባል ሰው ቤት ስብሰባ ስለነበር አንድ አንዴ እየሔድኩ ማዳመጥ ጀመርኩ:: እኔን ድሮ የሚውቁኝ የዛሬ የድርጅቱ ባለስልጣኖች፣ በተለይም እንቅፋት የሆንኩባቸው ኤርትራውያኖች የእኔን ፊት በዚህ ድርጅት ውስጥ እንደገና ማየት የፈለጉ አልመሰለኝም:: ስለዚህ አንድ አንዶቹ በተናጠል እየቀረቡኝ ይተነኳኩሱኝ ጀመር:: ለምሳሌ እስጢፋኖስ ንጉሤ የሚባል ኤርትራዊ እንሪኮ ቁጭ ብዬ ቡና ስጠጣ እንደአጋጣሚ ይመጣና ያነጋግረኝ ጀመር:: ውዲ የሚባል ቀደም ተብሎ እኔን የይሖዋ ድርጅት እንድገባ የሰበከኝ መሆኑ ነው፣ ከአዲስ አበባ

ወደ አስመራ ሔዶ እንዲሠራ በማሕበሩ ተዛውሮ ነበር:: እዚያ አዝመራ በነበረ ወቅት ከላይ ስሙ የተጠቀሰውን ሰውም ሰብኮ ወደ ድርጅቱ እንደ አገባው ይነገራል:: ወደ አዝመራ ከመዛወሩ በፊት አበበች አብሬ የምትባል የከንባታ ተወላጅ እህት ልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚ (Special Proneer) ሆነ አንዲት አገልግል ከወንድም ውዲ (Brother woody) እና ሚስቱ ጋር ወደ አስመራ አብሮአቸው ተዛውራ ነበር::

ከላይ የተጠቀሰው ግለሰብ ማለት እስጢፋኖስ ንጉሴ ከዚህች አበበች አብሬ ከተባለችው ጋር ይጋባሉ:: ታዲያ ይህ ግለሰብ ወይም አቶ እስጢፋኖስ ንጉሴ ፈረንጆች መልአኮች፣ ፍጹማን፣ የማይሣሣቱ፣ ጥቁሮች ግን ለጥቅም ብሎ ብቻ ከፈረንጆች ጋር እንደሚጠጉ እያነሳ መውቀስ ጀመረ:: በተለይም ኢትዮጵያኖች እያለ የማይገባውን ቃላት መወርወሩን ቀጠለ:: በዚህን ጊዜ ከቁጥጥር ወጭ ሆንኩና ያንተን ሚስት አበበችን ይህ የምትአመልከው ፈረንጅ እያገላበጣት . . . ነበር አልኩት:: ያልኩትን ቃላት እዚህ ላይ መድገም ነውር ሆኖብኝ በዳሽ አልፌዋለሁ::

ይህንን ምስጢር መናገር አልነበረብኝም ነበር:: ይህንን ምስጢር ለማወቅ የቻልኩት በነበረኝ ሥራ ሐላፊነት ምክንያት ስለነበር በዚህ መልኩ ያወቁትን መግለጡ ትክክል አልነበረም:: ግን ግለሰቡ በሚያሰማኝ የአነጋገር እብሪት የተነሣ አካፋን አካፋ ካላሉት እንዲሉ ዓይነት ሆነብኝና የማውቀውን ምስጢር አወጣሁ::

ይህ በአቶ እስጢፋኖስ ንጉሤ እንደመልአክ የተቆጠረው ፈረንጅ ከአቶ እስጢፋኖስ ሚስት ጋር እና ከሌሎችም



የወንድሞች ሚስቶች እህቶች ጋር ወሲብ ይፈጸም እንደነበር በመጋለጡ ማህበሩ ይህንኑ ጉዳይ እንድንከታተል በጽሑፍ አሳውቆኝ ነበር:: እራሱ ሕሊናው ወቅሶት ንስሐ በመግባት ለማሕበሩ ይናዘዝ ወይም ሌሎች በዚህ ዓይነት በደል የተፈፀመባቸው እህቶች ለማሕበሩ አጋልጠውት ይሁን በውል ባልታወቀ ምክንያት ይህ አሜሪካዊ ወንድም እንዲህ ያለ ተግባር መፈፀሙን ለእኛም ተጽፎ ከእርሱ ጋር ግንኙነት የፈፀሙት እህቶች እንዲጠየቁ ጭምር ተነግሮን ነበር:: ከተጠየቀችውና እውነት መሆኑን ከተናዘዘችው የዚሁ የአቶ እስጢፋኖስ ንጉሴ ባለቤት ነበረች:: እስጢፋኖስ አብሽቆኝ እራሴን መቆጣጠር ተስኖኝ ከላይ በገለጽኩት መልክ በተናገርኩት ጊዜ ተበሳጭቶና አፍሮ ከአጠገቤ ተነስቶ ሔደ:: በዚህ መልኩ በተለያየን ሁለት ሣምንት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ከጉባኤያቸው እንደተወገድኩና፣ አባላቸውም ስለአልሆንኩ ማንም እንዳያናግረኝ በየጉባኤያቸው አወጁ:: በማህበሩ ደንብ አንድ ሰው ካጠፋ ጠርቶ እምነትና ክህደት መጠየቅና ከካደ በ3 ምስክሮች ማስረጃ ማስወገድ የተገባው ነው:: ይህንኑ ጉዳይ በአለፈው ሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም. የተወገዱትን ወንድሞች እየዞሩ በማፅናናትና ወደ ድርጅቱ እንዲመለሱ የመርዳት አሠራር ስለተፈቀደ ወንድም በየነ እና ወንድም ፋሲል የተባሉት ወንድሞች መጠተው በአነጋገሩኝ ጊዜ በደፈና የተወገድኩበትን ምክንያት አላወኩም ምንም ሣላጠፋ ነው ብዬ ነግሬአቸው ነበር:: እስኪ እናጣራስን ብለው ከሄዱ በኋላ ከእለታት አንድ ቀን ወንድም በየነ የተባለውን መንገድ ላይ አግኝቼ ስለተወገድክበት ምክንያት አለማወቅን ጉዳይ ደብዳቤ ጽፈህ አምጣ የሚል መልስ ሰጥቶኛል:: ከእነዚህ ወንድሞች

በፊትም ሊያናግሩኝ ለመጡት ነግሬአቸው ነበር:: ሊያነጋግሩኝ ከመጡት አንዱ የማውቀው መኮንን ግዛቸው የሚባል ወንድም ነበር:: እነርሱም ቢሆን ተመልሰው አልመጡም::



## ምዕራፍ 15

## የድርጅቱ የአባላት ምልመላና የአእምሮ እጥበት ዘዴ

ይህ ድርጅት ከተመሠረተ ዕድሜው ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ሆኖዋል:: የመጀመሪያ የስብከት ርዕሳቸው የዓለም መጨረሻ ቀርቧል፣ ከእኛ ድርጅት ሌላ ሰው የሚድንበት የለም የሚለው ስብከታቸውን የሚያደምጥ ሰው እንደአገኙ በጥንቃቄ ልዩ ስልጠና ይሰጡታል:: ይህንን ስልጠና ጉልማሳ በሆነው በማህበሩ አባል ቢያንስ በሣምንት አንድ ጊዜ አሊያም በሣምንት ሁለት ጊዜ ያስለጥኑታል:: እያንዳንዱ የሥልጠና ሰዓት ርዝመት በምንም መልኩ ከአንድ ሰዓት የማያንስ ነው:: እንደዚህ ያለ ጥናት ቢያንስ ለ6 ወራት ይቀጥላል:: በዚህ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ በደንብ የአእምሮ እጥበት እንደተካሄደበት አስጠኚው ወይም አሰልጣኙ ካረጋገጠ በኋላ የቤት መጸሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አገልጋይ ወይም ሐላፊ ስለአለ፣ አዲሱን ሰልጣኝ ያየውና ካመነበት ወደ ጉባኤያቸው እንዲቀላቀል ይፈቅዳል፣ ወይም ደግሞ ሥልጠና ይቀረዋል ብሎ ካመነ ለሌለው 6 ወር እንዲቀጥል ያደርጋል:: ምናልባት የአሰልጣኙ ድክመት መስሎ ከታየው በዘዴ ልዩ የሥልጠና እርዳታ የሚያገኝበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥርለታል:: የድሮ አሰልጣኙ በማሰልጠኑ ሥራ እንዲቀጥል ዝም ይለውና በጉን ግንኙነት ተፈጥሮ የሚረዳበትን ዘዴ ሊቀይስ ይችላል:: ጥናቱ ግን ያው መጀመሪያውኑ ሰብኮ ጥናቱን ወይም ስልጠናን ያስጀመረው ወንድም ነው:: በሌላ አባባል አንድ ሰው አንድን አዲስ ሰው ሰብኮ ስልጠና እንዲጀምር ከአስደረገ ወይም ካሣመነ አዲሱ አማኝ የእገሌ ተማሪ ወይም ጥናት ወይም ሰልጣኝ ተብሎ ይጠራል:: እርሱ ሰብኮ ወደ

ጉባኤው በማምጣቱ ስንት ሰው እንደ አሳመነ ሪፖርት ስለሚያደርግ ማንም ሰው አይቀማውም:: ነገር ግን ከላይ እንደተባለው በሥልጠና ጥራትና ዘገምተኝነት የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት አገልጋይ ካመነበት ልዩ ተጨማሪ እርዳታ ሊያደርግለት ይችላል:: ከዚያም ብቃቱ ከተረጋገጠ ወደ ጉባኤ አዳራሽ ይወስድና ከጠቅላላው ስብሰባ ኘሮግራም ተካፋይ እንዲሆን ይጋበዛል:: የ6ቱ ወር ጥናት እንደአለ ሆኖ ስደት በሌለበት አገር ወደ ጉባኤው የሚወስደው ወዲያውኑ ነው:: በስደት ሥር በሆኑት አገሮች ነው ወደ ምስጢራዊ የስብሰባ ቦታቸው ለመውሰድ ከ6 ወር በኋላ ብቻ የሚፈቀደው:: የይሖዋ ምስክሮች የሆኑት አባላት ሁሉ በዚህ መልኩ የሚሰብኩ ሰባኪዎች ናቸው:: ይህ ሁሉ ሥራ የሚሠራው በነፃና በፈቃደኝነት ነው::

ከዚህ በኋላ ከሌሎች ሁሉ ተዋውቆ ሲያበቃ በስብሰባዎች ሁሉ የመገኘት አስፈላጊነት ተብራርቶለት ኘሮግራሞችን ይሰጡታል:: እንዲሁም ከቤት ወደ ቤት እየሔዱ መጽሐፍ ቅዱስን የመስበክ ዘዴ፣ መጽሐፎችንና መጽሔቶችን የመሸጥ ዘዴ፣ እንዴት እንደሆነ እንዲመለከት ከሌሎች ጋር ተመድቦ እንዲዞር ይደረጋል:: አንድ ሁለት ቀን እየዞረ ከተመለከተ በኋላ እራሱ ደግሞ እንዲሰብክ ያበረታቱታል:: እስኪ አሁን ይህ ቤት ያንተ ተራ ነው፣ እስኪ ሞክር እያሉ ያበረታቱታል:: በጽሑፌ ላይ እየደጋገምኩ ስለመጽሐፎቻቸው መሸጥ ጉዳይ አንስቼአለሁ:: የይሖዋ ምስክሮች የሠራተኞችን ደመወዝ አይከፍሉም፤ የይሖዋ ምስክሮች ስል ድርጅቱን ማለቴ ነው:: አባሎቻቸው ተራ እየገቡ በነፃ ይሠራሉ:: ሙሉ ጊዜያቸውን በማሕበሩ ሥራ ላይ የሚያሳልፉ ከሆነ መጠለያና ምግብ ብቻ ቤቴል በሚሉት ሆስቴል



ውስጥ እያኖሩአቸው ይመግቡአቸዋል:: ተራ እየገቡ ምግብን የሚያዘጋጁትም እራሳቸው ስለሆነ ለወጥ ቤት ሠራተኛም የሚከፍሉት ደመወዝ አይኖርም:: እንደዚህ ባለ መልኩ በነፃ ጉልበት ደመወዝና ቀረጥ ሣይከፍሉ የሚያሳትሙአቸውን ሕትመቶች በእጅ አዙር በከፍተኛ ዋጋ ተመን ስለሚሸጡ ነው:: መጽሐፎችን ይሸጣሉ በእጅ አዙር ሲባል እንዴት ነው? እንዲህ ነው:-

የይሖዋ ምስክሮች ድርጅታችን የበጐ አድራጐት ድርጅት ነው:: ዓላማውም የመጽሐፍ ቅዱስ እወነቶችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀስን ማስተማር ነው:: ይህንንም ስንአደርግ በመጽሔት፣ በጋዜጣ፣ በትንንሽ በራሪ ጽሑፎች (Tracts) እየፃፍን በነፃ ለሕዝብ ማደል፣ ማስረዳትና መግለጥ ነው ብለው በሕግ ዓላማቸውን ስለአስመዘገቡ፣ ከሽጡ ይህንን የተመሠረቱበትን ሕግ ስለሚጥሱና ስለሚከሰሱ፣ ከዚህም በላይ ቀረጥ ከፈሉ ስለሚባሉ መጽሐፎችን አንሸጥም ይላሉ:: በእንግሊዝኛ ቋንቋ "We are placing literatures" ሕተመቶቻችን ለፈላጊዎች እናበረክታለን ይላሉ:: ይህ አባባላቸው በነፃ መስጠትን ወይም ማደልን ያመለክታል:: እነርሱ ግን በውድ ዋጋ ይሸጣሉ:: ከሚገባ በላይም በእጅ አዙር ያስከፍላሉ:: ከላይ እንደተብራራው ድርጅቱ በምዕመናን ገንዘብና ጉልበት ስለሚንቀሳቀስ ምንም የሠራተኛ ወጪ የለውም ብለናል:: ስለዚህ እያንዳንዱን ፈቃደኛ ወይም ከእነርሱ ጋር ለማጥናት የሚፈልገው ሰው ይህ ዓይነቱ መጽሐፍ ይረዳሃል እያሉ ጽሑፎቻቸውን ያስተዋውቃሉ:: ዋጋ ስንት ነው? ሲባል እኛ ለዚህ ለአምላክ ድርጅት እንደአቅሙ ግለሰቡ አስቦ የአቅሙን ያህል ይከፍላል እንጂ ዋጋውን ተመን

አውጥተን ይህን ያህል ነው አንልም:: የማሕበሩም ደንብ አይደለም:: ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል እንዲሉ እያንዳንዱ ግለሰብ አስቦ የአቅሙን ይከፍላል:: ይህንን የአምላክ ድርጅት በመርዳትም ጭምር አቅም ያላቸው ጨመር አድርገው ይከፍላሉ:: አቅም የሌለው ደግሞ እንደ አቅሙ የሚችለውን አስተዋጽኦ በፈቃደኝነት ሊያደርግ ይችላል ይላሉ:: በዚህን ጊዜ በአብዛኛው ከእውነተኛው የመጽሐፍ ዋጋ በላይ በእርዳታ መልክ ጭምር ይከፍላል:: ምስክሮቹ ግን በዚህ መልክ ለሚሸጡት ሕትመቶችና መጽሐፎች ቀረጥ አይከፍሉም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ከመጽሐፎቹ ዋጋ ከሚገባ በላይ ያገኛሉ:: በዚህ መልኩ ተበረታቶ ወደ ድርጅታቸው የሚገባ ሰው ያው እንደነርሱ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ይሆናል:: እንዲህ ያለው አዲስ አማኝ ከጳጳስ የሚበልጥ ይመስለዋል እንዲሉ ከነባሮቹም ይልቅ ጋል ጋል የሚል ተስፈንጣሪ ይሆናል::

ከዚህ በኋላ ከድርጅቱ ጽሑፍ በስተቀር የማያነብ፣ ከድርጅቱ ሐሳብ ሌላ ሐሳብ የማይቀበል፣ የእነዚህ ዓለም ሃይማኖት ድርጅቶች፣ የዓለም መሪዎች፣ የንግድ ተቋማት በሙሉ የሠይጣን ድርጅቶች እንደሆኑ አምኖ መስበክ ነው:: እንደዚህ ባሉት ድርጅቶች የሚጻፍ፣ የሚሰነዝር ሐሳብ ሁሉ የሰይጣን ዲያብሎስ ድርጅቶች ፕሮፖጋንዳ እንደሆነ ተቆጥሮ ተቀባይነት ያጣል:: እራሱን በልዩ ማሕበረሰብ ውስጥ እንደገባ ቆጥሮ ይኩራራል:: «የአዲሲቱ ዓለም ማሕበር አባል ነኝ» እያለም ይሰብካል:: ከዚህ በኋላ እንደላስቲክ እየተሳበ በእውን የማይደረስበት የሕልም ሩጫውን ይቀጥላል::



## <u>የአባልነቱ ዋስትና እስከሰበከ ብቻ ነው</u>

ይህ ድርጅት በዚህ መልኩ አሰልጥኖ ያቀፈው ሰው በአባልነቱ የሚቀጥለው እየሰበከ በየወሩ ምን ያህል ሰዓት እንደሰበከ በሚያሳየው ፎርም ላይ ሞልቶ ሪፖርት ለድርጅቱ እስከመለሰ ጊዜ ድረስ ብቻ ነው:: አንድ ወር በሆነ ምክንያት ባይሰብክ ይህ ግለሰብ ለዚያች ወር የይሖዋ ምስክር ወይም አባላቸው እንደአልሆነ ይቆጠራል:: በሕመም ይሁን በልዩ ልዩ የግል ምክንያቶች በማከታተል መስበኩን የሚያሳይ ሪፖርት ካላደረገ እንደዚህ ላለው አባላቸው ልዩ ስም ያወጡለታል:: በጣሙን ጥሩ ስም ታሚል የሚል ይሆናል:: በጣሙን የከፋ ከመሰላቸው ሞቶዋል እያሉ ይጠሩታል:: በሞት ሣይለናበት እራሳቸው ያስናብቱታል:: ለምሳሌ ስለሁለት ባልና ሚስት ግለሰቦች ማውሳት ይቻላል:: ሚስቱ ፋንቱ ትባላለች፤ ፋንቱ በቴሌኮሙኒኬሽን በስልክ ኦፕሬተርነት ተቀጥራ ትሠራ ነበር:: ባልዋ ደገሞ ድሮ አርማ ጋራዥ እየተባለ ይጠራ በነበረው ድርጅት ወስጥ ይሠራ ነበር:: ወንድም ሽፈራው ይባላል:: ምንም እንኳን ድርጅቱ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መሥሪያ ቤት አባሎቻቸው እንዳይሠሩ በተቻለ መጠን የሚመክር ቢሆንም ፋንቱ የቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤትን ትታ ኢሲኤ ገብታለች:: ደመወዙ አጓጉቷት ይሆናል:: በዚህ መልክ አብረው እየኖሩ ሳለ አቶ ባልየው መስበኩን እና ወደ ጉባኤ መምጣቱን ያቋርጣል:: አንድ ሰው በጉባኤው ስብሰባ ላይም ሆነ በስብከቱ ሥራ ላይ ካልታየ እገሌ ምነው ጠፋ? እየተባለ እርስ በርስ የመጠያየቅ ባሕል አለ:: በዚሁ ባሕል የተነሣ ባለቤቴ ወይዘሮ እቴን ፀሐይ ዓለሙ እህት ፋንቱን ምነው? ወንድም ሽፈራው የት ሔደ?

በዚህ ሰሞን አላየሁም ብላ መጠየቅ፣ የሚስቲቱ መልስ ምን ይመስላችኋል? «ሞቷል» የሚል ነው። በዚህን ጊዜ የኔዋ ሞኝ እውነት መስሎአት ውይ! ውይ! ውይ! ወንድሜን ወንድሜን እያለች እሪታዋን አቀለጠች። በመጨረሻም ፋንቱ በመንፈስ ሞቷል ማለቴ እንጅ በሥጋማ አለ ብላ አረጋጋቻት። እኔም ትንሽ በባለቤቴ አድራጐት እንደምገፈር አልኩ ያኔ። ለምን? ቢባል ይህንን የድርጅቱን የቋንቋ ባሕል ለለማወቋ፣ የእኔው የጉባኤ አገልጋይ ባለቤት ሆና እንዴት እንዲህ አደረገች በሚል ስሜት ነዋ! በደንብ ባለማንቃቴ ነዋ!

በዚህ መልክ ነው ይህ ድርጅት ለጊዜው የሚከንፉትን ብቻ እያቀፈ፣ ነገር ግን ነባር አባሎቻቸውን እያገለለ ስም የሚያጠፋ። በመካከላቸው የብዙ ዘመን አዛውንት አባላት የላቸውም። የጥንት አባሎቻቸውን አቅፈው ቢይዙና በሆነው ባልሆነው ምክንያት እየነቀፉ ባያገልሏቸው እነዚህ የጥንት አባሎቻቸው መልካም አርአያና ሞገስ በሆኑላቸው ነበር። ነገር ግን የድርጅቱ ዓላማ በሰው መነገድ ስለሆነ፣ የሚነገድበት ሰው ደግሞ በወረት የሚከንፍ መሆን ስለአለበት፣ እነዚህ በወረት ከናፊዎች የማይከንፉትን ወይም የረጉትን አባላት አይተው እንደ እነርሱ እንዳይሆኑ፣ እነዚህን የማይከንፉትን ወይም እነዚህን ረጋ ያሉትን ማግለሉ የሚመረጥ ነው። እንደዚህ ካልሆነ በሰው ጉልበት በነፃ የመጠቀሙ ብልሃት ይበላሻል። እነርሱን ማግለል ማለት የድርጅቱን የትርፋማነት ሕልውና መጠበቅ ማለት ነው። ለዚህ አድራጐታቸው ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን የአንድ ባልና ሚስት ግለሰቦች ታሪክ ነው።



## የባልና ሚስቱ ታሪክ

አቶ ባል ወንድም ገብረማርያም አዲ ይባላል። ይህ ግለሰብ የነርስነት ሙያ ያለውና በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነበር። ያገባ ሲሆን ገና ልጅ አልወለዱም። በዚህ በምስክሮቹ የአእምሮ እጥበት ፕሮፖጋንዳ ካመኑ በኋላ የዓለም መጨረሻ ስለደረሰ እና ጊዜውም እጅግ አጣዳፊ ስለሆነ በዚህ በስብከት ሥራ ድርጅቱን ማገዝ ያፀድቃል፣ ሥራዬን ትቼ ልዩ ሙሉ ጊዜ አገልጋይ በመሆን ከባለቤቴ ጋር ላገልግል ብሎ ያመለክታል። እንደዚህ ብሎ እንዲያመለክት ይገፋፋል። ስለዚህ ልዩ ሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆኖ ከሚስቱ ጋር ለማገልገል ሁለቱም ፎርም ሞልተው ካመለከቱ በኋላ አቶ ባል ከትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት ይሰናበታል። በዚያን ጊዜ ልዩ ሙሉ ጊዜ አገልጋይ ማለት 65 የኢትዮጵያ ብር በወር እየተከፈለው ከ150 ሰዓት ያላነሰ ሪፖርት የሚያቀርብ ወይም 150 ሰዓት በወር የሚሠራ ሰው ነው። ስለዚህ ለባል 65 ብር፣ ለሚስት 65፣ በጠቅላላው 130 ብር እየተከፈላቸው በልዩ ሙሉ ጊዜ አቅኚነት እንዲያገለግሉ ወደ ጉሬ ይላካሉ። ልክ እዚያ ደርሰው ሥራ እንደጀመሩ በጠቅላይ ግዛቱ ጳጳስ ትእዛዝ በፖሊስ ተይዞ አቶ ባል ይታሠራል። ፍርድ ቤትም ቀርቦ የሕዝብን መልካም ባሕል የሚፃረር ሥራ ሲሠራ ተገኝቷል ተብሎ 6 ወር ተፈርዶበት ወህኒ ገብቶ አረፈ። እመት ሚስትንም በዓይነ ቁራኛ መከታተል ስለጀመሩ፣ አጠገብዋ ሆኖ የሚረዳት ማንም ስለአልነበረ ወደ አዲስ አበባ ትመለሳለች። አቶ ባልም 6 ወር ጠጥቶ ወደ አዲስ አበባ ይመለሳል። መታሠርንም ስለፈራች እዚያ መስራት ያስመቻልዋን ሁሉ በጊዜው ለማህበሩ ሪፖርት ተደርጓል። አሁን

ከ6 ወር እሥር በኋላ ወንድም ገብረማርያም አዲ መጥቶ በ65 ብር ተባዝቶ የ6 ወር ደመወዙ እንዲሰጠው ያመለክታል:: ይኸውም 65×6=390 መሆኑ ነው:: እንኳን የ6 ወር የአንድ ወርም አይከፈልም ተባለ:: ለምን ቢባል በእሥር ቤት ውስጥ እየሰበክ 150 ሰዓቶችን በየወሩ ሪፖርት ስላላቀረብክ ነው ብለውት አረፉ:: ለእነርሱ ሥራ ብሎ ቃስሮ፣ የግል ሥራውን ትቶ፣ በመታሠርህ 150 ሰዓት በወር ሠርታ ሪፖርት ስላላደረክ አይከፈልህም ስለተባለ ይህ ግለሰብ በጣሙን ተበሳጨ:: የባለሙያዎች እጥረት ስለነበር እንደገና አመልክተው ወደ ትምህርት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ተመለሰ:: አሁን ይህ ግለሰብ የት እንዳለ አላውቅም:: በሕይወት ካለ ስለዚሁ ጉዳይ እውነት እንዲመሰክር እጋብዘዋለሁ:: ምስክሮቹ አባሎቻቸው የከፍተኛ ተምህርት ተቋም ገብተው እንዲማሩ ለምን አይፈልጉም? እነርሱ ካላተሙት ጽሑፎች ሌላ ሌሎችን ጽሑፎች አባሎቻቸው እንዲያነቡ ለምን አይፈቅዱም? ለዚህ መልሱ አንድና አንድ ብቻ ነው:: ይኸውም የተማረ ሰው በማጭበርበር ሥራቸውና ዘዴአቸው ስለሚነቃ ነው:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን የሁለት አባላቸውን ታሪክ እንመልከት:- ግለሰቡ ቀኑ እሸት ይባላል:: ቀኑ እሸት ጥጋቡ አገኘሁ በተባለው ግለሰብ ይሰበክና ከይሖዋ ምስክሮች አንዱ ይሆናል:: ቀኑ እሸት ወደ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት ሲገባ ስንተኛ ክፍል እንደነበር አላስታውስም:: ጥጋቡ አገኘሁ የተባለውም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 8ኛን ያጠናቀቁትን እና የመግቢያ ፈተና ያለፉትን እየተቀበለ በቴክኒሽያንነት ያሰለጥን ስለነበር ወንድም ጥጋቡም በዚህ መልኩ ከዚያ ተመርቋል:: ቀኑ እሸት እና ጥጋቡ ፈተናውን አልፈው



በቴክኒሽያንነት ሰልጥነው ከተመረቁ በኋላ እዚያው ምኒልክ ሆስፒታል ውስጥ በጤና ጥበቃ ይቀጠራሉ:: እስከዚህ ድረስ ችግር አልተፈጠረም:: አገር ሰላም ነበር:: ጥጋቡ አገኘውም የላቦራቶሪ ቴክኒሽያን ሆኖ በምኒልክ ሆስፒታል ያገለግል ነበር:: ቀኑሽትና ጥጋቡ የማታ ትምህርታቸውን ቀጥሎ 12ኛን ካጠናቀቁ በኋላ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለተጨማሪ ከፍተኛ ስልጠና ቀኑ እሸትን ጭምር ወደ እንግሊዝ አገር ይልካቸዋል::

እንግሊዝ አገር ወደ አራት አመት ተምሮ ከተመለሱ በኋላ አቶ ቀኑ እሸት በቀጥታ ወደ ቤቴ ይመጣና አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ነው የመጣሁ ይለኛል:: እኔ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልወጣ፣ መጽሐፍ ቅዱስን እንደመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ የሥልጣን አካል ተቀብሎና አምኖበት የሚጠይቀኝ ስለመሰለኝ እጅጉን ሰፍ ብዬ በደስታ እንጂ ወንድም አልኩት:: ቀኑ እሸት ግን እግዚአብሔር ዝንብን ለምን ፈጠረ? ዝንብ ትጠቅማለች? አለኝ:: አትጠቅምም አልኩት:: ታዲያ እግዚአብሔር የማትጠቅመውን ነገር ለምን ፈጠረ አለኝ::

ለዚህ ጥያቄ በመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ እና የማያዳግም መልስ የለም:: አቋሜን ለመግለፅ በመላምት መተብተብ ይቻላል:: ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ በዚህ እና በዚህ ጥቅስ ምክንያት ነው ዝንብን እግዚአብሔር የፈጠረው ብዬ ለመመለስ አልቻልኩም:: ከኢቮሉሽን አንፃር እንዳልሞክር 1ኛ ከመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከትና መልስ ውጭ ይሆናል:: 2ኛ እራሴ የዚህ ሙሑርነት ብቃት የለኝም:: እንዲሁም ዝንብ ለእነሽረሪትና ለመሳሰሉት ለምግብነት ታገለግላለች ብዬ እንዳልል ታዲያ እግዚአብሔር ፍጡራንን እርስ በእርሱ ለምን እንደዚህ ያባላል?

የሚለኝ ሆነ:: ስለዚህ ይህ ጥያቄ ቀላል ስለአልሆነ እስኪ ከቻልኩ አስቤ እራሴ እመልስልሃለሁ ካልሆነም ማሕበሩን ጠይቄ መልስ እሰጥሃለሁ አልኩት::

በዚህን ጊዜ ከኪሱ አንድ ጽሑፍ አወጣና ሰጠኝ:: ወረቀቱም ከዛሬ ጀመሮ የይሖዋ ምስክር ስለአልሆንኩ፣ አባላችሁም ስለ አልሆንኩ ሠርዙኝ ወይም አስወግዱኝ የሚል ነው:: ከዚያ በኋላ አቶ ቀኑ እሸት ወደ ይሖዋ ምስክሮች ብቅ አላለም:: ቀኑ እሸት ብዙ ከውጭ ያሉትን መጽሐፎች አንብቦ የይሖዋ ምስክር መሆን አላስፈላጊ መሆኑን ስለተረዳ ምክንያት ፈልጐ ድርጅቱን እንደለቀቀ ነው የሚገባኝ:: ማህበሩም ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ገብቶ መማርን የሚቃወመው ሰዎች ዓይኖቻቸው ተገልጦ ክፉና ደጉን ለማወቅ እንዳይችሉ ነው:: በነገራችን ላይ ቀኑ እሸትን ሰብኮ ወደ ይሖዋ ምስክር ድርጅት ያመጣው እራሱ ጥጋቡ አገኘውም እንግሊዝ አገር ደርሶ ከተመለሰ በኋላ የይሖዋ ምስክሮችን ከቀኑ እሸት ጋር አብሮ ትቷቸዋል:: እኔ ወደ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት የገባሁት 12ኛን ሳልጨርስ ነው:: አቶ ጥጋቡ አገኘሁ ከእለታት አንድ ቀን ከማታ ትምህርት ቤት ሲመለስ ወደ እኔ ቤት ጐራ አለ:: ያኔ አቶ ጥጋቡ ከምኒልክ ሆስፒታል ቴክኒሻን ትምህርት ሙያ በዲኘሎማ ተመርቆ እዚያው ምኒልክ ሆስፒታል ይሠራ ነበር:: ወደ እንግሊዝ አገር ለመላክ የግድ 12ኛን መጨረስ አስፈላጊ ስለሆነ 12ኛን ለመጨረስ ማታ ማታ ይማር ነበር:: ያኔ ነው ታዲያ ወደ ቤቴ ጐራ ብሎ በነገር ፒን ወይም መርፌ ወጋ አድርጐኝ የሔደው::



እኔ በፍጹም አልረሣም! አቶ ጥጋቡ ምንነም ላያስታውስ ይችላል:: ከላይ እንደደጋገምኩት ከማታ ትምህርት ቤቱ እኔ ዘንድ በመጣ ጊዜ አንድ የሂሳብ መጽሐፍ በእጁ ይዞ ነበር:: የሂሳቡ መጽሐፍ እኛ ከተማርንበት የትምህርት ካሪኩለም ለየት ስለአለብኝ ይህ ምንድን ነው? ብዬ ጠየኩት:: ምን ያለኝ ይመስላችኋል? እንዲህ ነው ያለኝ:- «እባክህን አንተ ምን ታወቃለህ? ደክሞኛል ልሂድ» አለኝ:: ሣቅሁ! ግን አንጀቴን እያረረ ነበር:: ተልባም እያረረ ይስቃል ይባል የለም::

በዚህ ብሽቀት መሥሪያ ቤቴን ማታ እንድማር እንደምንም አስፈቅጄ በካቴድራል ማታ ትምህርት ቤት ገብቼ 12ኛን ከማጠናቀቄም በላይ የኢሴልሲ ፈተና ወስጄ ለዚያ ዘመን በ2.4 ለማለፍ ቻልኩ:: አቶ ጥጋቡ በፒን የነገር መርፌ ወግቶኝ ባያባንነኝ ኖሮ እስከዚህም ጥረት ባላደረኩም ነበር:: በዚህ አጋጣሚ አቶ ጥጋቡ አገኘሁን አመሰግናለሁ::

ምስክሮቹ ልክ እኔን እንደአስተኙኝ ሁሉንም አባሎቻቸውን በድንቁርና እንቅልፍ አስተኝተዋቸዋል:: ይሁን እንጂ ምስክሮቹ ምንም ሣያውቁ በዚህ ዓለም ካለው ሕዝብ ሁሉ እራሳቸውን እጅግ በጣም አዋቂዎች አድርገው ይቆጥራሉ:: ይህንን አሳዛኝ ሁኔታዎችን የሚያየው ሰው ከክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል ጋር እንደዚህ ለማለት ይገደዳል:-

«የደንቆሮ አእምሮ ምንኛ ታደለ፣
እውቀት አላጣውም ጅል እየመሰለ፣
እንኳን መጽሐፍ ማንበብ ፊደል ሣያጠና፣
ሁሉንም ያወቀ ይመስለዋልና::»

የይሖዋ ምስክሮች ጥራት ያለን የክርስቶስን ፈለግ የምንከተል ክርስቲያኖች ነን ይላሉ:: እንደአየነው ግን ታሪካቸው ይህንን አያረጋግጥም:: ከክርስቶስ አቋም አንፃር የማይንቀሳቀሱ በተግባራቸው ፀረ ክርስቶስ የሆኑ ናቸው:: ሰይጣን በብርሃን መልአክ እየመሰለ ይዋሻል እንደሚባለው መሆኑ ነው:: ለመሆኑ ፀረ ክርስቶስ ማን ነው? እንደ የይሖዋ ምስክሮች የክርስቶስ ተከታዮች ነን እያሉ ገንዘብ የሚያሳድዱ ዓይነቶቹ ሣይሆኑ ይቀራሉ? ከጠቅላላው ሕዝበ ክርስቲያን አንፃር ነገሮችን በአንክሮ ስንመለከት ፀረ ክርስቶስ ማን ነው?

ከሰባት ጊዜ በላይ ዓለም እንደምትጠፋም ወስነው፣ ለመዳን ከምድራዊ የይሖዋ ምስክሮች ጋር ሆናችሁ ሁለገብ አገልግሎት ካበረከታችሁ ነው ብሎ የሕዝብን ላብ ለድርጅታቸውና ለራሳቸው መበልፀጊያ ማድረጋቸው ምን ማለት ነው? ከዚሁ መጽሐፍ ከተገነዘብነው አንፃር ለጥያቄው መልሱን እንዲሰጥ አንባቢን መጋበዙ ይሻላል:: በጎች ልብ በሉ

ማጠቃለያ

ያንኪዎች በስመ ወንጌል ስብከት፣
ልበቢሶችን አታልለው፣ ጥቅም ለማግኘት፣
ወንጌል ጸሐፊዎች ባላስተማሩት፣
ለዓለም ንዋይ ብለው ሕዝብን አጭበረበሩት::
የጥንት ሐዋርያት በሞት አለፉና፣
ጊዜው አለፈና የኋላ የኋላ፣
በጉቹ እወቁ፣ የጥንቱ ትምህርት እንደተበከለ፣
ጌታ ቤተ መቅደሱን ሳደነቁት፣
እያለ አታድንቁ ይህን ነገር፣



በቅርቡ ይፈርሳል፣ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሣይቀር
ብሎ የተናገረው ትንቢት፣
በእርግጥ ተፈፅሟል በ70 ዓመተ ምሕረት::
ይህ የምነግራችሁ ቃል እስኪፈፀም፣
አጠገቤ የቆሙት ሞትን አይቀምሱም፣
ብሎ ሲያስተምር ያ ጌታ፣
ማንም ቃሉን አልተጠራጠረም ነበር፣ ለአንዳፍታ::
ኢየሩሳሌም ተጨንቃ ተጠባ፣
ከዚህም ከዚያም በጠላት ተከባ፣
ባያችሁት ጊዜ ይህንን እወቁ፣
ከእርስዋ እንድትሸሹ፣ በጣም ተጠንቀቁ::
በመሐልም ያሉት ወጥተው ይሸሹ፣
ከውጭ ያሉትም ወደ እርስዋ መግባት አይሹ::
ካያችሁ እንዲህ ያለ የጥፋት ምልክት ናሙና፣
ኢየሩሳሌም እንደምትጠፋ እወቁ፣ ትንቢቱ ነውና::
አትጠራጠሩ፣ ጥፋትዋ ቶሎ ይፈፀማል::
እንዳትታለሉ ይህ ትውልድ ይጠፋል::
ብሎ ኢየሱስ የተናገረው የትንቢት ቃል
በሉቃስ ምዕራፍ 21 ከቁ.20-24 ይገኛል::
በ70 ዓ.ም. መፈፀሙን ለሚጠራጠሩት
እናቆማለን ታሪክን በምስክርነት::
ነገር ግን የጥንት ሐዋርያት በሙሉ ካለፉ በኋላ፣
4ኛው መቶ ክፍለዘመን ሲሞላ፣
ትንቢቱ ስለዓለም መጨረሻ ነው ተባላ!
ከዚህ በኋላ ልበቢሶችን እያማለሉ ለማግዛት

አመቺ ሆነ፣ እንዲህ ያለ ብልሃት፡፡
በዚህ በተቀመረው ብልሃት፣
ይህንን ያለው ማቲዎስ፣
ያንን ያለው ደግሞ ሉቃስ፣
ወይም ደግሞ ኒቂያ ጉባኤ ነው፣
እያሉ በከንቱ መከራከር እንዲጠበቃ፣
መሆኑን አወቁ፣ ዳቦን መጠበቅ ከጨረቃ፡፡
ስርጎ ገቦች ከጊዜ በኋላ እንደፃፉ
እውነት ቢሆን ኖሮ ያኔ ዓለም የሚጠፋ
በማርቆስ ምዕራፍ 9 ቁ. 1 መሠረት ይከሰት ነበር በይፋ፡፡
በማቲዎስ ምዕራፍ አስራ ስድስ ቁጥር ሃያ ስምንት
ስለዓለም መጨረሻ ነው በተባለው መሠረት
በእነሐዋርያት ዘመን እውን ይሆን ነበር የዓለም ጥፋት፡፡
እውነት ቢሆን ኖሮ ያኔ ዓለም የሚጠፋ
የዘመኑ ትውልድ ሣያልፍ ይሆን ነበር ይፋ
አሁን ግን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስንት ትውልድ አለፈ?
በ52 ዓ.ም. ክርስቲያን የሆነ ጳውሎስም በሲቃ
ብሎ ነበር፣ አንሞትም በቃ፡፡
ጌታ ታጅቦ ሲመጣ በመልአክት አለቃ፣
እውነት ጳውሎስ ብሎ ቢሆን ኖሮ «አንሞትም በቃ»
ትንቢቱ ይፈፀም ነበር፣ አለቀ ደቀቀ፡፡
እውነት ስላልሆነ ጳውሎስም ሞተ፣ ትውልዱ ነጐደ፣
ታዲያ እየሱስ መቼ ከሰማይ ወረደ?
ይህ የምፅአት ስብከት እዚያው መቼ አበቃ፣
ይኸው እስከዛሬም እኛን አለቀቀ፡፡



ከላይ የተባለው ስብከት የተዘጋጀ፣
በኒቃ ጉባኤ ስመሆኑ አለን ማስረጃ፡፡
የዘመኑ ልበቢስ በጐች፣ አትአድክሙን እባካችሁ፣
ሌላ ነገር የለም፣ ይኸወ ነው ታሪካችሁ፡፡
የተቀነጨበን የክርስቲያን ታሪክ ይዛችሁ፣
በፈጠራ ታሪክ ሕዝብን አታወናብዱ እባካችሁ፡፡
እነዚያ ልባሞች የገኙ መደባችሁ፣
ይህንን ታሪክ የማያውቁ አይምስላችሁ፡፡
የጥንቱ ቅዱሳን ጽሑፍ ጠፍቷል ከተባለ
አሁን ለምትሰብኩት ምን ዋስትና አለ?
ጌቶቻችሁ እንዳልተበረዘ ቢሰብኩአችሁ፣
የጥቅም ጉዳይ ስለሆነ፣ አትፍረዱባቸው፡፡
በ1914 ዓ.ም. የሆነው በዕድሜ 14 ዓመት
ያያል ትላላችሁ የዚህን ዓለም ጥፋት፡፡
ከዚህ ላይ ልዩነቱን ከወሰድን (2006-1914) 92 ዓመት፣
እዚህ ላይ 14 ዓመት ስንደምርበት፣
የእነዚህ ቁጥሮች የድምር ውጤት፣
መሆኑን ተረዱ 106 ዓመት፡፡
የዘመናችን ማዕከላዊ የዕድሜ ዓመት፣
እንደማይበልጥ ታውቋል ከ69 ዓመት፡፡
ይህ ትውልድ አያልፍም ብሎ ማለት፣
ፍቺው ምን ይመስላል፣ እስኪ አስብበት፡፡
በካዲዎች ጠቋሚነት ቄሣር ታማኞችን ሲገድል፣
ጽሑፎቻቸውን ለቅሞ ሲያቃጥል፣
ካዲዎቹን ሾሞ፣ ሐቀኞችን ሲመነጥር፣

እነዚያ 318 የኒቃ ጳጳሳት
ለቁሣር ማደራቸውን አትጠርጥር::
እንዲህ ባይሆን ኖሮ በእውነት
ባልተጠመቀ ንጉስ የንቃ ጉባኤን መመራት
ይቃወሙት ነበር በፅናት::
ፖለቲካን በማይፃረር ዓይነት፣
ለመመሥረት ብለው፣ የሃይማኖቱን ሥርዓት፣
ያልተጠመቁ ንጉሥ ጉባኤውን መሩት::
እነዚያ 318 ጳጳሳት እያሉ በንቀት
ያልተጠመቀ ንጉሥ ጉባኤውን መምራት
ታዲያ ለምን ይመስልሃል ያልተቃወሙት?
ቅዳሚት ቀርታ፣ የአምላኩ የፀሐይ ቀን እንዲከበር፣
ከእነዚያ ጳጳሳት ማንም አልነበረም የሚከራከር::
ከዚህም ጉባኤ በኋላ
ከአለቃ እስከ ምንዝር እንዲነቃ
ማድረግ አስፈለገ ጉባኤዎችን እንደኒቃ
እነዚህም ጉባኤዎች የተደረጉት፣
በ325፣318፣431፣461 መሆኑን አትዘንጉት::
በእነዚህ ጉባኤያት የፀደቀን ሁሉ ቃል፣
ብለው ጠሩት ቅዱስ ወንጌል::
በእነዚህ ጉባኤዎች የረቀቁት ሕግጋት፣
በማይሻር መልኩ ተደነገገ፣ ሥርዓተ ሃይማኖት::
ከዚያ በኋላ እንኳን የኒቂያን ሕግ ሻረ የተባለ፣
ሣይፈቀድለት መጽሐፍ ቅዱስ ያነበበ ስንቱ ተቃጠለ?
የኒቂያን ሕግ ከተባለ እገሌ የሽራል፣



በግንድ እንጨት ላይ ታስሮ ይቃጠላል::
እናንተም እንዲህ ባለ ሕግ እየተመራችሁ፣
እንደመርዳት በኩርፊያ ታባርራላችሁ::
የምታስወግዱት የጥቅሶቹ ሕግጋት፣
የተደነገጉ ናቸው በኒቂያ ጉባኤያት::
እንደዚያ ዘመን መብት ቢ.'ራችሁ፣
እንኳን ማስወገድ ሰውን ታርዳላችሁ::
የማስወገዱ ሥርዓት የተደነገገው፣
የአምባገነኖች ሥርዓት እንዳይናጋ ነው::
በእንዲህ ታሪካዊ ሂደት በመጣ እምነታችሁ፣
ዛሬ ዓለም፣ ነጋ ዓለም ይጠፋል በማለት ሕዝብን
እታምሱ እባካችሁ?

ጠቅላላው ዓለም በእኛ ሃይማኖት ብቻ መመራት አለበት የሚሉት የይሖዋ ምስክሮች ብቻ አይደሉም:: ሌሎችም አሉ፤ ከእነዚህም:-

1ኛ. እራሳቸው የይሖዋ ምስክሮች

2ኛ. ሞርሞንስ የሚባል የሃይማኖት ድርጅት ሲሆን፣ መስራቹም ጆሴፍ ስሚዝ ጄ አር (Joseph Smith JR) በ1820 ዓ.ም. ዓምላክ ቀብቶኛል ብሎ የተነሣ ሰው ነው::

3ኛ. ሙኒስ የሚባሉ፣

4ኛ. ደግሞ በአይሁዲኢዝም ተጀምሮ በክርስትና እምነት እድገት አግኝቶ፣ በመጨረሻም ላይ በእስልምና ሃይማኖት የሚጠናቀቀውና በዓለም ሁሉ ተቀባይነት ማግኘት ያለበት የእኛ

ው ሃይማኖት ብቻ ነው የሚሉት አክራሪ ሙስሊሞችንም የሚያጠቃልል ነው:: የእስላሞቹ ምሑራን ከሆኑት አንዱ ያሉትን ቀጥለን እንመልከት:-

"Through Islam, with Christianity playing a preparatory role, the religious principles enshrined in the messianic prophecies find their complete development and achieved world wide acceptance. In this way Islam fulfills in more satisfactory and complete manner the old testament prediction that its religion will one day be accepted all over the world"

ISLAM - CHRISTIANITY AND THE STATE OF ISRAEL BY DR. AHMAD SHAFAAT 1991 INTRODUCTION AND PAGE 29.

ከላይ ከተጠቀሱት ከሃይማኖት ድርጅቶች አንዱ በዘመናዊ ሣይንስ፣ በቴክኖሎጂ በሀብት ብዛት፣ በደጋፊዎቻቸው ሕዝብ ብዛትም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ፣ የፖለቲካ ባለስልጣናትንም ቀልብ ከሣበ፣ ከእራሱ ድርጅት ውጭ ያሉት ሃይማኖቶች እንዳይኖሩ ሊያደርግ እንደሚችል ከአሁኑ አቋማቸው ተነስተን መረዳቱ ቀላል ነው:: ለምሳሌ አያድርገው እንጂ የይሖዋ ምስክሮች ከላይ የተጠቀሰውን የዕድገት ደረጃ በዓለም ላይ ቢቆናጠጡ ከእራሳቸው ሃይማኖት ድርጅት ውጭ የሆኑትን ሃይማኖቶችን ሁሉ ለማጥፋት ዓይናቸውን አያሹም:: ዛሬም ቢሆን እንኳን መላው ዓለም እንዲጠፋ ሌት ተቀን በመፀለይ ላይ ናቸው:: እንደዚህ ያለ ጉልበት ላይ ቢደርሱ ግን በዚህ መልኩ



ኃይል የሰጠን እግዚአብሔር ጠላቶቹን እንድንአጠፋለት ነው ብለው ሁሉንም ያጠፋሉ::

በዓለም ላይ በሃይማኖት ምክንያት ብዙ ጉዳት ደርሷል:: የመስቀል ጦርነት፣ ለ8 ዓመታት በኢራቅና ኢራን መካከል የተደረገው ጦርነት ክብሪት ጫሪ ሃይማኖት ነበር:: በሱናና በሻይድ ቡድኖች መካከል መገዳደሉ አልፎ አልፎ የሚካሔደው በሃይማኖት አመለካከት ሰበብ ነው:: በሕንዶች ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች መካከል፣ በናይጄሪያ የሸሪያን ሕግ በመከተልና ባለመከተል የተነሣ የጉሣ እልቂት ስንመለከት ከእነዚህ ሃይማኖቶች አንዱ በዓለም ላይ በሁሉም ጉልቶ የሚዋጣ ከሆነ፣ ሌሎችን ሃይማኖቶች አያጠፋም ብሎ ማሰብ የአእምሮ ድክመት ነው::

የጥንት ዘመን ስልጣኔም በሃይማኖት ጭቅጭቅ ምክንያት እንደጠፋችና ከአያሌ ዘመናት በኋላ ያ የጥንቱ ስልጣኔ በሚቲወሎጂ (Mythiology) መልክ ሲነገር ከቆየ በኋላ፣ ወደ እምነት ወይም ሃይማኖት ተለውጦ የሕዝብን አእምሮ በመግዛት ላይ እንደአለ የሚተርኩ ምሁራን አሉ:: እንደዚህ ስላለው የአእምሮ ፈጠራ እንደዚህ ለማለት የምንችል ይመስለኛል::

ሰው ለመሥራት በሐሳብ ሲቃኝ፣
አእምሮ አይልም በፍጹም በቃኝ::
ተቀርጾም ሆነ ተጽፎ የምንአየው ሁሉ፣
ከሰውሩ ሕሊና የተቀዳ ነው፣ በሙሉ::
ይህንን ጉዳይ ከሃይማኖት አንፃር ተመለከትን እንጂ፣
በዚህ ምክንያት የጥንቱ ስልጣኔ ጠፍቷል፣
እንደሜቲኦሎጂ::

ስለዚሁ ስለሜትዮሎጂ (Mythology) በጽሑፌ፣
ሣልመለስበት አልቀርም በ2ኛው መጽሐፌ::
ከዚህ አንፃር የሰውን አመለካከት አትኩረን ስናይ፣
የበላይነትን ሲሻ አንዱ በአንዱ ላይ፣
ለዓላማው ሲል አርፎም አይተኛ፣
የበላይ ካልሆነ እንደበሬ ሻኛ::
አመለካከታችን ሆኖ ካልተገኘ፣ ከሃይማኖት በላይ፣
ሴይፉን መማዘዙ አይቀር አንዱን በአንዱ ላይ



## ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| የሲ.ቲ. ራሴል ክደት | 9 |
| የራሴል ለጥቅም ወደ ሃይማኖት ድርጅት መመለስ | 10፣11 |
| ክርስቶስ እንዲወስዳቸው ተራራ ላይ ወጥተው ስለመጠባበቃቸው | 14፣15 |
| የራሴል አሮጊት ሴት ማግባት | 19 |
| የራሴል ሚስት ኩባኒያ ስም የፅዮን መጠበቂያ ማማ ይባል ነበር (Zion's Watch Tower) | 19 |
| የራሴል የሚስቱን ንብረት በስሙ የግል አሳታሚ ድርጅት ብሎ መቀየር | 21 |
| የሚሲስ ራሴል መብቷን አሳልፎ መስጠት | 22 |
| ራሴል በሚስቱ ላይ የወሰደው እርምጃ | 24፣25 |
| ለ3ኛ ጊዜ የራሴል በራሱ ስም የተመዘገበውን ንብረት ወደ በጉ አድራጎት ማዛወርና ስሙንም ዋች ታዎር ብሎ መሰየም | 26፣27፣28 |
| በ1914 ዓ.ም. የዚህ ዓለም መንግሥታት ድርሻቸው ይጠፋል ብለው መስበክ | 32፣33 |
| የቦርድ ዳይሬክተሮች ተብዬዎች መንቃት | 35፣36፣37 |
| የራሴል ሚስት ኩባንያን በሕግ ሽፋን ያስነጠቀወ ጠበቃ የጥቅም ተካፋይ መሆን | 34 |
| የይሖዋ ምስክሮች ክስረት ታሪክ | 42፣43 |
| ልበቢስ በጐቹ የድርጅቱ ሽቀጥ ናቸው | 44፣45 |
| የድርጅቱ ሹመትን በገንዘብ መሸጥ | 46፣47፣48፣49 |
| የጥንት ታማኝ ሰዎች ክአርማጌዶን በፊት መነሣትወይም ይነሣሉ ማለት | 54፣55፣57፣58 |

| | ገጽ |
|---|---|
| የምስክሮቹ ሕዝብን በሦስት መክፈል | 60፣61 |
| የእነአብርሃ በቶሎ አለመነሣት ጥያቄ | 63፣64 |
| ከዛሬ ነገ የጥንት ሰዎች በጉባኤያችን ትንሣኤ ያገኛሉ ብሎ በተስፋ ወደ ጉባኤ መሔድ | 58፣59 |
| የምስክሮቹ የድብቅ ትንሣኤን መስበክ | 72፣73 |
| ትንሣኤ የሚሆነው በአዋጅ ነው | 79፣80 |
| የምስክሮች በ1 የፍጥረት ቀን ላይ 6 ቀን መጨመር | 90 |
| ስለ የፍጥረት ቀን የተለያየ ትርጉም | 88፣89፣92 |
| በኢየሱስ የተሰጡ ሦስት ምልክቶች | 103፣108፣109፣110 |
| ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1974 ዓ.ም. ይፈፀማሉ የተባሉት ሁለት ትንቢቶች ሣይፈፀሙ መቅረት | 120፣121፣122 |
| ባቢሎን የሚል ስም ምስጢር ስለመሆኑ | 128 |
| የአውሬው ሰባቱን ራሶች እያፈራረቀ መጠቀም | 129፣130፣131፣132 |
| ከደራሲው አንፃር የቀዩ አውሬ ትርጉም | 134፣135 |
| ከደራሲው አንፃር የባቢሎን ትርጉም | 135፣136፣137 |
| የአሥሩ ቀንዶች ባቢሎንን የማጥፋት ትርጉም | 139፣140 |
| በ1968 ዓ.ም. የናይሮቢ ስብሰባ ታሪክ | 150፣151 |
| አለመጃጃል ክደት ከሆነ እነሆ፣ | 152፣153 |
| የኢየሱስ የኦሪትን ሕግ አክብሮ ማስከበር | 167፣168፣169 |
| የኢየሱስ ተከታዮች እስከ 66 ዓ.ም. ኦሪትን ማክበር | 171፣172፣173፣177 |
| በይሖዋ ዘንድ ኢትዮጵያውያኖች እንደ እሥራኤል ተቀባይነት ነበራቸው | 180፣181፣182 |
| ኢትዮጵያ እጆችዋን ዘርግታ መኳንንቶችን ተቀብላለች | 183፣184 |





| | ገጽ |
|---|---|
| የይሖዋ የበላይነት መገለጫ ሥርዓት | 200፣201፣203 |
| ለልዕለ ኃያላን መገበር የይሖዋን ሉዓላዊነትን አይሽርም | 203፣204 |
| የአምልኮቱን ሥርዓት እስካልነኩ ለልዕለ ኃያላን ገብሩ ብሎ የይሖዋ ማዘዝ | 205፣204 |
| በእሥራኤል መሪዎች ጥፋት በ607 ዓመተ ዓለም ጠፍቶ የነበረ ሥርዓት መመለስ | 207፣208፣209 |
| ኢየሩሳሌም ከ607 እስከ 537 ዓመተ ዓለም ባድማ ነበረች እንጂ ማንም አሕዛብ ረግጦ አልገዛትም | 210፣211 |
| ዮሐንስ ያየው ስለወገኖቹ እንጂ ምስክሮቹ ከጥቅም አንፃር በተቃኙ የሚሰጡት ትርጉም ዓይነት አይደለም | 214፣215፣216 |

| ይህንን መጽሐፍ ለመዳፍ በንባብ የተዳሰሱ እና በከፊል በየመጽሐፉ ገጽዎች የተጠቀሱት መጻሕፍት ዝርዝር **(Bibiliography)** | የታተመበት ዓመት፣ አሳታሚ ድርጅት ወይም ግለሰብ |
|---|---|
| 1. Jehovah's Witnbesses on Divine purpose | Watch Tower 1959 |
| 2. Mankind's search for God | " " 1990 |
| 3. በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ | " " 1991 |
| 4. Faith on the March | " " 1957 |
| 5. Panel by eminent personality About Ruwanda genocide | OAU 2000 |
| 6. Islamic, Christianity and state of ISRAEL | Dr. Ahimd Shaffaat |
| 7. Aid to Bible understanding | Watch Tower |
| 8. The sign and the Seal | GramKankock 1992 |
| 9. Your will be done on earth | Watch Tower 1958 |
| 10. Yesterday, today and for ever | JeanDixon 1970 |
| 11. The cave of the Ancient | Dr. Rump 1975 |
| 12. A gift of prophecy | Jean Deaxon 1970 |
| 13. The blood and the holy grail | Henry Lincolin 1996 |





| | |
|---|---|
| 14. Life before life | Dr. Wabach 1979 |
| 15. Seth Speaks | Jean Roberts 1988 |
| 16. Clash of civilization and Remaking of world order of world order | Simon and Schuster 1996 |
| 17. The stellar man | Johon Baines 2002 |
| 18. Letyour name be sanctified | Watch Tower 1961 |
| 19. እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን አማርኛው | " " 1952 |
| 20. Life ever lasting | " " 1965 |
| 21. Life after life | Ray mond Moody 1975 |
| 22. Insight on the scruptures vol. 1 & 2 | Watch Tower 1988 |
| 23. የዳንኤልን ትንቢት በትኩረት ተከታተል | " " 1999 |
| 24. ታላቁ መደምደሚያው ደርሷል | " " 1993 |
| 25. Secret Science | John Baines 1994 |
| 26. Mystery of the Ages | Herbert W.Ahmstrong |
| 27. Awake! Volume 36 | Watch Tower 1955 |
| 28. The watch Tower volume of 1966 | " " 1966 |
| 29. Man's Religions by Johon B. Noss | Macmillan Company 1967 |
| 30. The Chaos of cults | JanvanBaalen 1956 |

August 22, 1970

Dear Friend:

A while back a brother called at the office to visit with us and we were happy to see him for a time. He gave sufficient proof that he was reliable for he had our phone number and he knew the name of one of the brothers who is a servant. He also mentioned the name of the circuit servant who visited the group when he was at Dessie.

So when it came about that he had Kenya money which he wanted to change and he did not have the time to make the arrangements to change it otherwise we thought it a good opportunity for him to leave the money with us and we told him that we could arrange for him to receive the equivalent amount in ET Dollars back in Addis. We gave him a receipt and also sent the credit memo to let you know that we have given the account the equivalent credit. We did not of course tell the brother where the money was to come from, but we felt that it would be a simple matter for you to give the money to Gebreyesus and then he give it to the brother. We hope that this letter clarifies the matter and that you will now kindly pay the money through Gebreyesus so that this trusting brother may receive what belongs to him. The amount in ET $ is 571.45. So kindly see that he gets this as soon as possible. At the same time as the brother left Nairobi we dropped a line to Gebreyesus as he was the one the brother mentioned, and in our letter we mentioned what we had done so that it would be known that what the brother was claiming was genuine.

We understand that the person we saw is not yet baptized. We did not know this or even question it due to the reason we mention above.

Assuring you of our love and best wishes,

Your friends,
JW

Copy: G W/M